ሰርሳሪ ተረከዞች

አዘጋጅ፡- የሺሐሳብ አበራ

ጥቅምት ፳፻፲፪ ዓ.ም.
ባሕር ዳር

© ሰርሳሪ ተረከዞች ፳፻፲፪ ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ፡-
E-mail:enbualele2010@gmail.com

አሳታሚና አከፋፋይ፡-
ብራና መጻሕፍት መደብር
0930364287/0944342223

ማውጫ

መዛለያ.. 6

ምዕራፍ አንድ

ያላገሩ በሬን በሀገሩ ሰርዶ... 8

1.1 ፓርቲ ሀ፤ ሁ... 8

1.2 ጥቋቁር ቦልሼቪኮች... 8

1.3 ያልተፈታው ተጣራሽ ሕልም.............................. 12

1.4 የኦሮሞ እና የኤርትራ ብሔርተኞች ተመሳስሎሽ.. 16

1.5 ተገንጣይነት እና ፍልፍሉኢሕአዴግ..................... 18

1.6 የአሳሪ እና የታሳሪ ጓዳዊነት................................ 21

1.7 የሸመገሉ ችግሮች እና የአዳሹ ለውጥ ተረከዞች...... 26

ምዕራፍ ሁለት

የስብራቱ አንጓዎች.. 28

2.1 ያልተጠገነው የታላቁ ስብራት መነሾ..................... 28

2.2 ከመደብ ወደ ብሔር... 32

2.3 የኢሕዴን ተረከዞች.. 40

2.4 የኢሕዴን ተረከዛዊ ስብራቶች............................... 43

ምዕራፍ ሦስት

የጥላቻው ተረከዝ እና የቀደደው ሽንቁር...................... 55

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ልሂቅ ሠራሽ ሆኖ ስለመተከሉ...... 55

3.1 ከማኅበረሰብ ኑባሬ የተፋታ ልሂቅነት.................... 57

3.2 የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት እና ተረከዙ ያረፈበት
መንፈስ.. 70

3.3 ሉዓላዊነት በወሰን.. 71

3.4 ሰንደቅ ዓላማ.. 74

3.5 የአማራ ጥላቻ እና ሕገ መንግሥቱ...................... 76

3.6 የአንቀጽ 39 ተረከዝ የከፈተው ቦይ...................... 82

3.7 የሕገ መንግሥቱ ስል ተረከዝ ያተመው ዱካ........ 84

3.8 ኢሕአዴግ አሐዳዊ ወይስ ፌደራላዊ መንግሥት?.. 87

3.9 የክልሎች አወቃቀር እና እሳቤያዊ ግጭቶች.......... 90

3.10 የወሎ ክፍለ ሀገር ጉዳይ እና የጉባኤተኞች ድምጽ 100

3.11 ተለጣጪ ቅዥት እና የሀገረ መንግሥት ግንባታው ፈተና.............................. 106

3.12 ኢትዮጵያዊነት ግን ምን ዓይነት ነው?.............. 127

ምዕራፍ አራት

የባህል ቀኖና እና ፖለቲካዊ ስንጥቆች......................... 139

4.1 ሃይማኖት እና ፖለቲካችን.................................. 139

4.2 ሃይማኖት እና የኢትዮጵያ አብዮት...................... 144

4.3 ሃይማኖታዊ መልኮች... 152

4.4 የክርስትና እና እስልምና ተዛናፊ ፖለቲካዊ ተረኮች 158

4.5 የሃይማኖት ዲፕሎማሲ....................................... 171

ምዕራፍ አምስት

አብዮቶች እና እርምጃቸው.. 174

5.1 አብዮት.. 174

5.2 የአብዮት መነሾዎች.. 177

5.3 አደድቦ መግዛት... 177

5.4 አደህይቶ መግዛት.. 179
5.5 የጭብጨባ ገጾች... 181
5.6 የአብዮት ጉዞ በኢትዮጵያ.................................. 189
5.7 ደርግ እንዴት ወደቀ?....................................... 190
5.8 ኢሕአዴጋዊው አብዮት..................................... 193
5.9 የኢሕአዴግ ሕልም.. 194
5.10 ኢሕአዴግ እና የዓረቡ ጸደያዊ አብዮት................ 197
5.11 የውጭ ጠላት ፈጠራ እና የዓረብ አብዮት
መቆረጥ በኢትዮጵያ.. 200
5.12 የዓባይ ግድብ እንደ እድገት በኅብረት ዘመቻ........ 202
5.13 ኢሕአዴግ እና ተቋማዊ ተረከዙ......................... 205
5.14 ተቋማዊ ስንጥቆች... 207
5.15 ሚዲያ... 211
5.16 ሚዲያ በኢትዮጵያ.. 212
5.17 ሚዲያ እና ኢሕአዴግ...................................... 214
5.18 ምሁሩ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ......................... 221
5.19 የምኒልክ የተቋም ተረከዝ እንደ አብነት............. 230
5.20 የተቋም መጨንገፍ የፈጠረው ሌላኛው ተቋም..... 233
5.21 ከነጋዊ ሥጋት የሚለቀም ፍሬ.......................... 238

መዛለያ

የዛሬ ፖለቲካ የነገ ታሪክ ነው። ታሪክ ካለፈ በኋላ የሚነገር ትናንታዊ ትዝታ እና ነጋዊ ሕልም ነው። ታሪክ በድርጊትነቱ ቢከስምም፤ በሕሊናዊ እሳቤው የገቢራዊ እውቀት መነሻ ሆኖ ዘላለማዊ ይሆናል። ስለዚህ ታሪክ አይሞትም። ከማይሞተው ታሪክ ጉያ የሚሞተውን የዛሬ ኑረታዊ ፖለቲካ እድገት ለመመልከት ሞክረናል። ይህ የምንኖርበት ፖለቲካ ጽንሰቱ ከወደኛ አይደለም። እድገቱ ግን ከእኛ ጋር ሆኗል። እናም ፖለቲካው እና እኛ ባይተዋር ሆነናል። ተዋውቀን፣ የተዛምዶ ምርጫችንን የመወሰን ዕድላችንን በራሳችን ጣቶች ለማስፈር የፍሬ ነገር ልየታ ላይ ተሰማርተናል ።

ፖለቲካ የማኅበረሰብ ፈጣሪ ነው። ማኅበረሰብ በፖለቲከኞች አርዓያ እና አምሳል የሚፈጠር የሰው ልጅ ስብስባዊ ቀለም ነው። ሕይወትም የፖለቲካ ድርሰት ናት። እኛ የደረስንበት ፖለቲካ ከወደኛ አለመሆኑ አድማሳዊ እሴታችንን እና ኑሯችንን የተቃርኖ አድርጎታል። ሕልማዊ ተጣርሶውን ውሉን እየፈታን ለማየት ተሞክሯል።

በኮሚኒስታዊ እሳቤ የበለጸገው ሥርዓተ መንግሥታችን ከልማዳዊ ህላዌያችን ጋር ተጋጣሚ አለመሆኑ ለመኖር ኅርብጦናል። ጉርባጤውም ተደጋግሞ ተነግሯል። አዎ። ያልተባለ አልነበረም፤ የተባለው ግን አልተደረገም። ከብዙ ማለት ቅንጣት የማድረግ ኃይል ቢመነጭ ወንበር ፈጠር ጉርባጤው ሽክረቱ ይቀንሳል።

ምንም ነገር ከማለት ቃል ይጀምራል፡፡ እኛም ቃሉን አልን፡፡ እነሆ እኛ ያልነው በነቢብ፤ በገቢር ተተርጉሞ ይዘተ ነገሩ ምድራችንን በአዎንታ ይለውጥ ዘንድ የብራና ድርደራችንን በአባቶቻችን ወግ በእልፍኝ አስከልካያችን በኩል እንዲህ ከፈትን፡፡

ምዕራፍ አንድ

ያካገሩ በሬን በሀገሩ ሰርዩ

1.1 ፓርቲ ሀ፤ ሁ...

ይህ የምንኖርበት ዓለም የሦስት ይሁዳዎች መዋጮ ነው:: የካርል ማርክስ፣ ሲግመንድ ፍሩድ እና የአልበርት አንስታይን-ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር::: ስብሐት እንዳለውም በየትኛውም ኤክሮስ እና ኤንትሮስ ዓለም የሦስቱ ሰዎች ጥገኛ ነው::

...የትግል መሠረቱን ውቅያኖስ አቋርጦ፣ በዘመኑ ንፋስ ተዛሞ.... ከማርክስና ከኤንግልስ ማስታወሻ ኮርጇል:: የማርክስ ማስታወሻ በምሥራቅ አውሮፓ የቦልሼቪክን አብዮት በታላቋ ሩሲያ ምድር ፈጥሯል:: የቦልሼቪክ አብዮት የሩሲያ ዐፄዎችን ፈንግሎ ታላቋ ሶቭየት ኅብረትን በመልክዓ ሌኒን እና ስታሊን አዋቅሯል:: በምሥራቁ የአውሮፓ ክፍል የተዛመተው ይህ ሰደድ የ1966ቱን ትውልድ በኢትዮጵያም ፈጥሯል::

1.2 ጥቋቁር ቦልሼቪኮች

ቦልሼቪክ በሕግ ባለሙያው ቭላድሚር ሌኒን አማካኝነት በ1917 ዓ.ም. በሩሲያ ምድር መጣ:: መጥቶም የሩሲያን ዐፄያዊ ሥርዓት አክትሟል:: የሌኒን ፍጡር የሆነው የቦልሼቪክ አብዮት ትናንትን ፍቆ ዛሬን በመሥራት ላይ የተመሠረተ ነው:: ሌኒን ሃይማኖት

የለሽነት በይፋ ያወጀ መሪ ሲሆን፤ የሀገሩን ዐፄያዊ (ዛር) ሥርዓት ለማሸነፍ ሲል ሀገሩን ከጀርመን ጋር ሆኖ ተዋግቷል። የአንደኛው ዓለም ጦርነት በ1914 ዓ.ም ሲፈነዳ ጀርመን ሩሲያን ለመውጋት ተነሣች። ሌኒንም ከጀርመን ጎን ሆኖ ሩሲያን ተዋጋ። የሩሲያ ዐፄያዊ ሥርዎ መንግሥት ሲደክም በ1917 ዓ.ም. የቦልሼቪክ አብዮት በሩሲያ ምድር ታወጀ።

የ1966 ዓ.ም. አብዮት ተከትሎ በኢትዮጵያም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ብቅ አለ። ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ከተሞች ተተክሎ ጭንቅላቱን ከነ ሌኒን ጋር አገናኘ። እኔ የጥቁር ቦልሼቪክ መሪ ነኝ ብሎ አንዴ ከሱዳን ሌላ ጊዜ ከኢራቅና ከአልጀሪያ መሰል ሀገራት ጋር ቆሞ ለኢትዮጵያ ነጻነት አዋጋለሁ ብሎ ተነሳሣ። የኢሕአፓ ማኀበረ መሠረቱን የተከለው ከኢትዮጵያ በተቃርኖ ከቆሙ ሀገራት ጋር ስለነበር በሀገር ውስጥ ከኢትዮጵያን እሴት ጋር ተዛምዶ ለድል ለመብቃት ተቸግሯል።

ኢሕአፓ የነሌኒን ውልድ ነውና ደርግን ለማሸነፍ በ1970 ዓ.ም. ከሶማሊያ ጦርነት አልሳተፍም[1] ብሎ ከሶማሊያ ጎን ተሰለፈ። በወቅቱ ደርግ ከሶማሊያው ዚያድ ባሬ ጦር ያፈገፈገ እንዲገድል ነጻ ፈቃድ ሰጠ። አፈግፋጊ የኢሕአፓ አባላትም መገደላቸው ሕጋዊ ሆነ።

የኦነግ መሥራቹ አቶ ሌንጮ ለታ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ2011 ዓ.ም. የዛን ትውልድ ባሕርይ ሲገልጹ “የኛ ትውልድ ማሸነፍን እንጂ እውነት ፍለጋ ላይ አልባጀም” ብለዋል።

ሌንጮ እንዳሉትም ለማሸነፍ ሲባል ሀገርን ለተረካቢ ጠላት አሳልፎ መስጠት፣ ለጎዳዊነት አለመታመን፣ በመገዳደል መሰላል ደም እየረገጡ የሥልጣን ወንበር ለመያዝ መሞከር የዛ ትውልድ

[1] ዶክተር ፈንታሁን አየለ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከድል ወደ ውድቀት (ከ1967 እስከ 1983)

ሥነ-ቁሳዊ ማርክሳዊ ፍልስፍናው አስገድዶታል። የመኢሶን እና የኢሕአፓ፣ የኢሠፓ እና የብሔር የግንጠላ ድርጅቶች እስካሁን በታሪክ ሂደት እንኳን ራሳቸውን ቅዱስ አድርገው ሌላውን ለማርከስ ይጽፋሉ። መርሐቸውም አንዱ ካልረከሰ ሌላው የሚቀደስ አይመስላቸውም። ብዙዎቹ የኢሕአፓ ሰዎች ዛሬም ድረስ መኢሶን ከደርግ ጋር ተለጥፎ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን አብዮት ቀርጥፎ እንደበላ ይጽፋሉ።

መኢሶኖች ደግሞ ኢሕአፓ ከሻዕቢያ እና ከጀባህ ፍርሥራሾች ጋር ሆኖ ኤርትራ እንድትገነጠል ለገንጣይ ቡድኖች የሀገር መረጃ ከማቀበል እስከ ወግኖ መዋጋት ድረስ የደረሰ የባንዳነት ሥራ መሥራቱን በታሪክ ይጠይቃሉ። መኢሶን እና ኢሕአፓ በፖለቲካ እና በጦር ተሸንፈው እንኳን ከስህተታቸው ለመማር ሳይሞክሩ ዛሬም በታሪክ ጦርነት ላይ ናቸው። ደርግ ሁለቱንም በማዕከላዊ እሥር ቤት ሲያሰቃያቸው እንኳን የኢሕአፓ እና የመኢሶን አባላት ትግላቸው ደርግን በጋራ ታግለን እንዴት ነጻ እንውጣ የሚል ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ነበር።

የደርግ (የኢሠፓ) ታሪክ ነጋሪዎችም ፓርቲያቸውን ዛሬም ድረስ እንከን አልባ አድርገው ይስሉ እና ኃጢአቱን ሁሉ የዛኔ ለነበሩ የተገንጣይ ዘውጌ ብሔርተኞች ይሰጣሉ። ዘውጌዎችም መንግሥት ሆነው ሀገር እየመሩ፣ የፖለቲካ ስኬታቸውን ደርግን ማሸነፋቸው እንደሆነ ይሰብካሉ።

የደርግን ጊዜ የባርነት በማድረግ ዘውጌ መሯን ኢትዮጵያ በነጻነት ሰይመው በመቀሌ፣ በአዳማ፣ በባሕር ዳር… በደርግ የተገደሉ የሰማዕታት ሃውልቶች ከሁሉም ሕንጻዎች ከፍ ብለው ይታያሉ። የ1966ቱ አመጻ የወለዳቸው ፓርቲዎች ምንም የጋራ ግብ እና ሀገራዊ እሴት ስለሌላቸው በጠላትነት እየተፈላለጉ ዘልቀዋል።

ኢሕአፓ በውስጠ ዴሞክራሲያዊ ብልሽቱ እና በተከተለው የከተማ[2] ቀመስ ትግል በቀይ ሽብር ዘመቻ ብዙ ሳይጓዝ ተደመሰሰ:: ከ1983ቱ ሽግግር መንግሥት አንኳን በወጉ ሳይሳተፍ ቀረ:: በሽግግር መንግሥቱ ኢሠፓ በገዳይነት፣ መኢሶን እና ኢሕአፓም በሽግግር መንግሥቱ ሽብር ፈጣሪነት ተፈርጀው ከመንግሥትነት ተፍቀው ከፓርቲነት ሳይዘሉ ቀሩ:: የዜግነት ፖለቲካም በዘውጌ ፖለቲካ የበላይነት አብሮ ተደፈቀ::

ከኅዳር 7-11 ቀን 1973 ዓ.ም. ጉባኤውን ያደረጉ የቀድሞ የኢሕአፓ አንዳንድ አፈንጋጭ አመራሮች የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ኢሕዴን) ብለው ተነሥተው ነበር:: ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ኢሕዴን በጎንደር በለሳ አካባቢ እና በወሎ ዋግህምራ ሰቆጣ አካባቢ የትግሉ ማኅበረ መሠረቱን ተከለ:: ኢሕአፓ በመጀመሪያው አካባቢ የብሔር ብሔረሰቦች መብትን እስከ መገንጠል እና የኤርትራ ጥያቄንም የቅኝ ግዛት አድርጎ ተቀብሎ ነበር:: በጀርመን በርሊን በ1964 ዓ.ም. የተመሠረተው ኢሕአፓ በኢትዮጵያ የፓርቲነት ታሪክ ውስጥ በኩር ተደርጎ ይወሰዳል:: በእርግጥ በህቡዕ ይደራጅ እንጂ መኢሶንም ከኢሕአፓ የቀደመ የፖለቲካ ፓርቲነት ታሪክ እንዳለው የኢሕአፓ መሪ የነበረው ክፍሉ ታደሰ ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ በ2011 ዓ.ም. በሰጠው ቃለ መጠይቅ አንስቷል::

መኢሶን በጀርመን ሀምቡርግ የተመሠረተ ሶሻሊስታዊ ፓርቲ ሲሆን ከኢሕአፓ ጋር የተቀራረበ ዓላማ ነበረው:: ነገር ግን መኢሶን ደርግን ሕዝባዊ ማድረግ ይቻላል በሚል ተስፋ ከደርግ ጋር ተቀጠለ:: ደርግ የኢሕአፓ አባል በተገኘበት ይገደል ብሎ በመስከረም 2 ቀን 1969 ዓ.ም. አወጀ:: **"የአንድ አብዮታዊ ሕይወት በሺ ፀረ-ሕዝቦች ሕይወት ይመነዘራል"** የሚለው መፎክር በደርግ ዘንድ ጎልቶ

[2] የኢሕዴን ብአዴን ታሪክ ከ1973 እስከ 2008

ተሰማ:: ክፍሉ ታደሰ እንደሚለው ደርግ ሠራተኛው እንዳይደራጅ[3] አደረገ:: የተደራጀውንም አሰረ፤ በተነ:: ደርግ ዘወዳዊውን ንጉሥ ጥሎ ራሱ ወታደራዊ ንጉሥ ሆነ::

ይህም ኢሕአፓን ወደ አመጻ መንገድ ገፋው:: እንደ ባሕሩ ዘውዴ ደግሞ የሞት አዋጅ ቀድሞ ያስጀመረ ማነው የሚለውን ለሁለቱም ይሰጣሉ:: በመስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም. ኢሕአፓ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለመግደል [4]ሞክሮ ባይሳከለትም፤ የመኢሶኑን የሕዝብ ግንኙነት ሓላፊ ዶክተር ፍቅሬ መርዕድን ግን ገድሏል:: ኢሕአፓ ነጭ ሽብርን ሲጀምር ደርግ ቀይ ሽብር ብሎ የጅምላ ፍጅቱን መበቀል ተያያዘው:: ኢሕአፓ ከቻይናው ማኦ ዘዱንግ ገጠርን መሠረት ካደረገ ትግል ወጥቶ፤ ፈጥኖ ሥልጣን በመያዝ የከተማ ትግልን መረጠ:: ትግሉ የተቀናጀ አልነበረምና በቀይ ሽብር ተደመሰሰ:: ኢሕአፓ በኤርትራ ላይ በነበረው አቋም እና ከሕወሓት ጋር በነበረው ቅራኔ ሙሉ በሙሉ በ1972 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ተዳከመ::

በሕወሓት አጋዥነት ከኢሕአፓ 120 ከሚደርሱ ግንጣዮች መካከል በ35 ወንዶች እና በ2 ሴቶች ኅዳር 11 ቀን 1973 ዓ.ም ኢሕዴን ተፈጠረ::

1.3 ያልተፈታው ተጣራሽ ሕልም

ከንዑሳን ብሔር የተቀዳው ሕወሓት ተገንጣይ ቡድን ቢሆንም፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ እያለ ራሱን የሚገልጸውን የአማራውን ትውልድ ለመያዝ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን የሙጥኝ አለ:: ኢሕዴን ሕወሓት ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ለሚያደርገው

[3] ክፍሉ ታደሰ፤ ያ ትውልድ እና አዲስ አድማስ ጋዜጣ 2011 ዓ.ም.።

[4]ባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983

ጉዞ የፖለቲካ ገበታውን አሰፋው:: በ1980ዎቹ መጀመሪያ ኢሕዴን እና ሕወሓት ተጣምረው ኢሕአዴግን ፈጠሩ:: ሕወሓት በ1968 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ ትግሉ ፀረ አማራ እና ፀረ አውሮፓ[5] ኢምፔሪያሊዝም ነበር:: ኢሕዴን የአማራ ሥነ-ልቦና ቢኖረው ኑሮ ከሕወሓት ጋር ተዋሕዶ ኢሕአዴግን አይፈጥርም ነበር::

ሀብታሙ አለባቸው እንደሚለው ሕወሓት ከማዕከላዊ መንግሥት ርቆ[6] የተጠለለ እና በሕዝብ ቁጥር አነስተኛ ሕዝብን ወክሎ የመጣ ቢሆንም፤ ሀገርን በአምሳያው ፈጥሯል:: ሀብታሙ ይሄን በታላቅ ተቃርኖ ይመለከተዋል:: ሀገር ግንባታ በአብዛኛው ሕዝብ (majority nation) እና በብዛት በመካከለኛው የሀገር ክፍል የሚገነባ ቢሆንም፣ የሕወሓት የሀገር ግንባታ ታሪክ ግን ከዚህ ሀቅ ያፈነገጠ ነበር::

የሕወሓት ሠራዊት የአስተምህሮ ቅኝቱ ከታላቋ ትግራይ ሉዓላዊነት ያለፈ ሀገራዊ ሕልም ስላልነበረው ትናንሽ መሣሪያዎችን (በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ጀኔሬተሮች እና የቢሮ እቃዎች) ሳይቀር ወደ መቀሌ ማጋዙን ተያያዘው:: ሕወሓት ለትንሹ የትግራይ ሪፐብሊክ ታግሎ ሰፊውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ማዕድ መቋደሱ ድሎታዊ ድንጋጤ ፈጥሮበታል:: ለማዕዱ መስፋት ግን የኢሕዴን የኢትዮጵያዊነት እሳቤ በረከቱን ችሮታል::

ሕወሓት መጠነኛ ቁጥር ካለው ሕዝብ ስለመጣ ገዥ ለመሆን ዴሞክራሲ አያሻውም:: ዴሞክራሲ የብዙኃን አሸናፊነትን እና የጥቂቶችን መብት ተከባሪነት የሚያውጅ ጽንሰ ሐሳብ በመሆኑ ከሀገሪቱ ስድስት በመቶ ለሚወክለው ሕወሓት አይስማማውም::

[5] በ1966 የተነሡ ብዙዎቹ ፓርቲዎች ከሶሻሊስት አውሮፓ እና አረብ ሀገራት ጋር አጋርነት መሥርተዋል:: የምዕራቡን የአውሮፓ ክፍል በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ካፒታሊዚም በመሆኑ ጸረ አውሮፓ መስለው ተነሥተዋል::

[6] ሀብታሙ አለባቸው፣ታላቁ ተቃርኖ

ንዑሳን በሥልጣን ለመቆየት አምባገነን መሆን ምርጫቸው ሳይሆን ግዴታቸው ይሆናል፡፡ የብዙኃንን ትብብር ለማጥፋት ደግም በብሔር ቋጠሮ የተሸበለሉ ክልሎች በጥርጣሬ እንዲተያዩ ሆኗል፡፡ ሁሉም ብሔሮች አማራን እንዲጠሉ ሲደረጉ፣ ከሀገሪቱ ሕዝብ አብዛኛውን የሚወክሉት አማራ እና ኦሮሞ በፍፁም ተቃርኖ ውስጥ ገብተው ባጁ፡፡ ግንኙነታቸውም እሳት እና ጭድ ሆኖ ዘንዶዎቹ በእንቁራሪቶች እንዲመሩ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ እስካሁን አብላጫ ቁጥር ያለው ብሔር[7](Majority nation) የላትም፡፡ የአማራ እና የኦሮሞ ብሔሮች ተደምረው 62 ከመቶውን የሀገሪቱን ሕዝብ ሸፍነው አብዛኛ ብሔር ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ በዴሞክራሲም ሆነ በአምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ የሁለቱ ሕዝቦች መስማማት እና አለመስማማት የሀገሪቱን ፖለቲካ የመወሰን አቅም አለው፡፡ ሕወሓት ግን ይህን አቅም በመረዳት ሁለቱ ሕዝቦች የጎሪጥ እንዲተያዩ በማድረግ ንዑስ ሆና እንድትነግስ አድርጋለች፡፡

ከታሪክ አንጻር ሕወሓት የሥልጣን ፍላጎት ከፈጠረው ፍትጊያ በስተቀር ከኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ጋር መሠረታዊ ተቃርኖ የለውም፡፡ በዐፄዎቹ ዘመን ዐፄ ዮሐንስ የዐፄ ቴዎድሮስን ሀገር የመገንባት ሂደት አስቀጥለዋል፡፡ ዐፄ ዮሐንስ ሥልጣኑን ያገኙት ዐፄ ቴዎድሮስን በእንግሊዞች በማስገደል ነበር፡፡ ግድያው የፖለቲካ ዙፋንን ለመንጠቅ እንጂ በመሠረታዊው የሀገር ግንባታ ሂደት ላይ መጣረስ የሚፈጥር አልነበረም፡፡ ዐፄ ዮሐንስ አማርኛን

---

[7] ኢትዮጵያ የተለያዩ ማንነቶች ተፍላልተው እና ቀልጠው የፈጠሯት ሀገር እንጂ ልክ እንደ የን ቻይና ቻይና፣ እንደ ሩስኮ ሩሲያ፣ እንደ ጃፓን ጃፓን፣ እንደ ኢንግሊሽ እንግሊዝ… አንድ ብሔር አብላጫ ሆኖ የፈጠራት ሀገር አይደለችም፡፡ አማርኛ ቋንቋ እንኳን መነሻው ከአማራ ሆኖ ለብዙ ኢትዮጵያውያን መግባቢያ በመሆኑ የሴሜቲክ እና የኩሽቲክ ቋንቋዎችን ባሕርይ ቀይጦ ሊይዝ ተገዷል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ነጠላ ማንነት ብዙ የለም፡፡ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከተለያዩ ማንነቶች የተደባለቀ እንጂ ሙሉ በሙሉ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ሶማሌ… ሆኖ የሚቆም የለም፡፡ ምክንያቱም የሀገረ መንግሥት ግንባታው የጸናው የተለያዩ ማንነቶችን በጦር ሜዳ፣ በገበያ ቦታ፣ በሰፈራ፣ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ በሆኑ ሁኔታዎች በማገናኘት ነው፡፡

የወል ቋንቋ(ሊንጓፍራንካ) አድርገው፤ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ደግሞ የመንግሥታቸው ሃይማኖት አድርገው አስቀጠሉ። የዐፄው ሂደት በአካላዊም ይሁን በሕሊናዊ እሳቤ ከዐፄ ቴዎድሮስም የሚለይበት ይዘት አልነበረም። ሥልጣን ከዐፄ ዮሐንስ ወደ ምኒልክ ሲሸጋገር ዳግማዊ ምኒልክ የሰሜኑን የሀገረ መንግሥት ግንባታ እንዳነበሩ፤ ወደ ደቡብ ገስግሰው የዛሬዋን ኢትዮጵያ በአካል ፈጠሩ።

ሕወሓት ዐፄ ምኒልክን ከዐፄ ዮሐንስ ሥልጣን ወስደዋል በሚል ሃቲት ከአማራነት እና ከዐፄ ምኒልክ ተቃርኖ ቆሟል። ስለዚህ ሕወሓት በአንድ ገጹ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ የመሆን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ የተጨቋኝ ብሔረሰብ ወኪልነቱን በዘውጌነቱ ይገልጻል። ይህ ጣምራ ባሕርይው ለኢትዮጵያዊነት ቅርብ የሆነውን አማራን በኢትዮጵያዊነት፣ የግንጠላ አራማጁን ዘውጌ የኦሮሞ ፖለቲከኞችን በተጨቋኝ ብሔር ነጻ አውጭነት[8] ተዛመደ። ጣምራ ባሕርይው በአማራ እና በኦሮሞ ተቃርኖአዊ ፖለቲካ መሃል ላይ ሆኖ በራሱ በሚመቸው መንገድ እንዲጫዎት አስችሎታል።

ነገር ግን የኦሮሞ ፖለቲካ ከቅኝ ተገዥነት ታሪክ ወጥቶ ኢትዮጵያ የእኔም ናት ብሎ ሲነሣ ከአማራ ፖለቲካ ጋር ተገጣጠመ። ግጥምጥሞሹ የአማራ እና የኦሮሞ ሕዝባዊ ኅብረትን (ኦሮማራን) ፈጠረ። የሁለቱ ሕዝቦች የፖለቲካ ተረክ በምኒልክ ሀገር ገንቢነት እና ቅኝ ገዥነት ላይ የተፈተለ ነው። የኦሮሞ ፖለቲከኞች ከሜጫ እና ቱለማ ምሥረታ ከ1956 ዓ.ም. ጀምሮ አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ኦሮሞን ቅኝ ገዝታለች የሚል የፖለቲካ ትንታኔ አዳብረዋል።

[8] ሀብታሙ አለባቸው፣ታላቁ ተቃርኖ (2009)

1.4 የኦሮሞ እና የኤርትራ ብሔርተኞች ተመሳስሎሽ

የኦሮሞ ፖለቲከኞች ጥያቄ ከኤርትራ ፖለቲከኞች ጥያቄ ጋር በተመሳስሎሽ የተቀረጸ ነው:: የሁለቱም ትግል ነጻ ሀገር የመመሥረት ሲሆን፣ ትርክቱም አማራ የፈጠራት ኢትዮጵያ በምኒልክ እና በተከታዮቹ ዐፄዎች አማካኝነት ቅኝ ገዝታናለች የሚል ነው::

የኦሮሞ ዲያስፖራዎች በተለያዩ ጊዜያት ባደረጓቸው ሰልፎች **"ኢትዮጵያ ከኦሮሚያ ትውጣ"** የሚል መፎክር አሰምተዋል:: ኤርትራ በ1985 ዓ.ም. [9]ሙሉ ሀገርነቷን ስታውጅ በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር አልመራም ብላ የአውሮፓን የዘመን ስሌት ተውሳለች:: የኦሮሞ ብሔርተኞችም የዘመን ቀመሩ በአውሮፓ እንዲሆን ፍላጎት አላቸው:: ከኢትዮጵያ ለመሸሽ የግእዝ ፊደልን በላቲን ተክተዋል:: አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩን ሰንደቅ ዓላማም የነጻነት ምልክት ሳይሆን የባርነት መለያ አድርገው ይወስዱታል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የቅኝ ገዥ ተቋም አድርገው በዘመን ቆጠራው[10] ላይም ጥርጣሬ አለባቸው:: የእነ ኦነግ ትርክት ተከታዮች ዛሬም ዘመንን በአውሮፓ አቆጣጠር ይሰፍራሉ:: የኦነግ አስተምህሮ ተከታይ ልሂቃን በሕሊናዊ አረዳድ(በመንፈስ) ከኢትዮጵያ ተገንጥለዋል:: ከኢትዮጵያ ጋር የሚያያይዛቸውን መንግሥቱ ሁሉ ቆርጠው ለመጣልም ይታገላሉ:: በአካል(በግዛት) ብቻ ኦሮሚያን ከኢትዮጵያ ጋር የተቆራኘ አድርገው ይወስዳሉ::

---

[9] ኤርትራ የነጻነት ቀኔ ነው ብላ የምታከብረው በነፍጥ ደርግን አሸንፋ ከአስመራ ያስወጣችበትን ግንቦት 16/1983 ዓ.ም.ን ነው እንጂ በሕዝበ ውሳኔ ሀገር የሆነችበትን ሚያዝያ 17 ቀን 1985 ዓ.ም.ን ዓይደለም:: ኢሕአዴግ የምኒልክን ቤተ መንግሥት ከተቆጣጠረበት ግንቦት 20 ቀን 4 ቀን ቀድማ ነጻነቷን አውጃለች:: ለዚህም ሕገ መንግሥቱ ሲረቀቅ ኤርትራ የተገነጠለችው በደርግ ዘመን ነው የሚል አስተያየት ይቀርብ ነበር::

[10] አሥራት አብርሃም የሕገ መንግሥቱ ፈረሰኞች

እስከ 1983 ዓ.ም. የኤርትራ አርሶ አደሮች በከፊል መሠረተ ትምህርት በአማርኛ ይማሩ ነበር። ከነጻነት በኋላ ግን በአማርኛ ሙዚቃ ማዳመጥ፣ ማስታወቂያ መሥራት፣ ቴሌቪዥን መከታተል ወንጀል ተደርጎ ተፈረጀ። የኦሮሞ ፖለቲከኞች በአማርኛ ቋንቋ መጠቀምን ቢያወግዙትም፣ ማኅበረ ኢኮኖሚው አልፈቀደላቸውም። በኦነግ ቀመስ ልሂቃን ዘንድ ምኒልክ ፈጠሯ/ሠራሷ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ ጥቁሮችን ቅኝ የገዛች ብቸኛዋ ቅኝ ገዥ ሀገር ናት።

ይህ ሁሉ የተቃርኖ ስንክሳር የተደገሰበት የቅኝ ገዥ እና ተገዥ ተረክ ጠቦ አማራ እና ኦሮሞ አንድ ሕዝብ ነው የሚል የጋራ መድረክ በባሕር ዳር ጥቅምት 25 ቀን 2010 ዓ.ም. ተደረገ። በ2009 ዓ.ም. አቶ ጌታቸው ረዳ የተባሉ የሕወሓት ሰው የሁለቱን ሕዝቦች ግንኙነት በእሳት እና ጭድ መስለው ተናግረው ነበር። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከሳይንሥነቱ ይልቅ ሴራ እና ቂምበቀልነቱ ስለሚያመዝን ሁለቱ ሕዝቦች ጠላት ናችሁ ስለተባሉ የበለጠ ተዋደዱ። በወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳደር የነበሩት አቶ ለማ መገርሳ ‹‹ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው።›› የሚል ዲስኩር አሰሙ። ዲስኩሩ ከኦሮሞ ፖለቲከኞች የመገንጠል ተረክ ጋር የተቃረነ በመሆኑ ቅቡላዊ ግርምትን ፈጠረ። የኦሮሞ ፖለቲካ ከዳር ተገንጣይነት ወደ መሃሉ ሲገባ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ዶክተር አብይ አህመድን ከኦዴፓ ለጠቅላይ ሚኒስተርነት አበቃ።

ኦሮማራ የሕወሓትን የበላይነት ለማክሰም የአማራ እና የኦሮሞ ልሂቃን የኮንትራንት(ጊዜያዊ) ስምምነት ነበር። ኮንትራቱ ሕወሓትን ከምኒልክ ቤተ መንግሥት ወደ መቀሌ ሸኝቶ፣ ኦዴፓን ከጨፌው መንበር ወደ ምኒልክ ሰገነት አውጥቶታል። ኢሕአዴግም ከሰሜናዊ የበላይነት ወደ ደቡቡ ሲጠጋ የበለጠ የመንገራገጭ ድምጽ አሰምቷል። ኢሕአዴግ ወደ ደቡቡ በቀረበ ቁጥር የሀገረ

መንግሥት ውጥኑ የበለጠ እየተናጋ፣ አዲስ ሀገር የመፍጠር ሂደቱም እየፈጠነ ሂዷል። ፌደራሊስት እና አሐዳውያን የሚል አቦዳደንም ተፈጥሯል።

ለዜግነት ፖለቲካ ቅርብ የሆኑት ኃይላት በአሐዳዊነት ሲፈረጁ፤ ከሀገር በላይ ዘውጋዊ ማንነትን አድምቀው ፖለቲካቸውን የሠሩ አካላት እንደ ፌደራሊስት ኃይል ራሳቸውን ይቆጥራሉ። የሀገሪቱ ፖለቲካ አሁንም እንደ ትናንቱ ከአንጃ አልወጣም። ብሔራዊ ክልሎች ለዘላቂ ዓላማ ሳይሆን፤ ሌላኛውን አቻ ብሔራዊ ክልልን ለማድከም ይቀናጃሉ። አንዱን ጠልቶ ሌላውን ወዶ በተነሣ የፍረጃ እና የአንጃ መንገድ ሀገረ መንግሥት ማቆም ክቡድ ይሆናል። የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች የቋንቋ ቤተሰባቸው "ከኩሽ" የሆኑ ብሔሮችን በመሰብሰብ ከሰሜኑ ለመላቅ ሲሞክሩ፤ ሕወሓት ደግሞ ፖለቲካዊ ሥሪቱን ለማንበር ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን የተቀበሉ የፌደራሊስት ኃይሎች ከሚላቸው ሁሉ ጉድኝቱን አጠናክሯል። የአማራ ፖለቲካ ደግሞ ኢሕአዴግ ሀገረ መንግሥቱን ያዋቀረበትን ሥሪት ተቃርኖ ቁሟል። የኢሕአዴግ ፖለቲካ ተረከዙን ያሳረፈው በአማራ መሠረታዊ ፍላጎት ተቃርኖ ላይ ስለሆነ አማራ ኢሕአዴግ ላዋቀረው ሀገረ መንግሥት ኢ-ተገጣጣሚ ፍላጎት አለው።

1.5 ተገንጣይነት እና ፍልፍሉ[11]ኢሕአዴግ

ኢሕአዴግ በተገንጣይ ኃይሎች የተመሠረተ የእስከዚያው ድርጅት ነው። በኢሕአዴግ ውስጥ ኢትዮጵያ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያለች ሀገር ናት። የከፋው ብሔራዊ ድርጅት ብሔሩን ይዞ ከኢትዮጵያ ይነጠል ዘንድ በአንቀጽ 39 ታውጇል። ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ብሔሮች ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት[12] ሆነው በሕገ መንግሥቱ ተመርጠዋል።

[11] ፍልፍሉ ኢሕአዴግ በኢሕአዴግ ውስጥ ተፍላልቶ የተፈጠረ፤ የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን መልቀቅ እና የአብይ አህመድን መተካት ያመለክታል።

[12] የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 8 ብሔሮች የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው ይላል።

ኢትዮጵያዊነትን በነቢብ የሥልጣን መሸጋገሪያ ያደረገው ከሕወሓት የተፈለፈለው ኦዴፓ በግብ ያስቀመጠው ግን የኦነግን ትርክት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ኦዴፓ ሥልጣን ከያዘ ዓመት ሳይደፍን ‹‹አዲስ አበባ የኦሮሞ ናት›› ብሎ ተነሣ፡፡ የአዲስ አባባ ፖለቲካ የኢሕአዴግን ፖለቲካ መልሶ አሳመመው፡፡ የኦሮሞን ፖለቲካም ከመሃሉ መንገድ ወደ ዳሩ የቁልቁለት ነዳው፡፡

የተገንጣይነት አጀንዳ በኢሕአዴግ መንፈስ ውስጥ ግዝፈት አለው፡፡ መንፈሱ የሚገለጸው በወሰን ሽኩቻ እና በትርክት ደረጃ ነው፡፡ በክልል ቅንፍ ውስጥ ያሉ ብሔሮች ሀገር ለመሆን የሚያስችላቸውን ምጣኔ ሀብት እና ታሪክ[13] ለመሰብሰብ ብርቱ ፋክክር ውስጥ ሰጥመዋል፡፡ የትግራይ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል "የትግራይ[14] ሕዝብ በመገንጠል ስሜት ውስጥ ነው ያለው፡፡ የደረሰበት በደል እንዲገነጠል ያስገድደዋል" ብለው በ2011 ዓ.ም. በግላጭ ተናግረዋል፡፡

ክልሎች ለአስተዳደር ምቹነት የተሰመሩ የኢትዮጵያ ጨረሮች ሳይሆኑ፤ ማንነታዊ እና ግዛታዊ ሉዓላዊነትን የተጎናጸፉ ሀገር የመሆን ሕልም ያላቸው በሌላ ትልቅ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ትናንሽ ሀገሮች ሆነዋል፡፡ የራሳቸውን የጸጥታ መዋቅር እና የውጭ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሥርተዋል፡፡ የብሔራዊ ክልሎች ፍላጎትም የማይታረቅ እና በፍጹም ተቃርኖ የቆመ ነው፡፡ በዘውጌ ብሔርተኛ ልሂቃን ዘንድ ወደ ዜግነታዊ ብሔርተኝነት ከመመለስ

[13]ኦዴፓ ኦሮሞ ከ150 ዓመት በላይ ተጨቁኗል ይላል፡፡ የጭቆናውን ውጥን የምኒልክን ሀገረ መንግሥት ምሥረታን ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር በማያያዝ ይነሣል፡፡ ኦዴፓ የ150 ዓመት እዳ እንዳለው አስቦ ኦሮሞን ሀገር ወይም ኦሮሞ የሆነች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ይሠራል፡፡ ሕወሓትም ከምኒልክ መንገሥ እና ከዮሐንስ መውደቅ በኋላ ያለውን የኢትዮጲያ ታሪክ የጭቆና አድርጎ ይወስደዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ትናንትን በማፍረስ እና ነገን በራስ አምሳል በመቅረጽ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በቀላሉ አስማሚ አይሆንም፡፡

[14]ሪፓርተር ጋዜጣ ሰኔ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ያወጣው ዘገባ፡፡

ኢትዮጵያ ተበታትና ወደ ብዙ ሀገር ብትፈለፈል ምርጫ አድርገው ፖለቲካ ይተነትናሉ። ኢሕአዴግ ከሌኒናዊ የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊ እዝነት ሲፈታ ግንባሮቹ ሁሉ በራሳቸው ለመቆም ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጋር ወደ ግጥሚያ ገቡ። በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በተወሰነ የገዥው ኃይል ልሂቃን የተከማቸውን ኃይል መከፋፈል ሲመጣ የኢሕአዴግ ህልውና እንደ ድሃ አደግ ልጅ እያደር እየከሳ መጣ። ሀገሪቱም በፌደራሊስት ኃይሎች ሳይሆን በኮንፌደሬሽን ኃይሎች የተዋቀረች ስስ ሥር ያላት መስላ ታየች።

የዶክተር አብይን መምጣት ሕወሓት ከጅምሩ እንደለውጥ ሳይቀበለው ቀረ። ሌሎቹ የግንባሩ አባላት ደግሞ ለውጥ አለ ቢሉም የተለወጠውን ነገር ሥርዓታዊ አድርገው ሳያሳዩ ቀሩ። ኢሕአዴግ ለውጥ የለም በሚለው ሕወሓት እና ለውጥ አለ ብለው በተሰለፉ ግንባሮች መካከል ያለው መካረር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በለውጥ አራማጆች መካከልም አስማሚ የፖለቲካ ትንተና እና ተግባር የለም።

በዘውጌ ብሔርተኝነት ውስጥ ማዕከላዊ መንግሥቱ ላይ ብልጫ የፖለቲካ ኃይልን የሰበሰበ የዘውጉን የበላይነት ማረጋገጡ ሃቅ ነው። ዘውጌ ብሔርተኝነት ተፈጥሮው ለራስ ማድላት ነው። በራስ ማድላት ውስጥ ከሌሎች መንጠቅ አለ። ለዚህም ነው፤ ዘውገኛ ፌደራሊዝም ዴሞክራሲን ለማስፈን አስቸጋሪ የሚሆነው። ቡድናዊ እኔነት ከፍ ብሎ ስለሚዘመር እንደ ሀገር እኛነት ሊነግሥ አይችልም።

ዘውገኛ ፓርቲዎች በአቻነት የሚቆም የብሔርተኝነት ጫፍ ከኖራቸው፤ ሁሉም አሸናፊ በሆነበት ድርድር ሀገርን ማስቀጠል ይቻላል። ከ1983 እስከ 2010 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ሕወሓት በላጭ የብሔርተኝነት መንገድን ሲከተል፤ ሌሎቹ እያነከሱ

በኤሊነት እርምጃ ተከተሉት። በዚህ መንገድ በመበላለጡ ፍትሕ ርቆ አድሎአዊነቱ ተፈጠረ። ለአድሎአዊነቱ መፈጠር መንስኤ የሕወሓት ፖለቲካዊ ብልግና ብቻ ሳይሆን የሌሎቹ ከኢሕአዴግ ግንባር የፈጠሩ ፓርቲዎች ትኙነት(አዝጋሚነት) ጭምር ነው።

ከሕወሓት በኋላ ባለው ኢሕአዴግ የተፈጠረው ሁኔታም ኦዴፓ ሕወሓትን ለመሆን በሚያደርገው ይሉኝታ አልባ መፍጨርጨር እና ሌሎቹ ደግሞ የኦዴፓን ሕወሓታዊ ጉዞ ለመግታት በሚያደርጉት ፍትጊያ የተሞላ ነው። የደቡብ ወኪል የሆነው ደኢሕዴን የደቡብ ሕዝቦችን የጋራ ሕልም አምክኖ ብሔረሰባዊ ዞኖችን ወደ ክልል ለማሳደግ እና ለመነጣጠል ተጋ። በክልልነት ጥያቄው ግዛት ማስፋት የደቡባዊ ብሔሮች እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሕልም ሆኖ ተነሣ። ደኢሕዴን ብሔረሰቦች ክልልነትን ሲጠይቁ የፓንዶራ ሳጥኑ ተከፍቶ መልሶ ለመክደን ቸገረው። ቀበሌዎች ወረዳ፣ ወረዳዎች ዞን፣ ዞኖች ክልል፣ ክልሎች ሀገር ለመሆን ምናባዊ ሕልም ጋገሩ። ኢሕአዴግም ይህን ሕልም ታቅፎ ከወንበሩ ተሰይሟል።

1.6 የአሳሪ እና የታሳሪ ኀዳዊነት

ለውጥ ከተባለበት ግዜ ጀምሮ ሌላው የተፈጠረው እንግዳ ነገር የታሳሪ እና የአሳሪ ኀዳዊነት ነው። ለውጡ ሥር-ነቀላዊ ሳይሆን አዳሽ በመሆኑ ነባሩንና አዲሱን አመራር አሰባጥሮ ይዞ ቀጠለ። የብሔራዊ ደኅንነቱ አለቃ የነበሩት አቶ ጌታቸው አሰፋ በአዴፓም ሆነ በኦዴፓ ያሉ አመራሮችን በማሰር ይታወቃሉ። በለውጡ ሰበብ ግን ሁለቱም ቡድኖች እኩል ኢሕአዴግ ተብለው ስለሀገር ሊመክሩ ተሰይመዋል።

ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ለዶክተር አብይ ድጋፍ ሰልፍ ሲደረግ ቦንብ ተወርውሮ ጥቂቶች ሙተው ብዙዎች ቆሰሉ። የዚህ ደርጊት አስፈጻሚ ደግሞ በሕወሓት በኩል አቶ ጌታቸው አሰፋ እንደሆኑ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ በሚዲያ ተናገረ። አቶ ጌታቸው ክስ ቢቀርብባቸውም፤ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ባጁ። ኢሕአዴግም የገዳይ እና የተገዳይ፣ የአሳሪ እና የታሳሪ፣ የአዛዥ እና የታዛዥ... የተቃራኒ ሕልመኞች ወንበር ሆነ።

በአዴፓ አመራሮች መካከል ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም የተፈጸመው ግድያም አንዱ የታሳሪ እና የአሳሪ ሕልማዊ ግጭት ውጤት ነው።

ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው ጽጌ በ1999 ዓ.ም. የሕወሓትን በወታደሩ በኩል ያለውን የበላይነት አቶ መለስ እንዲያስተካክሉ ነገሯቸው። አቶ መለስ በእብሪት ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው ጽጌን እስከማዕረጋቸው ገፈው አባረሯቸው። ከማባረር አልፈውም፤ ከየትኛውም መሥሪያ ቤት እንዳይሠሩ እና ወደ ውጭም እንዳይወጡ የቁም እስረኛ አደረጓቸው። ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው ጽጌ በአቶ መለስ እብሪት የተባረሩ የመከላከያ ኃይሎችን አሰባስበው በ2001 ዓ.ም. ያልተሳካ መፈንቀለ መንግሥት አደረጉ። በዚህም የዕድሜ ዘመን እስረኛ እንዲሆኑ ተፈረደባቸው። ከ9 ዓመታት በኋላ በሕዝብ ትግል በ59 ዓመታቸው በ2010 ዓ.ም. ከእሥር ተለቀቁ። ማዕረጋቸውም ተመለሰ። በ2011 ዓ.ም. መስከረም አጋማሽ የአዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኑ። በኋላም የአማራ ክልልን አስተዳደር እና ጸጥታውን በሓላፊነት እንዲመሩ ተሰየሙ። የአማራ ሕዝብ ትጥቁ ሕጋዊ እንዲሆንም ከአዴፓ ጋር ሆነው ከወኑ። የአማራ ብሔርተኝነትን እና የኢትዮጵያ ፖለቲካን መዳረሻ በማስላት የተሰጣቸውን ቢሮ ለመምራት ሞከሩ። የኢትዮጵያ ፖለቲካ መቋጫው ነፍጥ መሆኑን ተገንዝበው ወታደራዊ አደረጃጀታቸውን አፈረጠሙ።

ነገር ግን ጀኔራሉ በነባሩ እና በአዲሱ አመራር የአካሄድ ልዩነት ተፈጠረባቸው:: የጸጥታ መዋቅሩን ከታች እስከ ላይ በአዲስ ለማደራጀት አሰቡ:: በዚህ መሃል ነባሩ የጸጥታ ኃይል እና ሥሪቱ እንዲቀጥል የሚፈልገው የፖለቲካ አመራር አካሄዳቸውን ተቃውሞ ቆመ:: ጀኔራሉ ኢ-መደበኛ የሆነውን የፋኖ እና ልዩ ልዩ አማራዊ አደረጃጀቶችን ልብ ማረኩ:: ወጣቶች የአሳምነውን መንገድ ደገፉ:: የአዴፓ ሥርዓታዊ ዝንፈት በኢ-መደበኛ ብሔርተኛ አደረጃጅቶች ተሞርዶ የአማራ ፖለቲካ ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት መቆም መደገፊያ ባላ እንዲሆን ጣሩ::

ጀኔራሉ አንድ ቢሮ እየመሩ ከግማሽ በላይ ጥቅል የመንግሥትነት ድርሻ አገኙ:: የድርሻቸው መስፋት በአዴፓ አመራሮች ብቻ ሳይሆን በኢሕአዴግ ግንባሮች መካከልም ፍርሃትን ፈጠረ:: ጀኔራሉን ከሥልጣን ለማውረድም ሆነ በሰበብ ለማሰር ማኅበረሰባዊ መሠረታቸው አልፈቅድ አለ:: የግምገማ ብትርም ወረደባቸው:: ከሥልጣን ማባረር እስከ አላግባብ ኃይልን በመጠቀም በሚል ወንጀል ለመክሰስ ተሴረባቸው:: ይህ የተቃርኖ እና የጥርጣሬ መንገድ ክረቱን እያረዘመ ሂዶ የሰኔ 15ቱን መገዳደል ፈጥሯል::

በኢሕአዴግም ሆነ በአባል ድርጅቶች ያለው የእርስ በርስ ግንኙነታዊ እርከን የአጥፊ እና የጠፊ መደብን የያዘ ነው:: ይህ የፓርቲው ሽሪኮችን በርዕዮተ ዓለም እና በሀገራዊ ዓላማ ብቻ ሳይሆን ካድሬዎቹ በራሳቸው በግለሰብ ደረጃ እንኳን አብሮ ለመሥራት የሚያስችል ማኅበራዊ መደላድል እንደሌላቸው ያሳያል:: መደመር ከሚለው ዝርው ሐሳብ እስከ ኮሚኒስታዊው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስማሚ እና ተተንታኝ ሐሳብ ነጠፈበት::

አዴፓ የውስጥ ችግር ገጥሞት በሰኔ 15ቱ ክስተት ለመሰንጠቅ እያጣጣረ ባለበት ሁኔታ እንኳን ሕወሓት “**አዴፓ የትምክህት**

ኃይሉ መሰባሰቢያ በመሆኑ አብሬው ልሠራ አልፈቅድም» አለ። በሌላ በኩል ኦዴፓ ደግሞ የእዝ ሰንሰለቱ በፈቀደለት ሁሉ በርካታ አማራዎችን በሰበብ አስባቡ ማሰሩን ተያያዘው። የኢሕአዴግ ግንባሮች እና አጋሮች በአንዱ ሞት ላይ ሌላ ሕይዎት ለማኖር የሚሯሯጡ በኪሳራ ለማትረፍ የተገናኙ ቁማርተኞች ናቸው።

በሌላ ሐሳባዊ ጫፍ ደግሞ ኢሕአዴግን ከጫካ ስታሊናዊ እሳቤው ያወጡታል ተብለው የተጠበቁት ዶክተር አብይ አህመድ የአጀማመራቸውን የአቦሸማኔ የለውጥ ፍጥነት ወደ መስመር ሳያስገቡት ቀሩ። በጅማሯቸው ለዜግነታዊ ፖለቲካ (ከዘውግ ይልቅ ለአንድነት ፖለቲካ) የቀረበ ስልት ተከትለው ነበር። ይህም በሕወሓት ዘንድ በአሐዳዊነት ሲያስፈርጃቸው፣ በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ ደግሞ ‹‹የምኒልክ ግልገል›› የሚል ተቀጽላ ተቸራቸው። በዚህ መሃል ግን ለዶክተር አብይ አህመድ አካሄድ ቅርበት የነበረው የአንድነት ፖለቲካው ስትራቴጂ ቀርጾ ማኅበራዊ መሠረቱን ሳያስጠብቅ ቀረ። በነፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ግንቦት ሰባት ያለምንም መርህ ለውጡን እንደግፍ ብሎ እንደ ደርግ አጋሩ መኢሶን [15]በለውጥ ስም በኢሕአዴግ መዳፍ ውስጥ ሟሟ። የዜግነት(የሰውነት) ፖለቲካ አራማጅ ፖለቲከኞችም በዶክተር አብዩ ኢሕአዴግ ባልተጠና ድጋፍ ሥር ገብተው ተፎካካሪነታቸውን ዘንግተው ተቀመጡ። ክፉኛም ሟሸሹ።

የአማራ ብሔርተኝነት ለዶክተር አብይ አስተዳደር በጅማሬ ደረጃ ተመጋጋቢ ቢሆንም፤ ብሔርተኝነቱ መንግሥት ሳይሆን ቀርቷል።

---

[15] ግንቦት ሰባት ከኤርትራ የትጥቅ ትግል መልስ ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ.ም. ራሱን አክስሞ፤ የኢትዮጵያ ዜጎች ማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ብሎ ከሌሎች ዜግነት ተኮር ፓርቲዎች ጋር ተቀላቅሏል። ግንቦት ሰባት (ኢዜማ) ሕወሓትን መነሻ አድርጎ ብሔርተኞችን እያወገዘ ከቆየ በኋላ፤ የዶክተር አብይ አስተዳድር ከአክራሪ ብሔርተኝነት ጋር የተፋታ ይመስል ቅዋሜውን አበቃ። ብዙዎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች ትግል ሕወሓትን መጣል ብቻ መስሏቸው ተቸክለው ቀሩ። ይህም የዶክተር አብይ አስተዳድር ለውጡን በጽኑ መሠረት ላይ እንዳያነብረው/እንዳያስቀምጠው የማስነፍ አሉታዊ ሚና ተጫውቷል።

በአንጻሩ የኦሮሞ ኦነግ ቀመስ ብሔርተኝነት ከኦዴፓ ጋር በቀላሉ ወደ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት መንግሥት ሆኖ ቁሟል:: ኦነጋዊው የኦሮሞ ፖለቲካ ቤተ መንግሥት ቢገባም፣ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዥ ዓይን የማየቱ የቆየ ሥሪቱ መንግሥታዊ ባሕርይ እንዳይላበስ ተጽእኖ አሳድሮበታል::

የአማራን መንግሥት የሚመራው አዴፓ መነሻ ሥሪቱ ስላልፈቀደለት የአማራ ብሔርተኝነት ያነሣቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎች ሸሸ:: የአማራ ብሔርተኝነትም ሆነ የአንድነት ፖለቲካው ከንግርት ያለፈ ገቢራዊ ትርጓሜ አጠረው:: ይልቁንም በኦሮሞ የኦነግ ክንፍ፣ በትግራይም ሕወሓት፣ በደቡብ አዲስ የክልል እንሁን ጠያቂ ብሔርተኞች ጎልብተው ወጡ:: በዚህ ከበባ ውስጥ የገቡት ዶክተር አብይ የፖለቲካ የኃይል ሚዛኑ ወደወፈረበት ጫፍ ረገጥ ብሔርተኝነት አጋደሉ:: ጠቅላይ ሚንስትሩ ጫፍ ረገጥ ብሔርተኞችን በመሥጋት "አዲስ አበባ የአዲስ አበቦች ናት" ለማለት እንኳን ተሽኮረመሙ::

የኦሮሞ ፖለቲካ በአንጻሩ ከማዕከላዊ መንግሥቱ የተሻለ ጉልበት ያገኘ መስሎ ታየ:: ለውጡ ሕወሓትን በኦዴፓ የተካ የተረኝነት አሰላለፍ ተደርጎም ተተረጎመ:: ነገር ግን የኦሮሞ ብሔርተኝነት ቅኝቱ በዝቅተኝነት ደዌ የተመታ፣ መንፈሱም በቅኝ ተገዥነት ትርክት የጎለበተ ስለሆነ ሀገር እየመሩ ኦሮሚያ ክልልንም በዳግማዊ ምኒልክ ተከታዮች እናጣለን በሚል ሥጋት ውስጥ ወደቁ:: አድማሳቸውም ከኦሮሚያ ክልል ሊወጣ አልቻለም:: ለብሔርተኝነታቸው ስሑት ምክንያት ስላላቸውም፤ ብዙ ጊዜ የኦሮሞ ፖለቲካ አይመለሴ ጥያቄ አለው:: ፖለቲካቸውም ደንጋጣ በመሆኑ ከግጭት ሊወጣ አልቻለም:: የኦሮሞ ልሂቃን የኢትዮጵያዊነት ተረከዝ ያረፈበትን ዱካ ሁሉ በማጥፋት ኦሮሞ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ትዝታ አልባ እንዲሆን እያደረጉ ነው:: በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ ከሃይማኖት እና ከሀገር ይልቅ ኦሮሞነት በላጭ እና ገዥ መንፈስ ሆኖ ታትሟል::

1.7 የሸመገሉ ችግሮች እና የአዳሹ ለውጥ ተረከዞች

ኢሕአዴግ በሚከተለው የፖለቲካ መርሀ ህጸጽ የተፈጠሩ ከራሚ ችግሮች አድገው እና ሸምግለው ለዶክተር አብይ አስተዳደር ደረሱት:: ኢሕአዴግ ከትናንቱ እና ከነገው ጋር ሳይስማማ ከራሱ የተወለደው ችግር ከቁመናው በልጦ ሸፈነው:: የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሕልሙም የበለጠ ተንገራገጨ:: ለውጡም ለክሽፈት እጁን ሰጠ:: ኢሕአዴግ ሥራቱን አስጠብቆ ሲያሻው በሰላምታ፤ ሲመረው በጥፊ (carrot and stick approach) እየተማታ በሃዲዱ ተሳፍሯል:: የኢሕአዴግ ጉዞ ባለበት ያለሥርዓታዊ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ከቀጠለ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመቀጠል ሕልሟ ይቀጭጫል:: የኢሕአዴግ ተረከዝ የኢትዮጵያን ማኅበረ ፖለቲካ የረገጠበት መንገድ የጥላቻ እና የመመቃቀን ዱካ በየመንደሩ እንደ ጠዋት ጤዛ የሚጥል ነው::

ከኢሕአዴግ ምሥረታ ጀምሮ የተዘሩ የጥላቻ ቡቃያዎች ሲያሸቱ በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ሕዝቦች እንደ ፍልስጥኤም እና እስራኤል፣ እንደ አሜሪካ እና ሩሲያ፣ እንደ ኢራን እና ሳውዲ… ለጦር ይደባባሉ:: ሁሉም ከሁሉም ጋር አሸናፊ የሌለው ጦርነት መግጠሙ ቅርብ ይሆናል::

ወላዊ(የጋራ) የሆነ ሀገራዊ ሕልም እየከሳ ስለመጣ፣ ሀገራዊ አጀንዳዎች የቅቡልነት ፈተና ገጥሟቸዋል:: ለአብነት በትምህርት ዘርፉ በቋንቋ ማስተማር ጉዳይ ስምምነት ጠፍቷል:: ሀገራዊ ፈተናውም አጨቃጫቂ ሆኗል:: በቀጣይ ዓመታት ማዕከላዊ መንግሥቱን የሚያግባባ ቋንቋ ላይኖር ይችላል:: አንዱ ከአንዱ በቋንቋ መግባባት ካልቻለ ደግሞ የኢኮኖሚ እና የባህል ግንኙነቱ ሙሉ በሙሉ ይቋረጣል:: ሃይማኖቶች ሳይቀር ከሰውነት እና ከኢትዮጵያዊነት መደብ ወጥተው ብሔር ታከው መቆም ጀምረዋል:: ይህ የሀገረ

መንግሥቱ ማክተም ትልቁ ማሳያ ነው፡፡ ዘውጌዎች ብሔራቸውን ማንነት እና ዜግነት አድርገው ለማቆም የኢሕአዴግ መንገድ ምቹ መፍሰሻ ቦይ ሆኖላቸዋል፡፡ ሀገሪቱ የምትከተለው የፖለቲካ ትርክት ጎሰኝነት እና ዘውጌ ብሔርተኝነትን በጥላቻ በማወፈር አድማሳዊ እይታውም ከነገዳዊ ማንነት ያለፈ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በአካል እንጂ ያለችው በሕሊና ዩጎዝላቪያን እየሆነች ነው፡፡ ኢሕአዴግ ስሑት ተቋማትንና ሥርዓት በመፍጠር ስሑት ትውልድ ፈጥሯል፡፡ የኢሕአዴግ ስሑት ትውልድ እንደ ኢሕአዴግ ሀገር አያውቅም፡፡ ስለዚህ ትውልዱ ሀገር ለማፍረስ ቢነሣ የኢሕአዴግ ሥሪተ-ፖለቲካ ፍሬ ሆኖ ይመዘገባል ማለት ነው፡፡ ኢሕአዴግ የተሠራች ሀገር ተረክቦ የፈረሰች ሀገር ለተተኪው ትውልድ ሊያስረክብ ከምኒልክ ቤተ መንግሥት በር ላይ ተሰይሟል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

የስብራቱ አንጓዎች

2.1 ያልተጠገነው የታላቁ ስብራት መነሾ

የኢየሱስ ክርስቶስ እና ማርክስ ወንጌል የሚለያየው በአንድ ነገር ብቻ ነው። ሁለቱም ለድሆች(ለተገፉት) ዘብ ቢቆሙም፤ ልዩነታቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ገነትን በሰማይ ቤት ሲፈጥር፤ ካርል ማርክስ ገነትን በመሬት ላይ ለመዘርጋት ይሞክራል- ስብሐት።[16]

ከ1953ቱ የታኅሳሱ መፈንቀለ መንግሥት ያልተሳካ ሙከራ በኋላ የዘውዳዊው መንግሥት ክብር እየደበዘዘ[17]ሂዷል። በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የዐፄ ኃይለሥላሴ ምስል ተሰቅሎ ምዕመኑ [18]ይሰግድላቸው ነበር። የምድሩ ፈጣሪ ተደርገው ስለታሰቡ፤ እንኳን ታግሎ መጣል መተቸት ንስሐ አልባ ኃጢአት ተደርጎ ይታሰባል።

[16] ዘነበ ወላ፣ ማስታወሻ (2006 ዓ.ም.)

[17] ከሁለተኛው የጣሊያን የወረራ ሙከራ በኋላ በተለይም (ከማይጨው ጦርነት በኋላ) ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሽሽት ወደ አውሮፓ መኮብለላቸው የዘውዱ ክብር እንዲወርድ አድርጓል የሚሉ አሉ። በእርግጥም ከነጻነት በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን በጎጃም በነደጃዝማች አበረ ይማም እና በላይ ዘለቀ፣ በራያ እና አካባቢው የወያኔ እንቅስቃሴ፣ የባሌ ገበሬዎች ቅድመ አመጽ ስንመለከት በዘውዱ እና በመሳፍንቱ ላይ ማመጽ ቀደም ብሎ እንደተጀመረ ማየት ይቻላል። ለዲፕሎማሲ ነው ቢባልም፤ የኢትዮጵያ መሪዎች ወደ ውጭ ለማምለጥ መሄድን ሳይሆን በሀገራቸው ላይ መስዋዕትነትን መክፈል ልማዳቸው ነበር። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቁሞ ከመሞት ይልቅ በፖለቲካ ዲፕሎማሲ ጣሊያንን ለማንበርከክ ወደ አውሮፓ አቅንተዋል። ይህ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ በአርበኞች ዘንድ እንደ ክዳት እና ፍርሃት መቆጠሩ በመሳፍንቱ እና በዘውዱ ለማመጽ በሩን የከፈተ ይመስላል።

[18] አሰፋ ጫቦ አዲስ አድማስ ጋዜጣ 2011 ዓ.ም.።

በጃንሆይ ሹመኞች የተሞከረው ዙፋን የመንቀል ሙከራ ግን የዘውዳዊውን መንግሥት አይነኬነት ሽሯል። ለ13 ተከታታይ ዓመታት በተደረገው ዙፋን የማሳሳት ሂደት ተዛላዩን የየካቲት 1966 አብዮት ወልዷል።

ጃንሆይ በ1966 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም ሂደው ‹‹የሚወደን እና የምንወደው›› የሚሉት ሕዝባቸው ደፍሮ ቲማቲም ወረወረባቸው። ጥር 12 ቀን 1966 ዓ.ም. ደግሞ በአዲስ አበባ የቃና ዘገሊላን በዓል ከሩሲያው ጳጳስ ከአቡነ ፒሜንን[19] ጋር በማክበር ላይ እያሉ በታቦቱ ፊት የድንጋይ ናዳ ወረደባቸው። የዛኔው ወጣቶች ሽማግሌነት ጋር ብቻ ሳይሆን ከትናንት ጋርም ሥር ነቀል ጥላቻ ውስጥ ገቡ። ወጣቱ በሥነ-ቁሳዊ ማርክሳዊ ፍልስፍና ተሞልቷል። ሽማግሌው ደግሞ በመንፈሳዊ ግብረገብነት ላይ ፈዞ ቁሟል። የ1966ቱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የተቃርኖ ትንተና የሚጀምረው ከነዚህ ጫፍ ረገጥ አለመናበቦች ነው።

የዙፋን ንቅነቃው አጋፋሪ መንግሥቱ ንዋይ ወደ ሞት አደባባይ ሲገፋ ከኪሱ ውስጥ የተገኘው ደብዳቤ የተቃርኖውን ጫፍ የበለጠ ጎተተው።

“ከ40 ዓመት በላይ እድሜ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲገደል ወጣቱ ወስኗል”። የሚል ደብዳቤ ከመንግሥቱ ኪስ ተገኘ ተብሎ በኢትዮጵያ ራዲዮ[20] ተደጋግሞ ተነበበ። እድሜያቸው ከ40 ዓመት በላይ የሆናቸው ሁሉ የወጣቱን ንቅናቄ በዓይነ ቁራኛ ተመለከቱት።

---

19 ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

20 በኢትዮጵያ ሚዲያ ያሸናፊው ገረድ፤ ጋዜጠኛውም ሎሌ መሆኑ በትውልዶች መካከል ጥቁር ግርዶሽ ጥሏል።

በዚህ ትይዩ ወጣቱ አዛውንቱን እንደ ኋላቀር እና ወግ አጥባቂ ተመለከተው። የኢትዮጵያ ራዲዮ ያነበበው ዜና በጃንሆይ ሹማምንት፤ ወላጆች ልጆቻቸውን ከንቅናቄው እንዲመልሱ የተፈበረከ ፖለቲካዊ ውሸት እንጂ እውነት አልነበረም። በወቅቱ የመንግሥቱ ንዋይ አድሜ 44[21] ዓመት ሲሆን፤ በደብዳቤው መሠረት ራሱም ከሚገደሉት ዝርዝር ውስጥ ነው ማለት ነው። የትውልዱ መተላለፍ ቀጥሎ ወጣቱ ከወላጁ ጉያ እያፈተለከ ከማርክስ እና [22]ኤንግልስ ማስታወሻዎች ላይ ሰፈረ። ማርክስ እና ሌኒን ወጣቱን እንዲህ እያሉ መከሩት፤

"ሃይማኖት የገዥው ወገን ነው። የዘውዳዊው መንግሥትም የሥልጣን ማራዘሚያ አንቀላፊ ክኒን ነው። አደንዛዥ እጽም ነው[23]።" ማርክስ እና ኤንግልስ የካቶሊክ ሃይማኖትን የገዥው መደብ የጭቆና ቀንበር አድርገው ሲወስዱ፤ እነ ሌኒን እና ስታሊን ደግሞ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን አደንዛዥ እጽ አድርገው ወስደዋል። እነ ዋለልኝ መኮንን እና የዘመን ጓዶቻቸው ደግሞ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የአማራ እና የትግሬ የቅኝ መግዣ መሣሪያ››[24] አድርገው ወስደዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ መንግሥት ግንባታ እና ታሪክ ላይ ከ 3 ሺህ ዘመን የሚልቅ ወፍራም አሻራ ስላኖረች፣ ቤተ ክርስቲያኗን በጥላቻ መታከክ የሀገሪቱን ቀለም በቀጥታ ያደበዝዛል። ይህም አብዮቱን ከትናንት ጋር ጥል የገጠመ

---

21 ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

22 ሀብታሙ አለባቸው ታላቁ ተቃርኖ ባለው መጽሐፉ፣ በሌላ ሀገር ተሞክሮ ከኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሳይስማማ የተሞከረውን ኮሚኒዝም እንደ ታላቅ ሥነ እውቀታዊ ጥቃት ያሄሰዋል። ሀብታሙ የ1966 አብዮት ይዞት ከመጣው ወታደራዊ ጥቃት በላይ ሥነ እውቀታዊ መጣረሱን (epistemological violence) እንደ ታላቅ ሀገራዊ የእሳቤ ስብራት ይመለከተዋል።

23 The communist manifesto

24 The struggle magazine, nov17, 1969)

እና ከነገ ጋርም የማይስማማ ትዝታ አልባ ትውልድ እንዲበቅል ስሑታዊ መንገዱን አስፍቷል።

ኮሚኒስቶች የጋለ ርዕዮተ ዓለማቸውን በበቀል አቡክተው፤ በጥላቻ ለመጋገር ቀይ ቀለምን ምርጫቸው አደረጉ። በቤተ ክርስቲያን ቀይ ቀለም ጌታ በቀራንዮ አደባባይ ሲሰቀል፣ ሰማዕታት እና ጻድቃን ለሃይማኖታቸው ሲሰቃዩ ላፈሰሱት ደም መታወሻ ሆኖ በብራና ክታቦች ላይ ይሰፍራል። ኮሚኒስቶችም መንፈሳዊውን ብያኔ ቁሳዊ አድርገው ፊውዳሎች እና ዐዔዎች በወዛደሩ እና በጭሰኛው ያደረሱትን ሰቆቃ ለመዘከር ቀይ ቀለምን መረጡ። በዛውም በባላባቱ እና በገባሪው መካከል ሁሉም እኩል ነው። የሰው ልጅ በሙሉ የፊት ቆዳው ቢለያይም ደሙ ቀይ ነው ለማለት እና ኅብረተሰባዊ ጋርዮሻዊ አብዮትን ለመትከል ተጠቀሙበት። ከዛም ዓለም በቀይ ሽብር፣ በቀዩ ጦር፣ በቀዩ አርሚ... እያለ ደምን በደም ለመመለስ እነ ስታሊን ሚሊየኖችን ይረሽኑ ዘንድ አብዮቱ ገፋቸው። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም[25] መስቀል አደበባይን አብዮት አደባባይ ብለው የእንጎቻ ስም ካደረጎቱት በኋላ የሦስቱ ሥላሴ ምልክቶችን/ ስእል ደግሞ ማርክስ፣ ኤንግልስ እና ሌኒን ብለው የክርስትና ስም አወጡ። በዚህ አደባባይ በጠርሙስ ደም እየደፉ የቀይ ሽብር ዘመቻን በኢሕአፓ ላይ አወጁ። የምኒልክ ቤተ መንግሥትም በምርጫ ካርድ ሳይሆን በበቀል በቀለመ ደም የሚገባበት ሆኖ ልማዳዊ ታሪኩን ጻፈ።

---

25 *ባሕሩ ዘውዴ መንግሥቱ ንዋይን እና መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ሁለቱን አብዮተኛ እና ወታደራዊ ስመ ሞክሸዎች ሲያነጻጽሩ፤ መንግሥቱ ንዋይን የመጨረሻውን መጀመሪያ ሞክሮ የወደቀ አብዮተኛ አድርገው ይወስዱታል። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ግን እንደ ንዋይ ልጅ ችኩል ሳይሆን እውነተኛ ስሜቱን፣ ውጥኑን እና ዳራውን በመሸፈን ብልጥ ሆኖ በተማሪዎች የበሰለውን አብዮት እንደ ሩሲያው ስታሊን ገናና ሆኖ ሊመራው ችሏል። መንግሥቱ የሰዎችን እና የሁኔታዎችን አዝማሚያ መገምገም መቻሉ፣ በወቅቱ ፖለቲካ ሥልጣን ከጠመንጃ ብቻ እንደሚመነጭ አውቆ ጉልበትን መጠቀሙ ኅብረተሰባዊ አብዮቱን አውራ ሆኖ እንዲመራው አስችሎታል።*

2.2 ከመደብ ወደ ብሔር

ሶሻሊዝምም ሆነ ኮሚኒዝም በመሠረተ ሐሳቡ በመደብ ትግል ጭሰኛውን ነጻ ማውጣትን ታላሚ ያደረገ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መርሆ ነው፡፡ የትግል መሠረቱም ‹‹እያተረፉ የሚድሩትን ትራፊ ከሚለቅሙት ደሀዎች ጋር ማመጣጠን እና ጋርዮሻዊ ኅብረተሰብ መፍጠር ነው፡፡›› ዓለምን በፍትሃዊነት መደልደል የማርክስ ፍልስፍና ፍሬ ነገር ነው፡፡ የደርግን ኮሚኒዝማዊ ጽንሰ ሐሳቦች ወደ አማርኛ በመመለስ የሠራው ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ‹‹ማርክስ ገነትን በመሬት ላይ ለመዘርጋት ታግሏል›› የሚለው ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ በመነሣት ይመስላል፡፡ በ1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተነሡት የፖለቲካ ቡድኖች ብዙኃኑ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ስቧቸው ኮሚኒዝም ማርኳቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሕልም አለፍ ሆኖ ገቢራዊ መሆን አልቻለም፡፡ በእርግጥም በደሀ ሀገር ገነትን በመሬት መዘርጋት ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን የማርክስ ተከታዮች በሰማይ የኢየሱስ ክርስቶስ ገነትን ከመፈለግ ይልቅ በምድር የካርል ማርክስን ገነት ለመፈለግ ሻቱ፡፡ ኮሚኒዝም በባሕርይው ከሃይማኖት ጋር ሙሉ በሙሉ ሰማኒያ ቀዶ/ተፋትቶ ፍልስፍናውን ለማንበር የሞከረውም በዚህ ለሰው ቅርብ በሆነ ሥነ ቁሳዊ ፍልስፍናው ምክንያት ነው፡፡

በአውሮፓ እ.ኤ.አ በ1750 በተቀሰቀሰው የኢንዱስትሪ አብዮት ጥቂት ከበርቴዎች ጸጋውን ይዘው፤ ብዙዎቹ ለከበርቴዎች ሠራተኛ ሆኑ፡፡ በዚህ ምክንያት የከበርቴ (ቡርዣ) እና የደሀ ወይም የገባር ሥርዓት ተፈጠረ፡፡ በትውልድ ጀርመናዊ፤ በዘር አይሁዳዊ የሆነው ካርል ማርክስ በግለሰብ መደቡ ከጭቁኑ የሚመደብ ነው፡፡ የወረቀት እና የብዕር ገንዘብ ስለሌለው ማስታወሻ እንኳን የሚይዘው በአካል ክፍሎቹ ላይ እየጫረ (እየጻፈ) ነበር፡፡ የራሱ ሕይወት የፍልስፍና ዋቢ የሆነው ማርክስ ዓለም የሠራተኛው መደብ ነው፡፡ ለዚህ

ደግሞ የሶሻሊዝም ሥር-ነቀላዊ አብዮት ያስፈልጋል የሚል ምክረ ሐሳብ አፈለቀ፡፡

በአሜሪካ የሠራተኞች መብት እንዲከበር፤ የሥራ ሰዓትም ከ8 ሰዓት እንዳይዘል፣ ክፍያም በአግባቡ እንዲሆን ተደርጎ አብዮቱ በጠጋኝነት አልፎ ካፒታሊዝምን አንብሮ አለፈ፡፡ በምሥራቅ አውሮፓ እና በኤስያ ግን የፊውዳሊዝም እና የካፒታሊዝም ሥሪት በሥር ነቀል አብዮት ተነቀለ፡፡ ማርክስ ኮሚኒዝም ለድሀ ሀገር አይሆንም የሚል እሳቤ ቢኖረውም፤ እነ ሌኒን እና ማኦ ዘዱንግ በድሀ የሩሲያ እና የቻይና ገበሬ ላይ በጉልበት ጫኑበት፡፡

በእርግጥ በዓለም ላይ የኮሚኒዝምን ጫፍ የረገጠ ሀገረ መንግሥት በትክክል አልተፈጠረም፡፡ ከኮሚኒዝም በፊት በሶሻሊዝም ዜጎች፤ በወጣቶች፣ በሠራተኞች፣ በጾታ፤ በየሙያው ተደራጅተው ኅብረተሰባዊነትን መገንባት አለባቸው፡፡ የበለጸገው ሶሻሊዝም ኮሚኒዝምን ወልዶ ዓለም ምንም የመደብ ልዩነት የሌለባት ለሰው ልጆች ሁሉ በፍትሃዊነት የታደለች ገነት ትሆናለች፡፡ የማርክስን ካፒታል መጽሐፍ ለነኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተረጎመው የወቅቱ የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት አርታኢ ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ‹‹የማርክስ ሐሳብ ገነትን በምድር ለመዘርጋት ያለመ ነው›› የሚለው ከዚህ ሁሉ መነሻ ነው፡፡ ኮሚኒዝም እና ሶሻሊዝምን የተረዳው ልሂቅ ብዙ እንዳልነበር ስብሐት ታዝቧል፡፡ እንግሊዝኛውን እንኳን የሚረዳው ጠፍቶ ተንሻፎ እና ሰዎች በሚያውቁት እና በሚፈልጉት እያስጠጉ ይተረጉሙት እንደነበር ስብሐት በአርታኢነቱ አሂሷል፡፡ የ1966ቱ አብዮት የአውዳሚነቱ እና የክሹፍነቱ አንዱ መንስኤም የእነማርክስ ይዘተ ነገር እና የኢትዮጵያ ነባራዊ እሴት እርቅ አለመፈጸሙ ነው፡፡

ኅብረተሰባዊነት ወይም ኮሚኒዝማዊነት በራሱ በፍልስፍናው የጥፋት መንገድ አይደለም:: ዋናው የአተገባበር ሂደቱ አለመስተካከል ነው:: ቻይናም በሶሻሊዝም አድጋለች፤ አሜሪካም በካፒታሊዝም ተመንድጋለች:: ርዕዮተ ዓለምን ከንድፈ ሐሳቡ ይልቅ አተገባበሩ አሻራማ ያደርገዋል:: ሀገሪቱን ወደ ውድቀት የገፋው ሶሻሊዝም ወይም አብዮታዊ ዴሞክራሲ በራሱ በንድፈ ብቻ ሐሳቡ አይደለም:: ችግሩ እንዲተገበር የተፈለገበት ዓላማ እና የሀገሪቱ ነባራዊ እሴትን ንዶ ለመተግብር የተሔደበት አውዳሚ አካሄድ ነው::

ባልበለጸገ ሀገር ውስጥ ኮሚኒዝምን ማስፈን ድህነትን በፍትሃዊነት ማደል ነው:: ደርግ በእዝ ኢኮኖሚው ሀብታሙንም ድሀውንም እኩል ድሀ ከማድረግ ያለፈ ኢኮኖሚያዊ እመርታ ብዙ አላመጣም:: ደርግ ኢትዮጵያ ትቅደም እያለ የመደብ ትግል ውስጥ ገባ:: መሳፍንቱ እና ባለእርስት ጉልቱ የደርግ ባላንጣዎች ሆኑ:: ፓርቲውንም የሠራተኞች ፓርቲ ብሎ ጭሰኛ ተኮር መሆኑን አሰመረ:: ደርግ በተማሪዎች የተነሣውን መሬት ላራሹን በመደብ ትግል ለመፍታት ሲሞክር፤ የብሔርን እና የዴሞክራሲን ጥያቄ ዝግ አደረገው:: ደርግ የዘጋውን ለመክፈት የብሔር ድርጅቶች እንደ ጫጩት እየተፈለፈሉ ወደ ጫካ ተሰማሩ:: ደርግ በኢትዮጵያ ያለው ጭቆና የመደብ ነው ብሎ ማኅበራዊ እርከኑን ለመሙላት ሰፈራ፣ የመንደር ምሥረታ እና የመንግሥት እርሻ ላይ ተሰማራ:: የደርግ ተፎካካሪ ኃይሎች ደግሞ በኢትዮጵያ ያለው ጭቆና የአማራ ብሔራዊ እንጂ የመደብ አይደለም ብለው ማንነታዊ ፖለቲካን ለመዘርጋት የዜግነት ፖለቲካን ደፈቁት:: የማንነታዊ ፓለቲካ መንስኤዎች ሁለት ፈርጆች[26] ሊሆኑ ይችላሉ::

[26]Ali REZA, Identity Poltitics acase study of Afghanistan, The university of Sydney

ሀ) ሥነ ቁሳዊ ማርክሳዊ አተያይ

ይህ አተያይ እየጎለበተ የመጣው ከማርክስ ሥነ-ቁሳዊ ፍልስፍና በኋላ ነው፡፡ ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረው ባህል እና ማኅበራዊ ተራክቦውን በበላይነት ይመራዋል የሚል ጽንሰ ሐሳብ ያስተጋባል፡፡ በባህል የበላይነት የያዙ ቡድኖች ሌሎች የብሔራዊ ወይም የጎሳ ቡድኖችን ሊያገሉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በተገለሉ ቡድኖች እና ኢኮኖሚውን በተሸከሙት ዘውጋዊ ማንነቶች መካከል የሚደረግ ፍትጊያ ማንነታዊ ፖለቲካ (identitiy politics) እንዲጎለብት አድርጓል፡፡ ማንነታዊ መዋቅር ይዘው ኢ-ፍትሃዊ የሆነ የምጣኔ ሀብት እድገት ለማንነታዊ ፖለቲካ መነሣት እርሾ ጥሏል፡፡ ብሔሮች የቡርዣው መደብ ከሆኑ ከጭቁኑ ማኅበረሰብ ጋር የገባሪ እና የአስገባሪ ስልተ መንግሥት ሊፈጠር ይችላል የሚል አመክንዮ ይነሣል፡፡

ለ) ሰብዓዊያን ዝንባሌዎች

ሰብዓዊያን እንቅስቃሴዎች ለማንነታዊ ፖለቲካ መነሾ ይሆናሉ፡፡ በሰዎች ዘንድ የሚደርስን ግፍ እና በደል በመቃወም የሚጀመር ንቅናቄ ለማንነታዊ ፖለቲካ ጉልበት ይሰጣል፡፡ ለአብነት የነማርቲን ሉተር ኪንግ እና የነ ማርክስ ጋርቤ የጥቁር ንቅናቄን ተከትሎ የሰው ልጆች ሁሉም እኩል ናቸው፤ የሚል የነጠረ እውነት እንዲወጣ አድርጓል፡፡ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በዘር.. ልዩነቶች ምክንያት የሚደርስን በደል እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ለመቃወም መነቃነቅ በሰብዓዊ ምክንያት ለሚገነባ ማንነት መነሻ ይሆናል፡፡ ነጻ የመውጣት የአፍሪካ ብሔርተኝነት ንቅናቄ የጥቁር ማንነትን እና አፍሪካዊነትን ፈጥሯል፡፡

በኢትዮጵያ የተቀነቀነው ዘውጋዊ ብሔርተኝነት ‹‹ባህል እና ወጌን እስከ ኢኮኖሚው አማራው ወስዶብኛል›› ከሚል ስሑት ሥነ-ቁሳዊ ፍልስፍና የሚነሣ ይመስላል፡፡

ያገሩን ሰርዶ፣ ያላገሩ በሬ

የራሱን ምናባዊ ዓለም ፈጥሮ የኖረው ደራሲ አቤ ጉበኛ ከጃንሆይ ውድቀት በኋላ ለልጁ ጥቁር እና ነጭ ተቃራኒ ካልሲዎችን በአንዴ ያለብሳል። አቤ ለምን ተብሎ ሲጠየቅ ‹‹አሁን የምንኖርበት ሶሻሊዝም እና ሀገራችን (ዓለም) እንዲህ የማይገናኙ ናቸው›› ብሎ መለሰ።[27]አዎ። ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ ተረክዙን ያሳረፈበት መንገድ የተተከለውን በመንቀል ስለነበር ኢትዮጵያዊነትን ሳያጸድቀው ቀርቷል። ነቅሎ መትከልም የፖለቲካው ባሕርይ ሆኗል።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1950ዎቹ ለአፍሪካውያን ነጻነት ለሚታገሉ 200[28] ለሚደርሱ የአፍሪካ ተማሪዎች ነጻ የትምህርት ፈቃድ ሰጥተው በያኔው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ያስተምሩ ነበሩ። እነዚህ ተማሪዎች ኢትዮጵያዊ ተማሪዎችን ስለ ትግል እና አብዮት ሐሳብ አበድረዋቸዋል። ኬንያውያን ተማሪዎች ከእንግሊዝ ነጻ ለመውጣት ሲታገሉ ኢትዮጵያውያኑ ደግሞ ከኢትዮጵያ ነጻ ለመውጣት በብሔራቸው ስም ነጻ አውጭ ግንባር አደራጁ።

ኢሕአፓ በጥቅምት 1917 የሩሲያ አብዮትን እንደመራው የነሌኒን ቦልሼቪክ ፓርቲ ሕዝብን አነቃነቀ። ጥቁሩ ቦልሼቪክ ተባለ። ከ1964 እስከ 1972 ዓ.ም. የኢትዮጵያን ፖለቲካ ማንጸሪያ ሆኖ እንደተጓዘ በቀይ ሽብር፣ በፓርቲው ውስጥ በተፈጠረ ልዩነት፣ ከነሕወሓት ጋር በነበረው ቅራኔ ተዳክሞ ከሰመ። ኢሕአፓ የፖለቲካ ፖርቲነትን ካስተማሩ ድርጅቶች መካከል ቀዳሚ ከመሆኑ ባለፈ የፖለቲካ ስደትን በይፋ የጀመረም የፖለቲካ ንቅናቄ ነው። የመተማ ሱዳን መንገዶች በኢሕአፓ ስደተኞች ተሞልተው ከርመዋል። ከዛን ጊዜ

[27]ኤሊያስ አያልነህ፤ የአቤ ጉበኛ ብዕራዊ ተጋድሎ

[28] Nicole Stremalu,the press and the political restructuring of Ethiopia

ጀምሮ የስደት ፖለቲካ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አየር እያጣበጠው መጥቷል:: ይህ ‹‹ከሀገር ውስጥ ሆኖ አፋኝ ቡድንን መታገል አይቻልም›› የሚል ቅስም ሰባሪ መልእክት ከማስተናገዱም ባለፈ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መዳፈሩ አይቀርም::

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በተደጋጋሚ ነፍጥ አንጋች ተቃዋሚዎቻቸውን "ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር አብረው ሀገር ሳይኖራቸው ሀገር ለመምራት የሚታገሉ እንቆቅልሾች" ይሏቸዋል::

ለአብነት የጀብሀ ጽሕፈት ቤት ሊቢያ፣ ሳውዲ፣ ኢራን እና የመሳሰሉት ሀገራት ሲሆን የሕወሓትም ሆነ የኦነግ ማዘዣ ጣቢያ ሱዳን እና ሱማሊያ ነበሩ:: ሶማሊያ በ1971 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ስትወር የደርግ ተቃዋሚዎች ሞቃዲሾ ነበሩ:: ሱዳንም በተለያየ ጊዜ በመተማ በኩል ወረራ ለመፈጸም ስትዳዳ እነ ሕወሓት እና ሻዕቢያ ካርቱም መሽገዋል::

ደቡብ ሱዳን በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም በኩል የኢትዮጵያ ፍጡር ናት ማለት ይቻላል:: ለምን ቢባል ካርቱም የኢትዮጵያ[29]አማፂዎችን ስታሰለጥን በምላሹ ደርግ የደቡብ ሱዳን አማፂዎችን በጋምቤላ ብሎም በአዲስ አበባ ጽሕፈት ቤት በመክፈት አሰልጥኗል:: ከኢትዮጵያ አማፂዎች መካከል ሻዕቢያ በ1985 ዓ.ም. በይፋ ኤርትራን ሲገነጥል፣ የሱዳን ነጻ አውጭዎች ደግሞ ደቡብ ሱዳንን በ2003 ዓ.ም. አካባቢ ገነጠሉ:: በሴራ ፖለቲካ ምክንያት ከ1985 እስከ 2004 ዓ.ም. ምሥራቅ አፍሪካ ላይ ብቻ ሁለት ሉዓላዊ ሀገራት ተፈጥረዋል:: እነዚህ አዲስ የተፈጠሩ ሀገራት በሴራ ስለነበር ሰላምም ሆነ ልማት በዓይናቸው አላዩም:: የካርቱም ፍጡር የሆነችው ኤርትራ ከፈጣሪዋ ጋር ነፍጥ መዘው እስከ መታኮስ ደርሰዋል::

[29]ዶክተር ቴዎድሮስ ኃይለ ማርያም በኩር ጋዜጣ፣ ታኅሳስ 29 ቀን 2011 ዓ.ም.

ሱዳን ደርግን ለመጣል ስትል እስከ ሽግግር መንግሥቱ ድረስ አደራዳሪ ሆና ቀጥላ ነበር:: በኦነግ እና በሕወሓት መካከል ቅራኔ ሲነሣ ሽምጋይ ሱዳን ሆና እስከ 1984 ዓ.ም.[30] በነበረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ የቀጥታ ተጽዕኖ ማሳረፍ ችላለች:: የኢሕአዴግ ፖለቲካም በመሠረቱ ከምዕራባውያን ይልቅ የዓረባውያን እና የምሥራቃውያን ሀገራት ሚና ይጎላበታል::

ሻዕቢያ፣ ሕወሓት፣ ኦብነግ፣ ኦነግ፣ ኢሕአፓ… ወዘተ መሠረታቸው ዓረቡ ዓለም እና ለዓረቡ ዓለም ቅርብ የሆኑት የአፍሪካ ሀገራት ናቸው:: ደቡብ ሱዳን በአንጻሩ በምዕራባውያን እና በደርግ ስለምትደገፍ፤ የኢትዮጵያ የነገድ አማጺዎች የካርቱምን ኩርፊያ ተጠቅመው መወዳጀት ችለዋል::

በኢትዮጵያ እገዛ ሀገር የሆነችው ደቡብ ሱዳን በጋምቤላ በኩል ከኢትዮጵያ በኩል ሌላ ሥጋት ይዛ መጥታለች:: በአብዛኛው ጋምቤላ ክልል በአኝዋክ እና በኑዌር ብሔረሰቦች የተዋቀረ ክልል ነው:: አንዳንድ ኑዌሮች መነሻችን ደቡብ ሱዳን ነው ይላሉ:: ደቡብ ሱዳን ያሉ ኑዌሮችም የጋምቤላ ኑዌሮች የኛ ናቸው ይላሉ:: በዚህ መሃል ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር በዝቶ የኑዌሮች ቁጥር ከአኝዋኮች ጨምሯል:: አኝዋኮች በሕዝብ ብዛት ስብጥር አናሳ እየሆኑ ነው:: በደቡብ ሱዳን የብሔር ግጭት ምክንያት ወደ ጋምቤላ የሚተሙ ስደተኞች ቁጥራቸው እየጨመረ ሂዶ ጋምቤላ ዋና ከተማየ ጁባ እንጅ አዲስ አበባ አይደለም ልትል[31] ትችላለች::

---

[30] ዶክተር ዲማ ነገዎ፤ የኦነግ የመጀመሪያው ሊቀመንበር ኢሳት መስከረም 9 ቀን 2012 ዓ.ም. ከሰጡት ቃለ መጠይቅ ሐሳብ ተወስዷል::

[31] ሚያዚያ 7 ዓርብ ቀን 2008 ዓ.ም. ሙርሌ የተባሉ የደቡብ ሱዳን ጎሳዎች ወደ ጋምቤላ ድንበር ተሻግረው ገብተው 208 ጋምቤላዎችን ሲገሉ፣ ከ100 በላዮችን ደግሞ አግተው ወደ ደቡብ ሱዳን ተሻግረዋል:: የታገቱ ሕጻናት ብዙዎቹ ሳይመለሱ ቀርተዋል:: በወቅቱ ብዙ ከብቶችም ተዘርፈዋል::

በእርግጥ ምሥራቅ አፍሪካ የተመሠረተው በቅኝ ገዥዎች የፖለቲካ ፍላጎት እንጂ በሕዝብ ዝምድና አይደለም። ቢሆንማ አፋር ከኤርትራ እና ከጅቡቲ አፋር ጋር ሆኖ አፋር የተባለ ሀገር ወይም ክልል ይመሠረት ነበር። ሶማሌው ከሞቃዲሾው፣ ከአርጌሳው፣ ከጅግጅጋው፣ ከኬንያው ሶማሌ ጋር ኅብረት ፈጥሮ ሀገር ሆኖ ይቆም ነበር። ትግሬውም ከኤርትራው ትግሬ፣ ኦሮሞው ከኬንያው ኦሮሞ ጋር ኅብረት እየፈጠረ በዝምድናው ተማድቦ ሀገር ወይም ክልል ለመሥራት የሚያግደው ነገር አልነበረም። ነገር ግን ሀገርና ታሪክ የፖለቲከኞች የእጅ ሥራ ነው። ሀገር በቋንቋ ብሔራዊ ዝምድና ሳይሆን በፖለቲካ አስተዳደር ይጸናል። ማኅበረሰቦች ሁሉ የፖለቲከኞች የእጅ ሥራዎች ናቸው። ማኅበረሰብና ሀገር የፖለቲከኞች የእጅ ሥራ ናቸው ካልን ደግሞ፣ በውጭ ሆነው የሚታገሉ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ድርጅቶች የሚታገሉበትን ሀገር ፖለቲካ ሊሸከሙ ስለሚችሉ ለኢትዮጵያ ህልውና ፈታኝ ይሆናሉ።

ከኢትዮጵያውያን ነባር እሴት የሚበቅል፣ ሀገር ሠራሽ ፖለቲካ ለመፍጠር በውጭ የሚደረጉ ትግሎች አስቻይ መንገዳቸው የጠበበ ነው። በልዩ ልዩ ውጫዊ ፍላጎቶች የተጠለፈ ስለሚሆን ሀገር በቀል ፖለቲካ ለመሥራት አዳጋች ሊሆን ይችላል። የ1966ቱ ፖለቲካ ‹‹ቆርቋሪ ተረከዙን›› በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ያሳረፈበት ምክንያት የሐሳብ ምንጩ ሀገር በቀል አለመሆኑ ነው። አዲሱን ሐሳብ በግድ ለመትከል በሚደረግ ፍትጊያ ምክንያት መገዳደል፣ መፈራረጅ እና መጠራጠር የኢትዮጵያ ፖለቲካ መልክ ሆነ።

2.3 የኢሕዴን ተረከዞች

ከኢሕአፓ የተሸረፈው ኢሕዴን የኢሕአዴግ ነርብ ነው:: ኢሕአዴግ የኖረው በኢሕዴን የድርድር ጠረንጴዛ ላይ ነው:: በ1983 ዓ.ም. ሽግግር መንግሥቱ ወቅት ቢያንስ ኢትዮጵያ የሚል ስም የኖረው በኢሕዴን መኖር ምክንያት ነው:: ከኢሕዴን ኦሕዴድና ዴኢሕዴን ተፈልፍለዋል:: ኢሕአዴግ የተመሠረተው በኢሕዴን አማካኝነት ሲሆን፤ እነ ኦነግ፣ ሕወሓት፣ ኦብነግ እንደ ቀዳሚ ዓላማቸው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ያከትምላት ነበር::

ከ37ቱ መሥራቾች መካከል አንዱ የሆኑት አቶ ያሬድ ጥበቡ ‹‹ወጥቶ አልወጣሁም›› ብለው በሰየሙት መጽሐፋቸው ኢሕዴንን በሁለት ጉዳዮች ለኢትዮጵያ ፖለቲካ በረከቱን አሳርፏል ይላሉ::

ሀ) ሕወሓትን ከጠባብ ብሔርተኝነቱ ማውጣቱ[32]

የሕወሓት ቀዳማዊ ሕልሙ ትግራይ የተባለች ሀገር መመሥረት ነበር:: የወታደሩ አስተምህሮም ስለ መገንጠል፤ የሚታገለውም አማራን እንደሆነ ነበር:: ሕወሓት ከኢሕዴን ጋር ሆኖ ደርግን በ1982 ዓ.ም. ደብረ ታቦር ላይ ሆኖ ሲዋጋ 30ሺህ የሕወሓት ሠራዊት ትግሉን አቋረጦ ወጥቷል:: ምክንያቱም ትግራይ ነጻ ከሆነች ሌላው የሌላ ሀገር ነው የሚል ወታደራዊ አስተምህሮ በሕወሓት የፖለቲካ መስመር ቀድሞ አብቧልና:: ኢሕዴን(ብአዴን) ከሕወሓት ጋር ጥምረት ፈጥሮ በ1981 ዓ.ም. ኢሕአዴግን ፈጥሯል:: ኢሕአዴግ መፈጠሩ ደግሞ ኢትዮጵያን ከመበታተን አድኗል:: ያ ወቅት በሀገሪቱ በሁሉም አቅጣጫዎች ነጻ አውጭዎች የገነኑበት ወቅት በመሆኑ ኢትዮጵያ እንደ ዩጎዝላቪያ ወደ ብዙ ሀገር ልትከፋፈል እንደምትችል ያሰጋ ነበር:: በምሥራቅ ኢትዮጵያ የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር፣ በማዕከላዊና ምዕራባዊ የኢትዮጵያ

[32] ያሬድ ጥበቡ ወጥቼ አልወጣሁም፣ የሩብ ክፍለ ዘመን ዋይታዎች ከ1983 እስከ 2008 ዓ.ም.

ክፍል የኦሮሞ ነጻነት ግንባር፣ በደቡብ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ… ወ.ዘ.ተ ከሚታወቁ የነጻነት ግንባሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በዚህ መሃል ኢሕዴን የኢትዮጵያን ሕዝቦች ብሎ በአካታችነቱ መነሣቱ በሕወሓት ላይ የአቋም እድገት እንዲያሳይ አድርጐታል። ኢሕአዴግ ደግሞ ከጥምረቱ በኋላ የነጻነት ግንባሮችን እስከ ብሔር ቁጥራቸው ሰብስቦ በሰፊው የኢትዮጵያዊነት የፖለቲካ ማዕድ እንዲቋደሱ አድርጓል።

በወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 39 የመገንጠል መብት መታወጅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ግዛት የሚመለከት ኃይል ለማሰባሰብ ሲከፋህ ትሄዳለህ እስከዚያው አብረን እንኑር ብሎ ማለዘቡ የፖለቲካ ልክነት አለው። የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 39 ችግር የሚሆነው ሀገሪቱ እንደተረጋጋች በመግቢያው ያተተው አንድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ዓላማን ለማስፈን ፈጥኖ ማሻሻያ አለማድረጉ ላይ ነው።

ሕገ መንግሥት ተለዋዋጭ የሰው ልጅ የማኅበራዊ ዕድገት እና የዓለም ነባራዊ ሁኔታ እንዲቀየር ያስገድደዋል። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ሳይቀየር መቆየቱ አንድም የተፈጥሮ የሰው ልጆችን መቀየር የሚቃረን ሲሆን፣ ሌላም ሕገ መንግሥቱን እንደ ዘውዳዊያን መንግሥታት የማይሻርና[33] የማይለውጥ ገዥ መንፈስ አድርጐ የመቁጠር ዝንባሌ ነው። ሕገ መንግሥት የሰውን ልጅ መብት አሳውቆ የገዥዎችን ሥልጣን ለመገደብ የሚወጣ የአንድ ሀገር

[33] የደቡብ አፍሪካ ሕገ መንግሥት ከነጮች አገዛዝ በኋላ እ.ኤ.አ በ1996 ከወጣ በኋላ ለ17 ጊዜ ተሻሽሏል። እ.ኤ.አ ከ1789 ጀምሮ እየተተገበረ የሚገኘው የአሜሪካ ሕገ መንግሥት ለ 27 ጊዜ ማሻሻያ ተደርጎበታል። ሕግ ከሰው ልጅ እድገት እና ለውጥ ጋር መሻሻል ተፈጥሮአዊ ባሕርይው ነው። አሜሪካ ቀደም ባሉት ሕጎቿ አሥር ባሪያን እንደ ስድስት ዜጋ ትቆጥር ነበር። የጥቁሮች መብትም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተገደበ ነበር። ነገር ግን ከ1920ዎቹ ጀምሮ የጥቁሮች ንቅናቄ አሜሪካ የምትተገብራቸውን ኢ-ሕጋዊ ሕጎችን በነማርቲን ሉተር አማካኝነት እንዲሰርዙ ሆነዋል። የሕገ መንግሥት መሻሻል ሐሳብ የሚመነጨውም ከእንደዚህ ዓይነት የማኅበራዊ ፖለቲካ እድገት ነው።

ዜጎች ተስማምተው የሚያጸድቁት የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። ሕገ መንግሥት ሕግ ሆኖ የሚገዛው በሕገ መንግሥቱ የሚተደደሩበትን ሕዝቦች እስከ ጠቀመ ድረስ ብቻ ነው።

ለ) ከኢሕአፓ ተፈልፍሎ ለሥልጣን መብቃቱ

አቶ ያሬድ እንደ ኢሕዴን ወፍራም ስኬት የሚመለከቱት ሌላው ጉዳይ የጥቁሩ ቦልሼቪክ መሪ እየተባለ ከሚሞካሸው ከአብዮተኛው ኢሕአፓ ወጥቶ ደቃቂ እና ማኅበራዊ መሠረቱ የላላው ኢሕዴን ለሥልጣን መብቃቱን ነው። ኢሕአፓ በውስጥም በውጭም ታክቲክ እና ስትራቴጅ ጉሎት የፖለቲካ ጉዞውን ከ1972 ዓ.ም. በኋላ ገትቷል። ልክ ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ በምርጫ 97 ፈጥሮት እንደነበረው አብዮት ኢሕአፓ በ1960ዎቹ መጨረሻ ቅቡልነት ያለው ንቅናቄ ፈጥሮ ነበር። ከዚህ ንቅናቄ አንጻር ኢሕዴን ከዝሆኑ ሥር የወጣ እንቁራሪት ነበር። እንቁራሪት ሆኖም ግን ከ1973 እስከ 1983 ዓ.ም. ለአሥር ተከታታይ ዓመታት ያህል በትግል ቆይቶ፣ ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ከሕወሓት ጋር ተቀጥሎ ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ገስግሷል። ገስግሶም ለዘብተኛ ሆኖ በአክራሪ ብሔርተኞች ገመድ ጉተታ ኢትዮጵያ እንዳትቆራረስ ማሠሪያ ሐረግ ሆኖ አገልግሏል። ብአዴን በአማራ ዋጋ ላይ ኢትዮጵያ እንዳትቆራረስ በመሃል ሰፋሪነቱ አድኗል።

በ1982 ዓ.ም. ኦነግ፣ ትሕነግ፣ ኦብነግ፣ ሲአን… ሁሉም ከኢትየጵያ ነጻ አውጭ ግንባሮች በነበሩበት ጊዜ ኢሕዴን ባይኖር ኖሮ ኢሕአዴግም የመፈጠር እድል ሊኖረው አይችልም። ኢትዮጵያም ታሪክ ልትሆን ትችል ነበር። በእርግጥ የኢሕአዴግ ሥሪትም ጊዜ ይሰጣል እንጂ ኢትዮጵያን የሚያድን አይደለም። ሥሪቱ በተራዘመ ሂደት ኢትዮጵያን እንድትመክን የሚያደርግ ነው።

2.4 የኢሕዴን ተረከዛዊ ስብራቶች

ሀ) ምሁር ጠልነት

ኢሕአፓ ትግሉ በንድፈ ሐሳብ (dejure)[34] ደረጃ እንደ ቻይናው ማኦ ዘዱንግ ገጠርን ማዕከል ያደረገ ሆኖ፤ በተግባር (defacto) ግን የትግል ማዕከሉን የተከለው በከተሞች ነው:: የከተማው ታጋይ ኢሕአፓ የከተማ ታጋይነቱ እንደጣለው ስላወቀ ኢሕዴን በተቃራኒው በገጠር ፍቅር ወደቀ:: የትግል መሠረቴ ከ80 ከመቶ በላይ የሆነው አርሶ አደሩ ነው አለ:: በ1983 ዓ.ም. መጨረሻ ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ሲገባ የፖለቲካ ሀ፣ሁ... ያልቆጠረውን በመሪነት እና በአባልነት አቀፈ:: በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት አቀንቃኞችም ሆኑ የአማራ ልሂቃን ይቀላቀሉት ዘንድ ክፍት አልሆነላቸውም:: በምትኩ ሕወሓት ፖለቲካን መተንተን በሚችሉ የቢሮክራሲ እና የፖለቲካ ምህዋሩን ሞላው:: ይህ አጋጣሚ ሕወሓትን ብቸኛ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ማመንጫ ጋን አደረገው:: ኢሕዴንም በቀጥታ ከትግርኛ ወደ አማርኛ እያስተረጐመ ፖሊሲና መመሪያ ለአማራው ያወርድ ጀመር:: አቶ ያሬድ ጥበቡ በመጽሐፋቸው እንደመዘገቡት በ1981 ዓ.ም. አቶ ታምራት ላይኔ ‹‹የኢሕዴን ማርክሲስት ሌኒኒስት ኃይል›› ብለው ካቋቋሙት ጅምር ሥራ ውጭ፤ በኢሕዴን ሰዎች የፖለቲካ መርሆ ተነድፎ አያውቅም::

---

34 በሕግ እና በፖለቲካው ዓለም በሰፊው አገልግሎት ላይ የሚውሉት ዲጁር (de-jure) እና ዲፋክቶ(de-facto) የሚሉት ቃላት ምንጫቸው ላቲን ነው:: ዲጁር በሕግ ታውጆ በተግባር ግን የሌለ ውክልናን ሲያሳይ፤ ዲፋክቶ ደግሞ ሕጋዊ ዕውቅና ሳይኖረው በተግባር ግን ውክልና (ኃላፊነት) ይዞ የተገኘ አካልን ያመላክታል::

ምሁር ጠልነቱን ኢሕዴን እንደሰነፍ ተማሪ ኮራጅ፣ አስመሳይና በራስ የመተማመን አቅሙን የተዳከመ አድርጐታል። ጋዜጠኛ ተስፋየ ገብረአብ የደራሲው እና የጋዜጠኛው ማስታወሻ በሚሉት ሁለት ጥራዞቹ በተደጋጋሚ ስለ ኢሕዴን(ብአዴን) ካሰፈራቸው የኩረጃ ሐሳቦች መካከል የምሥረታ ቀኑን ያነሣል። ተስፋየ እንደሚለው 11 ቁጥር በጃንሆይ ዘመን ትግሬዎች ከቅንድባቸው አካባቢ ይወቀሩ ነበር። የትግራዋይነት መገለጫም ሆኖ ተቀርጿል። ከዚህ ትውፊታዊ ተረክ በመነሣት ሕወሓት 11 ልዩ ቁጥሬ ናት ብሎ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም. ምሥረታውን አደረገ። ብአዴንም ከኅዳር 7-11 ቀን በ1973 ዓ.ም. ተሰብስቦ ምሥረታውን በኅዳር 11 ቀን አጸና። ይህን የቁጥር ጨዋታ ከኩረጃ ጋር ያያይዘዋል። ኢሕዴን ለአማራ ክልል የሰጠው ሰንደቅ ዓላማም ከሕወሓት የተኮረጀ የኮሚኒስት አርማ ነው። አማራ ብሎም ሌላው የኢትዮጵያ ክፍል በብዛት አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው ሰንደቅን ምርጫው ያደርጋል። ነገር ግን የወቅቱን የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም መገለጫ የሆነውን በቀይና በኮከብ ያሸበረቀ ሰንደቅ ዓላማ ምርጫው አድርጓል። ብአዴን የሚለው ስያሜም ለሕወሓት ቃና የቀረበ ስያሜ ነው። በአማርኛ ቢሆን ኖሮ ‹‹የአማራ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(አብዴን)›› ይባል ነበር። ብአዴን ስሙን በ2011 ዓ.ም. የቀየረበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ሰበብ ነው።

ሕወሓት በትግራይ ክልል በበጐ አድራጐት ስም ኢፈርት (Effort-Endowment fund for the Rehabilation of Tigray) የተባለ ኩባንያ ሲመሠርት ኢሕዴን (ብአዴንም) ለአማራ ክልል ‹‹Effort›› የሚለውን ወደ አማርኛ መልሶ ‹‹ጥረት›› የሚል ኩባንያ በ1988 ዓ.ም. አቋቁሟል።

ኢሕዴን የኦሮሞው ኦሕዴድ(ኦዴፓ)፣ የደቡቡ (ደኢሕዴን) ሁሉ ምንጭ ነው። ብዙዎች የኢሕዴን አባላት የሁሉም ሕዝብ

ስብጥር ስላላቸው ኦነግን ለመመከት ኦሕዴድ፣ እንደነ ሲዳማ አርነት ንቅናቄ ያሉትን የደቡብ ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ትክሻ ለትክሻ ለመቆም ደኢሕዴን፣ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ በፕሮፌሰር አሥራት የሚመራው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) ጉልቶ ሲወጣ ከኢሕዴን-ብአዴን ተፈልፍሏል። በእርግጥ ኢሕዴን በአመዛኙ በአማራው ክፍለ ግዛት አካባቢ ሲንቀሳቀስ ስለነበር ብዙውን የብአዴን እጅ ነው። ይሄን ያህል የሀገሪቱ የስበት ማዕከል የሆነ ድርጅት ምሁር ጠል በመሆኑ እንዳለው ማኅበረሰባዊ መሠረት ሳይጠናከር በደካማነቱ ላይ ሆኖ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ላይ አሻራውን አስቀመጠ።

መጋቢት 1985 ዓ.ም. 42 ምሁራን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲባረሩ ኢሕዴን የወቅቱ የትምህርት ምኒስትር በነበሩት በወይዘሮ ገነት ዘውዴ በኩል ቀዳሚ ፈራሚ ነበር። በብዛት የተባረሩት ደግሞ አማራዎች መሆናቸው ሲታይ ኢሕዴን ራሥነት የሌለው ብኩን ድርጅት እንደነበር መታዘብ ይቻላል። ብአዴን የተማረ ጠል በመሆኑ የዳግማዊ ምኒልክ አልጋ ወራሽ ቢሆንም፣ አስገባሪ ሳይሆን ገባር ለመሆን ተገዷል። ገባሪ በመሆኑም፣ ፖለቲካ ለብአዴን የዕለት እንጀራ የሚበላበት የሙያ ቅጥር እንጂ የፖለቲካ ሹመት አይመስለውም። ብዙዎቹ የብአዴን አባላት አባልነት እንደ ሥራ ቅጥር መፈጸሚያ ፋብሪካ እንጂ ዓላማ እንዳቀፈ ፖለቲካዊ ድርጅት አይመለከቱትም ነበር።

ለ) ንቅላዊ ማንነት

የብአዴን መሪዎች በብዛት የሚመሩትን ሕዝብ የሚመስል ሥነ-ልቦናዊ ባሕርይ አልነበራቸውም። እንዲያውም ከሚመሩት ሕዝብ ባሕርይ በተቃራኒ ማዶ የቆሙ ሆነው ይታያሉ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ኢሕዴን ኅብረ ብሔራዊ ስለነበር አካታችነቱ ያለብሔራዊ ማንነት ማሰባሰብ ችሎ ነበር። ይህ ግን በጠላትነት ለተፈረጀው

አማራ ሕዝብ መድኅን ለመሆን አያስችልም። ብዙዎች አማራው ሲፈናቀል በትምክህተኛ ባሕርይው ምክንያት ነው ብለው ምላሽ ይሰጣሉ። የሽግግር መንግሥቱ ወቅት የብአዴን ሊቀመንበር ብሎም የሀገሪቱ ጠቅላይ ምኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ በየመድረኩ ‹‹ነፍጠኛው፣ ትምህክተኛው›› እያሉ ለሌላ ብሔረሰብ አባላት አማራን በጠላትነት ለማስፈረጅ ይናገራሉ።

ብአዴን በጉዞው እንደ ስኬት የሚገመግመው የአማራ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት እና ያመጣውን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ነው። ትምክህተኝነትን እና ነፍጠኝነትን መዋጋቱንም እንደ ድል ያቀርበዋል። ትምክህተኛ ጠልነቱን በተግባር ደግሞ ሽለላ እና ፉከራ እንዳይሰማ የባህል ጭቆና አድርጓል። ባንዳንድ ወረዳዎች ምኒልክ፣ ቴዎድሮስ፣ ንጉሥ፣ ግዛቸው፣ በላይ… ብሎ ስም ማውጣትን ሁሉ አውግዟል። የአማራ ክልል ኮሚኒኬሽን ሓላፊ የነበሩት አቶ ንጉሡ ጥላሁን በ2008 ዓ.ም. ለተወለደው ልጃቸው ምኒልክ ብለው ስም አውጥተው እንደተገመገሙበት እና አጀንዳ ሆኖም ብአዴን የትምክህት ኃይሉን እንዳላጸዳ ተደርጎ እንደተወነጀሉበት ራሳቸው ሲያወሩ ሰምቻለሁ። ቴዎድሮስ ካሳሁን ጥቁር ሰው ብሎ ስለምኒልክ ያዜመው በሚዲያ እንዳይተላለፍ ከማድረጉ በተጨማሪ በ2007 እና በ2008 ዓ.ም. ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስለሰላም በሚሰጥ ሥልጠና በሰነድ አትሞ አውግዟል።

የብአዴን ሰዎች በብዛት በሥነ-ልቦና ደረጃ የታጠበ ጭንቅላት (Brain wash) ስላላቸው እውነት የሚመስላቸው አሸናፊ[35]ላይ ያለው ነበር።

---

[35]ከተሰብሳቢዎች አንዱ እንደነገረኝ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ግጨውን በተመለከተ ውሳኔ ለማሳለፍ ጉባኤ ይጠራል። ሕወሓትም በግጨው ጉዳይ የራሱን ማዕከላዊ ኮሚቴ ይሰበስባል። ብአዴን ሕወሓትን ለማስደሰት ግጨው የትግራይ ክልል ነው ብሎ ወሰነ። ሕወሓትም ለሃቅ ብሎ ግጨው የአማራ ክልል ነው አለ። ሕወሓት የብአዴንን ውሳኔ እንደሰማ እንደገና ስብሰባ ጠርቶ ግጨው የትግራይ ነው ብሎ ወሰነ። ብአዴንም ግጨውን ሸለመ። መተከል የሚገኘውን የፓዌ ልዩ ወረዳንም በ2001 ዓ.ም. ከልዩ ወረዳነት አሳልፎ የሰጠው ብአዴን ሲሆን፤ ከሸዋ ደራን ወደ ኦሮሚያ ክልል እንዲካለልም አድርጓል። የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ነሐሴ 19 ቀን 2008 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ስለወልቃይት ተነሥቶ የብአዴን

ለዚህም ይመስላል ለማሸነፍ ሳይሆን አሸናፊን በመከተል የፖለቲካ ጀምበራቸውን አምሸተው ያነጉት። ከታጠበ ሥነ-ልቦና ባሻገር ግን ብዙዎች በሥነ-ልቦና ስበት ከሌላ ብሔር ፍላጐት ጋር የሚሔዱ ናቸው። ከ1960ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ብሔራዊ ማንነት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሆኖ ተቀርጿል። ከዚህ ትንታኔ አንጻር ከተመለከትነው አማራ ከፍላጎቱ በተቃራኒ በሆነ በአጥቂው ርዕዮተ ዓለም ሲመራ ባጅቷል ማለት ይቻላል። ብአዴን ከዚህም ከዛም ያልሆኑ ንቅል ማንነት ባላቸው ሰዎች መመራቱ የኢትዮጵያ ብሔርተኞችንም ሆነ የአማራ ብሔርተኝነትን ሳይጠጋ በመሃል ላይ መቆሙ የተዋፅኦ ፖለቲካ መሙያ ብቻ አደረገው።

ብአዴን በተለይም ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ የተወሰነ ሞገስ ያገኘው በያዘው ማኅበረሰባዊ መሠረት ነበር። በጦርነቱ አይደፈር የነበረውን የሻዕቢያ ምሽግ ቀድሞ በመስበር፣ ጠላትን በመማረክ፣ ባለመክዳት እና በጦርነቱ ባሳተፈው የወታደር ብዛት አማራ የመጀመሪያው እንደነበር ያሬድ ጥበቡ ‹‹ወጥቶ አልወጣሁም›› በሚለው መጽሐፋቸው መዝግበዋል። ጎጃም ባሕር ዳር አካባቢ መራዊ ከተማ የተወለደው ዋሴ ገላ እና ደብረ ማርቆስ አካባቢ የተወለደው ቀሬ ደጉ የተባሉ ከአርሶ አደርነት የወጡ ወታደሮች የገዛኢ ሥላሴ ምሽግን በመስበር ለኢትዮጵያ የድል መንገዱን ቅርብ አድርገውታል። በዚህ ድል ምክንያት ብአዴን በኢሕአዴግ ግንባሮች የተሻለ ሞገስ እንዲያገኝ ቢያደርገውም፤ ድርጅቱ በራሱ ተክለ ቁመና ተገልጾ ወደ ፊት ለመምጣት አልቻለም። ጀግና ሕዝብ በደካማ መሪ መወከልም የአማራ እጣ ሆኖ ዘልቋል።

ወኪሎች አቶ በረከት ስምኦን እና አቶ አዲሱ ለገሰ ‹‹ወልቃይት የትግራይ ነው፤ ይሄን በማለታችንም በትምክህተኞች ዋጋ ከፍለናል። በተለይ አቶ አዲሱ በወልቃይት የሚኖር ምንም ዓይነት አማርኛ ተናጋሪ የለም ሲሉ ደምድመው እንደተናገሩ ሕወሓቱ ብርሃነ ጽጋብ የኢሕአዴግ የቁልቁለት ጉዞ (ከ2005 እስከ 2010) የስብሰባዎች ወግ ላይ ጽፏል።

አማራ እንደማኅበረሰብ የጕሰኝነት አደረጃጀት የለውም። በጐሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በልዩ ልዩ አቅርቦት ለመደራጀት ሥነ-ልቦናው ብዙ አይፈቅድም። አማራ ለረጅም ዓመታት የሥነ-መንግሥታዊ ባህል ስለነበረው እጠቃለሁ የሚል ሥጋት አላዳበረም። ይሄም በራሱ ማንነት እንዳይሰባሰብ አድርጎታል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሥርዓት ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ በይፋ ሲቃወም ዘውዳዊውን ሥርዓት በልዩ ሁኔታ የኔነው የሚል ስሜት አላዳበረም። በጐጃም[36] በተለያየ ጊዜ የገበሬ አመጾች ሲደረጉ መነሻቸው የሥርዓት ብልሽት ነበር። ደጅአዝማች በላይ ዘለቀ ገና ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ የመሳፍንቱን ሥርዓት ተቃውሞ እስከ መሰቀል ደርሷል። አማራው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሥርዓት እስኪወድቅ ድረስ ተቃውሟል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ መታጠፊያ በር የሆነው የ1953ቱ መፈንቅለ መንግሥትም የተመራው በሸዋ እና በጐንደር ሹመኞች ነበር። የደሴ ወይዘሮ ስሂን ትምህርት ቤት የመሳፍንቱን አገዛዝ እንዲወድቅ የትግል ማዕከል ሆኖ አገልግሏል። ይህ ሁሉ ትግል ታዲያ መዳረሻ ነጥቡ አማራው በተለየ ተጨቁኗል የሚል ሳይሆን የኢትዮጵያ ምቹ ሥርዓት መፍጠርን ታላሚ ያደረገ እንደሆነ መታዘብ ይቻላል። አማራ እንደ ማኅበረሰብ ከዘውግ ብሔራዊ ስሜት ይልቅ የራሱ

---

[36] የባሌ እና የቀዳማዊ ወያኔ የገበሬ አመጾችን እንደ ብሔር ትግል ተመልክተው ዘውዳዊው መንግሥት በብሔሮች ላይ ያደረገው ጭቆና ማሳያ አድርገው የሚተነትኑ ብሔርተኞች አሉ። የቀዳማዊ ወያኔ እንቅስቃሴን ሕወሓት በትግራይ ለደረሰ ብሔራዊ ጭቆና የተደረገ አብዮት አድርጎ ይወስዳል። ሕወሓት በትግርኛ ቋንቋ ‹‹ወያኔ›› የሚለውን የቀዳማዊ ወያኔን እንቅስቃሴ ስያሜ ተጠቅሞ ብሔርተኝነቱን አጎልብቶበታል። ወያኔ የራያ አካባቢ አብዮት ስለነበር የራያን ሕዝብ ለመያዝም ተጠቅሞበታል። ትክክለኛ የሕወሓት መጠሪያ በአማርኛ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር-Tigray Pepole Liberation Front (tplf-ትሕነግ ነው)። የባሌ እና የወያኔ የብሔር ጭቆና ወለድ አመጾች ከሆኑ፣ የጎጃም ገበሬዎች አመጽም ለምን ብሔር ተኮር አልሆነም? የጎጃም ገበሬዎችን አመጽ አማራ ተጨቁኗል ላለማለት ብዙዎች ያልፉታል። በጥቅሉ ግን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተደረጉ የገበሬ አመጾች የብሔር ጭቆና ወለዶች አልነበሩም። የገበሬ አመጽ በአካባቢያዊ አስተዳደር ብልሽት የሚመጣ፣ ግልጽ ዓላማ እና ግብ የሌለው፣ ዓለም አቀፋዊ ትብብሩ የላላ እና ከአካባቢያዊ የእለታዊ ችግር የሚነሣ ነው። በእርግጥ የባሌ ገበሬዎች አመጽን ሶማሊያ የሃይማኖት ቅርጽ ለማስያዝ ስትሠራበት ነበር።

የሆነ ማኅበረሰባዊ መደብ አለው:: መደቡ ከባህላዊ ኑባሬ የሚፈልቅ ነው:: አማራ እንደ ማኅበረሰብ ዕድገቱ ተዋረዳዊ[37] ነው::

ሕጻን፣ ሽማግሌ፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ሽማኔ፣ ገበሬ፣ ፋቂ፣ ጨዋ፣ ቄስ ወይም ሽህ.... የሚሰጣቸው የክብር ደረጃ አለ:: በዚህ ተዋረድ መሠረት ሥልጣንና ሀብት ተደልድሏል:: በቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ የመሬት ከበርቴዎች ሥልጣን ነበራቸው:: በደርግ ደግሞ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቅሪቶች ተብለው ወደ ሥልጣን አልመጡም:: በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ያልነበራቸው እና በማኅበረሰቡ የሚከበሩ በደርግ ወደ ሥልጣን መጡ:: በኢሕአዴግ ደግሞ በጃንሆይም ሆነ በደርግ ሥልጣን ያልነበራቸው በማኅበረሰቡ በብዛት የሚናቁ እና ክብር የሚነሣቸው ሰዎች የብአዴን አባል ሆኑ:: ስለዚህ ብዙ የብአዴን አባሎች በአማራ ባለው ማኅበረሰባዊ እርከን የተጨቆኑ የሚመስላቸው ስለሆኑ የጨቋኙ ማኅበረሰብ አለቃ ሆነው የተሾሙ ይመስላቸዋል:: ዘወትራዊ መፈክራቸውም በአማራ ገዥ መደብ የተጨቆን የጭቁኑ የአማራ መደብ አካል ነን የሚል የሽንፈት ዜማ ያሰማሉ::

አማራ ጠልነታቸው የሚመነጨውም ከዚህ ንቅል ማንነት ነው:: ከንቅል ማንነት የሚመነጩት የብአዴን አባላት በአማራነት ከመኩራት ይልቅ አማራውን ማዋረድ ምርጫቸው ሆነ:: ለአማራነት የሚሞቅ ወኔም ከዳቸው:: የአማራን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚውል ፖለቲካዊ ርዕይ ስለሌላቸው፤ የፖለቲካ አሰላለፋቸው በአውራጃዊነት የታጠረ ሆነ:: ብአዴኖች በብዛት አማራዊ ማኅበረሰባዊ እሳቤን የተላበሱ ሳይሆኑ፤

[37]አማራ ዝምድናን በችሎታ እንጂ በማንነታዊ ቅርበት አይመሠርትም። ወደ ካፒታሊዝም ፍልስፍና የተጠጋ የአኗኗር ዘይቤ አለው። ብሔርተኝነት ከንጥል አተያይ ይልቅ ደቦአዊ አተያይን ስለሚያስቀድም ወደፊት አማራ ማኅበረ ኑባሬው ቡድናዊ ተራክቦው የጎለበተበት እንደሚሆን አያጠራጥርም። ማኅበረሰብን ፖለቲካ ያንጸዋል። የአማራ የብሔር ፖለቲካ አማራውን አማራነትን እንደመሰባሰቢያ ጥላ ይጠቀምበታል። ይህ ስልተ ፖለቲካ አማራውን ወደ እኛነት አስተሳሰብ ይመነዝረዋል።

ከማኅበረሰባዊ ወላዊ እሳቤ የተነቀሉ ግለሰቦች[38] ናቸው። አማራ በቡድን በሚመራ ሀገር ውስጥ በግለሰቦች በመመራቱ ማኅበረሰባዊ ጥቅሙ ሳይጠበቅለት ቀርቷል።

ይህ የሥነ-ልቦና ሥሪት ብአዴንን ከኢሕአፓ እስከ አዴፓ ድረስ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ተጉዞ እግሩ እንዳይጸና አደረገው። ያሽናፊው ሁሉ ገረድ አደረገው። ብአዴን (አዴፓ) በ1999 ዓ.ም. የሕዝብ እና ቤት ቆጠራ የአማራ ሕዝብ ከትንበያው እና መሆን ከነበረበት ወደ 3 ሚሊየን የሚጠጋ ሕዝብ ቁጥር ተቀነሰበት። ይህ የሕዝብ ቁጥር ብዛት ከሀገር የነኳታርን ሕዝብ ቁጥር ሁሉ ይበልጣል። ከክልል ደግሞ የጋምቤላ፣ ሐረሬ፣ አፋር እና ቤንሻንጉል ክልል ሕዝቦች ተደምረው የጠፋውን የአማራ ሕዝብ ያክላሉ። ስለዚህ ለአማራ ክልል ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ በየዓመቱ የአራት ክልሎችን የሚያህል ዓመታዊ በጀት ይቀነስበታል።

የጠፋው የአማራ ሕዝብ ቁጥር በ1999 ዓ.ም. 2.4 ሚሊየን አካባቢ እንደሆነ በፓርላማ ተነግሯል። ይህ ቁጥር በየዓመቱ ያድጋል።

[38]ብአዴን ከማኅበረሰባዊ የወል ጥቅም የተዛነፈ በመሆኑ ግቡም ግለሰባዊ ነው። በመሆኑም ሥልጣንን ለግለሰብ በሚሰጠው ፋይዳ ለክቶ በአበልጅ፣ በአምቻ ጋብቻ፣ በወንዜነት፣ በቅርርብ እና ተዛምዶ... ያድላል። ይህ ባሕርይው አማራነትን አማራዊ ሕልም ጋግሮ ለማቆም ሲቸገር ተስተውሏል። ወንዜነቱ አይሎበት በሰኔ 15ቱ ክስተት አለመተማመኑ ሲፈትነው ተስተውሏል። ብአዴን መንግሥት በመሆኑ ባሕርይው በቀላሉ ወደ ሕዝብ ይወርዳል። ወደ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ወደ ፖለቲካ ልሂቃንም ተዛምቶ አብንም ከብአዴን በተሻገረ ወንዜነት ተፈትኗል። የአማራ ፖለቲካም በወንዜነት ታስሮ ወደላይ ወጥቶ ወንበር ለመሳብ ቁመት አጥሮት ቆይቷል።
የወንዜነት ምንጩ ግለሰብነት ነው። ወንዜነት ልክ እንደመሳፍንቱ ዘመን በየአካባቢው ግለሰቦች ለመሳፍንነት የሚሯሯጡበት የግዙፍ ዓላማ እጦት ነው። ዘመነ መሳፍንትነት የሰሜኑ ክፍል በዐፄ ቴዎድሮስ፤ የደቡቡ ደግሞ በዐፄ ምኒልክ ሙሉ በሙሉ ከትሟል። ዐፄ ምኒልክ የአካባቢውን መሳፍንት ገዝፈው ባይጫኑት ኖሮ አካባቢያዊ የእርስ በርስ ጦርነት መነሳሣቱ አይቀርም ነበር። የጅማው ከከፋው፣ የወለጋው ከጉሙዙ፣ የሐረሩ ከሶማሌው.... ወዘተ መጠቃቃታቸው አይቀሬ ነበር። ዐፄ ምኒልክ ሁሉንም በአንድ እዝ ማስገባታቸው አግድሞሻዊ ጦርነቱን አምክኗል። ከዐፄ ቴዎድሮስ እና ምኒልክ አብራክ የወጡት የዚህ ዘመን የፖለቲካ ልሂቃን 150 ዓመት ወደ ኋላ ተጉዘው የተሠራ አፍርሰው የአካባቢ ጌታ ለመሆን ወንዜነትን መታከክ አብዝተው ታይተዋል። ወንዜነት አግድሞሻዊ ትግል በመሆኑ ፓለቲካዊ ድንክነትን (poltical dawarfism) ይፈጥራል።

ነገር ግን የጠፋ ወይም ያልተመዘገበ አያድግም። የ1999 ዓ.ም. ቆጠራን ብቻ ብንመለከት 2.4 ሚሊየን ሕዝብ በ100ሺህ ሕዝብ ተደልድሎ ቢሠራ 24 ወረዳ ይሆናል። ወረዳዎች የምክርቤት ወኪል አላቸው። አማራ 24 ወኪሎች ተቀንሰውበታል ማለት ነው። ወይም አንድ ወረዳ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አለው። በዚህ ስሌት አማራ 24 ሆስፒታሎችን አጥቷል። አማራ ከቁጥር መጉደሉ ከመሠረተ ልማት እና ከፖለቲካ ውክልና ብዙ ነገር እንደሚያጎልበት ቢታወቅም ብአዴን ይሄን ለማረም እንኳ አልቻለም። በመሠረተ ልማት ሸዋ ከጎጃም፣ ወሎ ከጎንደር እንዳይያያዝ ስለተደረገ ከአማራነት ይልቅ የአማራ መልክዓ ምድራዊ አሃዶች ማንነት ሆነው ወጥተዋል። ለአማራነትም ወንዜነት ፈተና ነው።

ሰፊ መልክዓ ምድር ያለው ሕዝብ የጋራ ማንነት እንዲገነባ በመሠረተ ልማት መተሳሰር አለበት። ትግራይ በዚህ በኩል በመሠረተ ልማት የተያያዘ እና መልክዓ ምድሩም ጠባብ በመሆኑ ትግሬነት የነጠረ ማንነት ሆኖ ወጥቷል። በኦሮሚያ ክልልም ኦሮሞነትን በክልሉ ለማስረጽ ገና የሚጣረሱ ፍላጎቶች አሉ። ኦሮምኛ ቋንቋ ለኦሮሞ መደበኛ ሆኖ ስላልወጣ በወለጋው እና በሐረሩ፤ በሸዋው እና በአርሲው መካከል ልዩነት አለው። ይሄ ሁሉ መጥበብ የሚችለው የጋራ ኢኮኖሚያዊ ገበያ በመፍጠር ነው።

አማርኛ የፖለቲካ ቋንቋ ስለሆነ በአንድ የበየዳ፣ የሸበል በረንታ፣ የአማራ ሳይንት፣ የምንጃር ወረዳ አርሶ አደሮች መካከል ከ99 በመቶ በላይ እኩል መግባባት ይችላሉ። የአማራ ፈተናው በመሠረተ ልማት የተበጣጠሰ መሆኑ የጋራ ሥነ-ልቦናን አጎልብቶ አማራነትን እኩል ከመልበስ ጋር የተያያዘ ነው። ለዚህ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ መገለሉ መንስዔ ነው። ብአዴን አማራነትን በአካላዊ ገጽታም ሆነ በሕሊናዊ መልክ መገንባት አልቻለም። አማራነት የተበተነ

ገና ያልተሰበሰበ ማንነት ሆኗል። አማራነት በኢትዮጵያዊነት ማሕቀፍ ሥር የሚሟ ማንነት ስለሆነ፤ በአማራነት ለመሰብሰብ አስቸጋሪነት ይኖረዋል። አማራነት የተበተነ ማንነት ሲኖረው፤ እንደ ትግራይ፣ ኦሮሞ እና መሰል ብሔሮች ደግሞ በቋንቋቸው ዙሪያ ተሰባስበው የታጨቀ ማንነት አዳብረዋል። የታጨቀ ማንነት ለዜግነታዊ(ሀገራዊ) እይታ የሳሳ ስሜትን ይሰጣል።

በአንጻሩ ብትን ማንነት ለሀገራዊ መልክ ወዝ ሆኖ ይወጣል። ነገር ግን የተበተነ ማንነት በቀላሉ ተሰባስቦ ፖለቲካ ኢኮኖሚውን ስለማይመራ የታጨቀ ማንነት ባላቸው ይቀደማል። ሥጋት አልባ በመሆኑም ለመደራጀት ስለሚያመነታ ፖለቲካው ላይ መግነን አይችልም። የአማራ እና የብአዴን(የአዴፓ) መሠረታዊ ችግርም ከዚህ ሃቅ ይቀዳል። አዴፓ ብትን ማንነት ስላደበረ ራሱን በኢትዮጵያዊነት እና በአማራነት ደብዛዛ ቀለሞች ይገልጻል። አዴፓ ደማቅ ቀለም እንዲኖረው ከተፈለገ ወይ አማራነትን አጠናክሮ ወደ ኢትዮጵያ መሄድ፤ ካልሆነም ጨርሶ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ መሆን ይጠበቅበታል። በብዛት ብሔርተኝነት አንድ ነው። በአንዴ የአማራ እና የኢትዮጵያ ብሔርተኛ መሆን አይቻልም። ብሔርተኝነት ለራስ ለሆነ ነገር በሞቀ ፍቅር ውስጥ መውደቅ ነው። ለራስ ማድላት ነው። ለራስ የተጋነነ ግምት መስጠት ነው።

ብሔርተኝነት የተጋፊነት ባሕርይ ስላለው በቀላሉ የዴሞክራሲያዊ ቅርጽ መያዝ አይችልም። ደርግ አክራሪ የኢትዮጵያ፤ ኢሕአዴግ ደግሞ አክራሪ ዘውጋዊ ብሔርተኞች በመሆናቸው ለዴሞክራሲ ሊገዙ አልፈቀዱም። ደርግ ዘውጋዊ ብሔርተኝነትን ሲያጠፋ፤ ኢሕአዴግ ሀገራዊ ብሔርተኝነት ቀበረ። ሁለቱም የዜሮ ድምር ፖለቲካዊ ጨዋታ ገጥመው ሀገረ መንግሥት ግንባታውን አጨናጎሉ።

አዴፓ ግን የአማራ ብሔርተኝነትን ዴሞክራሲያዊ አድርጌ አለሳልሳለሁ ብሎ የአማራን ብሔርተኝነት ሳያጎለብት ቀረ፡፡ ፖለቲካ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አደረጃጀትን ስለሚሻ የአማራ ብሔርተኝነት ሥርዓታዊ እና ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ መቆም አለበት፡፡ ይህ ሲሆን የፖለቲካ መመጣጠን ይፈጠር እና ድርድር ይጀመራል፡፡ ተመጣጣኝ ባልሆኑ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ድርድር አቻ አሸናፊነትን ስለማያመጣ እኩልነትን ያርቃል፡፡ አዴፓ[39] በብሔርተኝነት ደረጃው ፍዝ በመሆኑ ሸማግሌ እና

---

[39] *የ1966ቱ የየካቲት አብዮት ውሉድ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በብዛት ቡድን እንጂ ሕዝብን አይወክሉም። ሕወሓት በምንም ሁኔታ ትግራይን መወከል አይችልም። በጫካ ላይ እያለ ገና እነ ባድመን ለሻእቢያ በማጫረት ክህደቱን አሳይቷል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ በአንደበታቸው ዋልታ ቴሌቪዥን ጳጉሜ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ቀርበው እንደተናገሩት ሕወሓት የኤርትራ አጎራባች የሆኑ የትግራይ አካባቢዎችን ለሻእቢያ ለመሸጥ የተስማማው ገና ጫካ ላይ እያለ ነበር። በሌላ በኩል አንዳርጋቸው ጽጌ ኤርትራ ተገንጥላ ሀገር መሆን እንዳለባት የተወሰነው በውይይት ሳይሆን መቀሌ ካለ አንድ ቡና ቤት በኢ-መደበኛ አካሄድ እንደነበር ጽፈዋል። የሕወሓት ታሪክ ተጋሪ የሆነው ብአዴን(አዴፓ) ቡድን እንጂ አማራ አይደለም። የጎንደር ግዛት የነበሩ ቦታዎችን እነወልቃይት እና መሰሎችን፣ ከሸዋ እነ ደራ፣ ከጎጃም እነ መተከል ከወሎ እነ ራያን አሳልፈው የሰጡ ብአዴን የተባለው ቡድን ይኑር እንጂ ምን አገባኝ በሚል ፍዝ ስሜት ነበር። የብአዴን አመራር ስለምንም ነገር ትኩረተ ቢስ ነው። ምናልባትም የሚያስበው ስለ ብአዴን ሊሆን ይችላል። ስለሚመራው ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል እና ሀገር ምንነት እና ፖለቲካዊ ሂደት አይገለጥለትም። አዴፓ ሲያንስ የግለሰብን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚሯሯጡ ግለሰቦች የተሞላ ሲሆን፤ ሲበዛ የቡድን መብትን እንደ ብአዴን ለማስጠበቅ ይሠራል። ኦዴፓም(ኦሕዴድ) ተመሳሳይ ነው። ኦሕዴድም ቢሆን የቡድን መብቱ(የኦሕዴድነት) ከተጠበቀለት ኦሮሞነትን ለመሸጥ ዝግጁ ነው።*

ብዙ የከተማ መሬቶችን በሕገ ወጥ መንገድ ኦሕዴድ ይሸጥና ኦነግ ቀመስ የፖለቲካ ልሂቃኑ ሲጠይቁት አልሸጥኩም ብሎ ንጹሐንን ሕገ ወጥ ናቸው ብሎ ያፈናቅላል። በዚህም ለኦሮሞ ማሰቡን ለማሳየት ይሞክራል። ግቡ ግን ቡድኖች ፓርቲያቸውን ለማቆየት የሚያደርጉት መታተር ነው። ኢሕአዴግ ቡድኖች ግለሰባዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር የተጠራቀሙበት የፖለቲካ ማኅበር በመሆኑ ካዋጣው ሀገርን እስከ ሕዝቦቿ ለመሸጥ አያመነታም። በሂደቱም የሆነው ይሄው ነው። የሩሲያ ቦልሸቪክ መሪዎች ነገ እንመራታለን የሚሏትን ሀገር ከጀርመን ጋር አብረው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወግተዋል። የቦልሼቪክ ቅጅ ነን የሚሉት ኢሕአዴጎችም በሥራ ሂደታቸው አንዴ ከሱዳን ሌላ ጊዜ ከሶማሊያ፤ በቅርብ ደግሞ ከኤርትራ ጋር ሆነው ኢትዮጵያን ወግተዋል። የዛ ዘመን የፖለቲካ ፍጥረቶች የቡድን ድርጅታዊ መብታቸውን ለማስጠበቅ የሞከሩት በሕዝብ ሁነኛ ጥቅም ላይ በመቆም ነው።

የመሃል አደራዳሪ አድርጎታል። ሽማግሌ በመሆኑም ተከታይነትን እንጂ ቀዳሚነትን አልለመደም።

አንድ ተቋም ወይም ድርጅት የምሥረታው ይዘት በብዛት ሙሉ ጉዞውን እና ግቡን ይወሥነዋል። አዴፓም ኢሕዴን ሆኖ ሲመሠረት የነበረው ተቋማዊ ባህሉ ተጭኖት ከብአዴንነት እስከ አዴፓነት ድረስ ተከትሎታል። በተቋም ምሥረታ ሂደት ውስጥ አጀማማር አጨራረስን ይወሥነዋል።

ብአዴን በ2001 ዓ.ም. ከጎጃም ወደ ቤንሻንጉል የተካለለውን መተከልን ባያስመልስ እንኳ፣ ለራሱ አስተዳድርነት የተሰጠውን የፓዌ ልዩ ወረዳን ርቆኛል ብሎ ለቤንሻንጉል ሰጥቷል። ከሸዋ ደራን ለኦሮሚያ አስረክቧል። ማስረከቡ ለብአዴን በወቅቱ ቡድናዊ ጠቀሜታ ነበረው። ሩቅ ሂዶ ሕዝብ አለመምራቱ እረፍቱ ነበር። ከሌላ ድርጅት ጋርም ሙግት አይገጥምም። ይሄ ለብአዴን እረፍትን ይቸረዋል።

ሌላው የብአዴን አጋር የነበረው ሕወሓት በ1986 ዓ.ም. ሻዕቢያ ኢትዮጵያ ለኤርትራ ጥሬ ዕቃ ታቀርባለች፣ ኤርትራ ኢንዱስትሪ ታለማለች የሚል ስምምነት እንዲፈረም የፈቀደ ድርጅት እንደሆነ አቶ ታምራት ላይኔ ጳጉሜን 2 ቀን 2011 ዓ.ም. በናሁ ቴሌቪዥን ባደደረጉት ቃለ ምልልስ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ከ1989 ዓ.ም. በፊት ኤርትራ ቡና ወደ ውጭ በመላክ እና በጤፍ አቅርቦት ተወዳዳሪ የለሽ ሆና ነበር። የማታ ማታ ግን የሕወሓት ቡድን መቀሌን እንደ አስመራ እናደርጋለን ሲሉ ሻዕቢያ አዲግራትን አካባቢ ደበደበ። ጦርነቱ ለፖለቲካ ፍጆታ የድንበር ቢባልም ሥረ መንስኤው ግን የንግድ ጦርነት ነበር። እንጂማ ባድሜ የማያጣላ ጉዳይ ነበር። ምክንያቱም ሕወሓት ገና ጫካ እያለ ለሻዕቢያ በጉርሻ መልክ አሳልፎ ሰጥቶታል። በባድሜ ጦርነት በብዛት የተሳተፈው አማራው ሲሆን፣ ኦነግ ከሻዕቢያ ጎን ተሰልፎ የኦሮሞ ወጣት በጦርነቱ እንዳይሳተፍ ቀስቅሷል። ብአዴን የቡድን መብቱን ለማስጠበቅ ብዙዎችን ለጦር ልኳል። በጦርነቱም በአድዋ ጦርነት ከሞተው ኢትዮጵያዊ ይልቅ ከኤርትራ ጋር በነበረው ጦርነት ያለቀው ይበጣል። በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ከ60 ሺ በላይ ኢትየጵያውያን ሲያልቁ ጦርነቱም ከሁለት ዓመት በላይ ፈጅቷል። በአድዋ ደግሞ 7ሺህ አካባቢ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን እንደገበሩ ታሪክ ሲመሰክር፣ ጦርነቱ በአንድ ቀን በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቋል። ኢሕአዴግ የፈጠረው የአመራር ግድፈት ሀገሪቱን በብዙ መልኩ ዋጋ አስከፍሏል። ኢሕአዴግ ከመፈጠሩ በኋላ ብሔር ለብሔር በተደረጉ ሽኩቻዎች እና ግጭቶች የጠፋው የሰው ሕይዎት እና የተፈናቀለው ሕዝብ ብዛት ኢትዮጵያ ለሉዓላዊነቷ ካደረገቻቸው ጦርነቶች ሁሉ የላቀ ጉዳት አስከትሏል።

ምዕራፍ ሦስት

የጥላቻው ተረከዝ እና የቀደደው ሽንቁር

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ልሂቅ ሠራሽ ሆኖ ስለመተከሉ[40]

[40]የብሔርን አተያይ በሦስት ፈርጆች መመልከት ይቻላል። ሥነ-ፍጥረታዊ (primordialism)፣ ቁሳዊ (instrumentalism) እና ምሥረታዊ (constructivism) ናቸው። ፍጥረታዊ የብሔር አተያይ ብሔር በውልደት እና በሥጋ ዝምድና የሚመሠረት ነው ብሎ የሚበይን ደማዊ አተያይ ነው። በሥነ-ፍጥረት ትንታኔ መሠረት ብሔር ተፈጥሮአዊ ስለሆነ በምንም ሁኔታ አይለወጥም። ብሔር የደም ተዛምዶ ነው። የዘረመል ጉዳይ ነው። ይህ በመሆኑ ብሔርን በደም ተመሳስሎሽ የሚበይኑ ልሂቃን ብሔርን አይለወጤ ማኅበረሰባዊ ቡድን አድርገው ይመለከቱታል።

ቁሳውያን የብሔር ብያኔ ልሂቃን ደግሞ የብሔር ቡድንን የፈጠረው የሀብት ሽሚያ ቡድንነት(መቧደን) ነው። የሀብት ቡድንነቱ የራሱ ማኅበራዊ መዋቅር ይፈጥራል። ሀብቱ ፖለቲካን ይፈጥራል። ለዚህ አብነት በሩዋንዳ የሁቱ እና የቱትሲ ጅምላ ፍጅት እና ብያኔ ነው። ልሂቃኑ ሁለቱን ብሔሮች ለመለያየት መሠረት ያደረጉት የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ መዋቅራዊ ልዩነትን ነው። ቱትሲዎች በሩዋንዳ ኢኮኖሚ በተሻለ የሀገሪቱ ሀብታም መስለው ታይተዋል። በሃቅ ደረጃም ከብት አርቢዎች በብዛት ቱትሲዎች በመሆናቸው የሀገሪቱን ሀብት የተቆጣጠሩ መስለው ታይተዋል። ይህ መደባዊ ልዩነት የኀሳ እና የቀለም ልዩነት እንዳለ ሁኖ በልሂቃኑ ተተረጎመ። ትርጓሜውም ለጅምላ ጭፍጨፋ ዳርጓል። በኢትዮጵያም ያለው የብሔር ብያኔም በብዛት ለልሂቃኑ የፖለቲካ ጥም ማርኪያነት ቁሳዊ ሆኖ የተቀነቀነ ነው። በውሸት ታሪክ ማንነት ተገንብቶ፤ ማንነቶችም የልሂቃኑን ፖለቲካዊ ፍላጎት በሚመቹ መንገድ የተሠሩ ናቸው። በትርክት ደረጃ ከ1966 እስከ 1983 ዓ.ም. እና ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በተግባር፤ ከማኅበረሰቡ ነባራዊ እና ህሊናዊ ሁኔታ በማይገናኝ መልኩ ፖለቲካው ተሠርቷል።

ምሥረታዊ የብሔር አተያይ ደግሞ ብሔር በጦርነት፣ በስደት እና በሌሎች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚፈጠር የማኅበረሰቦች የመቀላቀል ውጤት ነው። በዚህ ብያኔ መሠረት ብሔር በታሪካዊ አጋጣሚዎች የሚፈጠር የቡድናዊ እሳቤ ውጤት ነው።

ፖለቲካ የሚፈልቀው ከማኅበረሰብ ነው ወይስ ከተወሰኑ ልሂቃን የሚለው ጉዳይ ክፍት የፖለቲካ ፍልስፍና ሃልዮት ነው፡፡ እንደነ ኤንግልስ ዓይነት የሥነ-ማኅበረሰብ ልሂቃን የፖለቲካ ሐሳብ የሚሠራው ከማኅበረሰቡ ከሚነሣ አውነት እንደሆነ ያትታሉ፡፡ መሪዎች ሐሳብ የሚበደሩት ከማኅበረሰቡ ወግ፣ ባህል እና የሞራል እሴት ነው የሚል ሐሳብ ያስተጋባሉ፡፡

‹‹ልዑሉ (The Prince)›› የሚል መጽሐፍ በመጻፍ ከጣሊያን ፍሎረንስ ከተማ ተነሥቶ ዝነኛ የዘመናዊው ዓለም የፖለቲካ ሳይንቲስት የሆነው ኒኮሎ ማካቬሊ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጣውን የነኤንግልስን ሐሳብ ቀድሞ ተቃርኖ ቆሟል፡፡ በአውሮፓ ህዳሴ ዘመን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቅ ብሎ የዓለም ፖለቲካን በሴራ የተነተነው ማካቬሊ እውነት የሚመነጨው ከአሸናፊው መንግሥት እንደሆነ ተፈላስፏል፡፡ ማኅበረሰብም በመሪዎች የሚሠራ እንጂ ማኅበረሰብ መሪዎችን የመቅረጽ ኃይሉ ደካማ ነው፤ የሚል ሐሳብ ያቀርባል፡፡ ፖለቲካ ከማኅበረሰብ ሞራል ጋር ጋብቻ የለውም ሲልም ፖለቲካን ከሰብአዊ ባሕርይ አርቆ ተመልክቶታል፡፡ ፖለቲከኛ ከሚፈቀር ይልቅ መፈራቱ ለማኅበረሰብ ቀረጻ በጎ ጎን አለውም ይላል፡፡

ማካቬሊ መሪው አንድን ማኅበረሰብ ባህሉን ለመቀየር ከማኅበረሰቡ ባልወጣ መሪ እንዲመራ በማደረግ ነባሩን የማኅበረሰብ እውነት አጥፍቶ ሌላ ውልድ ማኅበረሰብ መፍጠር ይቻላል የሚል ሐሳብ ያስተጋባል፡፡ የኒኮሎ ማካቬሊ ሐሳብ በእኛ ሀገር ፖለቲከኞች ዘንድ አድማሱን አስፍቶ ገብቷል፡፡ በተለይም ከ1966 አብዮት በኋላ ያለው ፖለቲካችን ከማኅበረሰብ አውነት ጋር የተፋታ እና በሴራ የተጠመቀ ሆኗል፡፡ ማካቬሊ ለአምባገነን መንግሥታት ሁሉ መርህ ነው፡፡

በእርግጥ ዓለም የተሠራበትን ሥርዓተ ማኅበር ስንመረምር፤ ማኅበረሰብ የፖለቲከኞች ፈጠራ ውጤት ነው። ሕዝብ መልክ እና ቅርጹ፣ ሐሳብ እና ምኞቱ፣ ትናንቱ እና ነገው ተወጥኖ የሚቋጨው በፖለቲከኞች አተያይ ልክ ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የነበረ ሕዝብ ኤርትራ የእኔ ናት ብሎ ከማሰቡ በላይ ጁቡቲም የእኔ ናት ይላል። ሥልጣን የሚገኘው ከፈጣሪ እንጂ ከምርጫ አይደለም ብሎ ደምድሟል። ክፍለ ሀገራዊ የመልክዓ ምድራዊ አከላሎች ግዛታዊ ማንነት ሆነዋል።

ለአብነት ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ ጎንደር፣ ተምቤን፣ አድዋ፣ ወለጋ፣… መልክዓ ምድር የፈጠራቸው መለስተኛ ማንነት ይዘው ቆይተዋል። አማራ እና ኦሮሞ የሚለውን ማንነት የገነባው ዘውጋዊ ፖለቲካው ነው። ፖለቲካ ባህል እና ታሪክን አንጥሮ የመፍጠር አቅም አለው። ይህ ሃቅ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያ እንደ ማኅበረሰብ ለ3ሺ ዘመን የተጓዘችበትን መንገድ ዱካ አጥፍቶ ሌላ መንገድ ለመገንባት መሞከር ግን ትናንት የተለፋበትን ሁሉ መና ማድረጉ አልቀረም። ማኅበረሰብ እና ልሂቃንንም በተቃርኖአዊ ቀኖና እዝ እንዲወድቁ አድርጓል።

ጉዳዩን አብነታዊ አስረጂ አክለን ብንመለከተው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ 99 ከመቶው ሃይማኖተኛ ነው። ሃይማኖትና ባህሉን ይወዳል። ሀቁ ይህ ከሆነ፤ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓላማዊ ቅኝት መነሻው የሚጋገረው ከሕዝቡ ኑባሬ ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፍፁም የማይተዋወቁ ባይተዋር መንገደኞች ናቸው። እስኪ ለአብነት የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከሰሜን ጫፍ እንጀምርና እንመልከተው።

3.1 ከማኅበረሰብ ኑባሬ የተፋታ ልሂቁነት

ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ወኪል ነኝ ብሎ ከየካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ተረከዙን ሲያሳርፍ የፖለቲካ መርሆው ፈጽሞ

የትግራይን ሕዝብ አይመስልም:: የትግራይ ሕዝብ በ1999 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባወጣው መረጃ መሠረት ከ90 ከመቶ በላይ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ነው:: የዚህ ሕዝብ መሪ ነኝ የሚለው ሕወሓት በ1968 ዓ.ም. ባወጣው የፓርቲው መግለጫ ትግሌ ፀረ ጽዮናዊ እና ፀረ አውሮፓ ኢምፔሪያሊዝም ነው ይልና ጓዳዊነቱ ወደ ዓረቡ ዓለም ያዳላ እንደሆነ ያትታል:: ይህን ብሎ ሲያበቃ ኮሚኒዝምን ያውጃል:: ሌኒንን ሕወሓት ፖለቲካ የስበት ማዕከሉ አድርጐ ይመለከተዋል:: ሕወሓት የትግራይን ነባር እሴት እና ታሪክ ይክዳል[41]:: ሌኒን ሕወሓትን ስለሃይማኖት እንዲህ ይመክረዋል::

ሃይማኖት አደንዛዥ እጽ ነው:: ሰዎች በመሬት እየተጨቆኑ ሌላኛው የሰማይ አምላክ ተስፋ በማድረግ ለጭቆና ሕዝቡን አመቻችቷል:: ሃይማኖት የገዥዎች ማስገቢያ መሣሪያ ነው:: ሃይማኖት አልባነት የወዝ አደሩን ነጻነት ለማወጅ ጠቃሚ ነው:: ሰው አምላክ የለሽነትን

[41]ሕወሓት በትግራይ ውስጥ የዳበረ የባህል እና እሴት ባለቤት ነው የሚለውን ተምቤን በበጎ አይመለከተውም። ለዚህም ተምቤንን ከአውራጃ ግዛትነት ወደ ወረዳነት ኮርኩሞታል። ተምቤን የእነ ንግስተ ሳባ፣ የእነ ዐፄ ዮሐንስ፣ አሉላ አባ ነጋ… በጥቅሉ የትግራይ መሳፍንት መንደር አድርጎ ስለሚመለከተው ቀናኢ እሳቤ የለውም። በ1993 ዓ.ም. ሕወሓት ሲከፋፈል የተምቤኑ ስየ አብርሃ ከሕወሓት አፈንግጦ ወጥቷል። ብዙዎቹ የአረና ፓርቲ አባላትም ተምቤኖች ናቸው። እንደ ጎንደር ሁሉ ተምቤን 44 ለሚደርሱ አብያተ ክርስቲያናት መገኛ ቦታ ነው። በሕወሓት የፖለቲካ ተፈጥሮ ምክንያት ተምቤን ምቹ ባለመሆኑ በልማትም የተጎዳ አካባቢ እንደሆነ ፍትሕ መጽሄት በቅጽ 01 በቁጥር 32 በሰኔ 2011 ዓ.ም. ሰፊ ሃተታ ይዛ ወጥታ አስነብባለች። ሕወሓት ለቤተ ክርስቲያን ቅርብ የነበረውን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከትግራይ ምዕመናን አስጥሎ ኮሚኒስታዊውን ባለኮከብ ሰንደቅ የቤተ ክርስቲያን መገለጫ ሁሉ አስመስሎታል። ሙስሊሞችም ለአረባውያኑ ቅርብ የነበረውን ጀለብያ አስጥሎ በሕወሓት አርማ ተክቶ ታይቷል። የሕወሓት ደጋፊ የሆኑ ውስን የትግራይ ልሂቃን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በዘር እንድትቧደን እና የትግራይ ሲኖዶስ እንዲመሠረት ይሻሉ። ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ስትቃጠል ቤተ ክርስቲያን የአማራ ናት ሕወሓት ስላለ መቃጠሏን እንደ በደል አይመለከቱትም። የሁሉም ራስ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በዘውግ መነጽር ለመመልከት ይሻሉ። ከሃይማኖት በላይ ነገድ እንዲመለክ የሕወሓት ልሂቃን ተግተው እየሠሩ ነው። አማራ የደገፈውን መጥላት የሕወሓት መንገድ በመሆኑ አማራ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀናኢ እሳቤ ካለው የሕወሓት ልሂቃን በተቃርኖ ይቆማሉ። **ሕወሓትን አማራ ከደገፈው ሕወሓት ራሱን ሁሉ የሚጠላ ይመስላል። ስሙን እና ተግባሩን ሁሉ ሊቀይር ይችላል። በሕዝብ ደረጃ ግን የአማራ እና የትግራይ ሕዝብ ኢ-ተነፃፃይ እሴት እና ፍላጎት አለው።**

ካልተቀበለ ከካፒታሊዝም ሥርዓት አምልጦ ኅብረተሰባዊ አብዮትን አይቀላቀልም። ሲል ሌኒን ለቦልሼቪክ ፓርቲ አምላክ የለሽነትን ይሰብካል። ሕወሓትም ይሄን ተጋርቷል።

ካርል ማርክስና ኤንግልስ በበኩላቸው የኮሚንስት ማኒፌስቶ ብለው በ1848 ዓ.ም. ባሰናዱት ጥራዝ ስለሃይማኖት እና ትውፊት እንደዚህ ይገልፃሉ። ‹‹መነኮሳት የካቶሊክ ቅዱሳንን[42] ርካሽ ገድል ሲጽፉ በጥንት አረማውያን ሥነ-ጽሑፍ ላይ ተመርኩዘው እንደነበር ግልፅ ነው።›› ሲሉ የቤተ ክርስቲያንን ሥነ-ጽሑፍ እና ‹‹የቅዱሳንን ክብረ-ቢሥነት›› ይተነተናሉ። ቅዱሳንን ‹‹እርካሽ›› እያሉ ይዘልፏቸዋል። የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከገኘው መደብ ጋር በደባልነት የቆመ በመሆኑ ትግል እንደሚያስፈልገው ጽፈዋል። ርዕዮተ ዓለምን ከግራዘመሙ የነማርክስ ፍልስፍና የቀዳው ሕወሓት በይፋ አምላክ የለሽነትን ባያውጅም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን የአማራው ሥልጣን ማራዘሚያ የዕዝ ሰንሰለት አድርጐ ፈርጇታል። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ለማድከም በረሃ እያለ የራሱን ሰላዮች[43] መለመለ።

ሕወሓት ይሄን የሚያደርገ በመቶኛ ሲሰላ ከአማራው ኦርቶዶክሳዊ ሕዝብ ቁጥር የበለጠ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና አማኝ ባለበት ክልል ነው። በኦርቶዶክስ እምነት አማራው ከ80 በመቶ በላይ ሲሆን የትግራይ ሕዝብ ከ90 በመቶ በላይ ነው። ፖለቲካ የሕዝብ ሆኖ ቢሆን ሕወሓት ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በሚቀዳ ሀገር በቀል

[42] ሕወሓትም በማዕከላዊ እስር ቤት የግንቦት ሰባት አባል ተብለው የሚታሰሩ ሲገረፉ በማሪያም ብለው ሲማጸኑ ‹‹ ማሪያም የግንቦት ሰባት አባል አሸባሪ ናት›› እንደተባሉ ታስረው የተፈቱ ሰዎች በታኅሳስ ወር በ2011 ዓ.ም. ለአማራ ቴሌቪዥን ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል።

[43]በዋልድባ ገዳም የሰለጠኑ የሕወሓት ካድሬ መነኩሴዎች ደጋግ የሃይማኖት አባቶችን እያሰለሉ ለእስር እና ለስቅይት ዳርገዋል። ዋልድባ ገዳም እንዲጠፋም ከሕወሓት ጎን ቆመው ባጅተዋል።

እውቀት ላይ የተመሠረተ የማኅበረ ፖለቲካ ፍልስፍና ይከተል ነበር። ከታሪክ መዝገብ ገልጠን ካየነው ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አጥብቀው መንግሥታዊ ሃይማኖት ያደረጉት ዐፄ ዮሐንስ ናቸው።

ከዐፄ ምኒልክ በላይ ዐፄ ዮሐንስ[44] ሃይማኖታዊ መሪ (ኦርቶዶክሳዊ) እንደነበሩ ተክለፃዲቅ መኩሪያ መዝግበዋል። እነ ዋለልኝ መኮነን እና ሌሎች የ1966ቱ አብዮት ገፊዎች ‹‹*የኢትዮጵያዊነት ማንነት የለም፤ ያለው የአማራና ትግራይ የባህል የበላይነት ነው። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የበላይነትም የሚመነጨው ከሁለቱ ሕዝቦች ገዥ መደብ ነው*›› ሲሉ ተንትነዋል።

የ1966ቱ አብዮት ከመነሻው የፈረጀው የትግራይና የአማራ ገዥ መደቦችን ነው። ሕወሓት በተማሪዎች ንቅናቄ ወቅት በትግራይ ተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ነበር። እናም የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከዳግማዊ ምኒልክ እንደሆነ ሰበኩ። ሕወሓት በሥልጣን በነበረበት ዘመን ዘመኑን የሚያሰላው የኢትዮጵያ ታሪክን የመቶ ዓመት ነው ብሎ ነው። ከዐፄ ምኒልክ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ያሉ መሪዎችን የአማራ ጨቋኝ መደቦች ብሎ ሲፈርጅ ትግራይም እንደተጨቆነች ደሰኮረ። በዚህም በተማሪዎች የተነሣውን የትግራይ ገዥ መደብነት እና የባህል የበላይነት ፋቀ። የዐፄ ዮሐንስን ሁለንተናዊ የፖለቲካ ተሳትፎ ከፖለቲካ ትንታኔው አወጣ።

የትግራይ ሕዝብ በሸዋ አማራ ገዥዎች ላይ እንዲዘምት እና ኢትዮጵያዊነትን ፍቀው ማንነታቸውንም ሆነ ዜግነታቸውን በትግራይ ሪፐብሊክ ሥር እንዲሰፍሩ ዐፄ ምኒልክ ዐፄ ዮሐንስን ያስገደሉት በትግሬነታቸው ነው ብሎ የጥላቻ ሐውልት ተተርክሎ

[44] ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት

(ተመሥርቶ) የራሱን ምስል ለሌሎች ብሔሮች ማሳየትን መረጠ። የአድዋ ድል ታሪክን እንኳን የትግራይን ሕዝብ ለመበዝበዝ የአማራ ገዥ መደብ ትግራይን የወረሩበት እንጂ ጦርነቱን በትግራዮች ብቻ ማሸነፍ ይቻል[45] እንደነበር ሰበከ። ሕወሓት ሃይማኖትን፣ ባህልን፣ ታሪክን ከትግራይ ሕዝብ እሳቤ[46] ውጭ አድርጐ ቀረፀ። ይህም በባህልና በታሪክ እንዳይለያይ ሆኖ የተያያዘውን የአማራ እና የትግራይ ሕዝብ በአንድ ሀገር ውስጥ እየኖረ ማዶ እና ማዶ ሆኖ የጐሪጥ እንዲተያይ አደረገ።

በነገራችን ላይ ልክ እንደ ሕወሓት ሁሉ አማራውም በአክራሪ ብሔርተኝነት የተደራጀ ኃይል ኖሮት ቢሆን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትርክት ከጅማሮው ይቀየር ነበር። አማራው ፈጥኖ አለመደራጀት እና በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ማንነቱንና ዜግነቱን መግለጹ ‹‹ኢትዮጵያ አማራው በአምሳሉ የፈጠራትና ብሔሮችን የጨቆነባት ሀገር ናት›› የሚለውን አፍራሽ ታሪክ እንዲጸና አድርጓል።

በሴራ ፖለቲካ ትንታኔ ውሸት ውሸት የሚሆነው ካልጠቀመ ብቻ ነው። በመሆኑም በ1966 ዓ.ም. አማራው እንደ ሁሉም ብሔሮች ኢትዮጵያ ጨቁናኛለች ብሎ ነጻ አውጭ ቢመሠርት ኑሮ ተጨቋኝ እንጂ ጨቋኝ ይጠፋል። ዳሩ ሁሉም ተጨቋኝ ፓርቲዎች በማን ጨቋኝነት ላይ ተስማምተው ሀገር ይመሠርታሉ የሚለው ጥያቄ ምላሽ አልባ ይሆናል። አማራው እንደ ሕወሓት፣ ኦብነግ፣ ኦነግ…

[45] የአድዋ 100ኛ ዓመት ሲከበር እነ ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ አድዋ በትግራይ አርበኞች ብቻ የተገኘ ድል አድርገው አቅርበው በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ታላቅ ቅሬታ ነበር። በአዲስ አበባ በመአህድ መሪነት ሰልፍ ተደርጎም ነበር።

[46] ሕወሓት የፓርቲውን ኮሚኒስታዊ መገለጫ ሰንደቅ የትግራይ ሕዝብ ባህል አድርጎታል። የትግራይ ሕዝብ በየአውደ ትዕይንቱ በቀያይ ኮከብ በደመቀ የኮሚኒስት መለያ በሆነ አልባስ መዋብ ጀምሯል። የሕወሓት ሰንደቅ ለትግራይ ሴቶች የባህል ቀሚስ መስሎ በየአደባባዩ መታየት ጀምሯል። አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለውን ሰንደቅ ሕወሓት ከቤተ ክርስቲያን ሳይቀር ከልክሎ፣ የራሱን የፓርቲውን መገለጫ ነውር አልባ ባህል አድርጎታል።

ነጻ አውጭ ግንባር ቢኖረው ኖሮ ኢትዮጵያ ዩጎዝላቪያን የመሆን እድሏ የሰፋ ይሆን ነበር። ኢትዮጵያ 1983ን ያለፈችው በአማራ የጥላቻ ተረከዝ ተደግፋ፤ ሌሎች ብሔሮቿን በኅብረት በማያያዝ ነው። አማራ ተጠልቶም በራሱ ኪሳራ ሀገር አቁሟል።

ሁሉንም ነጻ አውጭ የብሔር ፓርቲዎች በጋራ ሆነው በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር እንዲኖሩ ያደረገው ብቸኛው መስማሚያ ነጥብ የነፍጠኝነት እና የትምክህተኝነት ፍረጃ ወለድ የሆነው የአማራ ጥላቻ ነው። የኢሕአዴግ አፅመ ቅርጽ ፖለቲካው የተዋቀረው እና ተረከዘ ፖለቲካውን ያነበረው በአማራ ፖለቲካዊ ፍላጎት ተቃርኖ ላይ ነው። ብአዴንን ጨምሮ ሁሉም የብሔር ፓርቲዎች በማዕከላዊ ዴሞክራሲ ሲመሩ መስማሚያ እና የመታገያ መገጣጠሚያ ነጥባቸው ከአማራው እሳቤ ጋር የሚያያይዘው ትምክህተኝነትና ነፍጠኝነት ነው። ኢሕአዴግን ሲታገሉ የነበሩት የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች በማዕከላዊ እሥር ቤት በሕወሓት እየተንኮላሹና እግራቸው እየተቆረጠ ‹‹ሕወሓት የተሳሳተው የፌደራሊስት ወዳጃችን ነው፤ የዘላለም ጠላታችን አሐዳዊው አማራው ነው›› ብለው ለገራፊያቸው ጥብቅና ቁመዋል።

አንድ የኦሮሞ ወጣት ፖለቲከኛ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በዓይኑ እያየ በዘመኑ ከደረሰው ሰብዓዊ ቀውስ ይልቅ በ1880ዎቹ ዳግማዊ ምኒልክ በአርሲ ጨፌጨፌ የሚባለው ተረት ሕልም ሆኖ ያመዋል። ጭንቅላት እና እግሩን ያቆስለዋል። ያልኖረበት ዘመን እየኖረበት ያለውን ዘመን አጨልሞ ነገን በጽልመት ይዘጋበታል። ሃይማኖቱ ሳይቀር የምኒልክ የመግዣ መሣሪያ ይመስለዋል።

ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ.ም. የአማራ እና የኦሮሞ ሕዝብ ግንኙነት ተብሎ የኦሕዴድ(ኦዴፖ) ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ሓላፊው አቶ አዲሱ አረጋ በአምቦ በተካሄደ መድረክ ‹‹ተስፋየ

ገብረአብ የተባለው ልቦለድ ጸሐፊ በውሸት እየጻፈ የአማራን እና የኦሮሞን ሕዝብ አለያይቷል።›› ሲሉ ተናገሩ። ከመቅፅበት ግን ከተናገሩበት አዳራሽ ሳይወጡ የኦሮሞ የፖለቲካ ልሂቃን ለምን የተስፋየ ገብረአብ ልቦለድ ተተቸ ብለው ዘራፍ አሉ። አቶ አዲሱም ከወዲያው የአፍ ዳጥ ነው ብለው ይቅርታ ጠየቁ። ይቅርታቸውን ያልተቀበሉ ወጣቶች የአኖሌ ሐውልት አይተች፣ የተስፋየ ገብረአብ የቡርቃ ዝምታ ልቦለድ እውነተኛ ታሪክ ነው ብለው በኦሮሚያ ክልል ከተሞች ሰልፍ ወጡ።

አማራን መጥላት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባህሉ አድርጐታል። ይህም አማራውን ብቻ ሳይሆን ጠይውን አካል ክፉኛ ጎድቶታል። ሻዕቢያ አማራ በገነነበት ኢትዮጵያ አልኖርም ብሎ ኤርትራን እንደ ሀገር አቆመ። ኤርትራውያን ከባርነት እና ከነጻነት ተብለው በሕዝበ ውሳኔ ከእናት ሀገራቸው ተለዩ። ከጥላቻ ውጭ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ እሴት ግንባታ ሐሳብ ያልነበረው ሻዕቢያ ኤርትራን ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ የአማራን ጥላቻ ቀንሶ ወያኔ በኢትዮጵያ በኩል ይወረናል እያለ ሕዝቡን በፍርሃት ለመምራት ተገደደ። ኢትዮጵያ ትወረናለች በሚል ሥጋት በሳዋ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ማንኛውም ወጣት ለብሔራዊ አገልግሎት ይላካል። ትምህርት እና ሳይንስ ለኤርትራውያን ወጣቶች አልታደሉም። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጎለበተው አስመራ ዩኒቨርሲቲ እንኳን ኮስሷል። ቡና እና ጤፍን ከፍጆታ አልፋ ወደ ውጭ ለመሸጥ ስትኳትን የነበረችው ኤርትራ ጤፍን ለዕለት ምግብ ለመግዛት እንኳን ተቸግራ ከርማለች። ኤርትራውያኑም ኢትዮጵያ ትወረናለች በሚል ከንቱ ሥጋት የሻዕቢያ አገዛዝን ለመሞገት እድል አጥተዋል።

የሻዕቢያ የመግዣ መሣሪያው መጀመሪያ የአማራ፤ በኋላም የሕወሓት ጥላቻ ሆኗል። ምስኪኑ የኤርትራ ሕዝብ ያለ ሻዕቢያ ጥላ አልኖርም ብሎ በውሸት ከተፈጠረው ከትልቁ ጠላት

(ኢትዮጵያ) ለመደበቅ በእውናዊው ትንሹ ጠላት (ሻዕቢያ) ሥር ወድቆ ኑሮውን ይገፋል። ጥላቻ ለአምባገነን ልሂቃን መግዣ ምክንያት ሲሆን፤ ሕዝብን ደግሞ በምናባዊ ፍርሃት ለገዥዎች ጥገኛ እንዲሆን ያደርጋል። የጥላቻ ፖለቲካ ሕዝብን ወደ ውስጡ እንዳያስብ ስለሚያደርግ ለእድገት እና ለምክንያታዊ ማኅበረሰብ ፈጠራ አይበጅም። በአሜሪካ እና በጀርመን ክፉኛ የተደበደቡት ጃፓን እና እስራኤል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውድቀት ጥላቻን ሳይሆን መፍትሄን በመቀመር ገናና ሀገር ሆነው ወጥተዋል። ሁለቱ ገናና ሀገራት ጥላቻ እያኘኩ ለበቀል ተነሥተው ቢሆን ኑሮ ዛሬ የሆኑትን መሆን አይችሉም ነበር።

የ1966ቱ ፖለቲካ የወለደው የኢትዮጵያ የጥላቻ ፖለቲካ ግን ቂም በቀልን ተክሎ ሕዝቡን በፍርሃት እና በቁርሾ ጥሎታል። የትግራይ ሕዝብ እየተራበ፣ ሰባዊ መብቱ እየተረገጠ እና እየተጎሳቆለ ሕወሓት እኔ ከሌለሁ አማራ (ደርግ) ተመልሶ ይወርሃል ስለሚለው ከሕወሓት ጎን ለመሆን ተገዷል። ሕወሓት ቢሠራም ባይሠራም ትግራይን በአማራ እንዳይወረር አድርጓል በሚል ስንፍናውን ደብቆ ይገዛል።

የኦሮሞ ፖለቲከኞችም እርስ በእርሳቸው በፍጹም ሳይግባቡ ሲቀሩ ከተበታተን አማራው ያጠቃናል በሚል ይሰባሰባሉ። የመሰባሰባቸው ምክንያት ሕዝቡን የሚለውጥ ዓላማ ሳይሆን ፍርሃት ነው። ምናባዊ ፍርሃት በመፍጠርም ሕዝቡን አማራጭ አልባ ሆኖ ያለምክንያት እንዲገዛ አድርጓል። ወጣቱም ሳይንስ እና ቴክኖሎጂን ከመማር ይልቅ ሁሉን ነገር በጥርጣሬ እየተመለከተ ጥላቻን በልሂቃን እየተጋተ ምክንያታዊ አስተሳሰብ እየተጋረደበት ሂዷል። ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ የተተከለው የኢትዮጵ የፖለቲካ ፓርቲነት ታሪክ አጀማምሩን ያደረገው በሐሳብ የተለየውን በጠላትነት በመፈረጅ አለፍ ሲልም በመግደል ነበር። የፖለቲካ ልሂቃኑም ባህል አውዳሚ

እና የደመኝነት ፖለቲካ አራማጅነት ጎልቶ የሚንጸባረቅበት ሆኖ ተረክዙን ተክሏል። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ልሂቃን ሥነ-ልቦና ዘንድ ዴሞክራሲያዊ እሳቤ ነጥፏል። ጥላቻም ከፓርቲ እድገት ጋር አብሮ አድጓል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ አማራን መጥላት ርዕዮተ ዓለማዊ ባህል ሆኖ ተቀንቅኗል። ከባህል አልፎ ሕግም ሆኗል። ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. የጸደቀው ሕገ መንግሥት በመግቢያው የሚያውጀው የተዛባውን ታሪካዊ ግንኙነት ለማስተካከል ብሎ ነው። የሕገ መንግሥቱ ፍሬ ነገር ‹‹የአማራ ጨቋኝነትን ሁሉም ብሔሮች ተስማምተን አጽድቀናል›› ማለት ነው። የሕገ መንግሥቱ ተረከዝ ያረፈው ዳግማዊ ምኒልክ ያደላደሉትን ሜዳ በመናድ ነው።

በ1982 ዓ.ም. የኢሕአዴግ የነፍስ አባት ሆነው የመጡት አሜሪካዊው ኸርማን ኮኸን ከደርግ እስከ ሽግግሩ መንግሥት ድረስ የማደራደር ኃይል ፈጥረው ነበር። ኸርማን ኮኸን በፕሬዝዳንት ጆርጅ ደብልዩ ቡሽ ዘመን ከ1981 እስከ 1985 ዓ.ም. የአፍሪካ ጉዳዮች ልዩ ዲፕሎማት ሆነው ሲያገለግሉ፤ ኤርትራ እና ኢትዮጵያን በመነጠል የአንበሳውን ድርሻ ከመውሰዳቸው በተጨማሪ የደርግ አገዛዝ እንዲያበቃ አድርገዋል። ኮኸን ደርግን መጣል ኮሚኒስቷን ሩሲያን እንደመበቀል ቆጥረው አዲስ አበባም በኢሕአዴግ አስተዳደር እንድትገባ ትእዛዝ ሰጡ[47]። በአንዳንድ የፖለቲካ ልሂቃን ዘንድ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ‹‹**የኮኸን መፈንቅለ መንግሥት**›› እየተባለ ይጠራል። በዚሁም ኮኸን የአማራ ጥላቻን ከነኢሳይያስ እና መለስ ቃርሟል። በነኮኸን ዘንድ አማራ ማለት “በሩሲያ ተደግፎ ደርግን የፈጠረ ጸረ አሜሪካ ነው።”

[47] Newyork times .may29,1991

ሰኔ 15 ቀን ቅዳሜ ምሽት 11 ሰዓት ገደማ ባሕር ዳር ላይ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር አምባቸው መኮንን፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ አቶ ምግባሩ ከበደ እንዲሁም የአዴፓ የአደረጃጀት ዘርፍ ሓላፊው አቶ እዘዝ ዋሴ በደረሰባቸው ጥቃት ሕይዎታቸው አልፏል:: በዚሁ ቀን አዲስ አበባ ላይ ደግሞ የመከላከያ ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል ሰዓረ መኮንን እና በጡረታ የወጡት ጀኔራል ገዛዒ አበራ ተገድለዋል:: መንግሥት ግድያውን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አድርጎ ሲወስድ አቀናባሪውም፤ የቀድሞው የመከላከያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት በወቅቱ ደግሞ የአማራ ክልል ሰላም እና ደኅንነት ቢሮ ሓላፊ የነበሩት ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው ጽጌ እንደሆኑ ገለጸ::

ይሄን ተከትሎ ሁሉም የኢሕአዴግ ግንባሮች ትምክህተኞችን እንበቀላለን ከማለታቸው አልፎ፤ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) አባላትን እና ንጹሐን አማራዎች በየሀገሪቱ ጥግ እንዲታሰሩ አድርገዋል:: ኸርማን ኮኸንም ሰኔ 16 ቀን 2011 ዓ.ም. በቲውተር ገጻቸው ልክ እንደ ሌሎች የኢሕአዴግ ግንባሮች የአማራ ጥላቻቸውን እንዲህ አውጥተው ዘረገፉት፡- ***ያልተሳካው መፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ዒላማው የአማራን የበላይነት አምጥቶ ሌሎች ኢትዮጵያውያኖችን በአማራነት መግዛትን ግብ ያደረገ ነው:: ይህ ግብ በ1983 ዓ.ም. ሙሉ በሙሉ ወድቋል:: ካሁን በኋላ የአማራ የበላይነት ለዘላለም ከመቃብር በታች ሆኗል***[48] ሲሉ ልክ እንደ ሕወሓት ወይም ሻእቢያ ተናገሩ:: እነ ኮኸን እና መሰሎቹ አማራ

[48] ኮኸን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጳጉሜ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ስለ አማራ የሰጡትን ስሁት አስተያት ይቅርታ ጠይቀውበል። ስለ አማራ ስሁታዊ ትርክት እንደ ኮኸን ሁሉ እነ ታምራት ላይኔም ይቅርታ የጠየቁ ሲሆን፤ የኤርትራ የፖለቲካ ልሂቃንም ስለ አማራ ያላቸው ግንዛቤ ስህተት እንደሆነ ተገንዝበው ይቅርታ ጠይቀዋል። ይሁን እንጂ ስሁቱን ትርክት ኦዴፓ አጠናክሮ ቀጥሏል። በዶር አቢይ አህመድ የሚመራው ኦዴፓ በአቶ ሽመልስ አብዲሳ በኩል መስከረም 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ሆራ ፊንፊኔ ብለው በሰየሙት የኢሬቻ በኣል ነፍጠኛን ሰብረን ዋና ከተማ ተቆጣጠርን ሲሉ ስሁታዊ ትርክቱን እና ተረኛነትን አውጀዋል።

ወግ አጥባቂ በመሆኑ ለምዕራባውያኑ ባህል ሊያድር አይችልም የሚል ሥጋት አላቸው።

የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን በአፍሪካ ሁለተኛ፣ በዓለም አሥራሁለተኛ የሕዝብ ቁጥር ባላት ኢትዮጵያ ለማስለመድ ፈተናው ወግ እና ባህል አጥባቂው አማራ እንደሆነ በየሚዲያዎቻቸው ዛሬም ያስተጋባሉ። ቶቶ የተባለ መሠረቱን አሜሪካ ችካጎ ላይ የተከለ የግብረ ሰዶማውያን የጉዞ ወኪል ላሊበላን እና የጣና ገዳማትን ጥቅምት 14 ቀን 2012 ዓ.ም. እጎበኛለሁ ብሎ በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍ ያለ ወቀሳ ደርሶበታል። እነ ኮኸን በሠሩት ጥላቻ መሠረት ግን ከኢትዮጵያ ሕዝብም ቀድሞ የተወቀሰው አማራው ነበር። ሮማን ፕሮችስካ **ኢትዮጵያ የባሩድ በርሚል** ብሎ በሰየመው መጽሐፍ **አማራው ነጭን በኢትዮጵያ ክብር እንዳያገኝ አድርጓል** ሲል ገና በ1920ዎቹ ለአውሮፓ ፓርላማ አቅርቦ እንደነበር በወቅቱ ተዘግቧል።

የጀርመን ሉተራዊ ሰባኪያን እና የሮም የኢየሱስ ወታደሮች (Jesuits ወይም ሚሲዮናውያን) አማራ የቀደመ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና የእስልምና አማኝ እንዲሁም ባህላዊ ሕዝብ ነው በማለት በተቃርኖ ቁመው ታይተዋል። የአማራ ጥላቻ መነሾው ከውጭ ወራሪዎች ኢትዮጵያን የማድከም ሂደት ቢሆንም፤ የወራሪዎችን ምኞት ተጋሪ የሆኑት የሀገር ውስጥ በጥላቻ የሰከሩ ብሔርተኞችም በአማራ ጥላቻ ሕግ እና ተቋም ፈጥረዋል።

ኸርማን ኮኸን ከኢትዮጵያ ሳተላይት ሬድዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት(ኢሳት) ጥቅምት 2008 ዓ.ም. በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ አቶ መለስ ዜናዊን ‹‹መሬት የግለሰብ እንዲሆን መክሬው ነበር። ነገር ግን ይሄ ቀይ መስመር ነው አለኝ። ምክንያቱን ስጠይቀው አሁን ብዙው ባለሀብት አማራ ነው። መሬት የግለሰብ ከሆነ የኢትዮጵያ መሬት በሙሉ የአማራ ይሆናል። አማራ ሀብታም

ከሆነ ደርግ ተመልሶ ይመጣል፡፡ ስለዚህ ይህ የሀብት ክፍፍል እስኪስተካከል መሬት[49] የመንግሥት እና የሕዝብ (የብሔሮች) የማይሸጥ የማይለወጥ ንብረት ይሆናል፡፡›› አለኝ ሲሉ በአንደበታቸው ተናግረዋል፡፡ ኸርማን የአሜሪካ ካፒታሊዝምን በኢትዮጵያ ለመትከል ብዙ ነገሮች ለግል ባለሀብቱ እንዲሰጥ እንደሚሹ አያጠራጥርም፡፡

አቶ መለስም ከማርክሳዊ የአልባኒያ ኮሚኒዝም ወደ ምዕራባውያኑ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲሄዱ በምሥራቁ ክንፍ የኮሚኒዝም መፈራረስ ያስገድዳቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ከአሜሪካም ጉርሻ ይቅርብኝ ብለው የግለሰብ ሀብት ማፍራትን ከለከሉ፡፡ የከለከሉበት ሥጋታቸው ደግሞ ከአማራ ሕዝብ ብዙ ባለሀብት አለ የሚል ነው፡፡ ይሄን ሥጋታቸውን በሕገ መንግሥቱ አስፍረዋል፡፡ መሬት የሚሸጠው እና የሚለወጠው በኢሕአዴግ መቃብር ላይ ብቻ እንደሆነም በተደጋጋሚ ፓርቲው በአቋምነት ወስዷል፡፡ ሕገ መንግሥቱ የጥላቻ ዶሴ ነው የሚለው ትችት የሚመዘዘው ከእንዲህ ዓይነቱ የሴራ መነሻ ነው፡፡ መሬት የብሔር ሆኖ ሰፋሪ እና ነባር የሚለው ተረክም መነሾ ይህ ሃቅ ነው፡፡ ዘውጋዊ(ብሔር) መሆን የተሳናቸው ከተሞች የአፓርታይድ ሥርዓት ተጠቂ ሆነዋል፡፡ መሬትን ለብሔር መደልደል ከተሜዎች

[49] የመሬት ጉዳይ ከተማሪዎች የመሬት ላራሹ ንቅናቄ ጀምሮ ያልተመለሰ ጥያቄ ሆኖ ቀጥሏል። ዐፄ ቴዎድሮስ መሬትን የመንግ ስት ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ በመሬት አያያዝ ላይ ብዙ የተለወጠ ነገር የለም። ደርግም ሆነ ኢሕአዴግ የመሬት አያያዛቸው ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሶሻሊዝም ሥርዓት ተከታይ በመሆናቸው መሬትን የመንግሥት እዝ አድርገዋል። በተለይ ኢሕአዴግ መሬትን የብሔር አድርጎታል። ዋና ዋና ከተሞች ብሔር መሆን ስለማይችሉ መሬት አልባ ሆነዋል። ድሬድዋ እና ሐረር ከተማዎችን ብሔር ለማድርግ በአፓርታይድ ሥርዓት ውስጥ ወድቀዋል። ሐረር ግማሽ ለኦሮሞ ግማሽ ለሀደሬ ሆና የብሔሮች ሆናለች። ድሬድዋም ሶማሊያ እና ኦሮሞ ተካፍለዋታል። አዲስ አበባም ብሔሯን ስላልለየች ለመስፋፋት ተቸግራለች። በኢሕአዴግ የመሬት ሕግ መሠረት የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያውን ዜጎች አይደለም። የብሔሮች ነው። ከተማ ደግሞ በኢኮኖሚ መስተጋብር ምክንያት ቅይጥ ማንነት ሠርቶ አዲስ ማንነትን ይፈጥራል። የኢሕአዴግ የመሬት ሕግ ለከተሞች ፈተና ነው። አዲስ አበባ ከተማ 7 ሚሊየን ሕዝብ አካባቢ ይዛ በፌደሬሽን ምክር ቤት ብሔር ስላልሆነች ወኪል የላትም። አዲስ አበባ እና ሌሎች ታላላቅ ከተሞች ወኪል አልባ ሆነዋል።

በግለሰብ ደረጃ መሬት ለመግዛት፣ አብያተ እምነቶችን ለመገንባት ተቸግረዋል። በአማራ ጥላቻ ሰውነት ተክዶ በጅምላ ብሔረሰብነት መታወቂያ ሆኗል።

እንደ ናዝሬት(አዳማ)፣ ደብረዘይት ቢሾፍቱ)፣ ጅማ... የመሳሰሉት ከተሞች በባሕርያቸው በተለያዩ ማንነቶች ቀልጠው የተሠሩ ከተሞች ነበሩ። ይሁን እንጂ እነዚህን ከተሞች ዘውጌ ለማድረግ ከነዋሪዎች ፍላጎት ውጭ በኦሮሚያ ክልል ቋንቋ በኦሮሞኛ ብቻ እንዲገለገሉ ተደርጓል። በ1987 ዓ.ም. የጸደቀው ሕገ መንግሥት የተረከዙ ጫፍ ግለሰብን አለማወቁ፣ ኢትዮጵያን በብሔሮች እና ብሔረሰቦቿ ብቻ መበየኑ፣ መገንጠልን አልቆ ማበረታታቱ፣ ሕገ መንግሥቱ በራሱ ሊሻሻል የማይችል እና የብዙኃንን ድምጽ በንኡሳን ያስገዛ መሆኑ አውራ ህጸጾች ሆነው ይነሣሉ። ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የፌደሬሽን እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች፣ በአብዛኛው ክልሎች ሊያጸድቁት ይገባል። አማራ እና ኦሮሞ ብዙኃኑ ሕገ መንግሥቱ ይሻሻል ቢሉ አይሻሻልም። ምክንያቱም በሕገ መንግሥቱ ሐረሪም ሆነ ጋምቤላ ክልል በሕዝብ ቁጥር ሳይሆን በክልልነታቸው ከአማራ እና ከኦሮሞ ጋር እኩል ናቸው። ሕገ መንግሥቱ ለብዙኃን አሽናፊነት እና ለአናሶች መብት ጥበቃ የማይገዛ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባሕርይ አለው።

ሕገ መንግሥቱን የመተርጎሞ ሥልጣን ለሕግ ባለሙያዎች ሳይሆን ለካድሬዎች ስብስብ ለሆነው የፌደሬሽን ምክር ቤት መስጠቱ ሌላው የሕገ መንግሥቱ እንከን ነው። የፌደሬሽን ምክር ቤት ደግሞ ለብሔረሰብ ቁጥር ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጥ ደቡብ ክልል ከግማሽ በላይ ወኪል አለው። በፌደሬሽን ምክር ቤት ደቡብ ያለው ሐሳብ ገዥ ሕግ ይሆናል። በአንጻሩ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ሌሎች ብሔረሰብ ስላልሆኑ ወኪል የላቸውም። ከተሞች በብዛት በግለሰብነት ራሳቸውን የሚገልጹ ነዋሪዎች ስላሏቸው ሕገ

መንግሥቱ አያውቃቸውም:: ሕገ መንግሥቱ ደርግን ለመቃወም እና የኅብረተሰባዊ ኮሚኒስታዊ አብዮቱን በብሔረሰቦች ተርጉሞ ለማንበር የዳዳ የነስታሊን እና ሌኒን አስተምህሮ ውጤት ነው::

ሕገ መንግሥቱ ሲረቅ ባሳተፈው ሰው፣ በያዘው ይዘት እና በተተግባሪነቱ ላይም ሁነኛ ግድፈቶች ተስተውለውበታል::

3.2 የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት እና ተረከዙ ያረፈበት መንፈስ

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የባለሥልጣናትን የሥልጣን ጊዜ እንዳይገድብ ያደረግነው የኢሕአዴግን እድሜ ለማርዘም ነው:: ሕገ መንግሥቱ መንፈሱን የቀዳነው ጫካ እያለን ከኮሚኒስታዊ አስተሳሰብ ነው:: አንቀጽ 39ንም የቀዳነው ከሩሲያ ነው:: (የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ ዋልታ ቴሊቪዥን፣ ጳጉሜን 1 ቀን 2011 ዓ.ም.)

ሀ. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ክዷል

የሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ ሁለት የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌደራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተወሰነ ነው ይላል:: የዚህን ምን ማለትነት ለመረዳት የሕገ መንግሥቱን ረቂቅ ቃለ ጉባኤ መመልከት ያስፈልጋል:: ሕገ መንግሥቱ ሲረቀቅ 543 ሰዎች የተሳተፉበት ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል ከ86[50] ከመቶው የሚበልጡት የኢሕአዴግ አባላት ናቸው:: ስለዚህ ሕገ መንግሥቱ የኢሕአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፓርቲ ሰነድ እንጂ የሕዝብ የሚሆንበት ምንም ዓይነት ተጠየቅ(logic) የለም::

---

[50] አሥራት አብርሃም የሕገ መንግሥቱ ፈረሰኞች

3.3 ኩዓካዊነት በወሰን

የስኳር ኮርፖሬሽንን ከ77 ቢሊዮን ብር በላይ በማክሰር የሚታሙት የሕወሃቱ ጉምቱ ባለሥልጣን አቶ ዓባይ ፀሐየ በወቅቱ ‹‹የኢትዮጵያ ወሰን ሕዝብ ፈቅዶ ኢትዮጵያዊ ነኝ እስካለበት ድረስ ያለው ነው፡፡ እንደ ደርግና ንጉሡ ዘመን ኢትዮጵያዊ ያልሆነውን ሁሉ ኢትዮጵያዊ ለማድረግ ጦር አንማዘዝም›› ብለዋል፡፡ የአቶ ዓባይ ፀሐየን ሐሳብ ብዙዎቹ ተሳታፊዎች ተጋርተውታል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ረቂቅ መሠረት የመተማ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፣ ሱዳናዊ ነኝ ቢል ወደ ሱዳን መሄድ ይችላሉ፡፡ በደቡብ እነ ሞያሌ፣ በምዕራብ እነ ጋምቤላ፣ ወደ ኬንያና ወደ ደቡብ ሱዳን እንሒድ ካሉ መብታቸው ሆኖ ድንበሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባሉት ብቻ ይወሰናል፡፡

እንዲያውም አቶ ተስፋዬ ፊቻል የተባለ ተሳታፊ የኢትዮጵያ ድንበር ሰፍቷል ይቀነስ የሚል ይዘት ያለው ሐሳብ ሁሉ አስተጋብቷል፡፡ የኢትዮጵያ ወሰን ግዛት ኤርትራን ማካተት አለበት ተብሎ ለተነሣው ሙግትም 526ቱ ሲቃወሙ፣ 2 ሰዎች ብቻ ኤርትራን የኢትዮጵያ አካል ናት ሲሉ፣ 5 ሰዎች ድምፅ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ቡድኑ ኢትዮጵያ የባሕር በር አያስፈልጋትም ብሎ በ98 በመቶ ድምፅ ደግፏል፡፡ የኢትዮጵያ ወደብ ያስፈልጋታል ብለው የተከራከሩት ነፍጠኛ እና ትምህክተኛ የሚል የስድብ ናዳ ወርዶባቸዋል፡፡

በእርግጥ የኤርትራ መገንጠል ቀድሞ በ1960ዎቹ መጨረሻ በነሕወሓት መቀሌ ባለ አንድ ቡና ቤት ላይ የተወሰነ ስለሆነ የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ጉባኤው ለይስሙላ እጅ ከማውጣት የዘለለ ሚና አልነበረውም፡፡ ሕወሓት ባድሜን እና ሌሎች የትግራይ ግዛቶችን ሁሉ ለመስጠት ጫካ ላይ እያለ ለሻዕቢያ እንደፈረመ የቀድሞው

ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ ጳጉሜን 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ለዋልታ ቴሌቪዥን በሰጡት ቃለ መጠይቅ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። የስታሌናዊ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መሪው ሕወሓት የተናገረውን ይጥቀምም፤ አይጥቀምም ጉባኤተኞች ሁሉ ይደግሙት ዘንድ ይገደዳሉ። በወቅቱ ሕወሓት የጉባኤተኞች የግራ እጅ የነፍጠኞች ስለሆነ ይቆረጥ ቢል እንኳ ጉባኤተኞች እጃችን ይቆረጥ ብለው እጃቸውን ማውጣታቸው አይቀርም ነበር።

ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርም ግንቦት 13 ወደ ዚምባብዌ ሀራሬ እንደሸሹ ግንቦት 16 ቀን 1983 ዓ.ም. ኤርትራ ነጻ ሀገር መሆኗን አወጀች። ነጻ ሀገር ነኝ ስትል ኢሕአዴግ አይዞሽ ብሎ 300[51] ሚሊየን ብር ሸለማት። ከገንዘብ ስጦታው በተጨማሪ የሕዝብ ሁሉ ጠላት ተደርጐ የተፈረጀው አማራው አስመራ ድረስ ሂዶ በኢሕዴን (ብአዴን) መሪነት ይቅርታ ጠይቋል።

ሕገ መንግሥቱ ሲረቅ ኢትዮጵያ በዚያድ[52] ባሬ የምትመራውን ሶማሌን መተንኮሷ ዓለም አቀፍ ሕግን የሻረ እንደነበር አቶ ግርማ አዱኛ የተባለ ተሳታፊ በአፅንኦት ተናግሯል። ኢትዮጵያን ወንጀሏል። ኢትዮጵያ ግዛቷን ለማስከበር የምታደርገው ውጊያ በሙሉ በአንዳንድ ጉባኤተኞች በረቂቅ ሰነድ ተወግዟል።

ሶማሌ ከነእንግሊዝ ነጻ ስትወጣ ባለ አምስት ኮከብ ሰንደቅ ዓላማ አዘጋጀች። የኮከቡ ትርጉም አምስቱ ሶማሌዎችን በአንድ ሶማሊያ አካቶ ታላቅ ሀገርን መመሥረት ነበር። ዚያድ ባሬ የሞቃዲሾ እና የሀርጌሳ ሶማሌዎችን አጣምሮ በጅቡቲ፣ በኬንያ እና በኢትዮጵያ ያሉ ሶማሌዎችን ለመጠቅለል የመጀመሪያ ዘመቻውን ወደ ኢትዮጵያ አደረገ። ኢትዮጵያን እስከ ሐረር [53]ድረስ ወሮ 700

[51] ያሬድ ጥበቡ ወጥቸ አልወጣሁም

[52] አሥራት አብርሃም የሕገ መንግሥቱ ፈረሰኞች

[53] ዶክተር ፈንታሁን አየለ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከ1967 እስከ 1983

ካሬ ኪ.ሜ አካባቢ መሬት ተቆጣጠረ። በዚህ ጦርነት ሩሲያዎችና ኩባዎች ከኢትዮጵያ ጐን ሆነው ዚያድ ባሬን ተዋግተዋል።

ይሄን ሁሉ ሀቅ ሽሮ ኢትዮጵያ በደርግ [54]ዘመን ከሱማሊያ ጋር መጣላቷ ዓለም አቀፍ ሕግን የሻረ ነው የሚል ሐሳብ ተነሣ። በጉባኤተኞች ሐሳብ መሠረት ሐረር እና ድሬዳዋ የሞቃዲሾ ግዛት ሥር ቢሆኑ ችግር አልነበረውም።

መንግሥቱ ኃይለማርያም በሶማሊያ ጦርነት የአካባቢ አርሶ አደር ሚሊሻዎችን በማሰልጠን ወደ 300ሺህ[55] ወታደር አሳትፈዋል። ኮሎኔል መንግሥቱ፤ በሶማሊያ ጦርነት ያደረጉት ወታደር በፍጥነት የመመልመል ሂደት ጆሴፍ ስታሊን የሂትለርን ጀርመን ጦር ለመምታት ካደረገው ዝግጅት ጋር ይቀራረባል። ሁለቱም የሰለጠነ ጦር ሳይኖራቸው፤ ገበሬ እና ሚሊሻ በብዛት በማሳተፍ ገድል ሠርተዋል። መንግሥቱ የዚያድ ባሬን እና የሶማሊያን የመስፋፋት ሕልም እስከመጨረሻው ሲያስጨነግፉ፤ ስታሊን ደግሞ የአዶልፍ ሂትለርን እብጠት አስተንፍሶ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሩሲያ ድል አድራጊነት እንዲገባደድ አድርጓል። ይህን ኩራት ግን የሕገ መንግሥት አርቃቂ ቡድኖች የመንግሥቱ ኃይለማርያም ጥፋት እንደሆነ አድርገው ወስደዋል። ይሄን ተከትሎም ከግማሽ ሚሊየን

[54]ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ጀምሮ እየተደራጀ የመጣው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በ1983 ዓ.ም. የደርግ ተልዕኮ ተሸካሚ ነው ተብሎ ተበትኗል። ይህ ሠራዊት ኤርትራ ከእናት ምድሯ እንድትቆይ፣ የሶማሌን ወረራ በመመከት እና በልዩ የሀገር ፍቅሩ ይታወቃል። አስመራ እና አዲስ አበባ ያለው ወታደር ለሻእቢያ እና ለሕወሓት በ1983 ዓ.ም. ዝም ብሎ እንዲገቡ የፈቀደላቸው ሀገር እንዳይፈርስ ነበር እንጂ ቢያንስ ከተማ ማቃጠል እና መዝረፍ ይችል ነበር። ግን ይሄን አላደረገም። አስመራን ሻዕቢያ ሲቆጣጠር ወደ 100ሺ ወታደር በአካባቢው ነበር። ከተማ ሳያወድም በጨዋነት ሻእቢያን ተቀበለው። ይሄን የመሰለ ሠራዊት ግን ውለታ እና ክብሩ ተፍቆ ተበተነ። ጭራሽ ዚያድ ባሬን መውጋቱ ልክ እንዳልነበር ተነገረ። ኤርትራ እንዳትገነጠል መሥራቱ ወንጀል ሆኖበት የኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝ የትምክህት ኃይል ተደርጎ ተፈርጇል። ይህ ሠራዊት ቀድሞ የተሠራበትን ሴራ ፍቆ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ለሀገሩ ተዋግቷል።

[55]ባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983

በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የደርግ ወራሪ ነው በማለት እንዲበተን ሲደረግ፤ የኢሠፓ አባላትም በሽግግር መንግሥቱ እንዳይሳተፉ ተደርገዋል።

3.4 ሰንደቅ ዓላማ

ሰንደቅ ዓላማ የሀገር ምልክት ነው። አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከአድዋ እስከ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ድረስ የነጻነት ምልክት ሆኖ ቆይቷል። የጥቁር ሕዝቦች ነጻነትን ያስተማረችው ሀገራችን ሰንደቅ ዓላማዋ የአፍሪካ ብሔርተኝነት አርማ ተደርጐ ይወሰዳል። ከአፍሪካ ሰማይ ሥር ነጻነቷን ያስከበረች፤ የቅኝ ግዛት ሸካራ ቀንበር ወደ ትክሸዋ ያላስገባች ኢትዮጵያ ናት። ይህ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ተጋድሎ ደግሞ በሰንደቁ ይገለፃል። እነጋና፣ ቤኒን፣ ኮንጐ፣ ማሊ፣ ሴኔጋል... ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት የአፍሪካ ሀገራት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ምልክታቸው አድርገው ወስደዋል። የጃማይካ ራስታዎችም አረንግዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማውን መገለጫ አድርገዋል።

ይሄን ሰንደቅ ዓላማ ኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥቱን ሲያጸድቅ ያስቀጠለው ቢሆንም ከመሀል ኮኮብ አክሎበታል። ምልክትነቱም ለብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሁለንተናዊ እኩልነት አድርጐ ይወስዳል። ኮሚኒስቶች ኮከብን ከማን አህሎኝነት ተነሥተው ይመርጣሉ። በሕወሓት ኢሕአዴግም ይሄ መንፈስ ሳይሰርፅ አይቀርም። ለማንኛውም ሕገ መንግሥቱ ሲረቅ ስለዚህ ሰንደቅ ዓለማ ምን ተባለ የሚለውን ሐሳብ ከአሥራት አብርሃም ሰነድ ቃርመን እንመልከት። ጉባኤተኞች በብዛት የአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማውን የጨቋኞች ምልክት አድርገው ወስደዋል። ለአብነት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ ሀሰን አሊ ሰንደቅ ዓላማው የቅኝ ገዥዎች ምልክት አድርገው ሲወስዱት

ከደቡብ የተወከሉት አቶ ኤልያስ ተሮ እና ከሶማሌ ክልል የተወከሉት አቶ አብዱልከሪም አህመድ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማው በይፋ መቃጠል አለበት፤ የወረራ እና የብዝበዛ ምልክት ነው ብለዋል።

የእነዚህ ሰዎች ሰንደቅ ዓላማውን የወረራ[56] ምልክት የሚያደርጉት ብሔሮች እንደ ሀገር ሉዓላዊ ሥልጣን ነበራቸው ከሚል እሳቤ የመነጨ ነው። አቶ ሀሰን አሊ ሰንደቅ ዓላማው የቅኝ ገዥዎች ነው ወደ ሚል ሐሳብ ያስጠጉት ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ አይደለም ለማለት የፈለጉ ይመስላል። ዳግማዊ ምኒልክን ወራሪ አድርጐ መቁጠር ብሔሮች ራሳቸውን የቻሉ ሀገሮች ቢሆኑም አማራው ምኒልክ በቅኝግዛት ኢትዮጵያን ፈጥሯል የሚል አንድምታ አለው። ሕገ መንግሥቱ ሲረቅ የተሰበሰቡት ብዙዎች ተሳታፊዎች ኢትዮጵያዊነትን በይፋ መካድ ብቻ ሳይሆን ለማጥፋት ጥረዋል።

56 የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ጉባኤተኞች በሰንደቅ ዓላማው ላይ ያላቸው ጥላቻ በአድዋ ከተሸነፈችው ጣሊያን ባይበልጥም አያንስም። ጣሊያኖች ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም. አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩን ሰንደቅ በይፋ አቃጥለዋል። አውርደዋል። የዳግማዊ ምኒልክን አሻራ አዲስ አበባ ፒያሳ ያለውን ሐውልት ጨምሮ ለማጥፋት አላመነቱም። የኢትዮጵያን ነባር እሴት ሁሉ አውድመዋል። የኢትዮጵያዊነት አያያዥ ሐረግ ናቸው ብላ የለየቻቸውን ዘውዱን፣ አማራን እና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ጣሊያን ሞክራለች። በብሔር ለመከፋፈልም ሞክራለች።

የሕገ መንግሥቱ ጉባኤተኞች ከሞሶሎኒ በላይ ሞሶሎኒ፣ ከዚያድ ባሬ በላይ ዚያድ ባሬን ሆነው ቀርበዋል። ቤልጂየም በሩዋንዳ ሁቱ እና ቱትሲ ጎሳዎች መሃል የፈጠረችውን ክፍፍል፤ ጣሊያንም አማራን በማስጠላት ኢትዮጵያን ለቅኝ ግዛት ለማመቻቸት ያደረገችው ጥረት በአክራሪ ብሔርተኞች ቅቡል ሆኗል። በዚያድ ባሬ ወረራ ወቅት አንዳንድ የኢሕአፓ አባላት ሶማሊያን አንዋጋም ብለው የነበረ ሲሆን፤ ኦነግም በ1990 ዓ.ም. የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት አሮሞ ከኢትዮጵያ ጎን እንዳይሰለፍ አስመራ ሆኖ ይቀሰቅስ እንደነበር ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ በ1993 ዓ.ም ሪፖርተር የተባለ መጽሔት ባደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ተናግረዋል። የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ የተነሡ ፖለቲከኞች የዓላማ ቁርጠኝነታቸው የዳበረ ቢሆንም፤ የኢትዮጵያዊነትን እሴት የካዱ ነበሩ ማለት ይቻላል። የፖለቲካ ትግላቸው ጸረ ኢትዮጵያዊ አቋምን የሚያስተጋባ ነበር።

የሕገ መንግሥቱ መንፈስም የባለፉት ሥርዓቶችን አሻራ በበቀል ማረም ላይ ያተኮረ ነው። ነጋዊ ሕልምም የለውም። ትናንታዊ ትዝታን ጽልመት ያለብሳል። የሕገ መንግሥቱ አርቃቂዎች ‹‹የኢትዮጵያ ድንበር በታሪክ ሳይሆን በፌደራል ክልሎች ስምምነት ይወሰናል ሲሉ፤ ኢትዮጵያ በጉንደት፣ በጉራ፣ በአድዋ፣ በማይጨው፣ በካራማራ፣ በባድሜ... የተደረጉ ድንበር የማስከበር እና ሉዓላዊነትን የመጎናጸፍ ተጋድሎዎች አግባብ አልነበሩም›› የሚል ይዘተ ነገር ይወጣዋል። የሰንደቅ ዓላማ ጥላቻም ትናንትን በጭፍን ከመጥላት የሚመነጭ ነው።

ከአማራ ክልል የተወከሉት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ቡድን አባል ወይዘሮ ዓባይነሽ ካሳ ‹‹አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩ ሰንደቅ ዓላማ የብዝበዛ እና የጭቆና ምልክት ነው፤ ስለዚህ ይህ ባንዲራ ሙሉ በሙሉ መቀየር አለበት›› እንዳሉ የሕገ መንግሥቱን ረቂቅ ጠቅሶ አቶ አሥራት አብርሃምም ሰንዷል። ወይዘሮ ዓባይነሽ የአማራንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዴት ትወክላለች? የአማራ ሕዝብ ኢሕዴን (ብአዴን) አይወክለኝም የሚለው ከእንደዚህ ዓይነት መነሻም ይመስላል። የሕገ መንግሥቱ መንፈስ በረቂቅ ሰነዱ ላይ ለተመለከተው አጽዳቂዎቹ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችን መስለው ቀርበው ተውነውበታል። ለዚህም ይመስላል አንዳንዶቹ ‹‹ሕገ መንግሥቱን ሕገ አራዊት ነው›› የሚሉት።

3.5 የአማራ ጥላቻ እና ሕገ መንግሥቱ

ዳግማዊ ምኒልክ የነፍጠኛ እና የትምክህት ኃይል መሪ ተደርጎ ተወስዶ ዐፄ ዮሐንስ እንደ ነፍጠኛ የማይታየው ለሕወሓት ስለቀረበ አይደለም። የዐፄ ዮሐንስ ነፍጠኝነት ከሕወሓት ይልቅ ለእናንተ ይቀርባል። (እናንተ ሲባል ሻለቃ አድማሴ ዘለቀን ሲሆን፤

በይዘቱ ነገሩ አማራን ማለት ነው):: እኛ የዐፄ ዮሐንስን ዘር ቆጥሮ የተነሣውን ኢ.ዲ.ዩን ገና በ1967 ዓ.ም. በብረት ሕወሓት ተፋልሟል:: ለሕወሓት ከነፍጠኛው ዮሐንስ ይልቅ ጭቁኑ አማራ እና ኦሮሞ ይቀርበዋል:: (የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ አባል አቶ ዓለምሰገድ ገብረ አምላክ ከሕወሓት የተናገረው፣ አሥራት አብርሃምም እንደመዘገበው)

ለሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ጉባኤ የተጠሩት 543 ጉባኤተኞች ብዙዎቹ ሰውነታቸውን ክደው የቆሙ አምሳለ ሰው ቀፎዎች እንደነበሩ በአንደበታቸው የሚያወጡት ቃል ይመሰክራል:: የእሳቤ ሙሌታቸው በአማራ እና በኢትዮጵያዊነት ጥላቻ የሰከረ ስለነበረ የሚናገሩት ሐሳብ ተጠየቃዊነት ይጐለዋል:: በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ሰነድ ዝግጅት ላይ የተገኙ አባላት ትኩረት ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ከምድረ ገፅ ማጥፋት፣ ለኢትዮጵያዊነት የቀረበ ስሜት ያለውን ሕዝብ እና አማራን ትምክህተኛ እና ነፍጠኛ ብሎ ሀገር አልባ ባላገር ማድረግ ታላሚ ያደረገ ነበር:: የሃይማኖት አባቶች ሳይቀር የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ነው ብለው የሚያስቡትን ሰይጣን ትተው ሰይጣን አማራ ነው ብለው አስበው እንደነበር የሕገ መንግሥቱን ረቂቅ የመረመረው አሥራት አብርሃም ተንትኗል:: የሕገ መንገሥቱ አርቃቂዎች ራሳቸውን ከመካዳቸው ባሻገር የሌላውን ሰውነትንም በሕግ አግደዋል:: ሕገ መንግሥቱ ሰውነትን (ግለሰብነትን) በብሔር ብሔረሰቦች ሽፍኖ አንቆ ገሎታል:: አማራነትን እና ኢትዮጵያዊነትን የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ በሆነው ሕገ መንገሥት ተቋማዊ አድርጎ ማጥፋትም የአርቃቂዎቹ የሐሳብ መዳረሻ ሆኖ ቀርቧል::

በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ቤተሰባዊነት እና ጋብቻን በተመለከተ በተነሣ ሐሳብ ያላቻ ጋብቻን የሚያበረታቱት ትምክህተኞች እንደሆኑ ከአማራ ክልል የተወከሉ ቄስ ጌጡ ጉበና የተባሉ ካህን ተናግረዋል:: በወቅቱ

አማራነት ማለት ጥፋት ተደርጐ ሲተረጐም፣ ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በተፈለገ ጊዜ ተተክሎ የሚነቀል የኀዘን ወይም የደስታ ድንኳን ተደርጐ ተስሏል። ሕገ መንግሥቱ ራሱን ሲተረጉም፤ ኢትዮጵያዊነት የብሔሮች እዳ ሆኑን አስቀርቻለሁ ይላል። ኢትዮጵያዊነት ብሔሮች በፈቃዳቸው እስከተቀበሉት ድረስ የሚኖር ፕሮጀክት እንጂ በግዳጅ አይጫንም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ወሰን ታሪካዊ ድንበሮች ሳይሆኑ የፌደራል አባል ክልሎች ወሰን ተደርጎ ይወሰዳል። ሕገ መንግሥቱ ደርግን ለመቃወም ስለወጣ እንደ ደርግ በድንበር ምክንያት ከጎረቤት ሀገራት ጋር አንጣላም የሚል መንፈስ ታቅፏል። በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ጉባኤ ላይ እንደሰፈረው ደርግ የሠራውን መልካምም ሆነ መጥፎ ተግባር እኩል በመጥፎነት ተፈርጇል። የሀገር ሉዓላዊነት የማስከበር ሂደቱ ሳይቀር የደርግ ህጸጽ ተደርጎ ተወስዷል።

ሕገ መንግሥቱ የኢትዮጵያዊነትና የአማራ ኢምፔሪያሊዝምን ለመናድ እና ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን ከኢምፔሪያሊዝሙ ለመነጠል እንደወጣ ያሳያል። ለዚህም የሃይማኖት አባቶች ሳይቀር ኢትዮጵያዊነትን ክደው የብሔር ሰባኪያን ሆነው ተገኝተዋል።

ቄስ ሚካኤል ሁንዴሳ የተባሉ ካህን ደግሞ እግዚአብሔር የብሔሮች አባት ነው ሲሉ ለጉባኤተኞች ሰብከዋል። እግዚአ-ብሔር የሚለውን በቀጥታ ተርጉመው ‹‹የብሔር ብሔረሰቦች አባት›› ሲሉ አስረድተዋል። በሰንበት ትምህርት ቤት እንደተማርኩት እግዚእ-አብ-ሔር ማለት እግዚእ-ጌታ፣ አብ-አባት፣ ሔር-ሩህሩህ ማለት ሲሆን በጥቅሉ የሰው ልጆች ሁሉ ቸር አባት ማለት እንጅ የኩናማ፣ የሱማሌ፣ የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሞ አባት ማለት አይደለም። በነገራችን ላይ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶችም “ኢየሱስን የሰቀለው ነፍጠኛ አማራ ነው” ብለውም አስተምረዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ጾም መጾም ምኒልክ እንድንከሳ፣ በብሔራችን ላይ ጭቆና ለማድረግ ያመጣው የቅኝ ግዛት ማስፋፊያ በመሆኑ አንጾምም ያሉ ወጣቶችም አሉ፡፡ በተለይ በኦሮሚያ ክልል ይህ ስብከታዊ ህጸጽ ከፍ ብሎ ይሰማል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ዓይነት የሥነ-መለኮታዊ ታሪክ ተናጋሪዎች ‹‹ገነት ጣና ዳርን ተከትሎ በጎጃም ይገኛል፡፡ አዳምም ጎጃሜ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ሆኖ የጎጃምን መሬት ረግጧል›› የሚል ሃይማኖታዊ ንግርት አበልጽገዋል፡፡ ይሄን ተከትሎም አማራነትን እንደ ሰይጣንነት የሳሉ የተሳሳተ ምስል ያላቸው አንዳንድ የዋህ ብሔርተኞች ‹‹አዳም አማራ ከሆነ ከአዳም አልተፈጠርንም፤ ኢየሱስም በአማራ መሬት ከተገኘ የሰቀለው ነፍጠኛ እና ትምክህተኛው አማራ ነው›› የሚል ጥላቻ ወለድ ሞኛሞኝ ተረት ያሰማሉ፡፡ ጥላቻ ምክንያታዊነትን ፍቆ የሰውን ልጅ ወደ ሞኝነት ጎዳና ይገፋል፡፡ እውነትን ጋርዶ እውቀትን ያስጨነግፋል፡፡

ለዚህ እና መሰል ስብከቶች እጃቸውን የሰጡ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኦሮሞ መጨቆኛ ሆናለች በማለት የኦሮሞ ሲኖዶስ ተመሥርቶ በኦነግ የኦሮሞነት ቅኝት እንዲመሠረት ይሻሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ የሀገረ መንግሥት ምሥረታው አስኳል በመሆኗ፤ በሀገረ መንግሥት ግንባታው ያኮረፉ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ይገፋሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያኗን መግፋት ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ከማኮሰስ በተጨማሪ፤ ሀገራዊ ርዕይን የማስጨንገፍ ሂደት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመንን ከተፈጥሮ እና ከኢትዮጵያ እሴቶች ጋር አዋዳ ልዩ ቀለምን የፈጠረች የሀገረ መንግሥቱ ግንባታ ሥጋ እና ደም ናት፡፡ ኢትዮጵያ ብዙውን

ከአፍሪካ እና ከሌላው ዓለም የተለየ ነገሯን ያገኘችው ከቤተ ክርስቲያኗ ነው። ፊደል እና ሥርዓተ ጽሕፈት፣ ዘመን ቆጠራ እና ታሪክ፣ ባህል እና ትውፊት፣ ዳኝነትን አስከ ሕግ ሥርዓቱ… ወዘተ ቤተ ክርስቲያኗ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረገችባቸው ዘርፎች ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ አንጻር ስንመለከታት ለእራሷ እምነት ተከታዮች ብቻ ሳትሆን ለየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የወል ጸጋ ናት። ለአብነት ላሊበላ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለእምነት ገደብ ይቀርባል። በይዘቱ የሃይማኖት አሻራ ቢሆንም፤ ባለው ሀገራዊ ቀለምነት ምክንያት የወል ጸጋ ሆኗል። ነገር ግን የኦርቶዶክስንም ሆነ የእስልምና ሃይማኖቶችን ወላዊ ባሕርይ ወደ ንጥላዊ(ዘውጋዊ) ማንነት በመቀየር የፖለቲካ ልሂቃን በሃይማኖት ሳይቀር መጣረስ እየፈጠሩ ነው።

የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች እንደ መንግሥት አወቃቀር የዘውግ አደረጃጀት ከተከተሉ ሕዝቡ በቀጥታ ወደ ጎሳ አምልኮ ይገባል። ሶማሊያን እስልምና ሀገረ መንግስቷ እንዲጸና ያላደረገው ሶማሌዎች ከእስልምና ይልቅ ጎሳቸውን በማምለካቸው ምክንያት ነው። በሶማሊያ የጎሳ መሪዎች ከሃይማኖት መሪዎች የገዘፈ ክብር እና ሞገስ አላቸው። በአንጻሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና እና እስልምና ኢትዮጵያዊነትን በማስረጽ ሕዝቡ በብሔሩ እና በጎሳው ቅንፍ ውስጥ ተዘፍቆ እንዳይቀር አድርገዋል። የምዕመናኑን አድማስ በኢትዮጵያዊነት ሰፍረው ይለካሉ። የሃማኖቶች ዋነኛ ፈተናም ከግለሰብነት ወይም ከሰውነት አውጥቶ ሰውነትን በጅምላ በብሔር እና ብሔረሰብ በሚሰፍረው ስልቻ የፖለቲካ ልሂቃን ለማስገባት መሞከራቸው ነው።

የኢሕአዴግ ሥሪት በዚህ ከቀጠለ ነቢዩ መሀመድ አረባዊ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳዊ ነው ብሎ የሃይማኖት መሥራቾችን በብሔር

መስፈር ሊመጣ ይችላል። ሕወሓት ቤተ ክርስቲያንን ዘውጌ ለማድረግ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በሸዋ አማራነት ፈርጆ፤ አቡነ አረጋዊን በትግሬነት ለማቆም የሞከረው ገና ጫካ እያለ ነበር። ሕወሃቶች ከደርግ ለማምለጥ የመነኩሴ ቢጫ ልብስ እየለበሱ፣ በገዳማት እና በአድባራት እየተጠጉ…ለድል ቢበቁም የበሉበትን ወጭት ሰብረው ቤተ ክርስቲያንን የሚያደክም እና የሚሰልል ቡድን አቋቁመው ዙረው ታግለዋታል።[57]

በ1966 መጀመሪያ ጥራዝ ነጠቅ ብሔርተኞች ግን ሃይማኖት የአማራ ነው ብለው ሃይማኖት የለሽ (athiest) ሆነው ሲያበቁ፣ እንጀራ የአማራ ስለሆነ አንበላም ለማለት ሁሉ ሞክረዋል። ይህ ስሁታዊ ጥላቻ ትናንትን ሙሉ በሙሉ በመፋቅ ላይ የተመሠረተ ስለነበር የእምነት ተቋማትን ሳይቀር ክፉኛ አንገዳግዷል።

[57]ዶክተር አረጋዊ በርሄ፣ A poltical history of Tigray people liberation front (1975-1991) revolt ideology and mobilization in Ethiopia, እንዲሁም የሕወሓት የፋይናንስ ዘርፍ የነበሩት አቶ ገብረመድኅን አርአያ በ2008 ዓ.ም. ለኢሳት ቴሌቪዥን ከሰጡት ቃለ መጠይቅ ሐሳብ ተወስዷል። ራሳቸው አቶ ገብረመድኅን አርአያ ሙስሊም ሆነው እንደሚሠሩ ተናግረዋል። ሞሀመድ ተብለው ጀለብያ ለብሰው ከሱዳን እና መሰል አረብ ሀገራት ጋር በእስልምና አፍቃሪ ስም እርዳታ ለመቀበል ሞክረዋል። በ1977 ዓ.ም. ድርቅ በርካታ በቆሎ ለትግራይ ከውጭ እርዳታ ሁሉ ተቀብለው ሸጠው የጦር መግዣ አድርገውታል። ጸረ ሃይማኖት እና ጸረ እሴት ሆኖ የተነሣው ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ እስከ ሃይማኖቱ መበደል የጀመረው ገና ጫካ ላይ ነው። በወቅቱ እነ ደብረ ዳሞም ሆነ እነ አልነጃሽ በስብሐት ነጋ በሚመራ የሃይማኖት የስለላ ክንፍ ተመርተዋል። ሃይማኖቶች ዘውጌ እንዲሆኑ ተገደዋል። አቶ ታምራት ላይኔ ጫካ እያለን ብዙዎቻችን ሃይማኖት አልነበረንም። እኔ ራሴ ሃይማኖቴ ኮሚኒዝም እንጂ ክርስትና ወይም እስልምና አልነበረም ሲሉ ተናዘዋል። ነገር ግን አቶ ታምራት በ1984 ዓ.ም. ወዲያው ከጫካ ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንደገቡ፣ በቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ሥልጣን ሥር ገብተው አቡነ መርቆርዮስን አባረው አቡነ ጳውሎስ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑ አድርገዋል። ሕወሓት ግን ይሄም አልበቃ ብሎት በ1990 ዓ.ም. የትግራይ ቤተ ክህነት እና ሲኖዶስ ይመሥረት አስብሎ በመቀሌ ሰልፍ አስወጣ። ቤተ ክርስቲያን በዘር እንድትቧደን ጣረ። የኦሮሞ ብሔርተኞችም በተለይ ከነሀሴ 2011 ዓ.ም. ጀምረው ቤተ ክርስቲያን በዘር ተቧድና የኦሮሞ ብሔርተኝነትን አቀንቃኝ እንድትሆን ጥረዋል። በጥላቻ በተመሠረተ የዘውግ መንግሥት ውስጥ ሃይማኖቶች ሙሉ በሙሉ ኅሳ ወይም ነገድ አምላኪ እንዲሆኑ ይገደዳሉ። ይህ ደግሞ የሃይማኖት ቁመና አይደለም። ሃይማኖት ከብሔር እና ከነገድ አጥር ያመለጠ መዳረሻውን ሰውነት ያደረገ አስተምህሮ ነውና።

3.6 የአንቀጽ 39 ተረከዝ የከፈተው ቦዩ

ሕገ መንግሥቱ መገንጠልን ቀላል አድርጎ፤ ሕገ መንግሥቱ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ግን ዝግ እና ውስብስብ አድርጎታል። ሕገ መንግሥቱን ከማሻሻል መገንጠል በጣም ቀላል ነው። (አቶ ታምራታ ላይኔ፣ ናሁ ቲቪ ጳጉሜን 2 ቀን 2011 ዓ.ም.)

ለማንኛውም ወደ ሌላው የሕገ መንግሥቱ ዶሴ ስናቀና የመገንጠል አዋጅን በአንቀፅ 39 እንመለከታለን። በረቂቅ ሰነዱ ዝግጅት ወቅት ‹‹**ባልና ሚስትም ይፋታል እንኳን ብሔርና ሀገር**›› የሚል ሐሳብ ተነሥቷል። የመገንጠል ጉዳይ ፍሬነገሩ ከሰማኒያ ጋብቻ የሀገር አንድነት ጉዳይ በአርቃቂዎች አንሶ ተገምቷል። ሁሉም የብሔር ተወካዮች ኢትዮጵያን እንደተበላበት እቁብ የዘነጓት የአማራ አንጡራ ንብረት ናት ብለው በማሰባቸው ነው።

ወይዘሮ አለማሽ ግርማይ የተባሉ ከትግራይ የተወከሉ አርቃቂ አባል ‹‹በትዳር መጋባት እንዳለ መፋታት እንዳለው ሁሉ ብሔረሰቦች ካልፈቀዱ መገንጠል መብታቸው ነው ብለው ሲከራከሩ፤ አቶ ዓባይ ፀሐዬ ደግሞ መገንጠል ከዐፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ የነበረ የ100 ዓመት ጥያቄ ነው››[58] ሲሉ ታሪክ ጠቅሰው ደግፈዋል። ከአዲስ አበባ በግል ከገቡት ወኪሎች ውጭ ብዙዎች የኢሕአዴግ አባላት መገንጠልን ከጋብቻ ቀን በላይ ናፍቀው ታይተዋል። ትልቁ ምጸት ደግሞ በዚህ መንፈስ ለተጻፈው ሕገ መንግሥት ‹‹ሕገ መንግሥቱ ለብሔረሰቦች እስከ መገንጠል የደረሰ ሙሉ መብትን የሠጠ ከህንድ እና ከአሜሪካ ሕገ መንግሥቶች ሁሉ የተሻለ ነው››[59] ሲል ሕገ መንግሥቱ በትርጓሜው ላይ አስፍሯል።

---

58 አሥራት አብርሃም፣ የሐገ መንገሥቱ ፈረሰኞች

59 የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ትርጉም

በሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ቡድኖች ዘንድ አማራ ከእንግሊዝ እና ከፈረንሳይ የበለጠ ነፍጠኛ እና ትምክህተኛ ወራሪ ኃይል ሆኖ በጉባኤተኞች ተስሏል። ትምክህተኝነትና ነፍጠኝነት ጭራቅ ሆነው ሲሳሉበት ጊዜ አንድ ሆዱን ባር ባር ያለው ከደቡብ የመጣ የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ አባል ‹‹***አንድ ነፍጠኛ***[60] ***በደቡብ ሺ ሕዝብ ያስፈራል። እና ምክር ቤቱ ጥበቃ እንዲያደርግልን። አንድ ነፍጠኛ ካለ አካባቢው ይረበሻል።***›› ሲል በፍርሃት ተናግሯል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳም እኛ ሕግ ልንሠራ እንጅ ለእያንዳንዱ ጥበቃ ልንመድብ አልተሰበሰብንም የሚል ይዘት ያለው ምላሽ ሰጥተዋል። አማራነት ማስፈራሪያ ሆኖ በሰዎች ልቦና ገብቷል። በሰዎች ልቦና ያለው ፍርሀትና ጥላቻ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ሆኖ መዋቅር ተሠርቶበታል። ከ1983 ዓ.ም በኋላ ያለው ሥርዓተ መንግሥት ተቋምና ሥርዓቱ የተገነባው የአማራ ጥላቻን በበቀል መተርጐምን ያለመ ነው። ይህ መሆኑም በሕዝቦች መካከል የመፈራራትና የመጠራጠር ስሜት አሳድሯል። ጋብቻ፣ በሃይማኖት ማምለክ፣ ገበያ መገበያየት ሳይቀር በብሔር ቡድን ተከፍሏል። መገንጠልን በ21ኛው ክፍለ ዘመን የምታበረታታ የፕላኔቷ ብቸኛ ሀገርም ኢትዮጵያ ናት። ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከዮጎዝላቪያ እና ሶቭየት ኅብረት ሕገ መንግሥቶች የተኮረጀው የግንጠላ ምዕራፍ ሶቭየትን እና ዮጎዝላቪያን ሊገነጣጥላቸው ችሏል። ባለ ተራዋ ኢትዮጵያ ናት። ዳግማዊ ምኒልክ እና ተከታዮቻቸውም ሆነ ቀደምቶቻቸው ሀገረ መንግሥት ሲያዋቅሩ ሕሊናዊ እና አካላዊ መልክ በተወሰነም ቢሆን ስለሰጡት እንጂ እንደ ኢሕአዴግ መንፈስ ሆኖ ቢሆን ሀገሪቱ ሶቭየት ኅብረትን ለመሆን ቅርብ ነበረች።

[60] አሥራት አብርሃም፣ የሕገ-መንግሥቱ ፈረሰኞች

ኢሕአዴግ አምባገነን ነው። አምባገነን መሪዎች ለሀገር ሲሉ ሕዝብን ያላግባብ ይገላሉ እንጂ ሀገር ይወዳሉ። ማኦዘዱንግም ሆነ ጆሴፍ ስታሊን፣ ሂትለርም ሆነ ሞሶሊኒ ግዛታቸውን ለማስፋት የሰው ሕይዎት በማጥፋት ይታወሳሉ እንጂ ሀገርን በጅምላዋ ዘርዝሮ በመሸጥ እንደ ኢሕአዴግ ዓይነት ድርጅት በዓለም ብዙ አልተከሰተም። ኢሕአዴግ ሕዝቡንም፤ ሀገሩንም በእኩል ጠልቶ በወንበር ፍቅር ብቻ የወደቀ ድርጅት ነው።

3.7 የሕገ መንግሥቱ ስል ተረከዝ ያተመው ዱካ

የባለፉት ዓመታት ብዙ ቆሻሻ ሥራ ተሠርቶባቸዋል። መንግሥታዊ ሽብርም ተፈጽሟል። ወንድም ከወንድሙ ጋር ተጋድሎ በመሸናነፉ የአሸናፊ እና የተሸናፊ ኮሚኒስታዊ ፍረጃ ገኖ ወጥቷል። (ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ፣ በ2010 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና ወደ አሜሪካ ሂደው ከትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋራ በተወያዩበት ወቅት የተናገሩት።)

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የሕወኃቱን ኢሕአዴግ በሕዝብ ተወካዮች ፊት አሸባሪ ነበር ሲሉት፣ ከ1983 ዓ.ም. እስከ 2010 ዓ.ም. ያለው ጊዜም ብዙ ቆሻሻ ሥራ የተሠራበት እንደሆነ በይፋ ተናዘዋል። ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር የኢሕአዴግ አውራ ሆኖ በቆየው ሕወሓት ዘንድ የጥል ግንብ ሆኖ ተቀምጧል። መንግሥታዊ ሽብርና ጥላቻ በመንግሥታዊ ተቋማት ነፍስና ሥጋ ዘርቶ የጐለመሰበት ዓመት መቋጫው ኢሕአዴግን መንግሥታዊ ባሕርይ ነሥቶታል።

በአቶ መለስ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስተር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ናሁ ለተባለ የቴሌቪዥን ጣቢያ በሰጡት ቃለ መጠይቅ እንደገለፁት ተቋማት የተዋቀሩት ግለሰብን ሳይቀር ማጥቂያ ባደረገ መንገድ እንደነበር መስክረዋል።

በ1993 ዓ.ም. ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ በሕወሓት መካከል በነበረው መፈረካከስ በብአዴን አደራዳሪነት አቶ መለስ ፍፁም ንጉሥ ሆነው ወጡ። ተቀናቀኛቸውን ስየ አብርሃን ከፖለቲካው ገፍቶ ለማሰር አቶ መለስ የፀረ ሙስና ኮሚሽንን በአዋጅ አቋቋሙ። እጅ እንጂ ጭንቅላት የሌለው የሚመስለው ፓርላማውም የፀረ ሙስና ኮሚሽን መዋቀር የጀርባ ምክንያት ሳያስቀምጥ አፀደቀ። ይሄው አቶ ስየ አብርሃን ለመክሰስ የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚሽን ከፖለቲካው ጋር ላልተስማማው ሁሉ የበቀል ጅራፍ ሆኖ ባጀ። ራሳቸው አቶ ታምራት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በቤተ መንግሥት ታሰሩ። ታስረው ከሰነበቱ በኋላ ‹‹ጥፋተኛ ነኝ ብለህ ለምክር ቤቱ ተናዘዝ ፣ ካልሆነ ልጅህ ብሌንን እንገለዋለን››[61] ተባልኩ እያሉ ግለ ታሪካቸውን ይዘረዝራሉ።

‹‹እኔም ከልጄ መሞት ከፓርላማ ፊት ቀርቤ ምክር ስላልሰማሁ፣ ምግባርም ስሌለኝ ሥልጣን ልልቀቅ ብየ ተናገርኩ። ሥልጣን እንደለቀቅሁ በሙስና ተከስሸ ማዕከላዊ ገባሁ። በማዕከላዊ ተገረፍኩ፣ ራሴን ለማጥፋት ሞከረኩ፤ ግን አልተሳካልኝም›› ይላሉ የያኔው ጠቅላይ ሚኒስትሩ። አቶ ታምራት እንደ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ[62] ልጄን የፈለጋችሁን አድርጉ ከእውነት እና ከሀገሬ አይበልጥብኝም ለማለት አልደፈሩም። ወደ አቶ ታምራት ተረክ ስናመራ፤ ከእሥር ቤቱ ልብስ ሳይቀይሩ ሳምንት ታስረው ወደ ምክር ቤት ሲሄዱ፣ ባለቤታቸው ሙሉ ግርማይ ሱፍ እንዳቀበለቻቸውም ገልፀዋል። ይህ ሁሉ የሕወሓት ኢሕአዴግ የመግሥትነት ባሕርይ ሳይሆን የማፍያነቱ መገለጫ ነው። ተቋማት ግባቸው ሕዝባዊ አገልግሎት መስጠት ሳይሆን ፓርቲያዊ ፍላጎትን ማርኪያ እንደሆነ ፀረ ሙስናን ምስክር አድርገው አቶ ታምራት ላይኔ ያጠይቃሉ።

[61] ናሁ ቴሌቪዥን፣ መስከረም 2011 ዓ.ም.

[62] *ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ልጁ የሻሸወርቅ በላይ በጣሊያን ተይዛ እጅህን ስጥና እንፍታት ሲባል ልጄን ሀገሬ ካለች ወይ አስለቅቃታለሁ፤ አሊያም ሌላ እወልዳለሁ። ሀገሬ ከጠፋች ግን ተኪ የላትም ብሎ ከልጁ ሀገሩን መርጧል።*

የ1983ቱን ለውጥ ተከትሎ የኢሕአዴግ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ሚናውን ለተወሰኑ የፓርቲው ቡድኖች የሰጠ በመሆኑ፤ የተደራጀ መንግሥታዊ ተቋም እንኳን አልተፈጠረም። የተፈጠሩ ተቋማትም በመንግሥት ውስጥ ለተፈጠረው ቡድን የጥቅም ማስጠበቂያ ናቸው።

ብዙዎች የኢሕአዴግ አባላት በ1985 ዓ.ም. ኤርትራ ስትገነጠል ነጻነት ወይስ ባርነት ተብሎ ሲፈጸም መረጃ አልነበራቸውም። በወቅቱ ጠቅላይሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ሳይቀሩ ‹‹ብአዴን ስለ ኤርትራ የተስማማው ኮንፌደሬሽን፣ ፌደሬሽን እንዲሁም ራስን የቻለ ሀገር መሆን ›› የሚሉ አማራጮች ለኤርትራውያን እንዲቀርብ ነበር ። ‹‹ነገር ግን ከስምምነት ውጭ ኤርትራውያን ከባርነት እና ከነጻነት የሚል ሕዝበ ውሳኔ እያደረጉ እንደሆነ እኔ ራሴ በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ነው የሰማሁት››[63] ይላሉ። ኢሕአዴግ የፈጠረው ሥሪት ሕዝቡን እና የፖለቲካ ልሂቃኑን ብቻ ሳይሆን ራሱ ኢሕአዴግንም አግላይ ነው። ኢሕአዴግ የተወሰኑ ቡድኖች በፈላጭ ቆራጭነት ሹሞ መንግሥነት ያዋቀረ ማፍያዊ መንግሥት ነው።

‹‹በ1988 ዓ.ም. አካባቢ ኤርትራ ኢትዮጵያን እንደምትወር የመከላከያ ሚኒስትር ስለነበርኩ መረጃ አሰናድተን ለምክር ቤቱ አቀረብን። እነ አቶ መለስ ውሸት ነው አሉን። ከዛ እኔ ስታሰር ሌላ የመከላከያ ሚኒስትር ሲሾም፤ ኤርትራ የጦርነት ሐሳብ የላትም የሚል መረጃ ለፓርላማው በውሸት አቀረበ። ነገር ግን ኤርትራ በሳምንታት ውስጥ ኢትዮጵያን ወረረች። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ያለምንም ዝግጅት የተደረገ ስለነበር ዋጋ አስከፍሏል። ይህ የሆነው ደግሞ እነ አቶ መለስ እና ኢሳይያስ ባላቸው ግለሰባዊ ቅርበት ነበር። እስከ ጦርነቱ ጊዜ አቶ መለስ እና ኢሳይያስ መቀሌ

[63] ናሁ ቲቪ፣ ጳጉሜ 2 ቀን 2011 ዓ.ም.

እየተገናኙ መንግሥታዊ ባልሆነ ሁኔታ ምሥጢር ያወሩ ነበር›› ሲሉም በኢሕአዴግ ውስጥ ያለውን የተወሰኑ ቡድኖች ፍጹማዊ ፈላጭ ቆራጭነት ያወሳሉ። ኢሕአዴግ ከርዕዮተ ዓለም እስከ ተቋም አወቃቀር ድረስ በሴራ እና የተወሰኑ የሥርዓቱ የማፍያ ቡድኖችን ተጠቃሚነት ያሰላ ነው። ሕገ መንግሥቱ በዚህ መንፈስ የተረቀቀ እና የማፍያዎች ፍላጎት ማስጠበቂያ ሰነድ ነው።

3.8 ኢሕአዴግ አሐዳዊ ወይስ ፌደራላዊ መንግሥት?

አንድነት ወይም የዜግነት እሳቤ የጨፍላቂነት እና የአምባገነንነት ባሕርይ መገለጫ ተደርጐ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ይተነተናል። ዘመንን በዘመኑ ከሰፈርነው በሀገር በቀል እውቀት የተዋቀረው የእነ ዐፄ ምኒልክ አስተዳደር ከአሐዳዊነት ይልቅ ወደ ፌደራላዊ ሥርዓት የቀረበ ይሆናል። የሀገሪቱ ነገሥታት ንጉሠ ነገሥታት እንጂ ብቸኛ ንጉሦች አልነበሩም።

በየክፍለ ሀገሩ መልክዓ ምድርን መሠረት ያደረጉ የከፋ፣ የትግራይ፣ የኢሊባቡር፣ የወለጋ፣ የጅማ፣ የወላይታ፣ የሸዋ፣ የጐጃም፣ የወሎ አስተዳዳሪዎች ወይም ንጉሦች ነበሩ። ንጉሦች ከንጉሠ ነገሥቱ የሚገናኙት በግብር እና በብሔራዊ ደረጃ በሚከወኑ ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ፌደራላዊ ሥርዓትን ፈጥሬ ለብሔር ብሔረሰቦች ሉዓላዊ ሥልጣን ሰጥቻለሁ የሚለው ኢሕአዴግ በእውነተኛ ቁመናው ሲተነተን የሚባለው ሁሉ ስስ ሆኖ ይገኛል። ፌደራላዊ ሥርዓት በፌደራል አባሎች መካከል ሚዛናዊ ተጠቃሚነት እንዲኖር ዴሞክራሲን ይፈልጋል። በኢሕአዴግ ውስጥ ያለው በኅብረተሰባዊ አብዮት ውስጥ የተቃኘው ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ነው።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ንጉሠ ነገሥትነት ማለት ነው። የኢሕአዴግ አናት የሆነው ሊቀመንበር (ድርጅት) ያቀረበውን ሐሳብ እስከ ቀበሌ ያለው አመራር እንኳን የመሻርም ሆነ የመቃወም ሥልጣን የለውም። ብዙዎቹ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች ሥልጣን ሊለቁ አካባቢ ክልሉን አልመራነውም ብለው ይናዘዛሉ። ለአብነት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ ጁነዲን ሳዶ ርዕሰ መስተዳድር ሆነው ቢቆዩም ሙሉ ሓላፊነት እንዳልነበራቸው፤ ኦሮሚያንም እንዳልመሩ ተናግረዋል።

የሶማሊያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ አብዲ መሀመድ ኡመር (አብዲ ኢሌ) ርዕሰ መስተዳደር እንኳን የሚሾመው አቶ ጌታቸው አሰፋ የተባለው የደኅንነት ሓላፊ እንደነበር ተናዘዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያምም ቀጥታ ትእዛዝ የሚቀበሉት ከብሔራዊ ደኅንነቱ ሹም እንደሆነ አቶ አብዲ ኢሌ በወቅቱ ኑዛዜያቸውን አሰምተዋል። ልማታዊ መንግሥትም በባሕርይው ሀገራዊና ፓርቲያዊ እዞች እና መመሪያዎችን በተወሰኑ የፖለቲካ ልሂቃን መዳፍ ሥር ከቶ ሌሎችን የማጀብ ሚና ብቻ ይሰጣል። በመሆኑም የክልል መንግሥታት ለወያኔ አጃቢ ሆነው ባጅተዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር የነበሩት አቶ ገዱ አንዳርጋቸውም ክልሉን በእኛ ኃይል እየመራነው አልነበረም ብለው ለሕዝባቸው ተናዘዋል። ፌደራሊዝሙ እንደ እንግሊዝ የቅኝ ግዛት ዘመን የከፋፍለህ ግዛው (divide and rule) መርሆ እንጂ ተተግባሪ አይደለም። በትክክል ቢተገበር ኖሮ ሀብትና ሥልጣን የፖለቲካ የኃይል ሚዛኑ ወደ አጋደለበት ብቻ የሚፈስበት ሸለቆ አይፈጥርም ነበር። ይልቁንም ፌደራሊዝሙ ትብብርን በማሳሳት፣ ጥርጣሬን በማግነን፣ የእርስ በርስ ሽኩቻን በማባዛት በሳሎን ውስጥ አጀንዳ ፖለቲከኛው እንዲጠመድ አድርጐታል።

ይህ መሆኑ ደግሞ ለማዕከላዊ መንግሥቱ ቁም ነገር የለሽ ዕድሜ[64] ጨምሮለታል። በቅኝ ግዛት ዘመን እነ እንግሊዝ በተከተሉት የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲያቸው ብሔሮች ከብሔሮች ጋር ሲጓተቱ እንግሊዝ ጥሬ ሀብት ወደ ለንደን እንድታግዝ አስችሏታል።

የኢትዮጵያ የብሔር ፌደራሊዝምም ብዙዎች እርስ በርስ የጎሪጥ ሲተያዩ ጥቂቶች ማዕከላዊ መንግሥቱን የተቆጣጠሩት እንዲከብሩ አድርጓል። ምክንታዊነትን እና ሥርዓታዊነትን አጥፍቶ ሴራን የፖለቲካው መርሆ አድርጓል። በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ሰበብ ሥልጣን በተወሰኑ ቡድኖች ይከማች እና ሌሎቹ ታዛዥ ብቻ ይሆናሉ። በማዕከላዊ መንግሥቱ የበለጠ ሥልጣን ያለው ሌሎች የብሔር ክልሎችን የበለጠ ተጭኖ ያስገብራል። ኢሕአዴግ በገቢር ለአሐዳዊነት ሥርዓት የቀረበ ሲሆን፤ በነቢብ ደግሞ ብሔሮችን እስከ መገንጠል መብት የቸረ ተለጣጭ የዘውጌ ፌደራሊዝምን ያሰፈነ መንግሥት ነው። ኢሕአዴግ በተጣራሽ ህልሞች የሚቃዥ ሥርዓታዊ መንግሥትን ፈጥሯል። ብሔሮች እንደ ኢሕአዴግ ዘመን የተጨቆኑበት ጊዜም በታሪክ የለም። ኦሮሚያ ውስጥ የሚገኙት እነ ትግሬ ወርጂ እና ዛይ የመሳሰሉ ብሔረሰቦች ሙሉ በሙሉ ተጨፍልቀው ጠፍተዋል። ከክልሌ አትኖርም ተብሎ የሚፈናቀለው ብሔረሰብ ብዙ ነው። በጋምቤላ በአኝዋክ እና በኑዌር በየጊዜው የሚደርሰው መጠፋፋት የብሔር ፌደራሊዝሙ ውልድ ነው። አኝዋክም የህልውና ጥያቄ ማንሣት ጀምሯል። በኬንያ አቅራቢያ ሞያሌ ከተማ አካባቢ ኢትዮጵያ የምትታመሰው በኬንያ እና በኢትዮጵያ ጉርብትና ሳይሆን፤ በሶማሌ እና በኦሮሞ ፍትጊያ ነው። በሱዳን ድንበር በኩል በአማራ እና በትግራይ

[64]ለአብነት ጋምቤላ ክልል በአኝዋክ እና በኑዌር፣ ደቡብ በሲዳማ እና በወላይታ፣ ሶማሊያ በኦጋዴን እና በሌሎች የሶማሌ ጎሳዎች በክልል ውስጥ አጀንዳ የተጠመደ ነበር። እንደ ክልል ደግሞ አማራ ከኦሮሞ፣ ሶማሊያ ከኦሮሞ፣ አማራ ከትግራይ… በወሰን ግጭት የተወጠረ ስለነበር ማዕከላዊ መንግሥቱን ለመቃወምም ሆነ ለመተቸት ሁኔታው ፈቃጅ አልነበረም።

መካከል ያለው ሽኩቻ ከባድ ድምጽ አለው። አንዳንዴም ሕወሓት ከሱዳን ጎን ቁሞ የአማራ አርሶ አደሮችን ይወጋል የሚል ጥርጣሬ ይነሣል። ኢሕአዴግ የፈጠራት ኢትዮጵያ አንድ ብሔር ከአንዱ በልጦ ለመታየት በሚያደርጉት እሽቅድድም የተሞላ ነው። ይህ ደግሞ አብሮነትን ሕልም አድርጎ፣ መጠፋፋትን ይደግሳል።

3.9 የክልሎች አወቃቀር እና እሳቤያዊ ግጭቶች

የመልክዓ ምድራዊ አከላለል አንድን ሕዝብ በተለያዩ አስተዳድሮች የሚያስገባ ነው። ብሔሮች መገንጠል እና ራስን በራስ ለማስተዳደር ጥያቄ ማቅረብ የጀመሩት ከምኒልክ ዘመን ጀምሮ ነው። ኢሕአዴግ ለብሔረሰቦች የ100 ዓመት ጥያቄ ይፈታ ዘንድ ብሔረሰቦች በቋንቋቸው ተካለው ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር አለባቸው። አንቀጽ 39ኝም ተተግባሪ መሆን የሚችለው ብሔሮች በአንድ መልክዓ ምድር ሥር ከሆኑ ብቻ ነው። በመልክዓ ምድር ማዋቀር የደርግን ሥርዓት ማስቀጠል እና አንድን ቋንቋ ማግነን ነው። ይህ አሐዳዊነት ነው። (የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ቡድን አባላት ስለ ክልል አወቃቀር ያቀረቡት ጨመቀ ሐሳብ/ጭብጥ)

ከ1983 በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሀገር ማስፋትን እንጂ በሀገር ውስጥ ስላሉ የወሰን ጉዳዮች ብዙ አይጨነቅም ነበር። ላስተዳደር በሚመች መንገድ ሀገር በክፍለ ሀገር በአውራጃ እና በወረዳ ተዋቅሯል። በዚህ አደረጃጀት ውስጥ መልክዓ ምድራዊ ማንነት ካልሆነ ብሔረሰባዊ ማንነት አይታወቅም።

ዝቅተኛው አደረጃጀት ‹‹ወረዳ-ወራጅ›› ከሚለው የአማርኛ ቃል የተወረሰ ሲሆን በወራጅ ወንዞች የሚከለል የቀጠና እና ጉጥ ማዕከላዊ ግዛት ነው። ክፍለ ሀገር የሚዋቀርበት ማገር እና **አውራጅ** አውራጃ ተብሎ ይጠራል። አውራጃም የወረዳዎች ስብስብ ሲሆን በብዛት የሚከለለው በወራጅ ወንዞች እና በተራራዎች አማካኝነት ነው።

ክፍለ ሀገር ደግሞ አንዱ የሀገር አሃድ ነው። በደርግና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከ12 እስከ 14 የሚደርሱ ክፍለ ሀገሮች ነበሩ። በሕልም ደረጃ የመንን ሳይቀር እንደ አሥራ አምስተኛ ክፍለ ሀገር የመመልከት አዝማሚያ ነበር። በጃንሆይ ጊዜ የነበሩት እነ አክሊሉ ሀብተወልድ ኤርትራን ከእናት ምድሯ ለማገናኘት ከ700 ሰዓት በላይ ያለእንቅልፍ እንደበረሩ የአክሊሉ ማስታወሻ በሚለው ትውስታቸው ከትበዋል። ከአንድ ሚሊየን የሚያንስ ሕዝብ ያላትን የአፋር እና የሱማሌ ሕዝብ ውህድ የነበረችውን ጅቡቲን ወደ ኢትዮጵያ ለመቀላቀልም ከዳግማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከ ደርግ ጥረቶች ነበሩ።

በትርክት እና በምኞት ደረጃ የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ህንድ ውቅያኖስ ነው። ግማሹ ግብጽ የኢትዮጵያ ነው የሚሉ ዘለግላጋ ምኞቶች በሕዝቡ ይነሡ ነበር። ኢትዮጵያን በቆዳ ስፋትም ሆነ በዕድገት የዓለም ልዕለ ኃይል ለማድረግ ቀደምቶቻችን በላባቸው ብቻ ሳይሆን በደማቸውም ጭምር ለፍተዋል። ምኞታቸውም ከፍ ያለ ነበር። ከባቢያዊ አለቆች በየሰርጡ ሲሻኮቱ፤ እነ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኢየሩሳሌም ነጻነት እንታገላለን ብለው ለሩቁ ምሥራቅ ዓለሙ።

ይህ ሽቅብ የሚንጠራራ ሀገራዊ ሕልም በ1966 ዓ.ም. በተነሣው ጥራዝ ነጠቅ የብሔርተኞች ቅራኔ ጨነገፈ። የኢትዮጵያዊነት የመስፋት ምኞት ተከረከመ። ኢትዮጵያዊ መሆን እየተጠላ ኤርትራን የወከለው ሻዕቢያ ጥቁር ሮማዊ ነኝ ማለት ጀመረ። እድገቴም እንደ ሲንጋፖር ነው የሚሆነው ብሎ በተስፋ ወፈረ። ኢትዮጵያ ጥሬ እቃ አቅራቢ ትሆነኛለች እንጂ ከንግድ ማትረፊያነት ውጭ ምኄም አይደለችም ብላ ካደች። የትግራይ ወኪል ነኝ የሚለው ሕወሓት ጥቁሩ እስራኤል እኔ ነኝ አለ። ኦሮሞን የወከለው ኦነግ ደግሞ ኦሮሞ ጥቁር ጀርመናዊ ነው ሲል ራሱን ከኢትዮጵያዊነት አራቀ። በኢትዮጵያ ስም የተደራጁ እንደ መኢሶን እና ኢሕአፓ አይነቶችም

ጥቁር ቦልሼቪክ ነን ከማለት አልተመለሱም፡፡ በ1966 የተነሡ ብሔርተኞች ከቆዳ ቀለማቸው በስተቀር የኢትዮጵያዊነትን ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ… ፍቀው የነማርክስን ፍልስፍና ወርሰዋል፡፡ በወቅቱ አማራ ለተጠላችው ኢትዮጵያ ብቸኛ ወዳጅ በመሆኑ፣ የግንጠላ አራማጅ ብሔርተኞች ሁሉ ጠላት ተደርጎ ተፈርጇል፡፡

በጀርመናዊ ማርክስ እና በጓደኛው ኤንግልስ የተማሰለውን ኮሚኒዝም ሳያላምጡ የዋጡት የዛ ትውልድ አባላት ኢትዮጵያዊነትን ቶሎ ተፉት፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካም ትናንት እና ነገ አልባ ሆኖ ተዋቀረ፡፡ ትዝታ አልባ ፖለቲካ የጋራ መንፈስን ገድሎ አዲስ ተረክ ፍለጋ ላይ እንዲተኮር ጋበዘ፡፡ አዲሱ የፖለቲካ ተረክ በአንድ ሀገር ካርታ ውስጥ ፍጹም የሚጋጩ አስተኔ (አነስተኛ) ብሔራዊ ሀገሮችን ፈጠረ፡፡

የነማርክስን ሐሳብ ሩሲያ በነሌኒን እና ስታሊን፣ ቻይና በማኦዘዱንግ፣ አልባንያ በኢንቨር ሆጃ… አማካኝነት ከሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም ሞክረዋል፡፡ የኛ ፖለቲከኞች ግን ከማጣጣም ይልቅ የኢትዮጵያውያንን ነባር እሴት በመፋቅ አንዴ በሌኒን ሌላ ጊዜ በማኦ እሳቤ ለማደስ ሞክረዋል፡፡ እነ ሌኒን ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ሕዝብ የሚል ማንነታዊ የፖለቲካ አህድ ሲፈጥሩ የኛዎቹም ፈጠሩ፡፡ እነ ሌኒን ይሄን አደረጃጀት የፈጠሩት ከሩሲያ ውጭ ያሉ የሌሎች የምሥራቅ አውሮፖ ሀገሮችን ለማቀፍ ነው፡፡ አቅፈውም ትልቋን ሩሲያ ፈጠሩ፡፡ እነ ሌኒን ብሔርን ያቀነቀኑት ለማምጣት እና ሀገር ለማስፋት ሲሆን የእኛዎቹ ደግሞ ሀገር ለመገንጠል እና ሀገር ለማሳነስ ነው፡፡

ብሔር[65] (nation) ማለት ሀገር የሚያህል የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ መዋቅር ያለው የሕዝብ አደረጃጀት ማለት ነው፡፡ ሌኒን በ1922 ዓ.ም.

---

65 ኢትዮጵያ ውስጥ ራሱን በራሱ መርቶ የቆየ ሀገር አከል ብሔር የለም የሚል ሙግት ይነሳል፡፡ ለዚህም እንደነ አንዳርጋቸው ጽጌ እና መሰል የፖለቲካ ልሂቃን በኢትዮጵያ ብሔር የለም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ብሔር ያደገ ታሪክ፣ በታሪኩ ውስጥ የበለጸገ ጋርዮሻዊ ስነልቦና፣ በስነልቦና ትስስሩ የማኅበራዊ ተራክቦ ሂደቱ የጋራ ገበያ እና ኢኮኖሚን ይፈጥራል፡፡ በዚህ ሂደት የተፈጠረ የሀገር መልክ የያዘ ብሔር የለም፡፡ አሁን ብሔር ተብለው በክልል የተዋቀሩ ህዝቦች በኢኮኖሚም ሆነ በጋርዮሻዊ ስነልቦና የበለጸጉ አይደሉም የሚል ፖለቲካዊ ሂስ ይቀርባል፡፡ ብሔራዊ ክልሎች በራሳቸው መቆም አይችሉም የሚል ድምዳሜ ይሠጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ብሔር ናፋቅ የዘውጌ ብሔርተኝነት አቀንቃኞች ብሔር(ሀገር) ቀድሞ ነበረ፡፡ ነገር ግን በምኒልክ አማካኝነት ወረራ ተፈጸመ፡፡ ወረራው የባህል እና የኢኮኖሚ ብዝበዛን ስላስከተለ ብሔሮች ኮሰሱ ሲሉ ኢትዮጵያን ሀገረ መንግሥት ግንባታ መሠረትበዳግማዊ ምኒልክ አሸናፊነት ላይ ይተክሉታል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአሰላለፍ ረገድ በሁለት ጽንፈኛ ሃይላት ላይ ወድቋል፡፡ የመጀመሪያው የዘውጌ ብሔርተኝነትን አውግዞ፣ የዜግነታዊ ብሔርተኝነትን የሚያነግሰው ኃይል ነው፡፡ ይሄኛው ቡድን ብሔር የለም ብሎ ይነሣና ፌዴራሊዝሙን የጎሳ አደረጃጀት ይለዋል፡፡ ብሔርን እና ብሔርተኝነትን ወደ ዘር እና ጎሳ አውርዶ የፖለቲካ ሥርዓቱንም ከጥንታዊያኑ ሥራዓተ ጋርዮሽ ማኅበር ጋር አመሳስሎ ይተረጉማል፡፡ ብሔርን ወደ ስጋዊ ዝምድና ወስዶ (biological relation) ለሃሳብ እና ምክንያት የማይገዛ የደቦ ፖለቲካ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡

በሌላ በኩል ዘውጌ ብሔርተኞች የዜግነት ፖለቲካ አራማጆችን ከተጨባጩ አውነት የራቁ የምናብ ዓለም ፖለቲከኞች አድርገው ይረዷቸዋል፡፡ እንደ ጨፍላቂ እና የደርግ እና ከደርግ በፊት ለነበሩ ሥርዓቶች ወኪል ተደርገው ይሳላሉ፡፡ በዚህ የፖለቲካ አሰላለፍ ያሉ ልሂቃን የትነታቸው የትም ይሁን እንደ አማራ ይታያሉ፡፡ የዜግነት ፖለቲካ እና የዘውጌ ፖለቲካ አራማጆች በፍጹማዊ ተቃርኖ ውስጥ የወደቁ ናቸው፡፡ የመሃል መንገድ የላቸውም፡፡ ነገርግን ኢትዮጲያዊነትንም፤ዘውጋዊ ብሔርተኝነትንም ማውገዝ እኩል አደገኛ ነው፡፡ አንዱ ጥሩ ሌላው መጥፎ አድርጎ መመልከት ነባራዊ ሁኔታን ካለመረዳት ይመነጫል፡፡ ብዙ ብሔሮች ድርብ ማንነት ስላላቸው ለማንነታቸው መስፈሪያ ዜግነታቸውን ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ዜግነታቸውን ክደው ዜግነትም ማንነትም ብሄራቸውን ያደርጋሉ፡፡

በነዚህ መጣረሶች መሃል ለሚገነባ ፖለቲካ ሀገራዊ እና ዘውጋዊ ብሔርተኝነቱን ሳይገፋፉ ወደ መሃል መንገድ አምጥቶ የአንዱ መኖር ለሌላው ድጋፍ መሆኑን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የኢኮኖሚ መስተጋብርን መፍጠር በተገቢነት ይቀመጣል፡፡ የፌዴራል መንግሥት መንገዶችን፣ ፋብሪካዎችን፣ የኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ታላላቅ የኢንቨስትመንት አካባቢዎችን በራሱ እዝ ቢያደርግ የብሔሮች ተራክቦ በገበያ እና በማኅበራዊ ሂደቶች የጸና ይሆናል፡፡ ነገር ግን የፈየዴራሉ መንግሥት የራሱን ዋና ከተማ እንኳን የራሱ አድርጎ ማቆም አልቻለም፡፡ የማዕከላዊው መንግሥት ለመቀመጫ ዋና ከተማ ከብሔራዊ ክልሎች የሚመጸዎት ከሆነ ስልጣኑ ከክልል መንግሥትነት ያንሳል ማለት ነው፡፡ በዚህ ላይ የኢ-ተገጣጣሚ ሀገራዊ ፍላጎቶች ተደምረውበት ብሔራዊ አጀንዳ ለመቅረጽ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ብሔሮች ከማዕከላዊ መንግሥቱ በጋራ የሚጋሩት አንዳች ጥቅም ከሌለ መገንጠል አውራ አማራጭ ሆኖ ይመጣል፡፡ ፖለቲካ የጥቅም ሰሎ ነው፡፡ ፖለቲካ እንደ እምነታዊ ዶግማ በአንድ አውነት ላይ ለዘወትር አይጸናም፡፡ ፖለቲካ እንደ እስስት ባህሪ ከባቢ ሁኔታን አጥንቶ መቀያየርን ይጠይቃል፡፡ ፖለቲካ እንደ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ጣሊያን እና እንግሊዝን በጥቅም አጋጭቶ የኢትዮጵያን ነጻነት ከሁለቱ መካረሮች መሃል መፈለግን ይጠይቃል፡፡ ብዙ ጊዜ በፖለቲካ ልክነቱ ሂደቱ ሳይሆን ውጤቱ ነው(The end justifies the means)፡፡ ወደ ውጤቱ ለመድረስ በሚደረግ ሩጫ በሂደቱ ብዙ ጥፋቶች እና ነውሮች ይፈጸማሉ፡፡ ለደርግ ባለስልጣናት ‹‹የኛ መገደል ኢትዮጵያን ካዳነ ይሁን›› ያሉት ጃንሆይ እና ሹመኞቻቸው በውስጣቸው በመጥፎ ሂደት ውስጥ መልካም ውጤት ይኖር ይሆን ብለው የጠረጠሩ ይመስላል፡፡

15 ብሔሮችን ከምሥራቃዊ እና ሰሜናዊ አውሮፖ ሰብስቦ ታላቋ ሶቭየት ኅብረትን ቢፈጥርም በ1990 ዓ.ም. መልሰው ሊገነጣጠሉ ችለዋል:: ቢገነጣጠሉም ሩሲያን ብዙ ህልውናዋን የሚያደክም አልነበረም:: ጋብቻው ፖለቲካዊ ስለሆነ፣ ፍችውም ፖለቲካዊ ነበር:: የነሌኒንን ብሔር በሩሲያ ዙሪያ ከሞስኮ በብቸኝነት በሚመራ አሐዳዊ እዝ የተሰባሰበ ነው:: ፍጻሜው ብተና ቢሆንም፣ የነሌኒን ብሔር እና ብሔረሰብነት የሩሲያን ግዛት ለማስፋት መሰብሰብን በፍሬ ነገሩ የመረጠ ነበር:: በ1990ዎቹ የብሔሮች ቅሬታ ነበረው ማዕከላዊነት በዝቶ የሩሲያ(የሩስኮ) ብሔራዊ ባህል ተጭኖናል የሚል ነው:: የኛው ከነሌኒኑ በተቃራኒ በታኝ እና በቋንቋም ሆነ በዓላማም የማይግባቡ ብሔራዊ ክልሎችን ፈጥሯል:: ብሔር ሀገር ማለት ሲሆን፣ እነ ሌኒን ሀገሮችን በታላቋ ሶቭየት ኅብረት ጥላ ሥር የሰበሰቡበት ግዛት የማስፋት እና የመጠቅለል መንገድ ነው::

ብሔረሰብ የሚለው አደረጃጀት ሀገር ለመሆን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሁኔታው የማይፈቀድለት፣ የጋራ ማንነታዊ ተዛምዶ ያለው ብሔር ውስጥ ያለ ቅንጣተ አሃድ ነው:: የኦሮሞ ብሔረሰብ በአማራ ብሔራዊ መንግሥት ሥር አለ:: አማራ በነሌኒን እሳቤ መሠረት ሀገር መሆን ይችላል:: በአማራ ውስጥ ያለው የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር በአማራ ሀገር ውስጥ ያለ ኦሮሞ የተባለ ብሔረሰብ ሆኖ ይቀጥላል እንደማለት ነው:: እንደ ኢሕአዴግ፣ሕዝብ ደግሞ ከብሔረሰብም ያነሰ መለስተኛ ስብስብ ያለው የፖለቲካ አንድ ቅንጣት ነው::

በሌላ በኩል በፖለቲካዊ ቋንቋ በአንድ አስተዳደር ውስጥ ያለ ማኅበረሰብ ሕዝብ ይባላል:: ኢሕአዴግ ራሱን የኢትዮጵያ **ሕዝቦች** አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ብሎ ይጠራል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነት መስፈሪያ አንድ ነው:: ነገር ግን ኢሕአዴግ ከሌኒን በወረሰው የብሔር እሳቤ መሠረት ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣

ሶማሊያ፣ ወ.ዘ.ተ የብሔር (ሀገራዊ) መንግሥታት ናቸው:: ሀገር ናቸው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት የሉዓላዊ ብሔሮች(ሀገሮች) አስተዳደር ስለሆነ **ሕዝቦች** ለማለት ተገዷል:: የአሜሪካ ሕዝብ፣ የህንድ ሕዝብ፣ የዓለም ሕዝብ.... ብሎ መናገር ይችላል:: የአሜሪካ እና የህንድ **ሕዝቦች** ማለትም በፖለቲካ ቋንቋ ልዩ አስተዳደርነቱን ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውላል:: ሁለቱ በተለያየ የአስተዳደር አሀድ ውስጥ እንዳሉ ያመለክታል:: በፖለቲካ ቋንቋ በክልል ደረጃ የአማራ እና የኦሮሞ **ሕዝቦች** ማለት ተገቢ ነው:: እንደ ሀገር የኢትዮጵያ ሕዝቦች ማለት ግን አግባብነት የለውም:: በኢትዮጵያዊነት ማሕቀፍ ውስጥ በአንድ መንግሥት የሚመራ አንድ ሕዝብ[66] ነው ያለው:: ነገር ግን አንድ ሕዝብ ማለት በኢሕአዴግ ሠራሽ ፖለቲካ ዘንድ እንደ አሐዳዊነት ስለሚያስፈርጅ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝቦች›› ብሎ መጥራቱ ተለማጅ የኮንፌደራላዊ ኃይሎች ድምጸት ሆኗል::

የኢሕአዴግን የፖለቲካ ቋንቋን ከረገጠበት ተረገዝ ተነሥተን ስንተረጉመው ብሔራዊ ክልል ማለት በፌደሬሽን ሳይሆን በኮንፌደሬሽን ኢትዮጵያ ከተባለች ሀገር ጋር የተጣመረ ሀገር ማለት ሲሆን፤ ብሔረሰብ ደግሞ የዞን መዋቅር ያለው ክፍለ ሕዝብ ይሆንና ሕዝብ ደግሞ በወረዳ ደረጃ የተደራጀ አነስተኛ የማኅበረሰብ እርከን ነው:: ስለዚህ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ወረዳውም፤ ዞኑም ሆነ ክልሉ በእኩል የመገንጠል መብት አላቸው:: (ልዩነታቸው በድምጽ የማነስ እና የመብዛት ብቻ ነው:: ብዙ የሕዝብ ቁጥር አማራ እና ኦሮሞ ከፈቀዱ ከኢትዮጵያ ለመነጠል ከባል እና ከሚስት ፍቺ ባነሰ ሁኔታ ይፈጸማል:: የተወሰነ የሚከብዳቸው ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ወይም አነስተኛ ሕዝብ ይዘው በብሔር ደረጃ ያሉ እንደ ሐረሪ ያሉ ክልሎች ናቸው::) ሕገ መንግሥቱ በትርጓሜው በአንድ

[66] ሕዝብ በአንድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚመራ የማኅበረሰብ ውሕድ ነው። ኢሕአዴግ ሕዝብ የሚለውን ከብሔረሰብ ለሚያንሱ የማኅበረሰብ ቅንጣቶች ለቡድን መጠሪያነት ተጠቅሞበታል። ኢሕአዴግ ብሔር-ብሔረሰብ-ሕዝብ የሚሉ የማኅበረሰብ አደረጃጅቶችን ይጠቀማል።

ብሔር ውስጥ ያሉ አሃዶች መገንጠል አይችሉም ይላል። የሕገ መንግሥቱ ትርጓሜ በአብነት ሲያስረዳ ከክልል ሦስት ጎጃም፣ ከክልል አራት ወለጋ ልገንጠል ቢሉ አይቻልም የሚል ሐሳብ ያቀርባል።)

በሕገ መንግሥቱ ዋቢነት በአማራ ክልል የሚገኘው 40ሺህ ሕዝብ ያለው የአርጎባ ልዩ ወረዳ ተገንጥሎ ሀገር መሆን ይችላል። ሕገ መንግሥቱ ለብሔሮች፣ ለብሔረሰብም ሆነ ለሕዝብ ሉዓላዊነት እኩል መብት እና እድልን ሰጥቷልና። ማን ምን ያገኛል? በኢትዮጵያ ምን ያህል ብሔሮች? ብሔረሰቦች? እና ሕዝቦች እንዳሉ በየእርከናቸው ተለይቶም አልተቀመጠም። በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ማዕከል መሠረት በደርግ የነበሩ ብሔረሰቦች ብዛት 89 ነበሩ[67]። በ1987 ዓም በተደረገ የሕዝብና ቤት ቆጠራ 84 ብሔረሰቦች ብቻ ተቆጥረዋል። በ1999 ዓም ቆጠራ ደግሞ85 ተመዝግበዋል። የብሔረሰቦች ቁጥር በየዓመቱ ከመለያየቱ በተጨማሪ አንዴ አለ የተባለው ሌላ ጊዜ በየለም ሊዘጋ ይችላል። ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ትግሬ ወርጂ፣ ዛይ እና አርጎባ የተባሉ ብሔሮች በ1999 ዓ.ም. ቆጠራ አልተካተቱም። በሌላ በኩል ከ1999 ዓ.ም. ቆጠራ በኋላ በአማራ ክልል ጎንደር አካባቢ ቅማንት ዞን አከል አስተዳደር ዘርግቶ ብሔረሰብ ሆኖ ተመዝግቧል። በብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ መካከል ያለው ልዩነት አለመሰመሩ የችግር መፈልፈያ ጋን ሆኗል። በብዛት ብሔር በፖለቲከኞች የሚሠራ ማንነት (constructive) ስለሆነ ወለጋ፣ አድዋ፣ ጎጃም፣ መተከል፣ ድሬድዋ፣ ሊሊባቡር... በራሱ የብሔር ቀለም ይዞ ሊወጣ ይችላል።

የተደራጁ ልሂቃን ካሉ ማንም ብሔር አለመሆን አይችልም። ማንነት እና የሥነ ማኅበረሰብ እይታ በፖለቲካ ልሂቃን ይቀረጻል። ማንነት የማኅበራዊ ሳይንስ አንድ አንጓ በመሆኑ እንደተፈጥሮ

[67]በኩር ጋዜጣ ኅዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም.

ሳይንስ ተቆራጭ ቀመራዊ ባሕርይ የለውም። ስለሌለው ማንነት በፖለቲካዊ ፕሮፖጋንዳ ኃይል ይመሠረታል። ፕሮፖጋንዳ የማንነት ማምረቻ መንገድ ነው። በብዛት ማንነቶች የፕሮፖጋንዳ (ተረት፣ ትውፊታዊ ወጎች፣ ንግርቶች፣ ኪነ-ጥበብ…) ፍልፍሎች ናቸው።

ኢሕአዴግ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. የምኒልክን ቤተ መንግሥት ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከነጠቀ በኋላ በሽግግር መንግሥት እስከ 1987 ዓ.ም. ቆይቷል። የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት አሥራ ስድስተኛ መደበኛ ጉባኤውን አድርጐ የክልሎችን አወቃቀር በተመለከተ አቅጣጫ አስቀምጧል። የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዝዳንት እና የተወካዮች ምክር ቤት ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ ሲሆን፣ ክልሎችን ለማዋቀር ሰላሳ ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደተሳተፉ የቃለ-ጉባኤው ሰነድ ያሳያል። በሽግግሩ መንግሥት ጊዜ ክልሎችን ለመወሰን 67 ጉባኤተኞች በተሳታፊነት ተመዝግበዋል። ኦሮሞ በኦሕዴድ እና በኦነግ የተወከለ ሲሆን ከኦነግ 9፣ ከኦሕዴድ ደግሞ 10 ሰዎችን በድምሩ በ19 ሰዎች ተወክሏል። ሕወሓት አቶ መለስ ዜናዊን ጨምሮ በ8 ሰዎች ሲወከል፣ አማራ በወቅቱ ወኪል እንዳልበረው ቃለ ጉባኤው ያሳያል። ምናልባት ኢሕዴን እንደ ወኪል ከታየ፣ እንዲያሳትፍ ከተፈቀደለት 10 ሰዎች ውስጥ 6 ሰዎችን ያሳተፈ ሲሆን 4 ሰዎች ሳይገኙ ቀርተዋል። በወቅቱ ከ80 ሺህ ሕዝብ የማይበልጥ ሕዝብ ያለው የም ብሔረሰባዊ ንቅናቄ ፖርቲ ነበረው። ቡርጂ፣ አደሬ፣ ጋምቤላ፣ ከፋ ወ.ዘ.ተ የንቅናቄ የፖለቲካ ድርጅት ነበራቸው።

ሐረሬ ወይም አደሬ በ1999 ዓ.ም. ሕዝብና ቤት ቆጠራ እንኳን የሕዝብ ቁጥሩ ከ180 ሺህ የሚበልጥ አልነበረም። ነገር ግን በ1984 ዓ.ም. የሽግግር መንግሥት ሂደት ላይ በፓርቲ ተወክሏል። ከሀገሪቱ ሕዝብ ከ1/3ኛ በላይ ይሸፍናል የሚባለው አማራ

ራሱን አደራጅቶ አለመቅረቡ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በኦሮሚያ… በሁሉም ክልሎች እንዲፈናቀልና እንደ ተስፋፊ እንዲታይ አድርጉታል። የአማራ ልሂቃን መለኮታዊ የሆነ ፖለቲካን ብቻ በመከተል ስለኢትዮጵያዊነት ሲሰብኩ ባጅተዋል። ኢትዮጵያዊነት[68] መለኮታዊ መንፈስ ካልሆነ በፖለቲካ ውክልና የለውም። በኢሕአዴግ የመንግሥትነት ትርጓሜ መሠረት ኢትዮጵያዊ የሚባል የፓርቲ አደረጃጀት እንጂ ኢትዮጵያዊ የሆነ

[68]ኢትዮጵያዊ ማንነት እውቅና ቢሰጠው ለሀገረ መንግሥት ግንባታው የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረው ነበር። ቅይጥ ማንነት ያላቸው እና አንዱን ዘውግ ለመምረጥ የሚቸገሩት በኢትዮጵያዊ ማንነት ራሳቸውን መግለጽ ይችሉ ነበር። ከተሞች በብዛት ለዚህ ዓይነት ማንነት ግንባታ ምቹ ናቸው። ብዙዎች ቅይጥ ማንነት ያላቸው ከየትኛውም ዘውግ ሳይሆኑ መሃል ላይ ሆነው ቀርተዋል። ይህም ለማኅበራዊ እና ለሥነ አዕምሮ ቀውስ ዳርጓቸዋል። አንድ ልጅ ሃጎስ አራርሳ ተብሎ አማርኛ ቋንቋ ብቻ ቢናገር ይህ ልጅ በትግራይም ሆነ በኦሮሚያ ፖለቲካዊ መብቱ ይነፈገዋል። በአማራ ክልል የተሻለ እድል ቢኖረውም፣ የየሺ.ሐሳብ አበራን ያህል እድል የለውም። ስለዚህ ለሀጎስ አራርሳ ኢትዮጵያዊነት ቅይጥ ማንነቱ ታውቆለት የፖለቲካ ውክልና ካልተፈጠረለት በስተቀር ኢሕአዴግ መር በሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሀገር አልባ ባላገር ነው።
ኢሕአዴግ የተከተለው ብሔር ተኮር ፖለቲካ ብሔሮችን የበለጠ እንዲዋጡ አድርጓል። በኦሮሚያ የእነ ትግሬ ወርቅ እና ሌሎች መጥፋት አስረጅ ምሳሌ ነው። ከ7-10 በመቶ የኦሮሚያ ክልልን የሚሸፍነው የአማራ ሕዝብ በቋንቋው አይጠቀምም። የፖለቲካ ውክልና የለውም። አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሐረር ክልል ሆነው ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ከምባታ፣ ጉራጌ… ለምን ክልልነት እንደተነፈጋቸውም ግልጽ አይደለም። 9 ብሔራዊ ክልሎች ተፈጥረው ሌሎች 70 ምናምኑ በዘጠኙ ተውጠዋል። ፍትሃዊ ይሁን ተብሎም 85 ክልል በራሱ ቋንቋ የሚመራ ቢዘጋጅ ሀገራዊ ርዕይ እና መግባባት ሊገነባ አይችልም። ስለዚህ አካታች የፖለቲካ ውክልና የሚገኝበት ኢትዮጵያዊነት የተሰኘ የውህዳን ማንነት መፈጠር ነበረበት።

ከኢሕአዴግ ሙት የሀገር ስሜት በተጨማሪ፣ የአንድነት ፖለቲካ አቀንቃኞች ልፍስፍስነትም ለሀገረ መንግሥት ግንባታው ውድቀት አባሪ ምክንያት ናቸው። የአንድነት ኃይል ፖለቲከኞች የብሔሮችን የታሪክ እና የፖለቲካ ትንተና ተቃርኖ የሚፈቱበትን መንገድ አላዘጋጁም። ከፖለቲከኛነት ይልቅ ለሰባኪነት እና ለሰብአዊነት አመለካከት የቀረበ ዝንባሌ አላቸው። ኢትዮጵያን የሚተረጉሙበት መንገድም ከመሬት የማይወርድ በመለኮታዊ እሳቤ ነው። ይህ በመሆኑ በተለይ ከምርጫ 97 በኃላ የአንድነት ፖለቲካው እያረጠ ፣ የኢሕአዴግ ማጀቢያ ብቻ ሆኗል። የአንድነት ፖለቲከኞች የዘውግ ብሔርተኞችን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ተንትነው ልዩ የፖለተካ መርሆአቸውን ቢሠሩ ኖሮ ቢያንስ ከሀገሪቱ ሕዝብ ግማሽ ያህሉ ይከተላቸው ነበር። በአንድ ዘውግ ራሳቸውን መግለጽ ለማይፈልጉትም ከሥነ ልቦና ስብራት ለመፈወስ መድኅን ይሆኑ ነበር።

የብሔር መንግሥት የለም። ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ ለመኖር ዋስትና አይሆንም። ሉዓላዊ ባለሥልጣናት ብሔሮች ናቸው።

በሽግግሩ የክልል አወቃቀር ወቅት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (EDU)፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ENDO)፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (EPDM)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ቅንጅት(EDC)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (EPDORM) ወ.ዘ.ተ የሚባሉት በኢትዮጵያ ስም የተደራጁ የዜግነት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩም፣ የብሔርተኞች አጃቢ ከመሆን የዘለለ ሚና አልነበራቸውም። ክልሎች ሲዋቀሩ፣ ከተዋቀሩም በኋላ በየሕገ መንግሥታቸው ነባር እና መጤ ብለው አፓርታይዳዊ ሥርዓት ሲዘረጉ በኢትዮጵያ ስም የተደራጁ ፓርቲዎች የብሔር ፌደራሊዝሙን ከመተቸት ያለፈ ሚና አልነበራቸውም። ብሔርተኞች የተሻለ ጉልበት እና ማኅበራዊ መሠረታቸውን ስለተከሉ፣ በኢትዮጵያ ያለው የተቃርኖ የፖለቲካ ትንታኔ ለዜግነት ፖለቲካ ምቹም አልነበረም።

የሽግግር መንግሥቱ በቃለ ጉባኤው ክልል ለማዋቀር ቋንቋን፣ ኩታገጠምነትን እና የሥነ-ልቦና ተዛምዶን መሠረት እንዳደረገ ገልጧል። ወረዳን እንደ መጨረሻ የማደራጃ እርከንነት ወስዷል። በዚህ መሠረትም 14[69] ክልሎች የተዋቀሩ ሲሆን 14ኛዋ ክልል አዲስ አበባ ነበረች። ድሬድዋ ራስ ገዝ ሆና በሽግግር መንግሥቱ ወቅት አልተዋቀረችም። በእርግጥ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም ድሬድዋን አያውቃትም። ዛሬ ያሉት 8 ክልሎች እና ደቡብ ላይ ተፈጥረው የነበሩ 5 ክልሎች ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር ተደምረው 14 ክልሎች በሽግግር መንግሥቱ ተዋቅረዋል።

[69]የሽግግር መንግሥቱ 16ኛ ጉባዔ፣ መስከረም 27 ቀን 1984 ዓ.ምም. በ24 ገጽ ከረቀቀው ቃለጉባኤ።

በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ደቡብ ክልል ብሔረሰቦችን በመደልደል ወደ 5 ክልል ነበር:: የሽግግር መንግሥቱ ውሳኔ ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. ባፀደቀው ሕገ መንግሥት ተሸሮ ደቡብ 56 የሚደርሰው ብሔር ባንድ ማዕቀፍ እንዲሆን ተደርጓል:: በዚህ መሠረትም ደቡብና ጋምቤላ ብሔር ዘለል ስያሜ ሆነው ሊዋቀሩ ችለዋል:: ደቡብ አቅጣጫ ሲሆን፣ ጋምቤላ የአኝዋክ ብሔረሰብ ዋና ከተማ የነበር ቢሆንም፣ የጋምቤላ ክልል መጠሪያ ሆኗል:: የሱማሌ ክልልም አብዛኛ በሆነው በኦጋዴን ጐሳ ስም ኦጋዴን ክልል ተብሎ እንዲጠራ ሐሳብ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም፣ ውሳኔው ተሸሮ ከሀርጌሳ፣ ከሞቃዲሾ፣ ከኬንያ እና ከጅቡቲ ሱማሌዎች በሚለይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል እንዲባል ተወስኗል::

በ2011 ዓ.ም. የሶማሌ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ሙስጦፋ ሙሀመድ ኡመር እኛ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ስለሆንን ኢትዮጵያ የሚል ተቀጥያ አይገባንም:: ሶማሊያ ክልል ማለት በቂ ነው ብለዋል:: ይሄን ተከትሎም ሶማሌ ክልል ብሎ መጥራት የተለመደ ሆኗል::

3.10 የወሎ ክፍለ ሀገር ጉዳይ እና የጉባኤተኞች ድምጽ

በሽግግር መንግሥት የክልል አወቃቀር ወቅት አርሲ 75 ከመቶው ሃዲያ ነው:: ኦሮሞ በአርሲ ከሃዲያ ያንሳል:: የአርሲ ጉዳይ ግምት ውስጥ ገብቶ የሃዲያ የሕዝብ ቁጥር እና አደረጃጀት ሊሠራልኝ ይገባል አለ:: የሃዲያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሃብዴድ) ጉራጌ ቡታጅራ አካባቢ ያሉ ሁሉ የሃዲያ ሥነ-ልቦና አላቸው ከማለቱ በተጨማሪ በባሌ እና በምዕራብ ሐረርጌ በርካታ ሃዲያዎች ያሉ ቢሆንም የሥነ-ልቦና ጦርነት ተከፍቶባቸው ሃዲያነታቸውን[70]

[70] በ16ኛው የሽግግር ምክርቤቱ ሲካሄድ በወርሃ በመስከረም በቀን 22፣ 24 እና 27 በ1984 ዓ.ም. የሽግግር መንግሥቱ ሲዋቀር ከተያዘው የቃለ ጉባኤ ረቂቅ የተወሰደ::

ረስተዋል። ስለዚህ አከላሉ ይሄን ግንዛቤ ያድርግ ሲል ቅዋሜ አቅርቧል።

ብዙ ሙግት የተደረገበት ሌላው የወሎ ክፍለ ሀገር ጉዳይ ነበር። ወሎ በክፍለ ሀገር ደረጃ የአሁኑን ዋግ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎን ጨምሮ አፋር እና ወደ ኤርትራ በ1985 ዓ.ም. የተካለለውን አሰብን ሁሉ ያካትታል። በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ኦነግ ወሎ በሥነ-ልቦ እና በታሪክ እስከ ራያ አዘቦ ድረስ የኦሮሞ እንደሆነ ተከራከረ። የወሎ ሕዝብ አማራ ነኝ አይልም የሚል ስሕተት ሐሳብ በኦነግ በጉባኤተኞቹ ተሰተጋባ።

ኦነግ በወቅቱ መንግሥት[71] ሆኖ የማስታወቂያ፣ የግብርና፣ የትምህርት እና የንግድ ሚኒስትሮችን ከኢሕአዴግ ጋር ተደራድሮ ይመራ ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ ግን ኢትዮጵያን የተመለከተበት ዓይኑ ሁሉ የኦሮሞ በሚል ነበር።

የኦነግን አይጠግቤ ሥነ-ልቦና የተመለከቱት አቶ መለስ ዜናዊ *‹‹ኦነግ በሌሎች ጉዳዮችም ተመሳሳይ አቋም ማሳየት አለበት አሉና በኦሮሚያ ክልል*[72] *የትግሬ ወርጅ፣ አርጐባ፣ የዛይ ብሔረሰቦች*

[71]ዶክተር ዲማ ነገዎ፣ የኦነግ የመጀመሪያው ሊቀመንበር ኢሳት ቴሌቪዥን ላይ በቀን 9 በ2012 ዓ.ም. ወርሃ መስከረም ላይ ከተናገሩት ሐሳብ ተወስዷል።

[72]የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደሚያሳየው፤ ኦሮሚያ ክልል ሰፊ የቆዳ ስፋት ያለውና ልዩ ልዩ ብሔረሰቦችን የያዘ ቢሆንም፤ በክልሉ ውስጥ የነበሩ የእነ ትግሬ ወርጂ ብሔረሰብ ተውጠዋል። በኦሮሚያ ክልል በ1986 ዓ.ም. ቆጠራ ኦሮሞ 85 በመቶ ሲሸፍን፣ በ1999 ዓ.ም. ቆጠራ ደግሞ ኦሮሞ 87.8 በመቶ ይሸፍናል። አማራ ከ9.1 በመቶ ወደ 7.22 በመቶ ዝቅ ብሏል። እነ ዛይ እና ትግሬ ወርጂ የመሳሰሉት ብሔሮች ሙሉ በሙሉ ተውጠዋል። በአማራ ክልል አማራ 91.5 በመቶ አካባቢ ይሸፍናል። ነገር ግን አማራ ይሄን ያህል በላጭ ብሔር ቢሆንም በውስጡ ለ 5 ብሔረሰቦች ማንነታዊ አስተዳደር ሰጥቷል(ዋግኸምራ፣ አዊ፣ አርጎባ፣ ኦሮሞ፣ ቅማንት)። በአማራ ክልል፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ድርሻ ከክልሉ ሕዝብ ከ2 በመቶ ብቻ ቢሆንም፣ የዞን አስተዳደርነት ተሰጥቶታል። የአርጎባ ሕዝብ በአማራ ክልል ከ40ሺህ የማይበልጥ ቢሆንም፤ የወረዳ የራስ አስተዳድርነት ተሰጥቶታል።
አማራ ከክልሉ ውጭ ከክልሉ ከሚኖረው ሕዝብ ከግማሽ ዝቅ የሚለው ይገኛል። ነገር ግን በአንድም አካባቢ ራስ ገዝ አልሆነም። በቋንቋ እና ባህሉ ካለመጠቀሙ በላይ

ኦሮሞ አይደለንም ሲሉ ተቃውማችኃል:: ወሎ አማራ ነኝ ባይል እንኳ ኦሮሞ ነኝ ማለት አይደለም:: ከዚህም ባለፈ አቶ መለስ የብሔር ጉዳይ ሥነ-ፍጥረታዊ (Biological) ሳይሆን ታሪካዊ ሥነ-ልቦና ነው:: ወሎ ትናንት ኦሮሞ ቢሆን እንኳን፤ ዛሬ አማራ ነው:: ነገም ኦሮሞ መባል የለበትም:: ብሔርን የምናደራጀው ትናንቱን ለመመለስ ሳይሆን ዛሬውን ያለጭቆና ለማስቀጠል ነው:: ደግሞ ወሎ ከጥቂቶች በስተቀር ሁሉም አማርኛ ተናጋሪ እና በኩታገጠምነትም ሆነ ዛሬ ባለበት ሁኔታ ተዛምዶው ከአማራው ጋር ነው:: ›› የሚል ይዘት ያለው ንግግር አደረጉ::

ወሎን ኦነግ የኔነው ሲል ከኢሕዴን (ብአዴን) በኩል በቃለ ጉባኤው የተመዘገበ የተባለ ነገር የለም:: ወሎ የኢሕዴን መፈጠሪያ ቦታ ሲሆን ከነአቶ በረከት ስምኦን እስከ ጀኔራል አሳምነው ጽጌ የትግል ሜዳቸው ወሎ ነው:: ወሎ ለኢሕዴን መተከል ዋና መሠረቱ ሲሆን፣ ደርግ በዘመቻ ዋለልኝ የወደቀበት አካባቢም ወሎ ነው:: ነገር ግን ኢሕዴን በወቅቱ ለታገለበት አካባቢ ማንነት ብዙ የቆመ አይመስልም:: ከረጅም ክርክር በኋላ ወሎ አማራም ሆነ ለኦሮሞ ሳይሆን በራሱ ክልል የሚል እና ወሎ በአማራ ክልል ሆኖ ኦሮምኛ የሚናገረው የወሎ ክፍል በወረዳ ይደራጅ የሚል ሐሳብ ለውሳኔ ቀረበ:: በጉባኤው ከነበሩ ከ65 [73]ሰዎች መካከል 44ቱ ወሎ አማራ ነው:: ክልሉም አማራ ሆኖ ጥቂት ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ወረዳ ይሰጣቸው ብለው እጅ አወጡ::

መጤ እየተባለ ከሀገሩ በየጊዜው ይፈናቀላል። ኢሕአዴጋዊ ሥርዓቱ በአማራ መቃብር ላይ የቆመ ነው። አማራ እንደ ደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ግልጽ አፓርታይዳዊ ሥርዓት ተዘርግቶበታል። አማራ በመካከለኛው ምሥራቅ እንደሚገኘው የኩርድ ብሔር ተሳዳጅ ሆኗል። የኩርድ ሕዝብ 30 ሚሊየን ቢደርስም የራሱ መንግሥት ስለሌለው በቱርክ፣ በሶሪያ፣ በኢራን እና በቱርክ ተሰባጥሮ ተገልሎ ይኖራል። በተለይ በቱርክ መኖሩ ይካዳል። ኩርድ የሞሶፖታሚያ ጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት እንደሆነ ቢነገርም፤ የዛሬው የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ሀገር አልባ ሕዝብ አድርጎታል።

[73] በጉባኤው 67 ሰዎች የተሳተፉ ሲሆን፤ ሁለቱ ድምጸ ተአቅቦ ሆነዋል::

11 ሰዎች ብቻ ወሎ አማራም ኦሮሞም ያልሆነ ራሱን የቻለ አስተዳደር ይሁን አሉ፡፡ ወሎ ራሱን የቻለ ክልል ይሁን የሚለው ሐሳብ የኦነግ ሲሆን፣ በኩታ ገጠምነት ከኦሮሞ ጋር ስለማይገናኝ በእጅ አዙር ወሎን ‹‹ማወረም››ን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡ 11 ሰዎች ብቻ ወሎን ክልል ያሉት ከኦነግ 9 ሰዎች እና ሌሎች ሁለት ኦሮሞን ከወከሉ ፓርቲዎች ነበር፡፡ በኦሮሚያ በተለያዩ አካባቢዎች የሚታየው ካርታ ዛሬም ድረስ ወሎን እስከ ራያ ያካተተ ነው፡፡

ዛሬ የሚታዩት ብሔራዊ ክልሎች የተፈጠሩት ያለምንም የሕዝብ ውይይት በ65 ሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ መሆኑ ነገሩን አስገራሚ ያደርገዋል፡፡ ክልሎች የተዋቀሩበት መንገድ ቀልድ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ቀልድ ስለሆነም ይመስላል ብዙውን የሸዋ ክፍል ወደ ኦሮሚያ አካሎ ወሎንም የኦሮሞ ይሁን የሚል ጥያቄ የተነሣው፡፡ በጥናት እና በሕዝብ ፍላጎት ቢሆን ኑሮ አዲስ አበባን ጨምሮ ሁሉም የሸዋ እና ከፊሉ የወለጋ ክፍል በአማራ ክልል መሆን ነበረበት፡፡ የአማራ ክልል ዋና ከተማም ከጎጃም (ባሕር ዳር) ይልቅ ሸዋ (አዲስ አበባ) መሆን ይችል ነበር፡፡ በወቅቱ ቋንቋ እና ሥነ-ልቦና ሰፊ ግምት የተሰጣቸው የክልል ማደራጃ ስለነበሩ፤ ሙሉ ሸዋ በሀገረ መንግሥት ግንባታው ባለው ተረክ እና በቋንቋ ከኦሮሞነት ይልቅ ለአማራነት የቀረበ ፖለቲካዊ መስተጋብር ነበረው፡፡ የኦሮሚያ ክልል የኦሮሞነት መቆሚያው ጠፍቶት እስከ 1998 ዓ.ም. ዋና ከተማ እንኳን መምረጥ አቅቶት እንደመካከለኛው ክፍለ ዘመን እየተቀያየረ ለመምራት ተገዷል፡፡

ከአማራ ክልል ሸዋ ግዛት (ከምንጃር እና ሸንኮራ) 12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ናዝሬት (አዳማ) የነፍጠኛ ከተማ ተብላ ዋና ከተማ ለማድረግ ተሰግታ ነበር፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ አዲስ አበባ ለኢሕአዴግ ዘውጋዊ ፖለቲካ የራስ ምታት መሆኗ ሲገለጽ አቶ መለስ ኦሕዴድን ዋና ከተማውን ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ እንዲያዞር አደረጉ፡፡ ዋና

ዓላማውም አዲስ አበባን ለዘውግ ፖለቲካ ማመቻቸት እና የዜግነት ፖለቲካን መድፈቅን መሠረት ያደረገ አካሄድ ነበር። በሌላ በኩል ኦነግ ድሬድዋን እና ሐረርን ተጋርቶ ወሎንም ልጠቅልል ማለቱ ነጻ ኦሮሚያን የመገንባት ሂደተ አካል ተደርጎ ይወሰዳል። ለሀገር እና ለሕዝብ ከታሰበ፤ ክልልም ለአስተዳደር ምቹነት ተብሎ የተካለለ ከሆነ ሁሉም የሸዋ ክፍል፣ ከፊሉ ወለጋ በአማራ ክልል ሥር መሆን ይገባው እንደነበር በወቅቱ የነበረው የክልል ማደራጃ መስፈርት ይፈቅድ ነበር። ኩታገጠምነት፣ ሥነ-ልቦና፣ ታሪክ፣ ቋንቋ… የወቅቱ ገዥ የማደራጃ መስፈርቶች ነበሩ።

የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ወደ አዲስ አበባ የመጣበት መንገድ የምርጫ 97 የኢትዮጵያዊነት እሳቤ ለዘውገኞች የፈጠረውን ሥጋት ከመቀልበስ ውጭ ምንም ዓይነት የሕግም ሆነ የታሪክ መሠረት የለውም። ዘውጋዊው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እንኳን አዲስ አበባ የሚል ስም ሰጥቶ፣ የፌዴራሉ ራስ ገዝ ከተማ አድርጓታል። ነገር ግን የኦሮሚያ ክልል መንግሥት አዲስ አበባን ፊንፊኔ ብሎ ከማዕከላዊ መንግሥት እና ከሕገ መንግሥቱ ውጭ ሲጠራት እርምት አልተወሰደም። በእርግጥ ሕገ መንግሥቱ የተወሰኑ ቡድኖችን ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ በመሆኑ፣ ሥርቆቱን እና ብልሹ አሠራርን፣ መንግሥታዊ ሽብርን… ሁሉ ሕጋዊ ከለላ ሰጥቶ በተግባር (defacto) ደግፎ የቆመ መስሎ ታይቷል።

ወደ ወሎ ስናዘገም፤ ወሎ በቀደመ ስሙ ቤተ-አማራ ተብሎ ይጠራል። የአማራ ነገሥታት በጉልህ የሚታወቁትም በዚሁ በዛሬው ወሎ ነው። በ1270 ዓ.ም. አካባቢ ዐፄ ይኩኖዓምላክ ንጉሠ አማራ ብለው የነገሡት በወሎ ሃይቅ አካባቢ ነበር። የአማርኛ ቋንቋ መስፋፋት መሠረቱን የጣለውም በወሎ ነው። አማርኛ በንጉሥ ላሊበላ ወታደሮች አድማሱን አስፍቷል። ወሎ የአማራነት መሃል ነው። ኦነግ ግን ዘመኑን እና የኔነቱን የሚለካው ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኦሮሞ ከደቡብ ጫፍ ተነሥቶ ወደ ሰሜን እና

ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ካደረገው መስፋፋት ጀምሮ ነው። በዚህን መስፋፋት ወቅት የኦሮሞ ጎሳዎች ተረከዛቸው የነካውን ዱካ ሁሉም የኔ ነው ይላል። ወሎ የእኔ ነው ሲልም ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የነበረውን ታሪክ ፍቆ ነው። ከዳግማዊ ቴዎድሮስ መንገሥ በ1847 ዓ.ም. በኋላ እስከዛሬ ያለውን ይገድፍና በመሃል የ16ኛውን ወይም የ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነጥሎ ብቻ ያነሣል። ታሪክን ከዘመናት መሃል ቆርጦ በማውጣት የኔ ነው የሚል ከጥንተ ጋርዮሻዊ የአርብቶ አደርነት (pastoralist) ሥነ-ልቦና የሚመነጭ ተስፋፊነት እኔነትን በማክረር እኛነትን ይበጥሳል። ይህ ደግሞ ሀገረ መንግሥቱ ላይ መንገራገጭ ፈጥሯል። ሙሉ የኢትዮጵያ ታሪክ ከትናንት እስከ ዛሬ በትክክል ከተነገረ የኦሮሚያ ክፍለ ግዛት ከቦረና የሚያልፍ ዕድል የለውም። እነ ሸንብራ ኩሬ(ዝዋይ) ሁሉ በታሪክ ከተሔደ የአማራ መሃሎች ናቸው።

ኦነግ[74] ይሄ ታሪኩ ስለማይፈቅድለት ስም ቅየራ እና ማንነት ጨረታ ላይ ባጀ። ፖለቲካውም ከግጭት እና ከጥላቻ ውጭ አመክንዮ አልባ ሆኖ ተቀርጿል። አብዛኛው ኦሮሞ ዳራውን ሲያጠና ቅድመ አዝማዱን (ቅድመ አያቱን) ከኦሮሞ አያገኘውም። በብዛት በሞጋሳ እና በጉድፈቻ በምሥረታዊ (constructive) የብሔር ግንባታ የተፈጠረ ፖለቲካ ሠር ማንነት ነው።

[74]ኦነግ በመንፈስ(በሕሊና) እንጂ በአካል ሀገር አልመራም። ብኩን ድርጅት ነው። ነገር ግን የኦነግ ፖለቲካዊ ጥያቄ እና የብሔርተኝነት ጽንሰ ሐሳብ በብዛት በሁሉም የኦሮሞ ብሔርተኛ ልሂቃን ይስተጋባሉ። ኦነግ ማለት የኦሮሞ ፖለቲከኞች ድምጽ ነው። የኦሮሞ ፖለቲካ በቅርጽ ይለያይ እንጂ በይዘት የኦነግ አስተምህሮ ሚዛን ይደፋል። ስለዚህ የኦሮሞ ፖለቲካን በኦነግ ቅኝት መቃኘት አግባባዊ ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነው።

3.11 ተከጣጩ ቅኝት እና የሀገረ መንግሥት ግንባታው ፈተና

እኔ በተወለድሁበት ወሊጋ አካባቢ ቱሉ አማራ እና አማራ ካንቺ የሚል ስያሜ አለ። በኤርትራ ደግሞ በኦሮሞ ጎሳ ስም ባሬንቱ የሚል የቦታ ስም አለ። እኔ ፊንፊኔ የሚል ስያሜ በታሪክ አላውቅም። ደግሞ በስያሜ የሚሆን ነገር የለም። ሕገ መንግሥቱን ስናረቅ አዲስ አበባን ለፌደራል መንግሥት ነው የሰጠነው። (ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ፣ አዲስ አድማስ ጋዜጣ መጋቢት 7 ቀን 2011 ዓ.ም.)

ኦነግ ኦሮሞ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከደቡብ ወደ ሰሜን ባደረገው መስፋፋት የረገጠውን መሬት ሁሉ የእኔ ነው የሚል የመስፋፋት ሥነ-ልቦና ያለው ድርጅት ነው። የመስፋፋቱን ተረክ ደግሞ ኦሮምኛ ስያሜዎችን በማንሣት ሕጋዊ መሠረት ለመስጠት ይሞክራል። በራሱ መንገድ ሌሎች ድርጅቶች ተጉዘው ከኦሮሚያ ክልል ውስጥ የኔነት እንዳይነሣ ስያሜ ድለዛ ላይ ተሰማርቷል።

ለአብነት አሰበ ተፈሪ-ጭሮ፣ ዓለምማያ-ሀረማያ፣ ደብረ ዘይት-ቢሾፍቱ፣ ናዝሬት-አዳማ፣ ሀገረ ማርያም-ቡሌሆራ፣ ዝዋይ-ባቱ፣ ዝዋይ ሃይቅ-ሃሮ ደምበል፣ ጋላ-ኦሮሞ… ወደሚል ስያሜ ተቀይሯል። በስያሜ እና በትናንት ታሪክ ከተሄደ አርምኛ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እንኳን ብዙ አይገኝም።

አሁን ኦሮሚያ ክልል የሆነው በሙሉ የአማራ እና የሌላው ሕዝብ አሻራ ጎልቶ የሚታይበት ነው። በአማርኛ የተሰየመ ሁሉ የአማራ ነው ማለት እንዳልሆነ ሁሉ፤ በኦሮሞኛ የተሰየመ ሁሉ የኦሮሞ ነው ማለት አይደለም። ስያሜ እና አንድ ነጠላ ታሪክ መዞ ይሄ የእኔ ነው ማለት አይቻልም። ቢቻልማ ኑሮ እነመርካቶ እና ፒያሳ በሮም አስተዳደር ሥር ይሆኑ ነበር።

ስያሜ የእኔነት ማጽኛ የቃል ኪዳን ሰነድ አይደለም። ብዙ ጊዜ የኦሮሞ ብሔርተኞች ስያሜ የኔነት መገለጫ ስለሚመስላቸው የሀገሪቱን ዋና ከተማ ፊንፊኔ ብለው በክልላዊ ሕገ መንግሥታቸው ሳይቀር በይነዋል። ኢትዮጵያ በአብሮነት የተሠራች ናት ለማለት የኦሮሞው ስያሜ አክሱም፤ የተጋሩው በወለጋ፣ የአማራው በከፋ፣ የሶማሌው በአሰሳ፣ የጉራጌው በጋምቤላ… መገኘት አለበት። በዚህ በኩል የአማራ ክልል ምንም ዓይነት የስያሜ ለውጥ አለማድረጉ የሚያስመሰግነው ነው። ቢቀይር ኖሮ ወሎን ቤተ አማራ፤ ከሚሴን ምድረ ገኝ፣ ይልማና ዴንሳን-ይልማ(አዴት)… እያለ ሁሉንም ወደ ቀደመ ስማቸው መመለስ ይችል ነበር። ነገር ግን ያለፈ ታሪክ አይታረምም። ከታረመም መጪውን ታሪክ ማረም ይቀላል።

ኦነግ በኦሮሞ የፖለቲካ ትንታኔ ውስጥ ማንጸሪያ ተደርጎ የሚወሰደው የብሔርተኝነት ጠንሳሽ እና በኦሮሞ ፖለቲካዊ ሥነ-ልቦና ዘንድ ሰፊ ቦታን የያዘ ድርጅት ስለሆነ ነው። ኦዴፓ ጥሩ የኦሮሞ ፖለቲከኛ ለመሆን ካማረው የኦነግ መንፈስ ፖለቲካ መጋራት ምርጫው ያደርጋል።

በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ሕወሓት ኦነግን ለማክሰም ኦሕዴድን (ኦዴፓን) ሙሉ በሙሉ የኦነግን አጀንዳ ጭኖት ነበር። በዚህም ኦነግ አጀንዳ አልባ ሆነ። ሕወሓት መራሹ ኢሕአዴግ በ1983 ዓ.ም. መጨረሻ ለኦነግ የግብርና፣ የማስታወቂያ፣ የንግድ እና የትምህርት ሚኒስትሮችን በሓላፊነት እንዲመራ ቸረው። በሰኔ 1984 ዓ.ም. የቀበሌ የሚሚያ ምርጫን ለማድረግ ኦነግ እና ሕወሓት ተስማሙ። በስምምነታቸው መሠረት የኦነግ እና የሕወሓት ሠራዊት ወደ ምሽጋቸው እንዲገቡ ተፈራረሙ። በስምምነቱ መሠረት ኦነግ የተቆጣጠራቸውን ቦታዎች ለቆ ወታደሩን በሙሉ በ7 ምሽጎች ሲያስገባ፤ ሕወሓት ደግሞ ብዙ ጦር ስለነበረው በ20 ምሽጎች

ለማስገባት[75] ቃል ገባ። ኦነግ ቃሉን አክብሮ ወደ ምሽግ ሲያስገባ ሕወሓት የኦነግን ነጻ ቀጠና ወታደሩን ልኮ ተቆጣጠረ። ኦነግንም ከመንግሥትነቱ ነቅሎ ከሀገር ውስጥ አስወጣው። የኦነግን ሕዝባዊ ቅቡልነት ለመናድ አጀንዳውን በሙሉ ሕወሓታዊው ኢሕአዴግ ለኦሕዴድ አሸከመው። ኦነግ አማራን በሐረር እና በወለጋ በማሳደድ እና ኦሮሞን በመግደል ተፈርጆ ከፖለቲካ ገበያው ወጣ። የሰዎች ግድያም የሕወሓት የፖለቲካ መነገጃ ሆነ። ኦነግም በገዳይነቱ በሚዲያዎች ጎልቶ ተፈረጀ።

ነገር ግን ኦነግ የኦሮሞ ብሔርተኝነት መሠረቱን ጥሏል። የኦሮሞ ልሂቃንን ፖለቲካዊ ፍላጎት ለማወቅ የኦነግን የፖለቲካ ርዕይ መመልከት ትክክለኛ ዋቢ ነው። በዘውጌ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ኦነግነት የኦሮሞ ፖለቲካ ነገዳዊ ርዕዮተ ዓለም ሆኗል።

የኦሮሞ ብሔርተኝነት የ150 ዓመት ታሪክ ለማወራረድ ይሠራል። ኦዴፓ፣ የ150 ዓመት እዳ አለብን [76]ብሎ በድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ሓላፊ በአቶ አዲሱ አረጋ በኩል የካቲት 2011 ዓ.ም. አሥነግሯል። ኦዴፓ የ150 ዓመት ታሪክ ለማረም ይሠራል። ይህ ደግሞ 150 ዓመት ወደፊት ከመራመድ ይልቅ 150 ዓመትን ወደ ኃላ መንሸራተትን ይጠይቃል።

በሌላ በኩል ኦዴፓ የ150 ዓመት ጥያቄ አለኝ ሲል የኦነግን የቅኝ ግዛት ታሪክ መቀበሉን ያሳያል። ስለዚህ ኦዴፓ ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን በፊት የነበረች ኢትዮጵያን ለመመለስ ይሠራል ማለት ነው።

[75]ዶክተር ዲማ ነገዎ፣(የኦነግ ሊቀመንበር የነበሩት) ከኢሳት ጋር መስከረም 9 ቀን 2012 ዓ.ም. ካደረጉት ቃለ መጠይቅ

[76]ብዙዎች የብሔር ፓርቲዎች በዳግማዊ ምኒልክ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ስለማይስማሙ የኢትዮጵያን እድሜ ከምኒልክ የሀገር ግንባታ በኋላ ባለው ይለካሉ። የምኒልክን የሀገር ግንባታ ሂደት እንደ ልዩ ጭቆና እና ቅኝ ግዛት ይመለከቱታል።

ይህ ማለት ኦዴፓ የአሁኗ ኢትዮጵያ የሌለችበትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ይሠራል ማለት ነው:: ተስፋፊነት የሚመነጨውም ከዚህ ጠባብ እሳቤ እና ፍርሃት ነው::

የኦሮሞ ፖለቲከኞች ከጀርመን የሃይማኖት ሰባኪዎች (የፕሮቴስታንት ሚሽነሪዎች) ጋር በመሆን ኢትዮጵያ የሚለውን የሀገሪቱን ስያሜ በኩሽ ለመተካት ጥረት አድርገዋል:: የኩሽ ሕዝቦች ብለው የሶማሌን፣ የሲዳማን፣ የአፋርን ፖለቲከኞች ለማሰባሰብ ሙከራ አድርገዋል:: የኩሽነት እንቅስቃሴ በምሥራቅ አፍሪካ እነ ሶማሌን ሁሉ ስለሚደምር ኩሻዊ የምሥራቅ አፍሪካ ድርጅት (ኢጋድ) ይመሠረታል ስትል ኬንያ [77]ሥጋቷን ገልጻለች:: መርህ አልባ እና አግላይ አንጃ አይደለም ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ለአፍሪካም ጠንቅ ሆኖ ታይቷል::

ትናንት ጥቁር ጀርመንን ነን ያሉት ኦነጐች ጀርመንነት ባያወጣ ኩሽ ብለው በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ሰፊ ሚና የነበረውን የሰሜኑን ክፍል ለመኮርኮም ሞክረዋል:: የኦሮሞ ልሂቃን በኢሕአዴግ መዋቅር ሁለት ወፋፍራም ቅራኔ አላቸው:: የመጀመሪያው ኢሕአዴግ የብሔር እና ብሔረሰቦች ነጻ አውጭ ቢሆንም፣ የኦሮሞን ብሔር ነጻነት እና ራስን በራስ የማስተዳደር ፈቃድ ገና አልመለሰም የሚል ቅራኔ ጎልቶ ይነሣል:: በሌላ በኩል ግን ኢሕአዴግ ከመሠረቱ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግሥት ሲያቆም የኦሮሞ ሕዝብ እንደ ኤርትራ ሕዝብ በሕዝበ ውሳኔ(ሪፈረንደም) ፍላጎቱ መጠየቅ አለበት የሚሉ አንጃዎች አሉ::

እነዚህ አንጃዎች የኦሮሚያ ነጻ ሀገርነትን ለመመሥረት የሚናፍቁ ልሂቃን ናቸው:: ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ትናንታዊ ተዛምዶ እንደሌላቸው ፖለቲካቸውን አስልተው ይሰፍራሉ:: ትናንታዊ

[77]ፍትሕ መጽሄት፣ አንደኛ ዓመት ቁጥር 39 ሐምሌ 2011 ዓ.ም.

ተዛምዷቸውን የገዳ ባህላዊ ሥርዓት እና መዋቅር ብቻ ያደርጉና የሀገረ መንግሥት ግንባታ የእሳቤ አድማሳቸውን በኦሮሚያ ክልል ብቻ ይኮረኩሙታል:: እነዚህ ቡድኖች ህልማቸው ኦሮሚያ ብቻ መሆኑ ኦሮምኛ[78] ቋንቋ ዘውግ ዘለል ሆኖ እንዳይስፋፋ እና ከክልሉ እንዳይወጣ አግዶታል:: ባህል በሰጥቶ መቀበል፣ በገበያ፣ በማኅበራዊ ተራክቦ፣ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የመዛመት

[78]የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ(ኦፌኮ) ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አቶ በቀለ ገርባ ኦሮምኛን ለማስፋፋት እንከን የሆኑት ድቅሎች ናቸው ሲሉ ከሰዋል። በአባት ወይም በእናት ብቻ ኦሮሞ የሆኑት ከኦሮምኛ ቋንቋ ውጭ ሌላ ቋንቋ ይናገራሉ ሲሉ ወቅሰዋል። እንደ አቶ በቀለ፤ ኦሮምኛን ለማስፋፋት በክልሉ የገበያ ቦታዎች ኦሮምኛን ብቻ መናገር ተገቢነት አለው። በግዳጅ ኦሮምኛን ማስለመድን ምርጫ አድርገዋል። ይሄን ስብከት ተከትሎም በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ ከተሞች አልጋ ይዞ ለማደርም ሆነ በሆቴሎች ምግብ ለማዘዝ ከኦሮምኛ ቋንቋ ውጭ ሌላ ቋንቋ ተጠቅመው ሲያዝዙ ፈቃደኛ የማይሆኑ አስተናጋጆች እንዲፈጠሩ እያደረገ ነው። ቋንቋ ከኢኮኖሚው ጋር ተወዳድሮ ካላሸነፈ የወልነት ባሕርይ ያጥረዋል።

ኦሮምኛ የሀገሪቱ የሥራ ቋንቋ ቢሆን በእነ አቶ በቀለ ገርባ ስብከት መሠረት ኦሮምኛን ከአማራጭ ቋንቋነት ይልቅ ወደ ማስገደድ መውሰዳቸው አይቀርም። በማዕከላዊ መንግሥቱ ሳይቀር የኦሮምኛ እና የአማርኛ ተናጋሪዎችን ብዛት ማመጣጠን ሌላ ሥራ ይሆናል። ቋንቋ ከመግባቢያ መሣሪያነት አልፎ የፖለቲካ እና የማንነት ትርጉም ከተሠጠው አስማሚነቱ ይላላል። ቋንቋ ፖለቲካ ከሆነ ምኒልክን የሚጠላ ሁሉ አማርኛን ሊጠላ ይገደዳል። የኦነግን አስተምህሮ የሚቃረን ሁሉ ለኦሮምኛ በጎ እሳቤ አያዳብርም። ቋንቋ የማኅበረሰብ ሀብት እንጂ የፖለቲካ ልሂቃን ጸጋ ሆኖ ከተቀነቀነ ደጋፊ እና ተቃዋሚ ያፈራል። ይህ ደግሞ ቋንቋ በነጻነት እንዳይበለጽግ ያደርገዋል።

ኢትዮጵያ የበርካታ ቋንቋዎች ሀገር በመሆኗ ተጨማሪ የሥራ ቋንቋ ካስፈለገ ቢያንስ አስር ቋንቋዎችን በሥነ-ልሳን አጥኚዎች ምክረ ሐሳብ መሠረት ወደ ሥራ ቋንቋነት ማምጣት አለባት። ከአማርኛ በተጨማሪ ኦሮምኛን፣ ትግርኛን፣ ሶማሊኛን፣ አፋርኛን ብታደረግ ለምሥራቅ አፍሪካ መግባቢነት ይጠቅማሉ። ከሀገር ውስጥ እነ ሲዳምኛ፣ ወላይትኛ እና ጉራግኛ መሰል ቋንቋዎች ወደ ማዕከላዊ መንግሥቱ የሥራ ቋንቋነት ቢመጡ የቋንቋን ፖለቲካዊ ፍትጊያ ይቀንሳል። በአማርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋ መካከል ያለውን አጉል ውድድር ቀንሶ ዜጎች የሚመቻቸውን ለመምረጥ እድል ይፈጥርላቸዋል። አማርኛ እና ኦሮምኛን ብቻ የሥራ ቋንቋ ማድረግ ሀገሪቱን በአማርኛ እና በኦሮምኛ ተናጋሪዎች እጅ ጥሎ በሁለቱ ፍትጊያ መሙላት ነው።

ህንድ 22፣ ዝምባብዌ 16፣ ደቡብ አፍሪካ 11… ቋንቋዎችን በሥራ ቋንቋነት ለይተዋል። ይህ መሆኑ የቋንቋ ግፊን አስቀርቶ፤ ቋንቋን ከፖለቲከኞች አውጥቶ ለማኅበረሰቡ እና ለተናጋሪው ግለሰብ እንደ ምርጫው እንዲገለገልበት አድርጓል። በመንግሥት ደረጃ ደግሞ ለሁሉም ቋንቋዎች ጥበቃ እንዲደረግላቸው ሓላፊነት አሸክሟል። የእኔ ቋንቋ የሥራ ቋንቋ ይደረግልኝ የሚለውን ተኅታች ጥያቄም ፈትተውበታል። ቋንቋ ለጥናት እና ምርምር፣ ለገበያ፣ ለማኅበራዊ ተግባቦት… በሚያመች መንገድ ተናጋሪው መምረጥ አለበት። በግድ የተጫነ ቋንቋ ብዙ አያድግም። ቂም ስለሚያዝበት ለመልመድም ለአዕምሮ ሽክረትን ይፈጥራል።

ባሕርይ አለው። የኦሮሞ ልሂቃን ግን ሌላውን ሁሉ እየገፉ፣ ኦሮሞነትን ብቻ ንጥል አድርገው ለማቆም መሞከራቸው የኦሮሞ ባህል ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ባህሎች ጋር በቀላሉ ውሕደት እንዳይፈጥር አድርጓል።

የቻይና ቋንቋ (መንደሪን) በዓለም ብዙ ተናጋሪ ያለው ልሳን ነው። እነ ሂንዱ እና ስፓኒሽ ሁሉ ሰፊ ተናጋሪ አላቸው። እንግሊዝኛ ከመንደሪን፣ ከሂንዱ እና ከስፓኒሽ ያነሰ የተናጋሪ ብዛት ያለው ቋንቋ ነው። ነገር ግን ትንሽ ተናጋሪ ያለው ሓላፊነት ቋንቋ ወላዊ የዓለም መግባቢያ ልሳን ሆኖ ተሹሟል። ምክንያቱም እንግሊዝኛ ከብሪታኒያ ግዛት ከንዑሷ ከጀርመን ሥረ መንግሥት አካል ከነበረችው ከእንግሊሽ ብሔር(አንግሎ ሳክሶን) ተነሥቶ ዘውግ ዘለል አገልግሎት ለመስጠት ራሱን ክፍት አድርጓል። እንግሊዝኛ የቋንቋዎች ድምር እንጂ ነጠላ ታሪክ የለውም። ለምሳሌ ከላቲን እና ከፈረንሳይ ከ50 በመቶ በላይ ቃል ሲዋስ፤ ከግሪክ ደግሞ 6 ከመቶውን ተበድሮ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂን፣ ባህል እና ማኅበራዊ ተራክቦን፣ እውቀትን... መግለጽ በመቻሉ የዓለም ቋንቋ ሆኗል። የህንድ ቋንቋ የሆነው ሂንዱ በዓለም ላይ በአፍ ፈት ተናጋሪ ብዛት ከቻይናው መንደሪን ቀጥሎ ሁለተኛ ቋንቋ ቢሆንም፣ የህንድ ብሔራዊ ቋንቋ እንኳን መሆን አልቻለም። በህንድ ከሂንዱ ይልቅ እንግሊዝኛ ሰፊ ግልጋሎት አለው።

ቋንቋ ወይም ባህል እንዲስፋፋ ሰጥቶ መቀበል አለበት። የአሸናፊ ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ቋንቋ መሆን አለበት። የእንግሊዝ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ በዓለም ገናና ሆኖ ባይወጣ ኖሮ እንግሊዝኛ መሰልጠን እና ድንበር መሻገር አይችልም ነበር። በዚህ ረገድ አማርኛ በመዋቅር ከኵሽቲክ፣ በቃላት እና በቋንቋዊ ባሕርያቱ ከሴሜቲክ ቋንቋዎች ጋር ተነባብሮ ራሱን ወደ ደቡብም ሆነ ሰሜን እንዲሰፋ ባሕርይው ፈቅዶለታል። ከግእዝ እና ራሱ በፈጠረው ፊደላት ሀገርኛ አድርጎ

ለመጠቀም መሞከሩም ልዩ ቀለም ፈጥሮለታል፡፡ በዚህ ቀለሙም የፖለቲካ እና የገበያ ቋንቋ ሆኖ ወጥቷል፡፡

በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ኦነግ ከግእዝ ፊደል ይልቅ ላቲን ይመቸኛል፤ የ20 ዓመት ልምድም አለን ብሎ ተከራክሯል፡፡ በእርግጥ የመኢሶኑ መሪ የነበረው ኃይሌ ፊዳም ኦሮምኛ በቁቤ እንዲሰጥ ይጥር እንደነበር ፈረንሳያዊት ባለቤቱ ለአንድ ሬዲዮ ጣቢያ ስትናገር ሰምቻለሁ፡፡ ኦሮሚያ ክልል በክልልነት ሲቆም የዘመን ስሌቱን ሁሉ እንደ ኤርትራ በአውሮፓ አቆጣጠር ለመጠቀም ሙከራ አድርጐ ነበር፡፡ ሲዳማም በሽግግር መንግሥቱ ወቅት የፊደል ምርጫው ላቲን እንደሆነ መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገ ጉባኤ ፍላጐቱን አሳይቷል፡፡ ሲዳማ በንቅናቄ ደረጃ ቀድሞ የተደራጀ የፖለቲካ ፖርቲ የነበረው የደቡብ ብሔረሰብ አካል የነበረ ነው፡፡

ሲዳማ ከሽግግር መንግሥቱ ጀምሮ የክልልነት ጥያቄ ሲያነሣ ቆይቷል፡፡ የዶክተር አብይን ወደ ሥልጣን መምጣትን ተከትሎ ደግሞ የጉራጌ፣ የወላይታ፣ የጋሞጐፋ፣ የከምባታ… ሕዝብም የክልል እንሁን ጥያቄ እያነሡ ነው፡፡ ጥያቄው መቋጫ ስለማይኖረው ደቡብ ወደ 56 ክልል ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም ብሔረሰብ የክልልነት ጥያቄ ካነሣ ኢትዮጵያ ከ85 በላይ ክልል ይኖራታል፡፡ 85 ክልሎች 85 ቋንቋ ይኖራቸዋል፡፡ የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ የኢትዮጵያ የፓንዶራ ሳጥንን ይከፍታል፡፡ የፓንዶራ[79] ሳጥኑ መከፈት የዘመነ መሳፍንት ሥርዓት የመታወጂያው ምዕራፍ ነው፡፡

በሀገር ደረጃ መግባባት በኢትዮጵያ እንደ ባቢሎን ከባድ እየሆነ

[79] የፓንዶራ ሳጥን በግሪክ አፈ-ታሪክ ውስጥ የተፈጠረ ምናባዊ ሳጥን ነው፡፡ ይህ ሳጥን የዓለምን ክፋት እና ኃጢአት ሁሉ ከድኖ የያዘ ነው፡፡ ሳጥኑን መክፈት ክፋትን ሁሉ እንደመልቀቅ ይቆጠራል፡፡ ሀገራዊ ሕልም እና አሻጋሪ ሐሳብ የሌለው አስተዳደር የፓንዶራ ሳጥኑን ቧው አድርጎ ከፍቶታል፡፡ ብሔር እና ብሔረሰብ ወጥ ትርጓሜ ስለሌለው ንዑስ ከባቢያዊ ማንነቶች ሁሉ ብሔር ነኝ ብለው የራሳቸውን አስተዳደር ለመዘርጋት ሊነሡ ይችላሉ፡፡

ነው። በኦሮሚያ ክልል የተማሩ ተማሪዎች ዲግሪ ይዘው የግእዝ ፊደል ማንበብ ስለማይችሉ በፌደራል መሥሪያ ቤቶች ለመቀጠር ይቸገራሉ። በኢሕአዴግ ዘመን የተወለዱ ወጣቶች የሃይማኖት መጽሐፍትን በግእዝ ፊደል ለማንበብ ተቸግረዋል። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደሚያሳየው በኦሮሚያ ከ1986 እስከ 1999 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ብቻ 11 በመቶ አካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኞች ሃይማኖታቸውን ወደ ሌላ ሃይማኖት ቀይረዋል። የመቀየራቸው መንስኤ ደግሞ ብሔርተኝነት ሲሆን፤ ፕሮቴስታንት ለኦሮሞ ብሔርተኝነት መፈጠር የላቀ ሚና ስለተጫወተ ብዙዎቹን በአማኝነት መሰብሰብ ችሏል።

ኦሮሞኛን[80] የሥራ ቋንቋ አድርጐ ችግሩን ለመቅረፍ ቢሞክር እንኳን ሌላው ብሔረሰብ ደግሞ ጥያቄ ያነሣል። በጠላትነት፣ በአሸናፊነት እና ተሸናፊነት የተቀነቀነ ብሔርተኝነት በአንድ ሀገር ለመኖር እክል ይሆናል። ሲደላው ኢትዮጵያ ሲከፋው ልገንጠል ባይ ብሔርተኛ ባለበት ሀገር ውስጥ የትናንት ትዝታ እና የነገ ሀገራዊ ሕልም የለም።

በእንደዚህ ዓይነቱ ኢ-ተስማሚ ፍላጎት ምክንያት ኢትዮጵያዊነት ያሳሳባቸው ዶክተር ፀሐይ ጀምበሩ የአንጐሌ ሁካታ ብለው ባሳተሙት ጥራዛቸው ሀገራዊ ሕልም ከሌለን የብቻ መኖርን እመርጣለሁ ብለዋል። ለአብነትም ኖርዌይ እና ስዊድንን ሲንጋፖር እና ማሌዥያ ያደረጉትን ፍቺ ያስቀምጣሉ። እነዚህ ሀገራት ለየብቻ ሀገር ሲሆኑ የተሻለ ሕልምና እድገት አምጥተዋል። በእርግጥ ዶክተር ፀሐይ በሀገሪቱ ያለው የጥላቻ ውፍረት አስደንግጧቸው እንጂ መገንጠልን በጠቃሚነቱ አያነሡትም። ኢትዮጵያ ብሔሮቿ

[80] ኦሮምኛ ቋንቋን የሥራ ቋንቋ ሲደረግ የኦሮሞ ብሔርተኝነት መሪዎች በኦሮሚያ ክልል ምንም ዓይነት ቋንቋ እንዳይነገር ይከለክሉ እና የማዕከላዊ መንግሥት ላይ የኮታ ሽሚያ ይግላል። የኦሮሞ ፖለቲካ አግላይ እና አድማሱ ኦሮሞነት ብቻ እንዲሆን ተደርጎ ስለተሠራ ከሀገረ መንግሥት ግንባታው ጋር ኢ-ተጋጣሚ ፍላጎቶችን አሳድጓል።

ለየብቻ ሀገር ቢሆኑም፣ ሰላም የማግኘት እድላቸው የቀነጨረ ነው። የችግሩ ሥረ-መንስኤ በኮሚኒስታዊ ስሑት ፖለቲካ የመጣው የኢትዮጵያዊነት እና የፖለቲካ ተረክ የአተረጓጎም ብልሹ ብያኔ ነው።

ለምሳሌ ኦሮሞ ቢገነጠል ከትግራይ በስተቀር ሁሉንም ክልሎች ያዋስናል። ኦሮሞ በውኃማ አካል ሳይሆን በሀገር የተከበበ ደሴት ይሆናል። ለዕድገትም ሆነ ለጸጥታ አስቸጋሪ ነው። የኦሮሞ ውስጣዊ ፖለቲካውም እሳት እንዳልነካው ዳቦ የተፍረከረከ ነው። በሐረሩ እና በአሩሲው፣ በወለጋው እና በሸዋው[81]፣ በጅማው እና በጉጂው የኦሮሞ ፖለቲካ መካከል የሰፉ ልዩነቶች አሉ።

[81]በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለው ሸዋ ኦሮምኛ ከመናገር ውጭ በሥነ-ልቦና እና ታሪክ ከአማራ ወይም ከኢትዮጵያዊነት ንቅናቄ ጋር የተጋባ ስሜት አለው። በሀገር ግንባታ ሂደት በዳግማዊ ምኒልክ አማካኝነት ከአማራው ሸዋ ጋር የበረከተ አስተዋጽኦ አድርጓል። የኦሮሞ ብሔርተኝነት ከኦሮምኛ ተናጋሪው ሸዋ በተቃርኖ የቆመ ነው። ሸዋ የገኘው መደብ አካል ተደርጎ ከሸዋ የወጡ ቀደምት መሪዎች በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ የጠየመ መልክ ተሰጥቷቸዋል። በእርግጥ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ከ1983 በፊት በኢትዮጵያ በጎ አስተዋጥኦ ያደረጉትን ኦሮሞዎችን በጸረ ኦሮሞነት ወይም በአገልጋይነት ይከሳል። የኦሮሞ ብሔርተኝነት ከኦሮሞነት የወጣ አድማስ የለውም። ከኦሮሚያ ክልል ወጥተው ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን ያኮሩ አትሌቶችን ሳይቀር እንደ ኦሮሞ ብሔርተኛው ብዙ አይቀበላቸውም። ዶክተር አብይ ወደ ሥልጣን እንደመጡ ኢትዮጵያ በማለታቸው የምኒልክ ግልገል ተብለው ተፈርጀዋል።

እናም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገራዊ እሳቤ ስለነበራቸው በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ ቅቡልነት አልነበራቸውም። ራሱ ኦሕዴድ (ኦዴፓ) ከኢሕአዴግ ጋር ተቀናጅቶ ሀገራዊ ፓርቲ ቢፈጥርም፣ ከዞን በታች ያለው መዋቅሩ በኦነግ የተደራጀ ነው። ኦነግ ደግሞ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዥነት የሚፈርጅ ድርጅት ነው። በአንድ ወቅት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ‹‹እያንዳንዱ ኦሕዴድ ሲፋቅ ኦነግ ነው›› ብለው ነበር። እንዳሉትም በመከላከያ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው እነ ብርጋዴር ጀኔራል ከማል ገልቹ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ሆነው ለኦነግ ሲሠሩ እንደነበር በአንደበታቸው ተናግረዋል። ሸዋን የኦሮሞ ብሔርተኞች በሚያዩበት ልክ፣ ሕወሓት ተምቤንን ያያል። ተምቤን እነ ዐፄ ዮሐንስ እና የበርካታ ነጋሚዎች መንደር ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት(ኢዴኅ ወይም ኢዲዩ) ለሕወሓት ፈተና ሆኖ የተነሣው በብዛት ተምቤን አካባቢ ነው። ኢዲዩ ከ1966 በኋላ ዘውዳዊውን መንግሥት ዴሞክራሲያዊ አድርጎ ማስቀጠል ይቻላል ብሎ የተነሣ ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት በአማራ እና ትግራይ እግሩን ተክሎ ነበር። በትግራይ ሕወሓት ነቅሎ ጣለው። ተምቤን የፊውዳል መንበር ተደርጋ በሕወሓት ተፈረጀች። የነሕወሓትም ሆነ የነኦነግ ብሔርተኝነት ትናንትን ነቅሎ አዲስ ማንነት በመፍጠር ያምናል።

አውራጃዊነት ከኦሮሞ ፖለቲካ ጋር አድጓል:: በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለው የሸዋ ፖለቲካ ከምኒልክ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ጋር ኢ-ተነጣጣይ አሻራ ስላለው በኦሮሞ ብሔርተኝነት ውስጥ የመታመን እዳ አለበት:: በምኒልክ የጦር አበጋዝ በጎበና ዳጬ ስም የሸዋ ኦሮምኛ ተናጋሪዎችን አንዳንድ የኦሮሞ ብሔርተኛ ልሂቃን እንደ ከሃዲ ይቆጥራሉ:: ሕወሓትም በኢትዮጵያዊነት የማይደራደሩ ትግሬዎችን **የሸዋ ትግሬ** እያለ መጥራቱ የተለመደ ፍረጃ ነበር::

የኦሮሞ ብሔርተኝነት በተቃርኖ የታጀለ ነው:: ለዚህም ይመስላል፣ ኦሮሞን የሚወክል 17 የፖለቲካ ፓርቲ የተፈጠረው:: በሽግግር መንግሥቱ አካባቢ የኦሮሚያ እስላማዊ ግንባር ፓርቲ ተደራዳሪ ሆኖ ወጥቶ ነበር:: ኦሮሞነትን ከእስልምና ጋር አዳቅሎ የመተርጎም ሁኔታ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን ፖለቲካዊ ስምምነት አጉሎት ተስተውሏል:: ኦነግ እንኳን በወንዜነት እና በሃይማኖት ልዩነት ራሱን እንደ አሜባ ያራባ ድርጅት ነው:: በኢትዮጵያ በሰፈነው ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ውድቀት በወለደው ያለመተማመን እና የአብሮነት መሟሟት ምክንያት በሀገሪቱ በመቶ ሃምሳ በላይ ፓርቲዎች ተፈልፍለዋል:: የፓርቲዎችን ቁጥር ለሀገሪቱ ሕዝብ ስንደለድለው ቢያንስ 1ሚሊየን ሕዝብ አንድ ፓርቲ ይኖረዋል:: የኦሮሞ ሕዝብ ደግሞ በ17 ፓርቲ ተወክሏል::

በኦሮሞ ፖለቲካ ከአውራጃነቱ በላይ የሃይማኖት ጉዳይ ትልቅ መካረሮችን ያስተናግዳል:: ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የኦሮሞ ብሔርተኞች እንደ ምኒልክ ሃይማኖት ተመልክተው በጨቋኝነት ይፈርጃሉ:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ኦሮሞዎች የራሳቸው ሲኖዶስ በኦነግ አስተምህሮ ልክ እንዲቀርጹ ሲያግባቡ ባጅተዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ኦሮሞዎችን እንደ አማራ የመቁጠር አዝማሚያም አለ::

የኦሮሞ ፖለቲካ ከእምነት አንጻር በፕሮቴስታንት እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ፋክክር ውስጥ ገብቷል፡፡ ብዙዎች የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የኦዴፓን ፖለቲካ ሲቆጣጠሩት፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደተገፉ ማሰባቸው አልቀረም፡፡

የኦሮሞ ብሔርተኝነት ከገዳ ሥርዓት ነው የሚቀዳ የሚሉት ደግሞ እምነታችን ዋቄፈና ነው ይላሉ፡፡ ኦነግ የብሔርተኝነቱ ፈተና የሃይማኖት ጉዳይ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ወለጋ አካባቢ አውሮፓዊ ሰባኪያን ፕሮቴስታንትን ቀድመው ሰብከዋል፡፡ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ቀድሞ የተቀነቀነው በወለጋ ስለነበር ለፕሮቴስታንትነት እምነት የቀረበ ስሜት ስለነበረው ኦሮሞ ጥቁር ጀርመናዊ ነው እስከመባል ደርሷል፡፡ ዋል አደር ብሎ ግን የሃይማኖት ጉዳይ በእስልምና ተከታዮች ዘንድ ጥያቄ ሆኖ ስለተነሣ እነ ፍሬው ኢብሳ ስማቸውን ዳውድ ኢብሳ ተብለው ሸኔ ኦነግን ለመምራት ተገደዋል፡፡

የኦሮሞ አንድነት የተገነባው በመርህ እና በነጠረ ምክንያት ሳይሆን፤ በአማራ ፍራቻ እና ጥላቻ ላይ ነው፡፡ ኦሮሞ ሀገር ከሆነ ከአውራጃዊነት እስከ ሃይማኖት ያሉ ጉዳዮች ሌላ መካረር ይዘው ብቅ ይላሉ፡፡ የፖለቲካ ሥርዓቱ ባልተስተካከለበት ሁኔታ እንኳን ክልሎች ወረዳዎችም ሀገር ቢሆኑ ወንዜነቱ ሊራገፍ አይችልም፡፡ ፖለቲካ በድርድር የመስማማት ሂደት ነው፡፡ ይህን ሂደት አቻ አሸናፊነትን ባነበረ ፖለቲካ ከተመራ እንኳን ስማኒያ ምናምን ብሔር የህንድ እና የናይጀሪያ ከ300 የሚዘሉ ጎሳዎች እና ብሔረሰቦች በየሀገራቸው ጥላ ሥር የተሻለ ኢኮኖሚ፣ ዴሞክራሲ እና ማኅበራዊ ተራክቦ ማምጣት ችለዋል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ኤርትራ ከኢትዮጵያ፣ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ተፋትተው ለተሻለ ነጻነት ብለው ሀገር ቢሆኑም፤ ሀገርነታቸው ልዩ በረከት አላወረደላቸውም፡፡ ሀገረ መንግሥት አድርጎ

የሚያጸናቸውን ሥርዓት አካላዊ መዋቅር ገና አልፈጠሩም። አካላዊ መዋቅሩ ቢፈጠርም፤ የመዋቅሩ ብልቶች ተነባብረው አንድ ሀገረ መንግሥት መፍጠር አልቻሉም።

ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ራሷን ለመነጠል አንድ ሕዝብ ትመስል ነበር። በ2011 እ.ኤ.አ. ራሷን የቻለች ሀገር ስትሆን ግን እንደገና ደቡብ ሱዳናውያን እርስበርሳቸው መስማማት ተስኗቸዋል። ደቡብ ሱዳናውያን አጀንዳቸውን ከካርቱም ሲያነሡ፤ ወደ ጎሳ እና ብሔር ሽኩቻ ወርደዋል። ሶማሊያም የውስጥ ችግሯን ሳትፈታ ችግሯን በዚያድ ባሬ አማካኝነት ወደ ውጭ ብቻ አደረገች።

ሰሜኑንና ደቡብ ሶማሊያ ተስማምቶ ኢትዮጵያን ለመውረር ሲዳዳ ከኮሚኒዝም መውደቅ ጋር የዚያድ ባሬ ጉልበት ሲዝል ሱማሊያውያን በጎሳ ተፈረካከሱ። እነሶማሌ ላንድ ዋና ከተማቸውን ሀርጌሳ ላይ አድርገው ሀገር ነን ያሉ ሲሆን፣ የሞቃዲሾዋ ሶማሌ ደግሞ እኔ ማዕከላዊ መንግሥት ነኝ እያለች ነው። ተመሳሳይ ሃይማኖት እና ቋንቋ ያላቸው ሶማሌያውያን ከሃይማኖታቸው በላይ ጎሳቸውን በማምለክ አንድነታቸውን እና ዝምድናቸውን በጎሳ ይመሠርታሉ። ጎሰኝነት ሶማሌያውያንን ማዶ እና ማዶ አስቀምጦ መንግሥት እንዳይገነቡ አድርጓል።

በኢትዮጵያም መገነጣጠል ቢመጣ ችግሩ እስከ ቀበሌ ስለሚወርድ ሰላም ያለው ሀገር አይፈጠርም። ሶማሌዎች ተመሳሳይ ሃይማኖትና ቋንቋ ቢኖራቸውም ፖለቲካ ወለድ በሆነ የጉሰኝነት ትርክት ምክንያት የእነ አልሻባብ የጦር ሜዳ ሆነዋል። እነ የመን እና ኮርያ ደቡብ እና ሰሜን ተባብለው ተመሳሳይ ባህል እና ወግ (homogeneous) ቢኖራቸውም የተለያየ ሀገር ሆነው ቆይተዋል። በርሊን ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በአጥር ለሁለት ተከፍላ ነበር። ምሥራቅ እና ምዕራብ ጀርመን ተብላ ሀገሪቱም ለሁለት

ተሰንጥቃ እስከ 1990 ቆይታለች። እንደ ኮርያ ሁሉ የዚህ ስንጥቅ መንስኤው የብሔር እና የቋንቋ ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እና የኢኮኖሚ ፍልስፍና ነበር። ትልቁ የልዩነት አጥር ፈጣሪው የኢኮኖሚ እድገት አለመመጣጠን ነው።

ስለዚህ፤ ተመሳሳይ ቋንቋ እና ባህል ያላቸው ዜጐች ሁሉ ሰላም ላይሆኑ እንደሚችሉት ሁሉ፣ የተለያየ ቋንቋ እና ባህል ያላቸውም ሰላም ሊርቃቸው አይችልም። የተቃና ብሔረ መንግሥት ለመመሥረት በቋንቋ እና በሃይማኖት መመሳሰል ወይም አለመመሳሰል ልዩነት አይፈጥርም።

ዋናው የሰለጠነ ፖለቲካዊ ሥርዓትን መዘርጋት ነው። የምዕራቡ የአውሮፖ ክፍል የተለያየ ሀገር ቢሆንም በጋራ ለመደራጀት ሩሲያ እና ቻይናን በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ተቋቁሞ ቁሟል። ብሔሮች እና ሕዝቦች በኢኮኖሚ ከተዋሐዱ ልዩነታቸው አይታያቸውም። ማንነትን ቀላቅለው እና አቅልጠው ከተሞች አዲስ ማንነትን የሚፈጥሩት በኢኮኖሚ መስተጋብር ምክንያት ነው። ብዙውን ጊዜ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ብሔሮች ሉዓላዊ ሥልጣን ቢሰጣቸውም ከተሞች ዘውጋዊ ብሔርተኛ መሆን ብዙ አልቻሉም። ለአብነት አዲስ አበባን መውሰድ ይቻላል። በኢኮኖሚ መስተጋብር ምክንያት የአዲስ አበባ ነዋሪ ቅድመ ነገድ ማንነቱን ትቶ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ፈጥሯል። አዲስ አበባ የተከማቸውን የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ጉልበት ወደ ክልሎችም በትኖ እና አካፍሎ ብዙ ከተሞችን መፍጠር ከተቻለ ኢትዮጵያዊ ማንነት እየጎለበተ ይመጣል። በዚሁም ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገት ይጎለብታል።

ገርማሜ ንዋይ በ1940ዎቹ ወደ ሶማሊያ አቅንቶ የጅጅጋ ከተማን በንግድ እንድትበለጽግ አድርጓል። ዋና ዓላማውም ሰሜን ጫፍን ከምሥራቁ፣ ምሥራቁን ከምዕራቡ የኢኮኖሚ ውሕደት እንዲፈጽም ነው። የኢኮኖሚ ውሕደት የባህል ቅልቅልን ይፈጥራል። በዚህ

ምክንያት ነጠላ ማንነት ጠፍቶ ድርብ ማንነት ይፈጥራል። ድርቡ ማንነቱ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ነው። ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች በማዕከላዊ መንግሥቱ እየተዳደሩ ከየትኛውም ቦታ ሠራተኞች ቢቀጠሩ፣ የኢንዱትስሪ ምርቶች ተመጋጋቢ ሆነው አንዱ ያመረተውን ሌላው ቢገዛ የአንዱ መጥፋት ለሌላው ኪሳራ በመሆኑ ነጠላ ብሔርተኝነት ጠፍቶ ድርብ የዜግነት ጉዳይ ሊበለጽግ ይችላል። አንዱ ብሔር ከሌላው ብሔር ጥገኛ ይሆናል። ጥገኝነቱ ተደጋግፎን እና መሳሳብን ይፈጥራል። በመሳሳብ ሂደቱ ከሀገረ መንግሥት ግንባታ ወደ ብሔረ ሀገር ግንባታ ያደገ የሀገር ንድፍ ይበጃል። ኢትዮጵያም የሁሉም ብሔሮች ብሔራዊ ጥቅም ይሆናል።

ኢትዮጵያዊነትን በቂሶች እና በሸሆች ስብከት፤ በታዋቂ ሰዎች ዲስኩር፣ በፖለቲከኞች ተረት ብቻ መገንባት አይቻልም። ትልቁ አማራን ከኦሮሞ፣ ትግራይን ከደቡቡ፣ ሶማሌውን ከጉሙዝ እንዳይለይ አድርጎ የሚያገናኘው በመንገድ፣ በገበያ፣ በሥራ መጐዳኘት ሲችሉ ነው። መናኸሪያዎች፣ የኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የልማት ቀጠናዎች፣ ከተሞች… ለኢትዮጵያዊነት የቀረበ መንፈስ አላቸው። ምክንያቱም ደግሞ የገበያ ሁኔታው የደራ መሆኑ ነው።

በትክክል በኢትዮጵያ ነበረ የሚባለው የብሔር ጭቆና አልነበረም። የነበረው ድህነት ነው። ድህነቱ ሕዝቦች በመሠረተ ልማት እንዳይገናኙ አድርጎ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳቸው ባይተዋር አድርጓል። ለዚህም ይመስላል በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በኦጋዴን፣ በጋምቤላ…ነጻ አውጭዎች ዛሬም ድረስ የተሰማሩት። የዳር ሀገር ብሔረሰቦችን ከመሃል ሀገሩ ጋር የሚያገናኝ ልማት ባለመኖሩ የባህል ልውውጡን ገትቶታል።

በ1966 ዓ.ም. የተነሡት ብሔርተኞች ብሔራዊ ጭቆና አለ፤ ጨቋኙም አማራ ነው ብለው በስሕተት መተርጎማቸው የኢትዮጵያን

መሠረታዊ ችግር የሳተ ነበር:: ለዚህም ይመስላል፣ የብሔረሰብ ሕገ መንግሥት እና ተቋም ተገንብቶ እንኳን ብሔረሰቦች የበለጠ ወደ ፈተና የገቡት:: መፈናቀል እና የእርስ በእርስ ግጭቶች የናሩት፤ ስለብሔረሰቦች መሰበክ ከተጀመረ ወዲህ ነው:: አማራ ከፖለቲካው እና ከኢኮኖሚው ስለተገፋ የሌላው ብሔር ልማት የሚረጋገጥበት ምንም ዓይነት ተጠየቅ የለም::

በኢሕአዴግ የፖለቲካ ሥሪት መሠረት እኩልነት ማለት ሌሎች ብሔሮችን ከአማራ ጋር እኩል ማድረግ ማለት ነው:: እኩል ለማድረግ ደግሞ አማራውን ከእድገቱ ገድቦ በአማራው ድህነት ላይ ሌሎች ሀብታም የሆኑ በማስመሰል ድል እና ስኬቱን ይለካል:: አበበ ስለከፋው ቶላ የሚደሰትበት፣ ሃጎስ ስለተራበ ግዛቸው የሚጠግብበት፣ ቦንገር ስለሠራ ኡጅሉ የሚቦዝንበት.... የኢሕአዴግ የምቀኝነት የፖለቲካ መንፈስ አቻ አሸናፊነትን ስለማያመጣ ሀገርን አያድንም:: የኢሕአዴግ ሥሪት ከሥሩ ዋግ እንደመታው አገዳ ተቆርጦ ካልተጣለ በስተቀር ሁሉንም ሕዝቦች ሊያቀራርብ አይችልም:: ኢሕአዴግ የደመኛ ፖለቲካ አራማጅ ነው:: የኢሕአዴግ ተረከዝ መርዛም እና ሰርሳሪ በመሆኑ ደልዳላውን መሬት ሁሉ ገደል እያደረገው ነው::

በደርግ ጊዜ ኢትዮጵያ ትቅድም ተብሎ ስለዜግነት ፖለቲካ ተዘውትሮ ቢዘመርም፤ የብሔረሰቦች ጉዳይ ቸል የተባለ አልነበረም:: የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስትቲዩት ተቋቁሞ ብሔረሰቦች ተጠንተዋል:: ኢሕአዴግ የብሔረሰብ ጥናት ምንጬም ደርግ ነው[82]:: ክልል ለማዋቀር እንኳን በምንጭነት የተወሰደው የደርግ ጥናት ነበር:: ከደርግ በፊት በነበሩ ሰለሞናውያን ነገሥታትም፣ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች የኖሩት በራሳቸው መንገድ እንዲኖሩ ስለተፈቀደላቸው እንጂ ኢሕአዴግ በአዲስ የፈጠራቸው አልነበሩም::

[82]አቶ ታምራት ላይኔ፣ ዋልታ ቴቪ ጳጉሜ 1 ቀን 2011 ዓ.ም.

የዳግማዊ ምኒልክ ሀገር የማቅናት ጉዞ ልክ እንደ ፈረንሳይ የሀገር ምሥረታ ሆኖ ቢሆን በኢትዮጵያ አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ይኖር ነበር፡፡ በ1789 እ.ኤ.አ የተጀመረው የፈረንሳይ አብዮት በመቶ ዓመት በኋላ እንኳን የፈረንሳይኛ ተናጋሪው ብዛት ከ50 በመቶ የሚዘል አልነበረም፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት ፈረንሳይኛ ቋንቋ ሁሉንም ብሔረሰቦችን ውጦ አንዲት ፈረንሳይ የተባለች ብሔረ ሀገር እንድትመሠረት ሆኗል፡፡ ዐፄ ምኒልክ እና ተከታዮቻቸው አምባገነን እና ፍጹም አሐዳዊ ሆነው ቢሆን ኢትዮጵያ ፈረንሳይን የመሆን እድል ነበራት፡፡ ነገር ግን ዐፄ ምኒልክ ብሔረሰቦች በየአካባቢ ንጉሦቻቸው እርስ በእርሳቸው ለግድያ እና ለወረራ ሲፈላለጉ ከሁሉም በላይ ሆነው አስታራቂ ሆነዋል፡፡ ዐፄ ምኒልክ የሰፈር ንጉሦችን አሸነፈው ለአንዲት ሀገር እንዲገብሩ ባያደርጉ ኖሮ ንጉሦቹ እርስ በእርሳቸው መጫረሳቸው አይቀሬ ነበር፡፡ ንጉሦች በቀጥታ አቻ ሥጋት ሳይገባቸው ለማዕከላዊው መንግሥት ብቻ መገበራቸው ብሔረሰቦች በሌላ ብሔረሰብ እንዳይወረሩ እና እንዳይጠፉ[83] አድርጓል፡፡ የዐፄ ምኒልክ ሀገረ-መንግሥት ግንባታ እርሾ ባይሆን ኖሮ በኢሕአዴግ ዘመን ኢትዮጵያ የመፍረስ እድሏም ከፍ ያለ ነበር፡፡

ዐፄ ምኒልክ እንደ ጀርመኑ ኦቶቫን ቢስማርክ ‹‹ጀርመን በደም እና በብረት ትዋሐዳለች፡፡›› ብለው በሰዎች ደም ላይ ኢትዮጵያን ሊሠሩ አልተነሡም፡፡ እንደ ቢስማርክ ካቶሊክን ሃይማኖት የሀገረ መንግሥት ግንባታ ፈተና ናት ብሎ አንድን ሃይማኖት ወይም ነገድ ለይተው ሊያጠፉ አልተነሡም፡፡ ዐፄ ምኒልክ የሀገሪቱን አካላዊ ገጽ ካባጁ በኋላ፣ ሀገረ መንግሥታቸው ሕሊናዊ ቅርጽ ሊሰጡበት ያሰቡት በልማት ነው፡፡ ይህ ስኬታማ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ነው፡፡ በድሬዳዋ ጅቡቲ ባቡር ምሥራቁን የኢትዮጵያን ክፍል ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ እንዲገናኝ ሲያደርጉ፣ አሌክሳንደር ግርሃም

[83] አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ

ቤል የተባለ ሳይንቲስት በአሜሪካ ስልክን ከፈጠረ ከ17 ዓመት በኋላ ዐፄ ምኒልክ ፈጥነው ወደ ሀገራቸው አስገቡት። ፖስታ እና ጋዜጣም፣ ወፍጮ እና ተሽከርካሪ፣ ዋና ከተማ እና መንገድ አይደለም ከአፍሪካ ከዓለም ሀገራት ሁሉ ቀድመው ኢትዮጵያን ደረሱ። ልማት ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ሥጋ እና ደም ሆኖ የሚያቆም አምድ በመሆኑ የንጉሡ አካሄድ ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል። ሀገረ መንግሥት በመጀመሪያ በነፍጥ ከተገነባ በኋላ፤ በልማት ሕሊናዊ ቀለም ያገኛል። ልማት የቁስ አካል እና የመንፈስ ብልጽግና ድማሮ በመሆኑ የአንድ ሀገር ዜጎች በባህል እና በገበያ እንዲተሳሰሩ ያደርጋል።

ንጉሡ ነገሥቱ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ከውጭ ወራሪ ባያስጠብቁ እና በሀገር ውስጥ የውስጥ ሽኩቻን ባያጠፉ ኖሮ የዛሬዎቹ ብሔረሰቦች ህልውናቸው ገና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያከትም ነበር። ዐፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን የሠሩት የነበሩትን አፍረሰው ሳይሆን ያሉትን ሕዝቦች አጠናክረው እና አንድ ላይ እንዲኖሩ አድርገው ነው። በአንጻሩ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሀገረ መንግሥትነት ንዶታል። ብሔርተኝነትንም ደማዊ ዘረኝነት (primodial racism) አድርጎ ሠርቶታል። ድሀ እና በጥንተ ጋርዮሻዊው ግብርና የምትመራ ሀገር ውስጥ ብሔርተኝነትን በደም እና በጥላቻ ማንበር ሀገር የማጥፋት እርምጃ ተደርጎ ይወሰዳል።

በኢትዮጵያ የብሔርተኝነት ምንጩ ባህል ነው። ከትግራይ እስከ ኦሮሞ፣ ከአማራ እስከ ሲዳማ የሚቀነቀነው ብሔርተኝነት የባህል በመሆኑ የጋራ ሥነ-ልቦናን ለመገንባት ቀላል ነው። የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ወደ አገልግሎት እና ሸቀጥ ሲቀየር አክራሪ ብሔርተኝነት ይሟሟል። ግብርና በተቆራረጠ መልክዓ ምድር ስለሚከወን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማድረግ ዝግ ነው። ግብርናው ወደ ኢንዱስትሪ ሲሻገር ብዙዎችን በአንድ ላይ በሥራ እና በገበያ ስለሚያገናኝ የባህል ውሕደትን ይፈጥራል።

በሀገራችን ዘረኝነት እንጂ ዘር የለም። ዘር ከቆዳ ቀለም ጋር የሚገኝ ሥነ-ፍጥረታዊ ልዩነት ነው። እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ማርክስ ጋርቤ እና ማንዴላ... የተዋጉት ዘረኝነት እንጂ ባህል ላይ የተመሠረተውን ብሔርተኝነት አልነበረም። በደቡብ አፍሪካ በነጮች የነበረው ግልፅ አፖርታይድ የቆዳ ቀለምን መሠረት ያደረገ ነበር።

በኢትዮጵያ ያለው ብሔርተኝነት ቁስ ተኮር፣ ልሂቅ ሠራሽ ስለሆነ ወደ ዘረኝነት ቀረበ እንጂ የባህል መሆኑ በረከት እንጂ መርገም መሆን አይችልም። ነገር ግን በባሕልም ምክንያት የመጣውን የማኅበረሰባችንን ልዩነት ልሂቃን፣ ድሬድዋ ከተማን ለሶማሌ 40፣ ለኦሮሞ 40፣ ለሌላው ብሔር 20 የፖለቲካ ዕድል በመስጠት ግልፅ አፓርታይድ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሆኗል። በሐረርም የአደሬ 50፣ የኦሮሞ 50... የፖለቲካ ተሳትፎ እድል ይሰጣል። ሌላው ሁለት መቶ ዓመትም ይኑር የትነቱ ተጠንቶ በተወለደበት ቀየ ባይተዋር ይሆናል።

የምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል የጅቡቲም ሆነ የሶማሊያ ወደብ መናኸሪያ በመሆኑ የተሻለ የባህል ውሕደት ነበረው። ነገር ግን የባህል ውሕደቱን ለማጥፋት ብሔርተኝነት ዘረኝነት (Biolgy) ሆኖ ተዋቅሯል። አንድ አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ ኢትዮጵያዊ በክልሎች የመኖር ምቹ ሁኔታ የለውም። የአዲስ አበባ ልጆች ከኢትዮጵያ ይልቅ አሜሪካ ወይም አውሮፖ ቢሄዱ በተሻለ መንገድ ባለመብት ሊሆኑ ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያዊነት ዋጋ ቢስ ነው። ምናልባት ካገለገለ ወደ ውጭ ለመውጣት የይለፍ ወረቀት ለማግኘት ብቻ ነው። ሌላውን ነገር ባህል የለየውን ኅብረ ብሔራዊውን ሕዝብ ወደ ዘረኝነት አረንቋ ፖለቲከኞች ገፍተውታል። ለድብልቅ ማንነቶች እና ከተማ አካባቢ ላሉ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ለአናሳ ብሔረሰቦች የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት እጅጉን አስፈላጊ ነው።

የብሔር ፌደራሊዝሙ በኢሕአዴግ መንገድ ከቀጠለ ብዙ አነስተኛ ብሔረሰቦች ሙሉ በሙሉ ይዋጣሉ። ድርብ ማንነት ያላቸው ደግሞ በግለሰብነታቸው ስለማይታወቁ በተወለዱበት በሁለቱም ብሔር ታማኝነት አጥተው የሥነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ ይገባሉ። ለእንዲህ ዓይነቱ ሁነት ኢትዮጵያዊነት ማንነት ነው፤ ዜግነትም ነው። መዳኛውም የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ነው። ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚጋጩ ህልሞችን ለመፍታት በሚያስችል ሁኔታ ከተቀነቀነ ጉልበታም ሆኖ መውጣት ይችላል። የእስካሁኑ የኢትዮጵያዊነት አቀንቃኞች የዘውጌውን ተረክ አስማምተው እና ትክክለኛ ኢትዮጵያዊነት ለምን እና እንዴት የሚለውን ማሳየት እና መተግበር ስላልቻሉ ወድቀዋል።

እርስ በእርሳቸው በሚጣረሱ በሶሻሊዝም እና በካፒታሊዝም ጽንሰ ሐሳቦች የታጨቀው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም ኢትዮጵያዊነትን ክዷል። ከኢትዮጵያዊነት ጋር ሰውነትን ገድፏል። ኢትዮጵያን ከብተና አፋፍ ላይ አስቀምጧታል። ስለ ዴሞክራሲ ቢያወራም ዴሞክራሲን ለተቧደኑ ብሔሮች ብቻ አድርጎ አውጇል። አንድ አማራ በኦሮሚያ ክልል ምንም ዓይነት ዴሞክረሲያዊ መብት እንዳይኖረው አድርጓል። አንድ የትግራይ ሰው በኦሮሚያ ሂዶ መመረጥ ቀርቶ ባለሙያ ሆኖ ለመሥራት ሕገ መንግሥቱ አይፈቅድለትም። በተቃራኒውም ተመሳሳይ ነው። የመንቀሳቀስ ብሎም የመመረጥ እና የመወከል መሰል ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በተግባር ደረጃ ሕገ መንግሥቱ በፈጠራቸው የክልል መንግሥታት እና ሕገ መንግሥታቸው ገድበውታል።

እነሌኒን ወደ ሶሻሊስታዊ እና ኮሚኒስታዊ ማኅበረ ፖለቲካ ለመራመድ ማስጀመሪያ ምዕራፍ አድርገው ያሳደጉት አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሕገ መንግሥቱ የነፍስ አባት ሆኖ ተሰይሟል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሥልጣን በመጠቅለል እና አንድ አውራ

ፓርቲ በመፍጠር አገዛዙን በኢ-ዴሞክራሲ መንገድ የማስቀጠል ሂደት ነው። በአብዮታዊ ዴሞክረሲ ውስጥ ሥልጣን በኃይል ለማስቀጠል በሚደረግ ትግል ምክንያት ብዙዎች ተፈናቅለዋል፤ በርካቶች የሕይዎት ዋጋ ከፍለዋል። ብዙዎች ታስረው ግብረሰዶም እና የመንኮላሸት ነውረኛ ተግባር ተፈጽሞባቸዋል። ይህ ሁሉ ሕገ መንግሥታዊው ሥርዓቱ የፈጠረው በደል ነው። ዶክተር አብይ በፓርላማ በግልጽ እንደተናገሩት ‹‹ኢሕአዴግ መንግሥታዊ ሽብር ፈጣሪ ነው››። ኢሕአዴግን ወደ ማፍያ ቡድንነት የቀየረው ተረከዙን ያሳረፈበት ሥሪቱ ነው። የማፍያ እና ሃይማኖት የሚያራክሱ መጽሐፍትን በሚያነቡ ጸረ እሴት ሰዎች የተመሠረተው ኢሕአዴግ መንግሥት ሆኖም የመንግሥትነት ባሕርይ ከድቶታል።

በ1986 ዓ.ም. የሕገ መንግሥት ኮሚሽን ተብሎ 29 ሰዎችን ያቀፈ ስብስብ ተፈጠረ። የኮሚሽኑ ቃለ ጉባኤ እንደሚያሳየው አንድም ቀን 29 ሰዎች ተሟልተው ተገኝተው አያውቁም። በብዛት ከ50 በመቶ በታች አባላቱ እየተገኙ ሕገ መንግሥትን ያህል ሕሊናዊ ተቋም አርቅቀዋል። አቶ ታምራት ላይኔ ‹‹የሕገ መንግሥቱ ጉዳይ ዛሬ የያዘውን ቅርጽ እንዳይዝ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ አቶ ክፍሌ ወዳጆ ቅሬታቸውን ያቀርቡ ነበር። በተደጋጋሚ ቅሬታቸውን ለእኔ አቅርበዋል። እኔም ዘግይቶ እንደገባኝ ሕገ መንግሥቱ ሰውነትን የካደ እና የቆየውን የኢትዮጵያዊነት ትርክት የናደ ነው››[84] ሲሉ መስክረዋል። የሕገ መንግሥቱ ኮሚሽን ሰብሳቢ እንኳን በሕገ መንግሥቱ ልክነት አያምኑበትም ነበር።

ስለዚህ ሕገ መንግሥቱ በተወሰኑ ቡድኖች ፍላጎት በነዶክተር ፋሲል ናሆም ተረቆ፤ የወጣ ሰነድ ነው የሚለው የጥርጣሬ አስተያየት ሚዛን ይደፋል።

84 ታምራት ላይኔ፣ ናሁ ቴሌቪዥን ጳጉሜን 2 ቀን 2011 ዓ.ም.

29ኙ የሕገ መንግሥቱ ኮሚሽን አባላትም ሆኑ፤ 543ቱ የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ጉባኤ ተሳታፊዎች የራሳቸው ሐሳብ ያልነበራቸው፤ ቢኖራቸውም በሐሳባቸው በጥላቻ የሚፈረጁ ነበሩ። ለአብነት እነሻለቃ አድማሴ ዘለቀ[85] በሚያነሡት ሐሳብ ሁሉ ነፍጠኛ እና ትምክህተኛ እየተባሉ ጉባኤ አቋርጠው እስከ መውጣት ደርሰዋል። ፍረጃ እና አግላይነትን ኢሕአዴግ የወረሰው ከሕገ መንግሥቱ መንፈስ ነው።

ዶክተር ፋሲል ናሆም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ተግባራዊ ሳይሆን የቀረውን የአብዮቱ ዋዜማ ሕገ መንግሥት (1966 ዓ.ም.)፣ የደርግንም ሆነ የኢሕአዴግ በፍጹም ተቃርኖ ሥር ያሉ ሕገ መንግሥቶችን እንዳረቀቁ ይነገራል። ዶክተር ፋሲል በኢሕአዴግ ዘመን ለመጡ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሁሉ የሕግ አማካሪ ሆነው የዘለቁ መመሳሰል የሚችሉ የሕግ ሰው ናቸው[86]። ሕገ መንግሥትን የሀገር ህልውና እና መንገድ የሚወሰንበት የሕጎች ሁሉ ሕግ እንደዚህ በግለሰቦች እና በተወሰኑ ቡድኖች ፍላጎት መቀረጹ ሀገሪቱ የጸና መንግሥት እንዳታቆም አድርጓታል። ኢሕአዴግ አካታች መንግሥት የሆነ ፓርቲ ሳይመሠርት በውስን የፖለቲካ ልሂቃን ቁሞ የሀገሪቱን መንግሥታዊ እና ሕሊናዊ አፅማድ(ምሰሶዎች) እንዲያዘምሙ አድርጓል።

---

[85] ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ አዲስ አበባ በግል የገቡ የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ አባል ነበሩ። በወቅቱ ዛሬ የምናነሣቸውን ጥያቄዎች ቀድመው አንሥተው ነበር። የአማራ ግዛትን በተመለከተ በተለይ የወልቃይት አካባቢን አንሥተዋል። ከአማራ ክልል የተወከሉት ሳይቀሩ ነፍጠኛ እና ትምክህተኛ ብለው አሳቀዋቸዋል። የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ፣ የፌደራሊዝሙ አደረጃጀትን፣ የክልሎች አወቃቀርን፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን... በተመለከተ ንጥር ያለ ሐሳብ ይዘው ተከራክረዋል። ነገር ግን ነፍጠኛ እና ትምክህተኛ ተብለው ከስብሰባ ተማረው እስኪወጡ ተደርገዋል። የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሰ ሳይቀሩ ‹‹ነፍጠኛ ግዛቱ ዓይን በመለሰ ፈረስ በደረሰ እያለ ግዛት ማስፋት ይወዳል›› ሲሉ አማራን በተስፋፊነት ለመክሰስ ሞክረዋል።

[86] ተመስገን ደሳለኝ የፈራ ይመለስ እንዲሁም አሥራት አብርሃም የሕገ መንግሥቱ ፈረሰኞች በሚሉ መጽሐፎቻቸው ዝርዝር መረጃ አቅርበዋል። የሕግ ባለሙያው እና የፖለቲካ ተንታኙ ጋሽ አሰፋ ጫቦም በተለያዩ ጋዜ ዶክተር ፋሲል ናሆም የሦስት መንግሥታት የተለያዩ ዓይነት ሕገ መንግሥቶችን እንዳረቀቁ ጽፈዋል።

3.12 ኢትዮጵያዊነት ግን ምን ዓይነት ነው?

‹‹እኔ በዘሬ ትግሬ ነኝ፤ አንተ በዘርህ ጋሞ ነህ። በወሉ ቋንቋ-በሊንጓ ፍራንካው በአማርኛ ተግባባን። ዕድሜ ለሸዌው ምኒልክ እና ጦረኞቹ። ጣፋጭ የእንቁላል ቂጣ ለመሥራት እንቁላሎችን መስበር ግድ ነው። ሀገር ለመገንባትም የነገዶችን እና የጎሳዎችን እንቁላል መስበር ግድ ነው። ምኒልክ ይሄን አደረገ። ምክንያቱም ዘመኑ አዘዘው።›› (ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ደራሲ ዘነበ ወላ በማስታወሻው እንዳሰፈረው።)

ከዓለም ቀድማ ሀገረ መንግሥትን ያጸናች የአፍሪካውያን የሥልጣኔ ምንጭ ናት። የሥነ መንግሥት ጊዜዋም ከ3 ሺህ ዘመን ይልቃል። በዘመናት ውስጥ ፖለቲካው እንደ አየር ሁኔታ መቀያየሩ ግድ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ግን እንዳለች አለች። እንዲያውም በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ **ነብር ዥንጉርጉርነቱን፣ ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም** የተባለላት የሃይማኖት ሀገር ናት። ክርስትናን ከዓለም ቀድማ እንደተቀበለችው ሁሉ፣ እስልምናንም በኩር ሆና ተቀብላ ሃይማኖቶችን አስማምታ ዘመኗን ኑራለች። ክርስቲያኖች የእስልምና ወኪሎችን በፍቅር የተቀበሉባት የዓለም ልዩ ኅብራዊ ሀገር ናት። በዘመኗ ከአክሱም እስከ ላሊበላ፣ ከሐረር እስከ ጐንደር የተዘረጋ የሥልጣኔ አሻራዎችን አስቀምጣለች።

ሕዝቦቿም ከአድዋ እስከ ቅርቡ የኢትዮ-ኤርትራው ጦርነት ድረስ አብሮነት የታተመበት የጋራ ሞትና ድልን ተጋርተዋል። ኢትዮጵያ በራሷ ቀለም ዘመን ከመስፈር አልፎ፣ ለአፍሪካ ብሔርተኝነት የነጻነት ትግልም መነሻ ናት። በዚህ ሁሉ የታሪክ አንጓ፣ በኢትዮጵያ የተሠሩ ታሪኮች የጋርዮሽ እንጂ የአንድ አካባቢ በንጥልነት የሚቆም አይደለም። የጣሊያን ወረራን ለመመከት የወጣው የአርበኛ መጠን እንደ አካባቢው ሁኔታ ይለያይ እንጂ በብዛት የሁሉም አካባቢ ሕዝብ ለኢትዮጵያዊነቱ ደሙን ገብሯል።

ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያዊያን የጋራ ትዝታ ጥሎ አልፏል፡፡ ትዝታ ታሪክ ነው፡፡ ሀገር በጋራ በሚኮራበት ታሪክ ይመሠረታል፡፡

ዘመናዊው የኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ፕሮጀክት በዳግማዊ ቴዎድሮስ ተነድፎ፣በዐፄ ምኒሊክ አካላዊ ውቅሩ ቁሟል፡፡ አካላዊ ውቅሩ እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ብሎም በደርግ ቀጥሏል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ አካላዊ ውቅር በዘመናዊ ታሪኳ በዳግማዊ ምኒልክ ቢቆምም አስተኔ ብልቶቿ ተሰካክተው አይፈርሴ ሆነው ሥርዓታዊ መዋቅራቸው አልተሠራም፡፡ ሀብታሙ አለባቸው ታላቁ ተቃርኖ ባለው መጽሐፉ ‹‹የዳግማዊ ምኒልክ አካላዊት ኢትዮጵያ በወራሾቻቸው ሥጋ እና ደም እንዲያወጣ አልተደረገም›› ይላል፡፡ በእርግጥም ሀብታሙ እንደሚለው የኢትዮጵያ ብልቶች ሳይዛነፉ ተተክለው የአንዱ መጓደል ሙሉ ሥርዓተ አካሉን እንደሚያናጋው ታውቆ አልሰረጸም፡፡ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት በግዛታዊ አካላዊነት የቆመ እንጂ አካሉ ከሕሊናዊ እሳቤ ጋር አልተሳሰረም፡፡ ኢትዮጵያ በግዛት ደረጃ በአራቱም ማዕዘን አጽመ ቅርጽዋ ቢነደፍም፤ ሀገሪቱን ጭንቅላት አድርጎ የሀገሪቱ አስተኔ ግዛቶች(ብልቶች) ኢ-ተነጣጣይ አድርጎ ብሔረ ሀገር ለማድረግ ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ እክል ገጥሞታል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ክፉኛ የተናጋው ከ1966ቱ[87]

---

[87]ከአክሱም እስከ ዳግማዊ ምኒልክ በተዘረጋው የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ውስጥ የ1966ቱን የፖለቲካ ኃይል በሦስት አተያዮች መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በተገጣጣሚነት(thesis) የሚታይ ሲሆን፤ በዚህ ዝርዝር ውስጥ የአማራው የፖለቲካ ኃይል ሊመደብ ይችላል፡፡ አማራ ከአክሱም እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ኢትዮጵያን በማቆም ተሳትፌአለሁ ብሎ ስለሚያስብ ኢትዮጵያዊነት ለአማራው ግጥሙ ነው፡፡ አማራነት እና ኢትዮጵያዊነት እርስ በእርሱ ተገጣጣሚነት አለው፡፡ ሁለተኛው አተያይ ኢ-ተገጣጣሚነት (anti thesis)ነው፡፡

ኢትዮጵያ የተሠራችበት መንገድ በምንም ሁኔታ ከእኔ ባህል እና እሴት ጋር አይሄድም ብሎ ከማሰብ ይመነጫል፡፡ በኢትዮጵያ የሥነ-መንግሥት ምሥረታ የእኔ ሱታፌ የለም ከሚል ብያኔ ይነሣል፡፡ የኦሮሞ ፖለቲካ በአመዛኙ ለኢትዮጵያዊነት ኢ-ተገጣጣሚ ሆኖ

ተቀንቅኗል። ኦሮሞነት እና ኢትዮጵያዊነት ቤት እንዳይመቱ ሆነው ተሰናኝተዋል። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ታሪክ የገዘፈ አሻራ ያላቸው ኦሮሞዎች ለኦሮሞ ምልክት መሆን አልቻሉም። ምክንያቱም የኦሮሞ ፖለቲካ ትናንት አልባ ሆኗል። በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ የትናንት ትዝታ የለም። አለ ከተባለም የገዳ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓትም ከኦሮሞነት አድማስ ተሻግሮ ለመላው ኢትዮጵያ እንዲውል የኦሮሞ ፖለቲካ አይመችም። ከኢትጵያ ጋር ትዝታ አልባ ሆኖ ስለተቀነቀነም ከትናንት ይልቅ ነገ ላይ ኦሮሞ የተባለ ዜግነት እና ማንነት ተፈጥሮ ማየት ላይ አተኩሯል። የኦሮሞ ፖለቲካ ትዝታ ነገ ነው። ትናንቱን ሰርዟል። በትናንት ውስጥ የነበሩ የኦሮሞ ጀግኖች እነ አብዲሳ አጋ፣ እነ ጀኔራል ጃጋማ ኬሎ… በኦሮሞ ፖለቲከኞች ዘንድ እንደ ጀግና አይታዩም። ለኢትዮጵያ ብዙ አስተዋጽኦ ያደረገ ኦሮሞነትን እንደተጻረረ ይተረጎማል። ይህ ሁሉ የሚመነጨው ከኢ-ተገጣጣሚነት የፖለቲካ ትርክት ነው።

ሦስተኛው የሀገረ መንግሥት አተያይ ከፊል ኢ-ተጋጣሚነት (synthesis) ነው። የተደባለቀ አተያይ የሚበየንበት ሲሆን፣ በግማሹ የሀገር ግንባታ ተስማምቶ በሌላው አለመስማማት ማለት ነው። በዚህ ውስጥ ከሕወሓት የሚነሣው የትግራይ ፖለቲካ ይጠቀሳል። 1ኛው እስከ 10ኛው ያለውን የአክሱም ዘመን የትግራይ የፖለቲካ ኃይሎች በበጎነት ይመለከቱታል። ከጎንደር ስልጣኔ መዳከምን እና የዐፄ ቴዎድሮስ አነሣስን ተከትሎ እስከ ዐፄ ዮሐንስ ዘመን ያለውን ሀገር የመገንባት ሂደት በበጎ ጎኑ ይመለከቱታል። በዚህ ውስጥ የትግራይ ባህል በኢትዮጲያዊነት እንደተካተተም ያትታሉ። የትግራይ የፖለቲካ ኃይሎች ከአማራ የፖለቲካ ልሂቃን ጋር ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ተገጣጣሚ እይታ አላቸው። ለዚህም ይመስላል እነ ዋለልኝ መኮንን አማራ እና ኢትዮጵያን የገኘ መደብ አካል አድርገው የወሰዱት።

ነገር ግን ሕወሓት ይሄን ሂደት በ1967 ዓ.ም. ገልብጦ ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ኢ-ተገጣጣሚ አተያይ ይዞ መጣ። የሕወሓት የኢ-ተገጣጣሚነት ሃልዮቱ የሚጀምረው ዳግማዊ ምኒልክ ትግራይን ጨቁኗል ከሚል የታሪክ ትርጓሜ ነው። ስለዚህ ሕወሓት ለኢ-ተገጣጣሚ እይታው ይበጀው ዘንድ የኢትዮጵያን የሀገረ መንግሥት ግንባታ ከዐፄ ዮሐንስ በኋላ ጀመረው። ከዐፄ ምኒልክ እስከ ደርግ ያለውን ጊዜ በኢ-ተገጣጣሚነት ይመለከተው እና ይህን ዘመን በሙሉም ለአማራው ይሰጣል።

ኢትዮጵያ የአማራው መጨቆኛ ናት የሚለው የኢ-ተገጣጣሚነት የሀገራዊ ተረክ ለሕወሓት ኦነግንም ከጎኑ አሰልፎለታል።

ስለዚህ ከትግራይ እና ከኦሮሞ የሚነሣ ፖለቲካ በሀገረ መንግሥት ግንባታው ኢ-ተገጣጣሚ አተያይ ስላላቸው በዓላማ ተገጣጣሚ ናቸው። በአማራ ላይ የተፈጠረው የጥላቻ መንስኤ የሚመጣውም ከዚህ ሀገረ መንግሥትን ከመቀበል እና ካለመቀበል ከሚመነጭ የፖለቲካ አሰላለፍ የተነሣ ነው። በዚህ ፖለቲካዊ አተናተን ምክንያት አማራው ሀገራዊ የትናንት ትዝታውን እያደመጠ ነገን ረስቷል፣ ኦሮሞው የትናንት ትዝታውን የሐዘን እንጉርጉሮ አድርጎ ነገውን በኢትዮጵያ ላይ አጨልሟል። ፖለቲካው ከትናንቱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከዛሬውም ጋር ተገጣጣሚ ባለመሆኑ የነገ የጋራ መንገድም የለውም። ስለዚህ ኢ-ተገጣጣሚ ኃይላት የሀገሪቱን ቀለም ከራሳቸው ጋር እንዲጋጠም ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት አቻ አሸናፊነት እንዳይኖር አድርጓል።

ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ባለው የመንግሥትነት ጉዞ ውስጥ ደግሞ ነገሩ ተገልብጧል። የአማራ የፖለቲካ ኃይል ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ሀገር የመገንባት ሂደት በተቃርኖአዊ በኢ-ተገጣጣሚነት ቆሟል። ሕገ መንግሥቱንም ሆነ ሕገ መንግሥቱ የፈጠራቸውን ተቋማት እና አደረጃጀቶች አማራው አይቀበልም። በሌላ በኩል የትግራይ እና የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች ከ1983 ዓ.ም. በፊት በነበረው ሀገር የመገንባት ሂደት ውስጥ በኢ-ተጋጣሚነት ቆመው ስለነበር በዚህኛው ደግሞ በተጋጣሚነት ቆመዋል። ለዚህም ሁለቱም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ እና የፌዴራሊዝም ውቅሩ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ።

ነገም ይሄ የሚጋጭ ሕልም ሁሉንም በተቀራራቢነት ለማግባባት እና የብሔረ ሀገር ግንባታውን ስኬታማ እንዳይሆን ያደርጋል። በእርግጥ ኢትዮጵያ በቅርብ ብሔረ ሀገር የመሆን እድሏ ለዜሮ የቀረበ ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከቀጠለች ሀገረ መንግሥታት የመሆን እድል ይኖራታል። ብሔረ ሀገር በብዛት ተቀራራቢነት ካለው የሕዝብ ስብጥር የሚሠራ ነው። ልክ እንደ ጃፓን፣ ቻይና፣ ኮርያ..ማለት ነው። እነዚህ ሀገራት አንድ በላጭ ብሔር ስላላቸው ሀገረ መንግሥቱ ከብሔሩ ተገንብቷል።

እንደ አሜሪካ ያሉ ሀገራት ደግሞ የሀገረ መንግሥታት ቅርፅ ይዘው ተመሥርተዋል። በተለያየ ተዋረድ ያሉ መንግሥታት በአሜሪካ ጥላ ሥር ተሰባስበው ሀገር መሥርተዋል። በኢትዮጵያም ብሔሮች ንዑስ መንግሥት ሆነው በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባስበው ሀገረ መንግሥት ሊገነቡ ይችላሉ። የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ተራክቦው እያደገ ከሄደ ንኡስ መንግሥታት ጥላ በሆነው ሀገራዊ መንግሥት እየቀለጡ ዜግነት ትልቅ ማንነት ይሆናል። ኢትዮጵያዊነት የተለያዩ ማንነቶች ውጦ ራሱ ማንነት ሆኖ ሊወጣ ይችላል። በእነ ዐፄ ምኒልክ እና ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የተጀመረው የመንግሥት ግንባታ ኢትዮጵያዊነትን የጋራ ዜግነታዊ ማንነት አድርጎ መጥቶ ነበር። ዜግነታዊ ማንነቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፣ በአማራ እና ትግራይ የተሠራ ነው በሚል ብዙዎች ከኢትዮጵያዊነት እየሸሹ የራሳቸውን ቋንቋ ወለድ ከባቢያዊ ማንነት ለማሳደግ ታገሉ።

ማንነት በብዙው በመወለድ ሳይሆን በመልመድ ይገኛል። መልመድን ደግሞ ፖለቲከኛው በሚመቸው መንገድ ይፈጥረዋል። በኢትዮጵያ ያሉ ማንነቶችም በፖለቲካ ልሂቃን ለፖለቲካው አትራፊ እንዲሆኑ ሆነው የተሠሩ ናቸው። የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው አቶ ክርስቲያን ታደለ ‹‹ ሕይዎት የፖለቲካ ድርሰት ናት›› የሚል አነጋገር አለው። በእርግጥም ማኅበረሰብ ዓለምን የሚያይበት መነጸር እና የአኗኗር ዘይቤው የሚቀረጸው በፖለቲካ ነው። በምድር ላይ የመኖር ጣሪያ፣ የመወፈር እና የመክሳት፣ ንጹህ አየር የማግኘት እና ያለማግኘት… ወዘተ በፖለቲካ የተወሰነ ነው።

የጃፓን ፖለቲካ ለሥራ ምቹ ሆኖ ዜጎችን ባለሀብት አድርጓል። ውኃማ አካሎቻቸውን ለአሳ አድርገዋል። ስለዚህ የጃፓናውያን እድሜ ጣሪያ ከዓለም ረጅሙ ሆኗል። በሌላ በኩል በፖለቲካ ብልሽት ምክንያት በበሽታ፣ በርሀብ፣ በጦርነት፣ በስደት… ዘመናቸውን የሚገፉት አፍሪካውያን በመሬት የመኖር ጣሪያቸው ዝቅተኛ ነው። ይሄ ሁሉ የፖለቲካው ውጤት ነው።

በኢትዮጵያም የተስተካከለ ፖለቲካ ከተዘረጋ አይደለም የማንነቶች ኅብረት፤ ሕዝቦች በአካላቸው ሳይቀር ለውጥ እንዲያመጡ ያስችላል። ፖለቲካው ከተስተካከለ ቀጭኑ ወፍሮ፤ ደካማው ይጠነክራል።

መታጠፊያ ዘመን በኋላ ነው፡፡ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ለነፍጠኞችና ለትምክህተኞች ብቻ ተሰጠ፡፡ ትምክህተኛ እና ነፍጠኛ ያልሆነ መደብ ወይም ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን ሊላበስ እንዳይችል ተደርጐ ተሰበከ፡፡ ኢትዮጵያ የአማራ መጨቆኛ ተደርጋ ተሳለች፡፡ በዚህ እሳቤ ቀድማ ተረከዟን ያስገባችው ጣሊያን ናት፡፡ አማራነት ከአካባዊ ግዛትነት አልፎ ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥትነት ሕሊናዊ እሳቤን ይሰጣል፡፡ ይህ ሕሊናዊ (መንፈስ) ተሳካክቶ በአንድ ኢትዮጵያዊነት የውጭ ወረራን ከጥቁር መደብ ልቆ መከላከል ተችሏል፡፡ አማራን መምታት የኢትዮጵያን ሕሊናዊ እሳቤ አላልቶ በአካላዊ ቅርጽዋ ብቻ እድትቆም ያደርጋል፡፡ በአካላዊ ቅርጹ ብቻ

ኢሕአዴግ የተከለው የብሔር ፌደራሊዝም በጥላቻ እና ያለምክንያት ስለሆነ በኢሕአዴግ ዘመን የተፈጠረ የፖለቲካ ኃይል በብዛት ምክንያት አልባ ሆኗል፡፡ በ2011 ዓ.ም. አባባ ታምራት ገለታ የተባሉ የታወቁ ጠንቋይ ከእስር ተለቀቁ፡፡ ከተለቀቁ በኋላ ያስጠቃኝ እና የታሰርኩት በጠንቋይነቴ ሳይሆን በኦሮሞነቴ ነው ሲሉ ምክንያት ፈጠሩ፡፡ ውስን የኦሮሞ ፖለቲካ ልሂቃንም ጠንቋዩ በኦሮሞነታቸው እንደታሰሩ እያሰቡ እንደ ጀግና ቆጥረዋቸዋል፡፡ በ2010 ዓ.ም. በሕወሓት ታስረው የነበሩ ኃይሎች ሁሉ በብሔራቸው እየተጠሩ እንደ ጀግና ተቆጥረዋል፡፡ ሰርቆ የታሰረውም ሆነ በሌላ መደበኛ ወንጀል የታሰረው ሁሉ በመንጋ ድጋፍ ጀግና ተብሎ ተወድሷል፡፡ ከፖለቲካ ታሳሪዎች እና ከመብት ታጋዮች በላይ በስርቆት እና መሰል ጉዳዮች የታሰሩት ክብር አግኝተዋል፡፡ የብሔረሰባዊ ፖለቲካ አስተሳሰብ አንዱ ችግር ምክንያት እና ሐሳብ አልባ ሆኖ ሕዝብን ወደ መንጋነት መቀየሩ ነው፡፡ በብሔረሰባዊ ፖለቲካ ዘንድ በሐሳብ እና በችሎታ መመራት የለም፡፡ አንድ የትግራይ ሰው በጎበዝ አማራ ከሚመራ ይልቅ በሰነፍ ትግሬ መመራትን ይመርጣል፡፡ አንድ አማራ በሚችል ኦሮሞ ከሚመራ ይልቅ በሰነፍ አማራ ቢመራ የተሻለ መስሎ ይታየዋል፡፡ ብሔረሰባዊነት በዘር ጥራት እንጂ በሐሳብ ልዕልና አይገዛም፡፡

አጠቃላይ በኢትዮጵያ ብሔረሰባዊነት የተተከለበት መንገድም በውሸት ስለሆነ የብሔረሰባዊ ፖለቲካ ትክክል እና አስማሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ከ80 ብሔሮች መካከል ከአስር የማይበልጡት ብቻ ክልል ሆነው ሌሎቹ ከ70 በላይ በሌላ ብሔራዊ ክልል ሥር መተዳደራቸው እየቆየ ምቾት ይነሳቸዋል፡፡ ብሔረሰቦች ሀብት የሚመጣ በመሥራት ሳይሆን የራስ አስተዳድርን በመዘርጋት ይመስላቸዋል፡፡ የድህነታቸው ምንጭም ብዙ ብሔሮች አማራ ወይም ሌላ ብሔር ይመስላቸዋል፡፡ የብሔር ፌደራሊዝም ወቃሽ እና በተበዳይነት ላይ የተንጠለጠለ ስለሆነ አላግባብ መደገፍ እና መቃወም ይበዛበታል፡፡ የኢትዮጵያ የብሔር ፌደራሊዝም ፖለቲካ የሰው ልጅን አስተሳሰብ ሁሉ የገደለ ነው፡፡ የምክንያትን ጉልበት ሁሉ ሰብሮ የሰውን የማሰብ ልዕለና ገፏል፡፡ የግለሰብ ዓለምን አጥፍቶ የመንጋዊነት አስተሳሰብን ስላነበረ የግለሰቦች ፈጣሪነትን ቀንሷል፡፡

በቆመ ሀገር ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ለሀገሩ ቀናኢ ስለማይሆን የተገዥነት ሥነ-ልቦናን ያዳብራል፡፡ እምቢ ለሀገሬነት ይሟሸሻል፡፡ ይሰለባል፡፡

ከአድዋ ድል በኋላ፣ የኢትዮጵያን ቅቡልነት ለማሳነስ በአውሮፓ መድረክ ኢትዮጵያ ተብላ እንዳትጠራ ጣሊያን ታግላለች፡፡ የውጭው ዓለም በጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ምክንያት ኢትዮጵያ ሳይሆን አቢሲኒያ የሚለውን ስም ለመጠቀም መርጦ ቆይቷል፡፡ አቢሲኒያ ከሰሜን ኢትዮጵያ ከአማራነት እና ከአማራ ትግራይ ግዛት ጋር ይያያዛል፡፡ ከአቢሲኒያ ውጭ ያሉ ሕዝቦች በአማራ ቅኝ ግዛት የተያዙ እንጂ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም የምትለዋ ጣሊያን፤ በኢትዮጵያ ግዛት ሥር ከአማራ ውጭ ያሉ ሕዝቦችን ነጻ ለማውጣት በሚል በ1928 ዓ.ም. ዘምታ ሳይሳካላት ቀርቷል፡፡ ከነጻነት በኋላ፣ በ1944 ዓ.ም.[88] የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል በሁሉም የዓለም ክፍል ማንም ኢትዮጵያ እንጂ አቢሲኒያ ብሎ በሚዲያም ሆነ በደብዳቤ እንዳይጽፍ አገደ፡፡

በጣሊያን እርሾ በሀገር በቀል ብሔርተኞች በተቦካው ፖለቲካ ምክንያት የኢትዮጵያ ታሪክ የወራሪ እና የተወራሪ፣ የቅኝ ገዥ እና ተገዥ፣ የአሸናፊ እና የተሸናፊነት ሆኖ መቀንቀን ጀመረ፡፡ ጫፍ ረገጥ የሆኑ ተረኮች ተዛናፊ ፖለቲካን ፈጠሩ፡፡

በተዛነፈው ፖለቲካ ምክንያት ጣሊያን በኢትዮጵያ ያደረሰውን ወረራ እና የኢትዮጵያን ድል ከሚያመለክቱ ሀገራዊ ታሪኮች ይልቅ ደርግና ብሔርተኛ አማፂያን ስላደረጉት የእርስ በርስ ትግል በመስበክ፣ የአማፂያኑን አሸናፊነት የሚያሳይ ሐውልት በየአካባቢው ተተከለ፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ ሀገር ለመገንባት ያደረጉትን የማቅናት ጉዞ ከወረራ ጋር ተያይዞ በስሑት የታሪክ ብያኔ የምኒልክ የጡት

[88]ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ፣ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንደኛ መጽሐፍ ፣ 1996 ዓ.ም.

ቆረጣ ሐውልቶች ቆሙ፡፡ የኢትዮጵያን የአብሮነት ትዝታ በግድያ እና በብቀላ የተሞላ ሆኖ ተቀረፀ፡፡ ለሀገረ መንግሥቱ ግንባታ መሀንዲስ የሆኑትን ዳግማዊ ምኒልክ፣ አማራ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ ወራሪ ኃይላት እስከ ሀገር ውስጥ ምክንያት አልባ ብሔርተኞች ጠላት ተደርገው ተፈረጁ፡፡ ዓላማውም ኢትዮጵያን ማኮሰስ እና ማጥፋት ነው፡፡ በዚህም የጋራ ዋና ከተማ፣ ታሪክ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ሃይማኖት፣ ርዕይ ነጥፏል፡፡

ጫፍ ረገጥ የታሪክ አረዳዶች ባሉበት ሀገር ውስጥ የዜግነት ፖለቲካን ማቀንቀን ከባድ ያደርገዋል፡፡ ዜግነታዊ ማንነት ዋጋ ስለሚያጣ ዘውጋዊ ብሔርተኝነት ይሰፋል፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትንታኔ ከጎረቤት ሀገራት እና ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተፋትቶ ክልል ከክልል ጋር መንደራዊ ንጽጽሮሽ ላይ የተመሠረተ ሆኗል፡፡ ብሔራዊ ክልልን የሁሉ ነገር ማንጸሪያ አድርጎ ፖለቲካ ኢኮኖሚን መተንተን እየጎለበተ ከሐደ ክልሎች ከኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ በአካል ሊነጠሉ ይችላሉ፡፡ በመንፈስ ከተነጠሉ ቆይተዋል፡፡ ብሔራዊ ክልሎች ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጋር ሕሊናዊ ፍቺ ፈጽመዋል፡፡ አማራ፣ በከፊል ትግራይ፣ ጉራጌ እና ሌሎች መሰል ብሔሮች የኢትዮጵያን ብሔረ ሀገርነት ተቀብለው ኢትዮጵያዊነትን እንደማንነት እና ሌሎች አስተኔ ግዛቶችን እንደ አንድ የሀገር ብልት የመቁጠር አዝማሚያ አዳብረው ነበር፡፡ ዳሩ ግን አሁን ሁሉም ብሔሮች ኢትዮጵያን እስከ አካሏ ሸሽተው ግዛተ ክፍሎቿን መንግሥት ለማደረግ እየተሯሯጡ ነው፡፡

ዳሩ ግን በኢትዮጵያ በኢኮኖሚ እና በወሰን ራሱን የቻለ ልዩ ብሔር የለም፡፡ ለምሳሌ ኦሮሞ ቢገነጠል ድንበሩ የት እንደሚሆን ግልጽ አይደለም፡፡ ሕወሓት ለመገንጠል ቢያስብ ወልቃይት እና ራያ ላይ ፈተና ይገጥመዋል፡፡ ሶማሊያም በድሬድዋ እና በሞያሌ

አካባቢዎች ላይ ልይ(የተለየ) መስመር የለውም:: ዐፄ ምኒልክ ሀገራትን ሳይሆን ጎሳ እና ነገዶችን ቀላቅለው ሀገር ሰርተዋል:: ነገር ግን የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት እንደሚለው ራሳቸውን የቻሉ ብሔሮችን(ሀገሮችን) አፍርሰው ወይም ወረው ሀገር ስላልሠሩ ልይ ብሔር የለም:: በኢትዮጵያ ብሔሮች ቢገነጠሉ እንደ ሶቭየት ኅብረት መገነጣጠል እንኳ አንጻራዊ ሰላም አይሆንም:: ቀድሞም ወጥ ብሔሮች አልነበሩምና:: ብሔሮች የራሳቸው አስማሚ ድንበር እና ልይ ባህል የላቸውም:: የዛሬው የክልል አስተዳደር የተወሰነው 67 በሚደርሱ ፖለቲከኞች እንጂ በሳይንሳዊ ጥናት እና በሕዝብ ፍላጎት አይደለም::

ይህ ሆኖ እያለ ግን፣ አንድ የአማራ ወይም የኦሮሞ አሊያም የትግራይ ብሔርተኛ ፖለቲከኛ ፖለቲካን የሚተነትነው ከኬንያ ወይም በ60 ዓመት ውስጥ ብቻ የዓለም ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ሀገር ስለሆነችው ደቡብ ኮርያ ሳይሆን ከአማራ፣ ከትግራይ እና ከኦሮሞ አንጻር ነው:: አማራን አንገት ማስደፋት ለሕወሓት ስኬት ሊሆን ይችላል:: ኢትዮጵያን ኦሮሞ ማድረግም ኦነግ ቀመስ ለሆነው የኦሮሞ ፖለቲካ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ይህ ዓይነት የፖለቲካ መለኪያ ሽቅብ የሚገፋ ሳይሆን ቁልቁል እያንደረደረ ወደ አዘቅት የሚከት ነው::

በኢትዮጵያ ያለው ዘውግ ተኮር ፖለቲካ የሀገር መንፈስን ቀብሮ ሌላ ሀገር ለመፍጠር የሚደረግ እሽቅድድም ነው:: ለሁሉም የፖለቲካ ልሂቃን ቢያንስ በተቀራራቢነት የሚስማሙበት ታሪክ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ሀገራዊ መንፈስ፣ የፖለቲካ ተረክ… የለም:: ስለዚህ በዘውግ በተተከለው ፖለቲካዊ መንፈስ ውስጥ ኢትዮጵያ የለችም:: ኢትዮጵያን የሚመራው ኢሕአዴግም ኢትዮጵያዊነትን መወከል አይችልም::

ኢሕአዴግ ከ1983 እስከ 2010 ዓ.ም. አጋማሽ የሕወሓት ሥሪት ሆኖ ተጓዘ። ከመጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ወደ ኦዴፓ አዘንብሏል። ስለዚህ ኢሕአዴግ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያግባባ እና አመዛዝኖ የሚመራ ድርጅት ለመሆን የፖለቲካ ተረኩ አልፈቀደለትም። ኢሕአዴግ የግንባር ግጥምጥሙን አዋሕዶ ሥርዓተ አካል አድርጎ ለመዋሐድ የሚከብደውም ሁሉም የብሔር ወኪሎች የሚጋሩት ሀገራዊ ሕልም ስለሌለ ነው። ኢሕአዴግ ገና ከሥሪቱ ስሕተት ስለሆነ፤ በሀገረ ግንባታው ላይ ትክክል የመሆን እድል የለውም።

ኢሕአዴግ አይደለም ሀገረ መንግሥቱን ሕሊናዊ ቅርጽ ሊሰጠው፣ አካላዊ መዋቅሩንም እንዳያጣ ያሰጋል። ኢሕአዴግ ከኢትዮጵያ አንድ አካል የነበረችውን ኤርትራን መሸረፉ፤ የኢሕአዴግ አያያዝ ከሕሊናዊ ትስሥር አፋትቶ ወደ አካላዊ ልይይት የሚገፋ መስመር እንደሚከተል አስረጅ ነው።

ሀገረ መንግሥት በአካላዊ ቁመናው ፀንቶ በሕሊናዊ ሥርዓቱ ይጠብቅ ዘንድ በመልክዓ ምድር የተራራቁት በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ በባህል እና ቋንቋ አጥር የፈጠሩት ደግሞ የጋራ ገበያ በሚፈጥረው ኢኮኖሚ ሊቀራረቡ ይገባል። ሀገር ሕሊናዊ እና አካላዊ ገጽታው የሚሰፋው እና የሚጠገነው በገለልተኛ ተቋማት በሚፈጠር ልማት ነው። ያለልማት ዴሞክራሲም ሆነ የሰብአዊ መብት ከበራ ሊሰፍን አይችልም። ልማት የሀገርን አካላዊ አጽመ ቅርጽ ወዝ ይሠጣል። ልማቱ ግን በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ፍትሃዊ እና የኩርፊያ መንገዶችን ያጠበበ መሆን ይገባዋል። ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያ በተመሳሳይ መስመር ዴሞክራሲ እና ልማት ያስፈልጋታል የሚባለው። ይህ ከሆነ በባሕልም ሆነ በቦታ የተራራቁት ሁሉ በገበያ ተገጣጣሚ ሆነው ሀገረ መንግሥት

ግንባታው ተቃንቶ ወደ ብሔረ መንግሥት ውቅር ከፍ ሊል ይችላል፡፡

ኢሕአዴግ ሲያራምደው የቆየው ልማታዊ ዴሞክራሲ ከስም አጠራር አለማለፉ እንጂ በንድፈ ሐሳብ እንዳለው ልማትን እና ዴሞክራሲን በትይዩ ማስኬድ ከተቻለ ወደ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለማምራት እንደሚበጅ አያጠራጥርም፡፡ ነገር ግን ልማቱም ሆነ ዴሞክራሲው የሚመጣበት ተቋም እና ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ የኢሕአዴግ ሥርዓታዊ ውቅር ታሪክን ለማረም እና ተረኛ ለመሆን የተመቸ ነው፡፡ ተረኝነትም ሆነ ያለፈን ታሪክ ለማረም መሞከር ዴሞክራሲንም ሆነ ልማትን ያቀጭጫል፡፡ ምኒልክ ወይም መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ያቆሙትን ታሪክ ለማረም መንቀል የረገጡትን መልሶ ከመርገጥ ያለፈ ወደ ነገ አያሳልፍም፡፡ የኢህአዴግ መንግስታዊ ውቅር በይዘት ደረጃ በዐፄ ምኒሊክ ቅኝ ገዥነት እና በአኖሌ የነጻነት ምልክትነት የቆመ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ከዚህ አንጻር አማራ በሀገረ መንግሥቱ ግንባታ ያሳረፈውን አሻራ በማጥፋት የራሱን ቀለም ለመድፋት ታሳቢ አድርጓል፡፡ ይህ የጥላቻ ስምምነት ልማትንም ሆነ ዴሞክራሲን ሊወልድ ስለማይችል በአንድ ሀገር ውስጥ ሆነው ፍጹም የማይግባቡ እና የማይናበቡ ደመኛ አስተኔ መንግሥታትን ፈጥሯል፡፡ ደመኛ አስተኔ መንግሥታት ወደ እርስ በርስ ጦርነት ለመግባት የኢሕአዴግ ሥርዓታዊ ውቅር ይፈቅድላቸዋል፡፡ ስለዚህ በሀገሪቱ የሚታየው መፈናቀል እና ሞት፣ ቅራኔ እና ኢ-ተገጣጣሚነት፣ ክልላዊ አስተዳድራዊ ወሰንን ወደ ሉዓላዊ ግዛታዊ ድንበር የማሳደግ ሂደት የኢሕአዴግ መዋቅራዊ ሥርዓት ውጤት ነው፡፡

እንደገና ተወለድ!

እኛን አይወክልም፤ ከነጭ ነው ዝርያው

እብራይስጥ ነው ቋንቋው

ነገድ እና ጎሳው፣ ብሔሩ በሙሉ

የወንዝ ሰው አይደለም…ሩቅ ነው ባህሉ

እያሉ ያሙሃል የእስራኤል ንጉሥ

ሆነህ ሳለ ቅዱስ

የአላህ መልዕክተኛ መሀመድም ብትሆን

በብሔር ዓረብ ነህ ዘርህ ከኛ ማይሆን

እያሉ ያሙሃል ሩቅ ነው ለጎጡ

ለሰው ዘር በሙሉ ሆነህ ሳለ ምርጡ

እናም ይሄ ትውልድ ይፈልጋል አምላክ

ይፈልጋል ንጉሥ

ከቀየው ተወልዶ ከቀየው ላይ ሚነግስ

ምክንያት ብትለኝ በትውልዱ ማሳ

የአዳም ሥር ሰንሰለት ውሏ ተበጥሳ

መላ ሰውነቱ ከቀየው ከወንዙ እንደተቀለመ

እየተሳለመ

በአዶናይ ፊንታ ሊሆነው መከታ

ትውልዱ ያመልካል ባካባቢ ጌታ

ስለዚህ ፈጣሪ በኛ እንድትመለክ

 እንደገና ተወለድ

በዥንጉርጉር ልሳን፣ ይዘህ ዥንጉርጉር መልክ።

ምዕራፍ አራት

የባህል ቀኖና እና ፖለቲካዊ ስንጥቆች

4.1 ሃይማኖት እና ፖለቲካችን

ሃይማኖት ከፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም የተነጠለ ኑባሬ የለውም፡፡ የክርስትና ሃይማኖት ክርስቶስ ከተወለደ በ34ኛ[89] ዓመቱ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ፈቃጅ እና አምጭው የወቅቱ ፖለቲካዊ መንፈስ ነው፡፡ በወቅቷ ንግሥት ህንደኬ እና በጃንደረባዋ በባኮስ (አቤላክ) አማካኝነት የአዲስ ኪዳኑ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳኑ(old testatment) ጋር ተሳስሮ መሰበክ ጀመሯል፡፡ እንደ ወቅቱ እና እንደ አካባቢው ልዩነት ቢኖርም፣ ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ዘውዳዊው መንግሥት መገርሰስ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ድረስ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ሃይማኖት ሆና አንጋሽ እና የግማሽ መንግሥትነት ሚናን ይዛ ቆይታለች፡፡ በእርግጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአይሁዳዊቷ ዮዲት ጉዲት፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ፣ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ በካቶሊካውያኑ እምነታዊ እና መንግሥታዊ ሚናዋ ለጥቂት ጊዜያት ተሰናክሎባት ነበር፡፡

---

[89]እርቅይሁን በላይነህ፣ አምስቱ የመከራ ዘመናት ቅጽ 1

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ እና የርዕዮተ ዓለም ቅኝቱ ክርስትና ስለነበር ብዙው የታሪክ ግንኙነቶች ከምዕራባውያኑ ጋር የተሳሰረ ነበር። በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዐፄ ሱስንዮስ ካቶሊክን የሀገሪቱ ሃይማኖት አድርጎ ለማወጅ መሞከሩ በቀጣዩ ነጋሽ በፋሲለደስ ዘመን ሀገሪቱ ዝግ ፖሊሲ እንድትከተል አድርጓል። አውሮፖውያን ሃይማኖት የሚከልሱ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት አይችሉም ነበር። ዳግማዊ ቴዎድሮስ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የአገልጋዮቹን መጠን መገደቡ እና የቤተ ክርስቲያን መሬት ወደ መንግሥት ለማስገባት መሞከሩ እንዲዳክም አድርጎታል። ይህ ቤተ ክርቲያን በቤተ መንግሥቱ ላይ ያላትን ተጽዕኖ ያመለክታል።

ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍልን ያተኮረው የአቢሲኒያ ግዛተ ሀገር ክርስትናን ብሔራዊ ሃይማኖት ቀድሞ ሲያደርግ ወደ ምሥራቁ ኢትዮጵያ ክፍል ደግሞ እስልምና ምቹ ሁኔታን አግኝቶ መስፋፋት ችሏል። እነሐረር በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የገነቡት መስጊድ ለዛሬም ትውስታ ሆኗል። በሁለቱ ሃይማኖቶች የታሪክ ሂደት ውስጥ ክርስቲያናዊ እና እስላማዊ የሚመስሉ አካባቢያዊ መንግሥታት ሲነሡ ክርስቲያኑ ወደ አውሮፖ፣ ሙስሊሙ ደግሞ ወደ ኦቶማን ቱርክ ድጋፍ ማግኘቱ አልቀረም። ከፈረንሳዩ አብዮት ከ1789 በፊት ብዙዎች የዓለም መንግሥታት ሃይማኖታዊ መንግሥት ስለነበሩ ሃይማኖት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሆኖ ያገለግል ነበር። በሃይማኖት ውስጥ ያለው የእምነት አስተምህሮ በትልቁ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ውስጥ ያለ አስተኔ(ንዑስ) ርዕዮተ ዓለም ነው።

በአውሮፓ የካቶሊክ[90] ሃይማኖት ሰፊ ሀብት ለብቻዋ ተቆጣጥራ ቆይታለች። በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር የካቶሊክን ሃይማኖት ለማደስ በቅዋሜ ሲነሣ (Protestantism)

---

[90] የሮማ ካቶሊክ ኃጢአትን በገንዘብ ለማሰረዝ ግብር(መባ) በአማኝኞች ጥላ እንደነበር ይወሳል።

የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች ከሉተር በተቃርኖ መስቀል እና ነፍጥን በአቻነት የያዘ ኢየሱሳውያን (jesuits) የሚባል የሃይማኖት ማኅበር አቋቋሙ። ኢየሱሳውያኑ፣ በየሀገሩ ትምህርት ቤት በመክፈት የሀገሪቱን ባህል በማጥናት ሀገራትን ለቅኝ ግዛት እያመቻቹ ሃይማኖታቸውን ማስፋፋት ችለዋል። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የረጅም ልቦለድ ደራሲ የሆኑት አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን ጨምሮ እነ አለቃ ታየ[91] በኢየሱሳውያኑ አማካኝነት የካቶሊክ ሃይማኖትን እንደተቀበሉ ይጠረጠራሉ። እነ ዐፄ ሱስንዮስ በይፋ በኢየሱሳውያኑ አማካኝነት ካቶሊክን የመንግሥት ሃይማኖት ለማደረግ ሞክረው ሕዝቡን ለእልቂት ዳርገዋል። ኢየሱሳውያኑ ለፖሊተከኞች ነፍጥ እያደሉ፤ ለሕዝቡ ደግሞ የሚሲዮን ትምህርት በመስጠት ካቶሊክን በማስፋፋታቸው ከክርስትና ዘውጎች መካከል በቀዳሚነት በዓለም ላይ ከ 1.3 ቢሊየን ተከታይ በላይ ማፍራት ችለዋል። የካቶሊክ ሃይማኖት የአውሮፓን ብቻ ሳይሆን የዓለምን የሀገረ መንግሥት ቀለም ወስናለች።

በኢትዮጵያ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትናም የመሬት ባለቤትነት በቅድሚያ ስላገኘች እርሻ የክርስቲያኑ ሆኖ፣ ንግድ እና የዕደ ጥበብ ሥራ ደግሞ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሥራ ዘርፍ መስሎ ታይቷል። ሙስሊሙ ንግድ ላይ ማተኮሩ በንግድ ሰበብ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተቀላቀለ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር አድርጓል።

በአውሮፖ የካቶሊክ ሃይማኖትን መንግሥታዊ ሚና ለመለየት የሃይማኖትና የመንግሥት ፍቺ [92] በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

[91] ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከእነ ፈረንሳይ ድጋፍ ለማግኘት የካቶሊክን ሃይማኖት እንደሚደግፉ ይጠረጠራሉ። ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ገዳም እና ደብር ከመባል ይልቅ እንደ ካቶሊክ ባህል ካቴድራል የሚል ስያሜ ተችሮአቸዋል። የጳጳስ መቀመጫ ማለት ነው።

[92]በዓለም ላይ ከ22 በመቶው ሀገራት ብሔራዊ ሃይማኖት አላቸው። 43 የሚደርሱ በሰሜን አፍሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ሙስሊም ሀገራት እስልምናን ብሔራዊ

ቢጀምርም፣ ኢንዱትስሪያቸውን ለመመገብ ጥሬ ዕቃ ፍለጋ ወደ አፍሪካ ሲመጡ ሃይማኖትን በቅኝ ግዛት መሣሪያነቱ ተጠቅመዋል፡፡ በኬንያው የፀረ ቅኝ አገዛዝ አንቀሳቃሽ እና የመጀመሪያው የነጻይቱ ሀገር ኬንያ መሪ የነበሩት ጆም ኬንያታ ***የአውሮፖ ሰባኪያን ወደ አፍሪካ ሲመጡ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስን በእጃቸው ሲይዙ እኛ ደግሞ መሬት በእጃችን ይዘናል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እጃችንን ይዘው ተጨፍናችሁ ጸልዩ አሉን፡፡ ጸልየን ዓይናችንን ስንገልጥ እኛ መጽሐፍ ቅዱስን በእጃችን ስናስገባ እነርሱ ደግሞ መሬታችንን ወረው ጠበቁን*** ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አውሮፓውያን በቅኝ ግዛት ዓለምን በቁጥጥራቸው ሲያስገቡ ከነፍጥ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን አስቀድመዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ባርከውም ጦራቸውን ይልካሉ፡፡ በኢትዮጵያ በ1928 ዓ.ም. የጣሊያን ወረራ ወቅት የጣሊያንን ጦር የባረከችው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡ መንግሥታት ብዙ ጊዜ ሃይማኖቶችን እንደ ፖለቲካ መሣሪያ ይጠቀሙባቸዋል ጣሊያን በኢትዮጵያ በቆየችባቸው አምስት ዓመታት ውስጥ ነገሥታቱ የእስልምና ጠላቶች ናቸው የሚል ሰበካ በማስተጋባት ሙስሊሞችን ከወራሪ ጉን ለማሰለፍ ጥራለች፡፡ ነገር ግን በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍል በነደጃዝማች ኡመር ሰመትር የሚመራ ጦር ከጣሊያን ስብከት በተቃርኖ ቁሞ ፋሽስቱን ዶግ አመድ አደረገው፡፡

መንግሥታዊ ሃይማኖት አድርገዋል፡፡ ከዓለም ሀገራት መካከል 40 የሚደርሱት ወይም 20 በመቶዎቹ መንግሥታዊ ሃይማኖት ባይኖራቸውም፤ የሚያበረታቱት ሃይማኖት አላቸው፡፡ ለምሳሌ አውሮፓውያን በብዛት ክርስትናን በማበረታታት ይታወቀሉ፡፡ በመንግሥት በጀት የሃይማኖት ተቋማትን ይገነባሉ፡፡ ከዓለም ሀገራት መካከል 106 የሚደርሱት ወይም 53 በመቶዎቹ ሃይማኖት እና የመንግሥትን ግንኙነት የነጠሉ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያም በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ከዚህ መደብ ትካተታለች፡፡ 10 የሚደርሱት(5%) የዓለም ሀገራት ለሃይማኖት በጎ እሳቤ የሌላቸው ናቸው፡፡ በተለይም የኮሚኒዝም አሻራ ያለባቸው እነ ሰሜን ኮርያ፣ ኩባ፣ ቤትናም፣ ቻይና … በሃይማኖት ጠልነታቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ብዙዎቹ ክርስቲያኖች እስራኤልን ጌታ እንደተወለደባት ምድር እያዩ ሲደግፉ፤ ሙስሊሞች ደግሞ ሳውዲን የነቢዩ ሙሀመድ ምድር አድርገው በተለየ ሁኔታ ያቀርባሉ፡፡ በእስራኤል እና በፍልስጥኤም ባለው ጦርነት የክርስትና እምነት ተከታዮች እስራኤልን፣ ሙስሊሞች ደግሞ ፍልስጥኤምን የመደገፍ አዝማሚያ ያሳያሉ፡፡ ጦርነቶች የሚደረጉት ለሃይማኖት ይመስላቸዋል፡፡ ግን አይደለም፡፡ ምዕመኑ መሣሪያ ይሆናል እንጅ ትልቁ ግብ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ጉዳይ ነው፡፡

የአይሁዳውያንን ፈጠራ ለመጠቀም አስባ እንግሊዝ በውጭ ጉዳይ ሚኒስተሯ በባልፎር[93] አማካኝነት የእስራኤልን ሀገርነት አወጀች፡፡ በወቅቱ ፍልስጥኤም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነበረች፡፡ ከ1917-1948 የሰፈራ መርሐ-ግብር በጽዮናውያን ቡድኖች ሲደረግ ከቆየ በኋላ ግንቦት 14 ቀን በ1948 እስራኤል ሀገር መሆኗን አወጀች፡፡ በ1948 የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር ከ800 ሺህ አይበልጥም ነበር፡፡ ነገር ግን እሥራኤላውያን ለፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ቅድሚያ በመስጠት ብርቱ ብሔርተኝነታቸው ተደምሮ የዓረቡን ዓለም በተደጋጋሚ በማሸነፍ ሀገር እያሰፉ የበላይነታቸውን አረጋገጡ፡፡ የእስራኤል መፈጠር ለምዕራባውያን የሩቅና የመካከለኛው ምሥራቅ የዓረብ ሀገራት በመልክዓ ምድራዊ ጉርብትና ትብብር እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ ምዕራባያውያን በሻይት(ሺዓ) እና በሱኒ እስልምና ተከታዮች በነኢራን እና ሳውዲ መሃል በመግባትም የፖለቲካ ትርፍ ይቸረችራሉ፡፡ የሳውዲ ቤተሰባዊ መንግሥት የአሜሪካ እስረኛ ነው፡፡ አሜሪካ እና እስራኤል ደግሞ ኢ-ተነጣጣይ ወዳጆች ናቸው፡፡ ሳውዲ በእስራኤል መስፋፋት ጉዳይ ግልጽ አቋም ለማንጸባረቅ ታመነታለች፡፡ ምክንያቱም ይሄኛው ዘመን የፖለቲካ <u>አዋጭነት እንጂ</u> የሃይማኖት ቀኖና እና [94]ዶግማ ታይቶ ግንኙነት

[93]ሙሀመድ አሊ፣ እስልምና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

[94]ዐፄ ቴዎድርስ ዲፕሎማሲያቸውን ከክርስቲያን ሀገራት ጋር ብቻ ማድረጋቸው ለውድቀት ዳርጓቸዋል፡፡ በቀይ ባህር አካባቢ ኦቶማን ቱርኮች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመግባት ሲከጅሉ እርዳታ ከአውሮፓ

የሚመሠረትበት ጊዜ አይደለም። በዓለም ሃይማኖት የመደበኛው ሕዝብ ጉዳይ እንጂ በፖለቲከኞች ዘንድ የኢኮኖሚ እና የወንበር ማስጠበቂያ መሣሪያ ነው፡

4.2 ሃይማኖት እና የኢትዮጵያ አብዮት

የ1966 አብዮት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ከመንግሥትነት ድርሻዋ ነጠላት። ንብረቷም ተወረሰ። ብሔራዊ በዓላቶቿ ተቀነሱ። ከ1966 በፊት ነሐሴ 16 ቀን የፍልሰታ መውጫ እና ከፋሲካ በኋላ ያለው ሀሙስ እንደ ብሔራዊ በዓል ይቆጠር ነበር። እነዚህ በዓላት ተሽረው፤ በምትኩ አረፋ እና መውሊድ ወደ ብሔራዊ[95] በዓልነታቸው በ1968 ዓ.ም. አካባቢ መጡ።

የኅበረተሰባዊነት አብዮት ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ይልቅ ለእስልምና የተሻለ ዕድል ነበረው። ኮሚኒዝም የሩሲያ አብያተ ክርስቲያናትን ባዶ ባድማ አድርጓል። ቀሳውስቱን ከመስቀል ይልቅ ቀያይ ማጭድ እና ዶማ እንዲጨብጡ አስገድዷል። ቤተ ክርስቲያንን ከንዋየ ቅዱሳት መንበርነት አውጥቶ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መጋዘን ለማድረግ ዳድቷል። ክርስትናን ከኢየሱስ ክርስቶስ አስተምህሮ አፋትቶ፤ በኮሚኒዝም ንድፈ ሐሳብ ለማጥመቅ ሞክሯል።

ክርስቲያን ሀገራት ድጋፍ የሚያገኙ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን በወቅቱ እንግሊዝ ከቱርክ ጋር አብራ ሩሲያን እንደወረረች ሰሙ። እንግሊዝ የቱርክ አጋር ሆነች። ዐፄ ቴዎድሮስም በ1860 ዓ.ም. በእንግሊዝ መንግሥት ተወረሩ። በቀደመው ዘመን ፖርቹጋል ከእነ ዐፄ ልብነ ድንግል እና ልጃቸው ገላውዴዎስ ጎን ስትሰለፍ፤ ቱርክ ደግሞ ከግራኝ አህመድ ጎን ተሰልፋለች። ይህ አሰላለፍም ቢሆን የፖለቲካ የበላይነትን መያዝን ማዕከል ያደረገ ነው። በእግረ መንገድ፣ የፖለቲካ የኃይል ሚዛኑን የተቆጣጠረ ባህል እና ሃይማኖትን ያስፋፋል፤ ኢኮኖሚ እና ታሪኩን በራሱ መንገድ ይቀርጻል። ታሪክ የአሸናፊዎች የውሎ መዝገብ ነው።

[95]ፍቅረስላሴ ወግደረስ፤ እኛ እና አብዮቱ

በአንፃሩ እነ ሌኒን እና ስታሊን ዓረቡን ምድር ከክርስቲያኑ እና ከካፒታሊስቱ የአውሮፓው ክፍለ ዓለም ለመነጠል እስልምናን ለማቀጨጭ አልጣሩም፡፡ እስልምናን በተለየ መንገድ ለፖለቲካ ልክነት ደግፈውታል፡፡ በኢትዮጵያም በ1968 ዓ.ም. የሙስሊሞች ምክር ቤት[96] (ሙጅሊስ) ተቋቁሟል፡፡ ነገር ግን ኮሚኒዝም በመርሆው ፍጡር እንጅ ፈጣሪ የለም ብሎ ስለሚያስብ ለእስልምናም ሆነ ለክርስትና ከፖለቲካ መሣሪያነት ያለፈ ዕድል አልሰጠውም፡፡ ቀሳውስቱም ሆነ ኢማሙ በስመአብ፣ ቢስሚላሂ... ከማለት ይልቅ ሌኒን ወማርክስ ማለትን መረጡ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ፓትርያርክ የነበሩትን ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን[97] አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ጳጳሳቱ ፈረሙ፡፡ ጳጳሳቱ አብዮታዊ እርምጃ መወሰዱ ለቤተ ክርስቲያናችን ጠቃሚ ነው ብለው በፊርማቸው[98] አረጋግጠው፣ በ1971 ዓ.ም. ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎሎፍስ ታንቀው ተገደሉ፡፡ ቀብራቸውም ቤተ

[96] አህመዲን ጀበል፣ ሦስቱ ዐዔዎች እና ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ትግል እና መስዋዕትነት

[97] ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ኤሊያስ ወረዳ፣ ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም. ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ማርም ውቤ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ዘርትሁን አደላሁ ተወለዱ፡፡ የአቡነ ቴዎፍሎስ የዓለማዊ መጠሪያ ስማቸው መልእክቱ ወልደ ማርያም ሲሆን፤ ደርግ ለጵጵስናቸው ክብር ለመንሣት በእስር ቤት አባ መልእክቱ እያሉ እንዲፈርሙ ያስገድዳቸው ነበር፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም. ሁለተኛው ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ እና ከመሾማቸው በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሥራች እንድትሆን አድርገዋል፡፡ ለ1600 ዓመት ያህል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በግብጽ እስክንድርያ መንበር ሥር እንደ አንድ አገረ ስብከት ተቆጥራ ስትመራ የነበረበትን አሠራር እንዲያቆም ካደረጉ የሃይማኖት አባቶች አንዱ ናቸው፡፡ ፓትርያርኩ ነገን አሳቢ በመሆናቸው የወጣቶች ጉዳይ እና የክርስቲያን የልማት ተራዶኦ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ አድርገዋል፡፡ ደርግ ሲገባም፤ ደርግ የሚያደርሰውን ጅምላ ግድያ በማውገዝ፤ የቤተ ክርስቲያኗ ንብረትም መወረስ እንደሌለበት ተከራክረዋል፡፡ ይህን ሰበብ አድርጎ ደርግ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያለችሎታቸው የተመረጡ እና የካፒታሊዝም እሳቤ ያላቸው ጳጳስ ናቸው ብሎ የካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም. አሰራቸው፡፡ አቡኑ በስቃይ ለ28 ወራት ከቆቆ በኃላ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም. በገመድ ታንቀው ተገደሉ፡፡ ቀብራቸው እንኳን በቤተ ክርስቲያን እንዲሆን በወቅቱ የነበሩ ጳጳሳት ሳይጠይቁ ቀሩ፡፡ ደርግ ሥልጣኑን ከለቀቀቀ በኃላ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም. አስከሬናቸው ራሳቸው ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ በጎፋ ሚካኤል አርፏል፡፡

[98] ተገኘ ብልሃቱ፣ ፍሬ አልባ በለሶች(የቆብ ውስጥ ገመና)

ክርስቲያን ሳይሆን ሜዳ ላይ ነበር፡፡ ሪፖርተር መጽሔት በታኅሳስ 1992 ዓ.ም. በቅጽ 3 በቁጥር 23 የአበራ ጀምበሬን የእሥር ቤቱ አበሳ የሚለውን መጽሐፍ ጠቅሶ እንዳሥነበበው ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎሎፍስ በእሥር ቤት ከመጋቢት 3 ቀን እስከ ሚያዚያ 18 ቀን 1968 ዓ.ም. ድረስ ለ45 ቀናት ያለምንም እህል ውኃ በፍጹም ጾም ቆይተዋል፡፡ ፓትርያርኩ ደርግ ለእስረኞች 120 ብር እየከፈለ ስንቅ ሲያስቀርብ፤ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎሎፍስ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የተለመነ ቁራሽ እንጀራ እንጂ የደርግን ቡራኬ አልቀበልም ብለው ራሳቸውን ከመብል አቅበዋል፡፡ ፓትርያርኩ ከእሥር ቤት ያስቀመጡትን ስዕለ አድኖ(መንፈሳዊ ስዕሎች) ሁሉ እንዲያነሡ ከመደረጋቸው በተጨማሪ በጽጽስና ስማቸው እንዳይጠሩ በደርጎች ታግደዋል፡፡

በወቅቱ ገዳም ወስዳችሁ እሰሩኝ ብለው ቢማጸኑም ሰሚ አላገኙም፡፡ አቡኑ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም እንድትተዋወቅ እና ተቋማዊ አደረጃጀቷም እንዲዘምን ተኪ የለሽ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ነገር ግን አባታዊ ውለታቸው ተዘንግቶ ራሳቸው ያስተማሯቸው እና የሾሟቸው ጳጳሳት በፊርማቸው እንዲገደሉ በየኑባቸው፡፡ በወቅቱ ጳጳሳቱ ኢየሱስ ክርስቶስንም ቢሆን ለማርክስ እና ለኤንግልስ ሲሉ ከመስቀል እንደማይቆጠቡ በፓትርያርኩ ላይ የፈጸሙት ይሁዳነት አመላካች ነበር፡፡ ከዚህ እውነት በተቃራኒ ግን የግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ስለ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መታሰር እና በሕይዎት እያሉ ሌላ ፓትርያርክ ከቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ውጭ መሾምን በተመለከተ በጽኑ አውግዛለች፡፡

የሃይማኖት አባቶች በቆባቸው ሥር ኮሚኒዝምን ከኢየሱስ ክርስቶስ በላይ አምልከው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለአብዮቱ ሲባል እንዲወረስ ፈራሚ ሆኑ፡፡ አባቶች ከኢሠፓ በላይ የደርግ ካድሬ ሆነው ቀረቡ፡፡

በእስልምና በኩልም የተሰለፉ የሃይማኖት አባቶች ለኅብረተሰባዊ አብዮት እንጂ ለሐዲስ እና ለቁርአን አስተምህሮ ያደሩ አልነበሩም፡፡ በኢሕአዴግ ጊዜም በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ልክ እንደ ፖለቲካው ሁሉ የአድዋ የበላይነት እንጂ የሁሉም ፈጣሪ ስለሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አልፋ እና ኦሜጋነት የተሰበከበት ጊዜ ስስ ነበር፡፡ ጳጳሳትን እና የገዳም አስተዳዳሪዎችን ሳይቀር ብሔራዊ ደኅንነቱ የመሾም እና የመሻር ሥልጣን ይዞ መርቷል፡፡

አራተኛው ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በደርግነትና በአማራነት ተፈርጀው ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከውጭ ወደ ውስጥ ገብተው ፓትርያርክ ሆነዋል፡፡ አለቃ አያሌው ታምሩ በ1985 ዓ.ም. ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ እንደተናገሩት፣ **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ከ1966** ዓ.ም.[99] **በኋላ የለችም፡፡ አቡነ ጳውሎስ ተሾሙ የሚለው ለእኔ አይመለከተኝም፡፡ በትውፊቷ በሌለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ማን ምን ሊያደርግ ይሾማል?** የሚል ሐሳብ ተናግረዋል፡፡ በ1984 ዓ.ም. ‹‹ አቡነ መርቆርዮስ በህመም

[99]አለቃ አያሌው ታምሩ ቤተ ክርስቲያን በመሠረቷ የለችም የማለታቸው ምክንያት በ1967 ዓ.ም. ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሕይዎት እያሉ፣ በ1984 ዓ.ም. ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በመንበረ ፕትርክናቸው ላይ ተሰይመው እየመሩ በነበረበት ወቅት በመንግሥት ፈቃድ ተሽረው በሌላ ፓትርያርክ ተተክተዋል። ይህ ከቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ጋር የተቃረነ ነው። አንድ ሊቀ ጳጳስ በሕይዎት እያለ በሌላ መተካት አይቻልም። የቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓት በፖለቲከኞች መፋለሱ ያሳሰባቸው አለቃ አያሌው ቤተ ክርስቲያን የለችም ለማለታቸው ገፊ ምክንያት ሆኗቸዋል።
በወያኔ ፈቃድ የመጡት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ምንም እንኳን ለሕወሓት የዘውግ ፖለቲካ አስፈጻሚ ይሆናሉ ተብለው ቢታሰቡም ዘውጌ መሆን አልቻሉም። በ1990 ዓ.ም. የትግራይ ሲኖዶስ ራሱን ችሎ ይመሥረት የሚል ቡድን በሕወሓት አስተምህሮ ተሸካሚ ካህናት ተነሡ። ነገር ግን የዘውግ ሲኖዶስ ሳይፈቀድ ቀረ። ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስም በሕወሓት ጥርስ ተነከሰባቸውም፤ ሌላው ምዕመን ደግሞ በጥርጣሬ ብቻ በሕወሓት አዳሪነት ይከሳቸው ያዘ። ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በሁለት ስለታማ ቢላዋ ተወጉ።

በ2010 ዓ.ም. ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ከአሜሪካ ተመልሰው የጸሎት ዘርፍ ሊቀ ጳጳስ ሆነው፤ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ የአስተዳድር ዘርፉን እዲመሩ ተደረገ። ሕወሓት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስን ከአዲስ አበባ ወደ አክሱም አስኮርፎ ለመውሰድ አስቦ ነበር። ነገር ግን ሁለቱ አባቶች ተስማምተው ቤተ ክርስቲያንን መምራት መቻላቸው ለዘውጌዎች የራስ ምታት ሆኖ ለቤተ ክርስቲያን ደግሞ ድኅነት ሆኗል።

ምክንያት ሥልጣን ለቀቁ›› የሚል ዜና በማናፈስ በምትካቸው ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በኢሕአዴግ ተሾሙ። ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ አማካኝነት ከሥልጣን ሲነሡ፤ በኬንያ አድርገው አሜሪካ ገቡ። ቤተ ክርስቲያኗም ዋሽንግተን እና አዲስ አበባ ተቀማጭነታቸውን ያደረጉ ሁለት ሲኖዶሶች ኖራት።

እነዚህ መንታ ሲኖዶሶች እርስ በርሳቸው ሲካሰሱ እና ሲወጋገዙ ባጅተው ከ26 ዓመታት በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አማካኝነት ሐምሌ 2010 ዓ.ም. እርቅ ፈጽመዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔም ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስን ከ26 ዓመታት በኋላ በይፋ ይቅርታ ጠይቀዋቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ፖለቲካው ተጭኗት ምዕመኖቿ ሸሽተዋታል። ለአብነት በኦሮሚያ ክልል በ1986 ዓ.ም. በተደረገ የሕዝብ ቆጠራ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተከታዮች ብዛት 41.3 በመቶ የነበረ ሲሆን በ1999 ዓ.ም. በተደረገው ቆጠራ ደግሞ ከ10 በመቶ በላይ ቀንሶ 30.4 በመቶ ሆኗል። በተነጻጻሪ ፕሮቴስታንት ከ8.6 ወደ 17.7 በመቶ ከፍ ብሏል። በደቡብ ደግሞ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ከ27.6 በመቶ ወደ 19.8 ዝቅ ያለ ሲሆን፤ ፕሮቴስታንት ከ34.8 ወደ 55.5 በመቶ ከፍ ብሎ ተገኝቷል። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አሃዝ እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት በፍጥነት ሲስፋፋ፣ እስልምና በዝቅተኛ ፍጥነት እየጨመረ ሲሆን፤ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ከሀገሪቱ ሕዝብ ግማሽ ያህል ተከታይ ቢኖራትም የምዕመኖቿ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት ከእልፍኟ እየወጡባት ነው። ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታውን የሚመጥን መፍትሄ ቤተ ክርስቲያኗ ማለፊያ መንገድ አለማዘጋጀቷ፣ የእምነቷ መዋቅር በመሪዎቿ መላላቱ እና የመንግሥት ጫና በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የሃይማኖት ተቋማት የማይናወጥ ተቋምን በመገንባት ለዘመናዊ የቢሮክራሲ ሳይንስ አስተማሪ ናቸው ቢባሉም፤ የመሥራቾቻቸውን አስተምህሮ(የኢየሱስ ክርስቶስ እና የነቢዩ ሙሀመድን) በመካድ ፖለቲከኞችን አጥብቀው በመከተላቸው እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ተቀያያሪ ሆነዋል።

ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተች ቢሆንም፤ ያሏት አስተዳዳሪዎች ከቀራንዮው ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ይልቅ የምኒልክ ቤተ መንግሥቱ ድሎት ይማርካቸዋል። ኢሕአዴግ የተከተለው የብሔር ፌደራሊዝም በኢትዮጵያዊነት አስተምህሮት የታነፀችውን ቤተ ክርስቲያን ያንገዳገዳት ሲሆን ከጣሊያን ጊዜ ጀምሮም በጠላትነት ተፈርጃ ተቀምጣለች። ከጣሊያን እስከ ኢሕአዴግ የብሔር ፖለቲካ ትንተና ቤተ ክርስቲያን የነፍጠኞች ዋሻ ተደርጋ ተስላለች። በዚህ ምክንያት በርካታ ካህናት፣ ምዕመናን እና አብያተ ክርስቲያናት በገፍ ጠፍተዋል፤ ፈተና ውስጥም ወድቀዋል። ፈተናው የተደራረበባት ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለማዳን መሪዎቿ አልታደጓትም። ለጥፋቷም ተባባሪ ሆነዋል። ከኢሕአዴግ በላይ ኢሕአዴግ ሆነው ስለ ልማታዊ መንግሥት፣ ስለሰላም እና አብዮታዊ ዴሞክራሲን በየፓርቲ ክብረ በዓሉ፣ በተፈጥሮ ሀብት ሥራው፣ በየድግሱ፣ በየመንግሥታዊ ክዋኔው... ሰበካ ላይ መሪዎቿ ተሰማርተው ቆይተዋል።

ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም. አጋማሽ በተደረጉ የሕዝብ ሰላማዊ ሰልፎች በርካቶች እየሞቱ ወይም ታስረው ለሀገሪቱ ፖለቲካ መሻሻል እዳ እየከፈሉ፤ የሃይማኖት አባቶች ግን ተቃዋሚዎችን እያወገዙ፣ ሰላም ከገዥው መንግሥት ብቻ እንደሚመነጭ አስበው ሰላም አስፈላጊ ነው እያሉ አለሳልሰው ሸንግለዋል።

ከተለያዩ አካባቢዎች ሕዝቦች ተፈናቅለው ቤተ እምነቶችን ሲጠጉ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች የመንግሥትን ፊት በማየት ብቻ አማኞቻቸውን አባረዋል፡፡ የሕወሓቱ አስኳል የሆኑት አቶ ስብሐት ነጋ በአንድ ወቅት ‹‹የትኛው የሃይማኖት አባት ነው… የሃይማኖት እና የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ተከልክሏል ተብሎ በሕግ ታውጆ እንኳን እምነቱን አክብሩ ብሎ የተሰቀለው?›› ሲሉ የእምነት አባቶችን ይጠይቃሉ፡፡ ልክ እንደ አቶ ስብሐት ሁሉ የብአዴን (የአዴፓ) አባል የነበሩት ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ባሕር ዳር ላይ በተደረገ ስብሰባ ‹‹የሃይማኖት አባቶች ችግሩን መፍታት ላይ ሳታተኩሩ፣ አባቶች ሽምጋይ እና አደራዳሪ እየሆናችሁ የአማራን ሕዝብ ችግር እድሜ አትቀጥሉ፡፡ አማራም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም አያስፈልግም ያለ ይመስል ሰላም አስፈላጊ ነው ብላችሁ አታስመስሉ፡፡ ከቻላችሁ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ሁኑ፡፡ አሊያ ዝም በሉ፡፡›› ሲሉ አስመሳይ የሃይማኖት አባቶችን ወቅሰዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደ እነ ቅዱስ ላሊበላ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ንጉሥ ዘርዓያዕቆብ፣ አቡነ ጴጥሮስ.. የመሳሰሉ ለመንፈሳዊ እና ለዓለማዊ አተያዮች የነጠረ እውነት ያላቸው መሪዎች ነበሯት፡፡ የቅርብ ዘመን የሃይማኖት አባቶች ግን መንግሥትን ከአምላክ በላይ እየፈሩ፤ ከነፍሳቸው ይልቅ ለሥጋቸው ሲሉ በብዙዎች ሞት ላይ ዝምታን መርጠዋል፡፡ በሕወሓቱ ኢሕአዴግ እዝ በማእከላዊ ግብረ ሰዶም የተፈጸመባቸው፣ የተኮላሹ፣ የተገደሉ እስረኞችን እያዩ እንኳን ‹‹**ሕዝቡ በኃጢአቱ ያመጣው እዳ**›› አድርገው ወስደው ከንፈር ከመምጠጥ ያለፈ ተግባር አልሠሩም፡፡

እነ ማርክስ እና ሌኒን ‹‹ሃይማኖት፣ ጭቆናን ሕዝቡ እንዲለምድ በማድረግ ለፖሊተከኞች የሚንበረከክ ሕዝብ እንዲፈጠር አድርጓል›› ሲሉ ሃይማኖትን ይወቅሳሉ፡፡ በተለይ ሌኒን ‹‹ሃይማኖት ስለሰማዩ መንግሥት ብቻ በመጨነቅ በመሬት ላይ አምባገነን መሪዎች የሚያደርጉትን ጭቆና እንደ መሥዋዕትነት ይቆጥራል፡፡ ሃይማኖት

ስለሚታየው ሳይሆን ስለማይታየው ተስፋ እያደረገ በምድር ላይ ጾም የሚያድሩ እና ለጭቆና የተመቹ ሕዝቦችን ፈጥሯል›› ሲል ይወቅሳል፡፡ ሌኒን ሃይማኖትን የመተቸቱ መንስኤው ከሃይማኖታዊ ዶግማው አንጻር ሳይሆን ከስሑት አስተምህሮው የሚነሣ ይመስላል፡፡ በእርግጥም ሃይማኖት የነጻነት መንገድ ቢሆንም፤ መሪዎቹ አስተውታል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ከመሰቀሉ በፊት በምድር ላይ አምላክ ሲሆን ሰው ሆኖ የሰውን የመቻል አቅም ራሱ አሳይቷል፡፡ ለነጻነትም ተሰቅሏል፡፡ የትንሣኤ አስተምህሮ የነጻነት ማሳያ ነው፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑት የሃይማኖት አባቶች ግን ለልጆቻቸው እንኳን ሊሰቀሉ፤ ሲሰቀሉ ሰቃዮችን ተዉ ለማለት እንኳን ድፍረት ሸሽቷቸዋል፡፡

እንደውም አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች የአለመቻል ሰባኪ ሆነዋል፡፡ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በመላእክት ተሠራ እንጂ በሰው አይደለም እያሉ የሰውን የመቻል አቅም ያሳንሳሉ፡፡ አምባገነን መሪዎች ልጆቻቸውን ሲያሰቃ የፈጣሪ ቁጣ ነው በማለት ሕዝቡ ለነጻነቱ እንዳይታገል እክል ይሆናሉ፡፡ አምባገነን መሪዎችን ፈጣሪ እስኪያወርዳቸው ደረስ ሕዝቡ እየጸለየ ብቻ እንዲቀመጥ ይወተውታሉ፡፡

የሃይማኖት አባቶች ለሥነ መንግሥት ያላቸው አረዳድ ዝግ በመሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ቅርጽ የያዙት በፖለቲከኞች እንጂ በሃይማኖት አባቶች አይደለም፡፡ ሃይማኖት በሃይማኖት መሪዎች <u>ብዙ ሳይስፋፋ፤</u> በፖለቲከኞች ሊስፋፋ[100] ችሏል፡፡ ለአብነት

[100]በእርግጥ ፖለቲካ ከሃይማኖት በላይ የፈረጠመ ጡንቻ አለው፡፡ ፖለቲካ ሃይማኖትን ይሠራል፡፡ ቅርጽ ያወጣል፡፡ የቱርክ እስልምና የአታቱርክን የፖለቲካ ቅርጽ ይዟል፡፡ እነ ሰሜን ኮርያ ደግሞ ሃይማኖታቸው በኮሚኒዝም መር ፖለቲካቸው ጠፍቷል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ራሷን የመሰለ መሪ በመፍጠር ራሷን የሀገረ መንግሥት ምሥረታ አንድ የታሪክ አካል አድርጋ መራመዷ አሻራዋን አስፍቶታል፡፡
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀገረ መንግሥቱን ንደው ሌላ ሀገር ለማብቀል በሚፈልጉ አካላት ቤተ ክርስቲኗ ፈተና ውስጥ ወድቃለች፡፡ ሲኖዶሷ ሳይቀር ከ1984 እስከ 2010 ዓ.ም. ለሁለት ተከፍሎ ቆይቷል፡፡ ሥረ መንስኤው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሰማዩ አምላክ ሳይሆን ለምድሩ

የቤተክርስቲያን አግልግሎት የካህናት ምጣኔ በዐፄ ቴዎድሮስ ቅኖና የሆነ ሲሆን፤ፓትሪያሪክ ከግብጽ መሾም የቀረው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ አማካኝነት ነው:: በእስልምናም በሱኒ እና በሺኣ(ሻይት) የሃማኖት አስተምህሮቶች መካከል ያለው የልዩነት ሐሳብ የተነደፈው በፖለቲከኞች ሲሆን፤በሱኒ አስተምህሮ ሥር የሱፊ እና የሳለፊ የአስተምህሮ ንቅናቄዎች መነሾ የተሠራው በፖለቲካ ቀመስ ሃይማኖታዊ ልሂቃን ነው::

4.3 ሃይማኖታዊ መልኮች

ቡርሃን አዲስ(ሙሀመድ አሊ) የዘር ካርድ ብሎ በከተበው መጽሐፉ ሁለት እምነታዊ መልኮችን አጉልቶ ያሳየናል:: የመጀመሪያው የምዕራቡ (አውሮፓ እና አሜሪካ) ሲሆን፤ ሁለተኛው የምሥራቁን ክፍለ ዓለም(አረባዊ ሀገራት እና ሌሎችን) ነው:: ቡርሃን ኢቅባል የተባለ የፓኪስታንን ገጣሚ ሐሳብ ጠቅሶ ‹‹**የምዕራብ ሰው ፈጣሪውን ክዶ ራሱን አወቀ፤ የምሥራቅ ሰው ፈጣሪውን እያሰበ ራሱን ይረሳል**›› የሚል ሐሳብ ያቀርባል::

ሀ) ምዕራቡ ዓለም

ፈቃደ ፈጣሪን ብዙ አያስቡም:: የሁሉም ነገር አድራጊ እና ፈጣሪ፣ ጣይ እና አንሺ፣ ከሳሽ እና ዳኛ ግለሰቡ ነው:: የምዕራባውያኑ የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ፍልስፍና ግለሰቦችን ኢ-አክታሚ ለሆነ ውድድር ጥሏቸዋል:: ለዚህ ደግሞ ሰው ራሱን ሊያመልክ ተገዷል::

ጌታ(ፖለቲከኛ) ማደራቸው ነው:: የሃይማኖት መሪዎች ጎሳ አምላኪ መሆናቸውም ሌላኛው ፈተና ነው:: የኦሮሚያ ቤተ ክህነት እና ሲኖዶስ እንመሠርታለን የሚሉ አንዳንድ አባቶች ‹‹አዲስ አበባ የኦሮሞ ናት:: ቤተ ክርስቲያን የነፍጠኛ መስላለች›› የሚል የኦነግ አስተምህሮ ተካፋይ መስለው ታይተዋል:: ኦነግ ነጻይቱ ኦሮሚያን ለመመሥረት የዘመን ቆጠራው ሳይቀር በአውሮፓ እንዲሰላ ይሻ ነበር:: እንደ ሻዕቢያ እንቁጣጣሽ መስከረም ሳይሆን ጥር ይከበር የሚል ውስጣዊ ፍላጎት አለው:: ለዚህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኗን ማድከም አንድ ስልተ ሂደት መስሎ ታይቷል:: ቤተ ክርስቲያኗ የፊደል፣ የዘመን ቆጠራ፣ የታሪክ፣ የኢትዮጵያዊነት እሴት... ባለቤት በመሆኗ ለኦነግ ቀመስ ፖለቲካ ምቾት አልሰጠም:: የግእዝ ፊደልን ላለመጠቀም ለኦሮምኛ ቋንቋ በመጻፊያነት/ለጽሕፈት አገልግሎት ላቲን ተመርጧል::

ለእያንዳንዱ ሰው ፈጣሪ ራሱ ሰውየው እንደሆነ ይታሰባል። ሥነ-ቁሳዊ ፍልስፍና ገኖ ሞራላዊ ፍልስፍና ተፍቋል። ግለሰብ አምላክ ሆኗል። በዚህ ውስጥ ማኅበረሰባዊ ወግ፣ ማኅበራዊ ጉድኝት እና ሃይማኖተኛነት… ተሰርዘው የምሥራቁ ወግ አጥባቂ ባህል ተብለው ተፈርጀዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃን እሳቤ ከምዕራቡ ዓለም ሥነ-ቁሳዊ ፍልስፍና የሚቀዳ ይመስላል። በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ከምሥራቁ ጋር የሚገጣጠም የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ቢኖረውም፤ በተግባር ግን ከእኔ ወዲያ ላሳር በሚል ፍልስፍና የተጠመቀ መሪ አላት። የአውሮፓ ኅብረት በ2010 ዓ.ም. ባወጣው መረጃ ከአውሮፓ ሕዝብ ውስጥ 20 ከመቶው ኢ-ሃይማኖተኛ ነው። ለኢ-ሃይማኖተኝነት የኋላ መንስኤው በአውሮፓ እንደነ ፈረንሳይ ዓይነት አብዮቶች ምክንያታዊነትን እና ሳይንሳዊ ጥናትን ደግፈው መነሣታቸው ነው። ከዚህም በላይ ደግሞ የግለሰብ ሁሉን አድራጊነት በካፒታሊዝም ንድፍ ተሰብኳል። በኤስያ አካባቢ በነቻይና በ1949 በማኦዘዱንግ የተቀነቀነው የባህል አብዮት ምክንያት ሃይማኖተኛነት ውግዝ ሆኗል። በ2015 በወጣ ጥናት መሠረት ከቻይና ሕዝብ ከ60 በመቶ በላዩ ኢ- ሃይማኖተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል። ካፒታሊዝም ለግለሰብ ነጻነት አብዝቶ በመስጠት፤ በፈቃድ ሃይማኖታዊነት እንዲሟሽሽ አድርጓል። በምሥራቁ ደግሞ ኮሚኒስታዊ ፍጹም አምባገነን መንግሥታት ሃይማኖትን ሕዝቡ በግዳጅ እንዳይከተል አድርገዋል። በቻይና፣ በሰሜን ኮርያ፣ በቬትናም…ማምለክ የተወገዘው በኮሚኒዝም አገዛዞች ነው።

የምዕራቡ ክፍለ ዓለም ሃይማኖተኛው ሕዝብ እንኳን ሃይማኖትን ከምድራዊ ሕይወት ጋር ያቀራርበዋል። ለምሳሌ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮማ ወታደር የነበረው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ለጣኦት ስገድ ተብሎ ሲታዘዝ አሻፈረኝ አለ። ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለዓላማው እና ለእምነቱ እስከ ሞት ጸና። እነ እንግሊዝ እና ሩሲያ የቅዱስ ጊዮርጊስን ጽናት ለወታደሮቻቸው

የጽናት ማስተማሪያነት ይጠቀሙበታል፡፡ አውሮፓውያን ቅዱስ ጊዮርጊስን ጽናቱን ለማቅረብ የስያሜቸው መጠሪያ አድርገውታል፡፡ ‹‹ጆርጅ›› የሚለው መጠሪያ በበርካታ ሀገራት ተዘውታሪ መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ጆርጅ ዋሽንግተን፣ ጆርጅ ሃባሽ.... በነፍልስጥኤም ሳይቀር ከ10 ሰዎች መካከል የአንዱ በጆርጅ ስም ይጠራል፡፡ ጆርጅ (ጊዮርጊስ) የታማኝነት፣ የጽናት፣ የፍጥነት... መለያ ተደርጎ ለምድራዊ ሕይወት ጭምር ማስተማሪያ ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያም በዕለተ እሁድ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በተደረገው የኢትዮ-ጣሊያን ጦርነት በቅዱስ ጊዮርጊስ ጽላት ዙሪያ ዘማቾች ተሰባስበው የመንፈስ ብርታት አድርገው ተዋግተዋል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስን በጽላት ቀርጾ ለአምልኮ ከማዋል ባለፈ፤ ለተለያዩ ዓለማዊ ድርጅቶች መጠሪያ ሆኗል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ በ1915 ዓ.ም. ሲቋቋም፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ እግርኳስ ክለብም በ1928 ዓ.ም. አካባቢ ተመሥርቷል፡፡ ጣሊያን የቅዱስ ጊዮርጊስን የአድዋ የድል መንፈስ ስላወቀች ቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብን ‹‹ ለቶርዮ ውቤ ሰፈር አራዳ›› የእግር ኳስ ክለብ ብላ ልትጠራው ተገዳለች፡፡ በአድዋ ጦርነት ጊዜ ቅዱስ ጊዮርጊስን ለምድራዊ ሕይወት አቅርቦ የመመልከት ሁነት በመልካም አተያይ የሚነሣ ቢሆንም፤ በሌላው ጊዜ ግን ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን ጨምሮ ሌሎች የሃይማኖት ሰማዕታትን በመንፈሳዊ ሕይወት ብቻ ነጥሎ የማየት ችግር አለ፡፡ የማድረጋቸው ምሥጢርም አምላካዊ ልዩ ኃይል ስላላቸው እንጂ የሰውነት ባሕርያቸው አይፈቅደም ብሎ የማሰብ ሁኔታ በስፋት ይንጸባረቃል፡፡፡ ይህ ሂደት ሃይማኖትን ከምድራዊው ሕይወት አርቆ፤ የማይደረስበት የታምራት እና የገድላት ስንክሳር ብቻ ተደርጎ እንዲታሰብ አድርጓል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን በቀራንዮ መሰቀል እንደተአምር ብቻ ቆጥሮ አምላካዊ ባሕርይውን አጉልቶ ሰውኛ ባሕርይውን መዘንጋት አለ፡፡

አውሮፓውያን ‹‹ሰው ሚች አምላክ ነው›› ብለው የሰውነትን የመቻል አቅም ወደ አምላክነት ከፍ አድርገውታል። የኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁዶች በደቦ ፍርድ መሰቀሉ፤ እውነቱን እያወቁ እነ ንጉሥ ጲላጦስ በአስመሳይነት ከውሳኔ አሰጣጥ ችግር ትክክለኛ ብይን አለመስጠታቸው ለምድራዊው እና ለሰውኛው የማኅበረ-ፖለቲካ ተረክ ሁነኛ አስተማሪ ንግርት ነው።

ለ) የምሥራቁ ዓለም

የክርስትናውም ሆነ የእስልምና እምነት መነሻ የምሥራቁ የዓለም ክፍል ነው። ከሱሜራውያን እስከ ሞሶፓታሚያ፣ ከቻይና እስከ ዓረባውያን ሥልጣኔዎች… ለዓለም የተዋወቁት ከዚህኛው የዓለም ክፍለ አሕጉር ነው። የምሥራቅ ሀገር ሰው ራሱን በፈጣሪው ይመለከታል። የዓለም ሁነቶች ክዋኔ በፈጣሪ ትእዛዛት እንደተከናወኑ ያስባል። የአኗኗር ዘይቤው መሠረቱ የሃይማኖቱ ትውፊት እና ዶግማ ነው። ብዙዎቹ የዓረብ ሀገራት መንበረ መንግሥታቸው ሳይቀር ሃይማኖታዊ ነው። ወደ ፊት የዓለም ግዙፉ ሃይማኖት የመሆን እድል ያለው ከምሥራቁ ክፍለ አሕጉር የሚቀዳው እስልምና እንደሆነም ጥናቶች ከመተንበይ አልቦዘኑም። እስልምና የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሆኖ ሃይማኖትን መከተል በተዘዋዋሪ ግድ እንደሆነ ያበረታታል። በብዛት እስልምና ተከታዮች ብዙ ልጅ የመውለድ ምጣኔም አላቸው። እስልምና ለመስሊሙ ለዓለማዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው የሕይወት መንገድ ነው። ለዚህም በምሥራቁ ንፍቀ ክበብ የሚገኝ ሕዝብ ራሱን ረስቶ ፈጣሪውን ያውቃል። ፖለቲካ ኢኮኖሚውም ከሃይማኖቱ ሥሪት ይመነጫል።

በእርግጥ የጃፓን እና የቻይና የእምነት ሂደቶች ከምሥራቁ የተለየ እሳቤ አላቸው። በኮንፊሽስ ፍልስፍናዊ እምነት የምትመራው ቻይና ‹‹የሰው ልጅ ፈጣሪው ሥራ ነው። ሰው ከሥራ የተገኘ ነው።›› የሚል ዓለማዊ ግንዛቤን የሚያጎላ አተያይ አላቸው።

ጃፓን በሽንቶይዝም ሃይማኖቷ ‹‹ጃፓናውያን የመላእክት ቤተሰቦች ናቸው፤ የጃፓን ምድርም የተባረከ እና የተቀደሰ ነው። ሳይንስ የሚበለጽገውም ከጃፓን ባህል ውስጥ ተቀድቶ ነው›› ብለው ለራሳቸው በእምነታቸው ከፍ ያለ ግምት ሠርተዋል። ጃፓናውያን በዚህ ምክንያት ዝግ ባህል እና ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ሥነ-ልቦናን አዳብረዋል። ማን አህሎኝነታቸውን በሃይማኖታቸው ሠርተዋል።

ከሁለቱ ሀገራት ውጭ ያለው ብዙው የፈጣሪው ምርኮኛ እና በአምላኩ ስም ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው። ቡርሃን እንደሚለው የዓረብ ለ800 ዘመን ፀንቶ የኖረ ሥልጣኔ በምዕራባውያኑ የተደፈቀው[101] የምሥራቅ ሥልጣኔ ስለምድራዊ ሕይወት የሰጠው ትኩረት ማነሱ ነው። በሕዝብ ደረጃ የኢትዮጵያም ሕዝብ ከምሥራቁ ሀገር ሰው ጋር የሚቀራረብ ዝንባሌ ያለው ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ 99 ከመቶው አማኝ ነው። ሕልሙ፣ ተስፋው እና ስኬቱ በራሱ ብቻ ሳይሆን በአምላክ እርዳታ ነው ብሎ ያስባል። በነገሩ ሁሉ እንደ አምላክ ፈቃድ የሚለውን የትህትና ሐረግ ያዘወትራል። በኢትዮጵያውያን አማኞች ዘንድ ሕይወትን ቀድሞ የተተመነ አድርጎ ማሰብ ለምድራዊ ጨለምተኝነት ጋብዟል። ምንም ነገር የሚሆነው እና የሚደረገው ፈጣሪ ቀድሞ በወሰነው መሠረት ነው፤ ነጋችን ትናንት ተወስኗል በሚል ራስን በፈጣሪ አሳቦ ማስነፍ ይስተዋላል። ምንም እና እንዴትም ብናደርግ ፈጣሪ ከወሰነው ገደብ አናልፍም በሚል ለስንፍና ምክንያት መፈለግ ተለማጅ ስሁታዊ የአማኞች ልማድ ሆኗል።

[101]ቡርሃን አዲስ፣ የዘር ካርድ፤ 2011 ዓ.ም.

የኢትዮጵያውን እምነት አዘል አኗኗር ከፖለቲካ ገበታው ግን የለም፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበራዊ ኑባሬ እና ማርክሳዊ ሥነ-ቁሳዊ የሆነው ፖለቲካዊ ሥሪት በተቃርኖ ውስጥ ያሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በጥቅል ደግሞ በምሥራቁ እና በምዕራቡ ዓለም ያለው እምነታዊ የእሳቤ ተቃርኖ ለወደፊቷ ዓለም የግጭት መንስኤ ይሆናል ሲሉ አሜሪካዊው የፖለቲካዊ ሳይንስ ፕሮፌሰር ሀንቲንግተን በ1996 ዓ.ም. የሥልጣኔው ውድቀት[102] ብለው ለኅትመት ባበቁት መጽሐፋቸው አስነብበዋል፡፡ እንደ ሀንቲንግተን ከቀዝቃዛው ርዕዮተ ዓለማዊ(cold war) ጦርነት በኋላ ዓለም ወደ ሃይማኖት እና ባህላዊ ማንነት ተኮር ግጭቶች ታመራለች ሲሉም ይተነብያሉ፡፡

በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ደረጃም በምዕራቡ የነጭ ካፒታሊዝም ከፕሮቴስታንት እምነት ጋር ሲቆም፤ ምሥራቁ በብዛት የዓረብ ኢምፔሪያሊዚም ከእስልምና ጋር ይዞ ይታያል፡፡ በዓለም ያሉ የግጭቶች መነሻቸውም ይሄው ነው፡፡ የነየመን እና የሶሪያ ውድመት መነሻው እነዚህ ተላታሚ ፍላጎቶች ናቸው፡፡ ለአብነት በሶሪያ ጉዳይ አሜሪካ የሱኒ እስልምናን ደግፋ የሶሪያ ተቃዋሚዎችን ስትረዳ፤ ሩሲያ ከሻኣ ሙስሊሞች ጎን ቁማ የበሽር አላሳድን መንግሥት ከነኢራን ጋር ቁማ ትደግፋለች፡፡

ከሱኒው በኩል በአሜሪካ ጀርባ ሳውዲም ተንጠላጥላ የሶሪያ አማጺያንን ትደግፋለች፡፡ እንደ አጠቃላይ ደግሞ የኒዮ ሊበራሊዝም ፍልስፍና የምዕራባውያን ገዥ እሳቤ ሆኖ ስለወጣ ግብረ ሰዶማዊነት እና አምላክ የለሽነት ሲስፋፋ፤ በምሥራቁ ደግሞ ባህል እና ወግን በመጠበቅ ሃይማኖተኛነት ገዥ መርህ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ልዩነት በዓለም ላይ ዛሬ ላላው ግጭት መነሻ ሆኗል፡፡

[102] Samuel P.Huntington THE CLASH OF CIVILIZATIONS, Simon and Schuster publisher.

4.4 የክርስትና እና እስልምና ተዛናፊ ፓለቲካዊ ተረኮች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ቀለም በመሆኗ ቤተ ክርስቲያኗን ማጥፋት የኢትዮጵያዊነትን ውል የማላላት ሂደት ተደርጐ ተቆጥሯል። ሞሶሎኒ ከሮም እያዘዘ፣ ከጣሊያን ግዛት ከነበረችው ሊቢያ (ትሪፖሊ) ደግሞ ሴራውን ይጐነጉናል። የሊቢያ ሙስሊሞችን ነጻ እንዳወጣናቸው የኢትዮጵያ ሙሲሊሞችን ነጻ እናወጣለን ብለው እነ ግራዚያኒ በኢትዮጵያ ሰበኩ።

በቫቲካን የሮም ካቶሊክ ተባርኮ የመጣው የጣሊያን ጦር ከ2 ሺህ[103] በላይ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ። ኢትዮጵያን ለማጥፋት ጣሊያን **አማራን ማስጠላት፤ በጥላቻ ላይ የተዋቀረ የብሔር ክፍፍል መፍጠር፣ ፀረ ኦርቶዶክስ አቋም በመያዝ ሙስሊሙን ማነሣሣት እና ለፀረ ዘውድ ንቅናቄዋ** እንዲበጃትም የእስልምና እምነት ተከታዮችን በተለየ ሁኔታ ለመጥቀም ተንቀሳቀሰች። በአምስት ዓመቱ የጣሊያን ወረራ ወቅት የአዲስ አበባውን ታላቁ አንዋር መስጊድ እና የደሴውን ሸዋበር መስጊድን ጨምሮ 50 መስጊዶችን በአዲስ አሠርታ፤ 16ቱን ደግሞ ያረጁትን[104] አሳድሳለች። የሸሪአ ፍርድ ቤት፣ በሐረርና በጅማ የእስልምና ኮሌጆች የተቋቋሙ ሲሆን በሀገሪቱ የሚማሩ የሙስሊም ተማሪዎች ቁጥር ከጥቅል ከሀገሪቱ 50 ከመቶው ይሸፍኑ እንደነበር ምንጮችን ጠቅሶ አህመዲን ጀበል ይተነትናል።

የኒኮ ማካቬሊ ምድር የሆነችው ጣሊያን በዐፄ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ያኮረፉ ሙስሊሞችን በሃይማኖት ነጻነት ስም ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ በተቃራኒ ቆሞ በከፋፍለህ ግዛው ሕግ ልትመራ አስባ ነበር። ከሰሜን አፍሪካ ሊቢያን፣ ከምሥራቅ አፍሪካ ከፊል ሶማሊያን እና ኤርትራን ይዛ የጣሊያን ኢምፔሪያሊዝምን

[103] እርቅይሁን በላይነህ፣ አምስቱ የመከራ ዘመናት

[104] አህመዲን ጀበል፣ ሦስቱ ዐፄዎች እና የኢትዮጵያን ሙስሊሞች

ለመገንባት ብታልምም ሊሳካ አልቻለም፡፡ የጣሊያን ውርስ የሆነው ፀረ ዘውድ እንቅስቃሴው ከክርስትና ኃይማኖት ጋር ተዳብሎ በሀገር ውስጥ ቅርጽ እና መዋቅራዊ መስመር ይዞ መወቀስ የጀመረው ጀባህ[105] ዋና ከተማውን/መቀመጫውን ሊቢያ እና ካይሮ አድርጐ መንቀሳቀስ ሲጀምር ነው፡፡

በጣሊያን ወረራ ወቅት ግን ነገሩን ከድጡ ወደ ማጡ ያደረገው ግብጻዊው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በወረራው ወቅት የእምነት ልጆቻቸውን ትተው ወደ ካይሮ ሸሹ፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስ ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. እንዲሁም አቡነ ሚካኤል ኅዳር 24 ቀን 1929 ለሀገራቸው ሲሉ በግፍ ተረሸኑ፡፡ በአቡነ ቄርሎስ መሸሽ ምክንያት ሕዝቡም፤ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ መመራት እንዳለባት ሲሚገቱ ቆይተው በ1940 ዓ.ም. ከግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ስምምነት ተደረሰ፡፡ በሥልጣን ካለ ሊቀጳጳስ መሾም ስለማይቻል አቡነ ቄርሎስ እንዳረፉ ከሦስት ዓመት በኋላ አቡነ ባስልዮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከውሉደ ኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ ሆነው ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም. ተሾሙ፡፡ የጣሊያን ወረራ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ከባድ ፈተና አድርሶ አልፏል፡፡ (ፈተናው በወለደው መፍትሄም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በራሷ መመራት ጀምራለች፡፡)

በሌላ በኩል ከቆለኛው የኤርትራ ክፍል ከ1948 ዓ.ም. በኋላ የተነሣው ጀባህ የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥቱን የጽዮናውያን አካል አድርጎ ለማስቀጠር ማሰቡ በፍልስጥኤም ደጋፊዎች ዘንድ ምቹ ሁኔታን

105 ከጀባህ፤ በፊት ጣሊያን ጸረ አርቶዶክስ ተዋሕዶ አቋም ነበራት፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአድዋ ብሎም በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወቅት ከዘውዱ መሪ እና ከሕዝቡ ጋር አብራ መዝመቷ እና ለትግል ምእመናኗን ማነሣሣቷ የጣሊያን የእግር እሳት ስለሆነባት ለማጥፋት ጥራለች፡፡ በሀገር ደረጃ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ጀባህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትን ከእሥራኤል ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ነው ብሎ በፍልስጤም ደጋፊዎች ጎን ተሰለፈ፡፡

ፈጥሮለታል። እነሶሪያ ሳይቀሩ ከጀባህ እና ከተማሪዎች ጎን ቁመው ዘውዳዊው ሥርዓት እንዲነቀል አድርገዋል። በሶሻሊዝሙ ንቅናቄ ሩሲያ የሙስሊሙን ዓለም ስለያዘችው፤ የኢትዮጵያ አብዮተኞችም ከዚህ ሀቅ ማምለጥ አልቻሉም። ባሕሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983 ብለው ባሰናዱት የታሪክ ጥራዛቸው እንዳመለከቱት፤ ሚያዚያ 10 ቀን 1966 ዓ.ም. በተማሪዎች መሪነት ከ100 ሺህ በላይ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች ተቀናጅተው የሃይማኖት እና መንግሥት ፍቺ እንዲታወጅ፣ የእስልምና በዓላት ብሔራዊ በዓል ሆነው እንዲከበሩ ታላቅ ሰልፍ አድርገዋል።

ሃይማኖት እንደ ብሔር እና የመሬት ጉዳይ የ1966ቱ አብዮት ወፍራም ጥያቄ ሆኖ ተነሥቷል። በዚህም ይመስላል፤ ሕወሓት በአብዮቱ ማግስት ትግሌ ፀረ ጽዮናዊ እና ፀረ አውሮፖ ኢምፔሪያሊዝም ነው ብሎ የተነሣው። ይህ አነሣሡም፤ ከሙስሊሙ ዓለም ፖለቲካዊ ጉርሻ አስገኝቶለታል። ደርግም ቢሆን በ1967/68 ዓ.ም. ጀምሮ አረፋና መውሊድን በብሔራዊ በዓላትነት ሲያስቀጥል በዚሁ ዓመትም የእስልምና ምክር ቤት እንዲቋቋም አድርጓል። ይሄን ማድረጉ ከሊቢያው ሙሀመድ ጋዳፊ እስከ አምላክ የለሽ አማኙ የኩባው ፊደል ካስትሮ ድረስ የዲፕሎማሲ በሩን ይከፍታል።

ሃይማኖት ለምዕመናኑ የበጐ መንፈስ ምናብ ሲሆን ውጤቱም በደግነት ደግ ፍሬን ማፍራት ነው። ሃይማኖት ለፖለቲከኛው ግን የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ እና የኃይል አሰላለፍ ማስተካከያ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ነው። ሳውዲ በፍልስጥኤምና በእስራኤል ጉዳይ ኃይለ ቃል ማውጣት የሚከብዳት የፍልስጥኤምን እስልምና ተጠራጥራ ሳይሆን የአሜሪካን የፖለቲካ ጥቅም ማጣት ስለማትፈልግ ነው። ለሳውዲ ኢራንን የተቃመወ ሁሉ ወዳጅ ሲሆን፤ ለኢራን ደግሞ ከአሜሪካ ጋር የተጎዳኘ ሁሉ ጠላቷ ነው።

የሙስሊሙ[106] ዓለም የኃይል አሰላለፍ በቱርክ በኩል እነኪታር ሲሰለፉ፣ ግብፅ እና ሳውዲ ደግሞ የመንግሥታቸው ህልውና በምዕራባውያኑ በጐፈቃድ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርገዋል። ሳውዲ ከምእራባውያኑ ጎን መሰለፏ በነኢራን እንደ ሙስሊም ጸርነት ተፈርጃለች። በሌላ በኩል የእስልምና እምነትና ባህል አሸናፊ በሆነው የካፒታሊስቱ ዓለም እየተዋጠ መሄዱ በእስልምና ስም የሚደራጁ ታጣቂ ኃይሎችን (armed groups) ፈጥሯል።

ከሱኒ እስልምና የሚቀዳው የሳላፊዝም ንቅናቄ እስልምና አስተምህሮው እንዳይበረዝ፣ ከልማዳዊነቱ እንዲወጣ ይሻል። የዚህ አስተምህሮ ውስን ተከታዮች እ.ኤ.አ በ2001 የአሜሪካ የመከላከያ መሥሪያ ቤትን ካጠቁ በኋላ የሙስሊም አሸባሪዎች ጉዳይ የሚዲያዎች አጀንዳ ሆኗል። ከአልቃይዳ እስከ ታሊባን፣ ከአልሸባብ እስከ ቦኮሃራም፣ ከአይኤስ እስከ ሌሎች የጦር ቡድኖች ከእስልምና አስተምህሮ ያፈነገጠ ግብር ቢኖራቸውም መነሻቸው ግን የእስልምና አስተምህሮ በካፒታሊዝሙ ዓለም ተውጧል፤ የሚል ሥጋት ነው። ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ እስራኤል በሙስሊሙ ዓለም መሃል ገናና ሆና መውጧቷ፤ በምዕራቡ ክንፍ ቅቡል መሆኗ በምዕራቡ እና በዓረቡ ዓለም መካከል ልዩነቱን አስፍቷል። የዚህ ልዩነት ጠርዝ ሽብርተኝነትን ፈጥሯል።

106 እስልምና ሰዎች በአላህ ፈጣሪነት፣ በሙሀመድ ነብይነት፣ በቁርአን እና በሐዲስ አስተምህሮ... ብቻ የሚቆምበት ሃይማኖት አይደለም። እስልምና የሕይወት መንገድ እና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለምም ነው። በመሆኑም እስልምና የራሱ የሆኑ ፍልስፍና እና የሥልጣኔ ታሪክ አሉት። ክርስትናም ቢሆን ከአውሮፓውያኑ የዘመን ስሌት ጀምሮ የራሱ ዓለማዊ አሻራን ያሳለፈ ሃማኖት ነው። ሃይማኖት አንዱ የማኅበረሰብ መገንቢያ በመሆኑ የክርስትና ሃይማኖት ባህል እና ትውፊት የዓለምን ቅርጽ ሠርቷል። ክርስትና የልዕለ ኃያላን ሀገራት ሃይማኖት በመሆኑ በዓለም ላይ በቀላሉ በፖለቲካው እና በፍልስፍናው ተስፋፍቶ የዓለም ሕዝብ አኗኗር መልክ መሆን ችሏል።

በኢትዮጵያ ብዙው ሙስሊም፣ የሱኒ ሱፊዝም[107]አስተምህሮ ተከታይ ቢሆንም፤ ቀለም ቀመስ ሙስሊሞች ግን የሳላፊዝም አስተምህሮን ይቀርቡታል:: ሳላፊዎች ፊደላውያን ሲሆኑ፤ እስልምና በነቢዩ ሙሀመድ ሦስት ትውልዶች በነበረው ሕግ እና ሥርዓት ይዳኝ ይላሉ:: የእስልምና ልማዳዊ ትውፊቶችን ተቃርነው የሚቆሙ ሲሆን፤ በነቢያት መቃብር መስገድን ያወግዛሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ሳላፊዎች ከሱኒዎች ቅርስ እና ባህል አውዳሚዎች የሚል ትችት ይቀርብባቸዋል:: በእርግጥ ሳውዲ ሠራሽ ሆነው የሳላፊ አስተምህሮ ተቆርጦ የተበየነ የሃይማኖት አስተምህሮ የለውም:: አንዳንድ ሳለፊዎች የወሃቢያዊ አስተምህሮ ቅኝትን ይከተላሉ:: አንዳንዶች እነ አልቃይዳ፣ አልሸባብ፣ ታሊባን፣ ቦኮሃራም... የመሳሰሉት ነፍጥ አንጋች ሃይማኖት ቀመስ ታጋዮች የሳለፊ እስልምናን በኃይል እና በጦር ለማንበር ጫካ መርጠዋል:: ሱኒዎች ደግሞ በመሠረታዊ የእስልምና አስተምህሮው ከሳላፊ ጋር ልዩነት ባይኖራቸውም እስልምናን ከባህል እና ወግ ጋር ቀላቅለው መከወንን ይመርጣሉ::

መነሻውን ከጀርመን ያደረገው ፕሮቴስታንት በኢትዮጵያ በብዛት ከኦርቶዶክስ አማኞች የወጣ ሲሆን፤ በአውሮፓ ደግሞ ከካቶሊክ እምነት ተከታዮች ያፈነገጡት ሊከተሉት ችለዋል::

ከሱኒ እስልምናም ሳላፊዎች የወጡ ሲሆን የነቃ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ መስተጋብር ፈጣሪዎች ናቸው:: ፕሮቴስታንት እና ሳላፊ ስለ ዓለም ንቁ (active) ሥነ-ልቦና አላቸው:: በአንጻሩ ሱኒ እና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶዎች ከመሬቱ ዓለም ይልቅ የላይኛው ቤት የሚያስጨንቃቸው፣ ባህል እና ትውፊት ግድ የሚሠጣቸው ነገር ግን ለፖለቲካ ሱታፌ ትኙ(passive) እሳቤ አላቸው::

[107]ሱኒ ኦርቶዶክስ ሙስሊም እየተባለ ይጠራል:: ኦርቶዶክስ ቀዳሚ እና ነባር ሃይማኖት እንደማለት ይተረጎማል:: ኦርቶዶክስ ክርሲቲያን የመጀመሪያ ቀጥተኛ ሃይማኖት ማለት ተደርጎ ይታሰባል::

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በተለይም ከ2004 ዓ.ም. ጀምረው ነጻ የእስልምና[108] ተቋም እንዲገነባ ድምጻችን ይሰማ በማለት መንግሥትን ሲጠይቁ ባጅተዋል፡፡ በሐረር ተወላጁ በሼይኽ አብዱላህ አል-ሐረሪ (ሼክ አብዱላሂ ሙሀመድ ዩሱፍ) ተጸንሶ በሊባኖስ የእስልምና የተወሰኑ ልሂቃን አማካኝነት፤ በኢሕአዴግ አጋዥነት አህባሽ (የሀበሻ ሙስሊም) ለመትከል ሙከራ ተደርጎ ነበር፡፡

መንግሥት አህባሽን ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ቀለም አድርጎ ለመቅረጽ ዘውጉን በሚደግፉ የሃማኖት መሪዎች ጋር አስተምህሮውን ለማስረጽ ቢጥርም፤ ቀለም ቀመስ ሙስሊሞች በቅዋሜ ተነሥተውበታል፡፡ አህባሽ ለዘብተኛ የሙስሊም አስተምህሮን ይከተላል በሚል በምዕራባውያን ጎራ ሞሳድ የሚደግፌው ጸረ ፍልስጥኤም አቋም ያራምዳል በሚል የሚወቅሱት አሉ፤ የአህባሽ ተከታዮች ደግሞ የምስጉኑ ሀበሻ የሼህ አብደላ-ሐረሪ አስተምህሮ ነው ሲሉ አቅርበው ይመለከቱታል፡፡ ይህ የአስተምህሮ ልዩነት በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ለታላቅ ተቃውሞ ተዳርጓል፡፡

የዚህ ትግል መሪዎች በብዛት የሳለፊ አስተምህሮ አድናቂ ሲሆኑ፤ ቀለም ቀመስ በመሆናቸው በኢትዮጵያ የታሪክ ብያኔ ላይም ሂስ ያቀርባሉ፡፡

በተለይም የሙስሊሙ ሚና በሀገረ መንግሥት ግንባታው ላይ አልተጻፈም የሚል ቅራኔ አላቸው፡፡ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያሉ እንደ አዳል ዓይነት የእስላማዊ መንግሥታት በሰሜኑ ታሪክ

[108]የሙስሊም ልሂቃን ለእስልምና ነጻ አስተምሮ እና ተቋም ግንባታ ባደረጉት ተጋድሎ በአክራሪነት እና በጽንፈኝነት ተፈርጀዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠልም ‹‹ጅሃዳዊ ሃረካት›› እና ‹‹አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ›› የመሳሰሉ ዘጋቢ ፊልሞች ለዕይታ በቅተዋል፡፡ የእነዚህ ፊልሞች ተረክ ‹‹ድምጻችን ይሰማ›› የሚሉት ሙስሊሞች የሽብር እና የጦር አጋፋሪዎች ናቸው የሚል ጨመቀ ሐሳብ ለማስተላለፍ የታቀደ ነበር፡፡ የሳላፊ አስተምሮን በአልሀባሽ ለመተካት ኢሕአዴግ ሙከራ አድርጓል፡፡ አልህባሽ ሀገረኛ (ሀበሻ) የእስልምና ክፍል ተደርጎ ከሊባኖስ በመጡ የሃይማኖት አባቶች ተሰብኳል፡፡

ብቻ መዋጣቸውን ያሄሳሉ። የነቢዩ ሙሀመድ ወዳጆችን በ7ኛው መቶ ክፈለ ዘመን ፈቅዶ ያስገባው ንጉሥ አርማህ በክርስቲያን ልሂቃን ዘንድ እንደ ክርስቲያን ንጉሥ ሲታይ፤ በእስልምና ልሂቃን ደግሞ እንደሰለመ እና የአክሱም ሥልጣኔ በሙስሊም ንጉሥ እንደተመራ ይተነትናሉ። ለዚህም የትግራዩ የአልነጃሽ መስጊድ እስልምና በጥንታዊው ሀገረ መንግሥት ላይ አሻራውን እንዳኖረ አንዱ አካላዊ ማስገንዘቢ አብነት ሆኖ ይነሣል።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለ15 ዓመታት ያህል በበላይነት መርቶ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነሥቶ በሀገሪቱ የፖለቲካ ተረክ ላይ ልዩነት የፈጠረው ኢብራሂም አህመድ አልጋዚ (ግራኝ አህመድ) ክርስቲያኑ ልሂቅ እንደ ወራሪ እና አውዳሚ፣ የእስልምናው ደግሞ እንደ ሃይማኖት ጠባቂ የመመልከት አዝማሚያ አለ። በ1976 ዓ.ም. በምሥራቅ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጎሳዎች መካከል ኦጋዴንን ወክሎ የተነሣው የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻ አውጭ ግንባር(ኦብነግ) በፓርቲያዊ መዝሙሩ ‹‹**ግራኝ አልሞተም። ፈረሱም አልተሸነፈም።ደርቡሽ አልወደቀም።**››[109] የሚል የሃይማኖት ቀመስ የፖለቲካ መዝሙር ይዘምራል። ኦብነግ በመዝሙሩ ግራኝ አህመድን እንደ ሃይማኖት እና እንደ ሀገር ነጻ አውጭ በፓርቲ ደረጃ ተመልክቶታል። በእርግጥ ኦብነግ ከምዕራባውያኑ ፊት እንዳይነሣው ንቅናቄው እምነታዊ እንዳልሆነ ቢያስገነዝብም በተግባር ደረጃ ግን የሳላፊ ንቅናቄ ደጋፊ መስሎ ታይቷል። ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የሶማሊያን መንግሥት ለማጽናት ወደ ሞቃዲሾ ወታደሯን ስትልክ ለአልሸባብ ወግኖ የኢትዮጵያን ሠራዊት ተዋግቷል። የግራኝ አህመድን የ15 ዓመት እንቅስቃሴ በመሃል ያሉ ታሪክ አጥኚዎች ከሁለቱም እምነት ዘመም ተረኮች ወጥተው እንደ ፖለቲካ ንቅናቄ ይመለከቱታል።

[109] Mohammed Mealin Seid, The role of religion in the Ogaden conflict. Cirsis in the horn of Africa(journal) .january26,2009

በዐፄ ልብነ ድንግል ሥር ሙስሊሞች፤ በግራኝ አህመድ ጦር ውስጥ ክርስቲያኖች ነበሩ። ዓላማው የንግድ እና የግዛት የበላይነትን ማስፋት፤ የሀገሪቱን ማእከላዊ አስተዳደር መቆጣጠር ታላሚ ያደረገ ነው ሲሉ ይተነትናሉ። ሁነቱን ከእምነታዊ ንቅናቄ አውጥተው ወደ ፖለቲካዊ ሽኩቻ ይወስዱታል[110]። በእርግጥም እምነት የፖለቲካ መሣሪያ ይሆናል እንጂ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ብቻ የሚደረግ ጦርነት ብዙ የለም። የጦርነቶች ሁሉ ሥረ ነገር የተለጠጠ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ነው። በዚህ ዝርዝር ውስጥ እምነት፣ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ጎጥ እና ሌሎች መሰል ልዩነቶች… ለግጭት ማነሳሻ የፊት ምክንያት ይሆናሉ እንጂ ከመጋረጃው በስተጀርባ የተቀመጡ ዓላማዎች አይሆኑም።

በእርግጥ በእነ ዐፄ ልብነ ድንግል እና ግራኝ አህመድ ዘመን ሃይማኖት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ጭምር ስለሆነ ዐፄ ልብነ ድንግል የክርስትና፤ ግራኝ አህመድም የእስልምና ቅርጽ መያዛቸው አይቀርም። ያም ሆነ ይህ ግን ግራኝ አህመድ የተነሣበት የምሥራቅ ኢትዮጵያ እና የአዳል ሥርዎ መንግሥት አንድ የኢትዮጵያ ግዛተ አካል ስለሆነ ወራሪ መባል የለበትም። ከቱርክ ጋር ተነባብሮ በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ቅርሶች ላይ ውድመት ቢደርስም፤ ከወራሪነት ይልቅ ጥፋትን ያስከተለ አንድ የሀገረ መንግሥት ግንባታ አካል አድርጎ መውሰድ ለኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ የታሪክ መዛነፎች እርማት ይሰጣል።

በሃይማኖቶችም ሆነ በፖለቲካው ዘርፍ ያለው የተረክ ዝንፈት የኢኮኖሚ እና የባህል ግጭት ውጤት ነው። ለአብነት አሁን ላለው በእስልምና ስም የተደራጁ ነፍጥ አንጋች ቡድኖች መነሻ በብዛት ሃይማኖታዊ ሳይሆን የሥልጣኔ እና የኢኮኖሚ ግጭት ነው። ዓረቡ ዓለም በኢኮኖሚ ተቸክሎ መቅረቱ እና አለመማሩ በምእራባውያን

[110] አዲስ ታይምስ መጽሔት፣ መስከረም 2005 ዓ.ም. ቅጽ 1 ቁጥር 5።

ብልጫ ተወስዶበት ባህሉ እየተሸረሸረበት መጥቷል። *ሃያ አምስት ዓመት የሞላው አንድ የዓረብ ወጣት በአማካኝ በትምህርት የሚያሳልፈው ስድስት ዓመት ብቻ ነው። ምእራባውያኑ ደግሞ የዕድሜ ጉዟቸውን ከትምህርት ጋር አጣብቀዋል። ምራባውያን ሕፃናት በዓመት 200 ሰዓታትን ለንባብ ሲያውሉ፤ ዓረባውያን ሕፃናት በአማካኝ በዓመት 6 ደቂቃ ብቻ ያነባሉ። ምዕራባውያን ሕፃናት በዓመት 11 መጻሕፍትን በአማካኝ ሲያነቡ፤ ዓረባውያን ከአንድ ገጽ በታች ብቻ ያነባሉ*[111]። ይህ ልዩነት በኢኮኖሚው እና በቴክኖሎጂው ላይ ከፍተኛ ድንበር ፈጥሯል። ዓረብ ነዳጅ ባይኖረው ህልውናው አይረጋገጥም ነበር። ከፍተኛ ኢኮኖሚ ያለው ባህሉን ይሸጣል። ድሀ በሁሉም ነገር ሻጭ ሳይሆን ገዥ ነው። ድህነት ለሕገወጥነት ብሎም ለግጭት እና ለርኅራኄ አልባ ጦርነት ይዳርጋል። የእነ አልቃይዳ መነሻም ይሄው ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ እንደ ብሔሮች የታሪክ እና የሕልም ተቃርኖ ሁሉ፤ የሃይማኖቶች የባህል እና የፖለቲካ ንግርት(discourse) በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ገና ስምምነትን ይጠይቃል። ክርስቲያኑ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ40 ጊዜ በላይ እንደተጠቀሰች ያትታል። እንደ አህመዲን ጀበል ዓይነት የሙስሊም ልሂቃን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኩሽ እንጂ ኢትዮጵያ የሚባል ሀገር እንደሌለ ይጽፋሉ[112]። የብሉይ ኪዳኑ በእብራይስጥ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ኩሽ ብሎ እንጂ ኢትዮጵያ ብሎ አይደለም፤ ኩሽ ደግሞ ግብጽ እና ሱዳንን የሚያካልል የቀድሞ ግዛት እንጂ የዛሬዋን ኢትዮጵያ ማለት አይደለም የሚል ሐሳብ ይነሣል። ሱዳንም ኩሽ እኔ ነኝ ብላ ተቀብላለች።

---

[111]ፍትሕ መጽሔት ቅጽ 01 ቁጥር 42 ነሐሴ 2011 ዓ.ም. የአሊ ሶፋን The anatomy of terror ተጠቅሶ እንደተብራራው።

[112]አህመዲን ጀበል፣ ሦስቱ ዐዔዎች እና ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች

ኢትዮጵያ የሚለው ተገድፎ **‹‹ሱዳን እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች››** ተብሎ በተሻሻለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ መነገር እና መጻፍም ተጀምሯል፡፡ ይህን ግን ዓይን ያወጣ የታሪክ እና የእውነት ክህደት ነው ብላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1990ዎቹ መጀመሪያ ለየዓለም ማኅበረሰቡ በምክንያት እና ታሪክ በመጥቀስ ሞግታለች፡፡

በአንዳንድ ሙስሊም ልሂቃን ዘንድ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በሀገር ትውፊት ላይ የቆመ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም የሚል መሠረታዊ የእምነት አስተምህሮውን ሳይለቅ ትውፊቱን ሀገር በቀል ለማድረግ ሙከራ አድርገዋል፡፡ *ለምሳሌ ሂጃብ እና አበያን በሸማ ማድረግ፣ የራስን የዕደ ጥበብ እና የባህል ውጤቶች ለእስልምና መገለጫነት መጠቀም የሚል ሐሳብ ይነሣል፡፡ በዚህ ረገድ ቱርክ በአብዮተኛው መሪያቸው በሙስጠፋ ከማል አታቱርክ አማካኝነት እስልምናን የቱርክነት ቀለም ሰጥተውታል፡፡ ይህም ልትወድቅ ዳር ደርሳ የነበረችውን ቱርክ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ከፍ አድርጓታል፡፡*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምሥራቁም ሆነ ከኦሬንታሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲሁም ከሌሎች የክርስትና ዘውጎች በተለየ ሁኔታ ትውፊታዊ አስተምህሮዋን በኢትዮጵያዊነት ባህል ቃኝታለች፡፡ የያሬድ ዜማ፣ የግእዝ ፊደል፣ ሸማ አልባስን፣ የዘመን ቆጠራን፣ ልዩ ልዩ ትውፊታዊ ጨዋታዎች… ወዘተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልይ ሆና ትጠቀምበታለች፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ የራሷ ቀለም መፍጠሯ በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ተሻይ እድል ፈጥሮላታል፡፡

ሳውዲ እስልምናን በራሷ ቀለም ልክ መሥራቷ የሳውዲ ባህል በቀላሉ እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ ዓረብኛ የተስፋፋው በእስልምና ምክንያት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን

በግእዝ መገልገል እንደ ልዩ በረከት እንደሚቆጠረው ሁሉ፤ በእስልምናም በዓረብኛ መጠቀም እንደ ትክክለኛ የእስልምና መገለጫ ይታያል።

በኢትዮጵያ እስልምና ከእምነታዊ ሥርዓቱ ባለፈ በባሕልም ከዓረባውያን ጋር በከፍተኛ ሁኔታ መዛመዱ በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ የኦሮሞ ማንነትን በዓረብ ባህል እንዲዋጥ አድርጓል የሚል ወቀሳ ይነሣል። የገዳ ሥርዓት እንዲሟሸሽ እና የዋቄፈና እምነት እንዲላላ አድርጓል ይላሉ። በእርግጥ የኦሮሞ ብሔርተኞች ኦርቶዶክስ ተዋሕዶንም እንደ ዐፄዎች ማስገበሪያ በመመልከት፤ በኦሮሞ ማንነት አጥፊነት ይከሳሉ። በተለይ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን በገዳ መነጸር ብቻ የሚመለከቱ ብሔርተኞች ከክርስትናም ሆነ ከእስልምና የቀደመ ሀገር በቀል ሃይማኖት ዋቄፈና ነው ብለው ያትታሉ።

የኦሮሞ ብሔርተኝነት በባህል ደረጃ በይዘተ ነገሩ ከዋቄፈና የተቀዳ ይመስላል። የዛፍ(ኦዳ) ሥር ሸምግልና፣ የኢሬቻ(የዘመን መለወጫ የምሥጋና በዓል)፣ የገዳ ትውፊታዊ ሥርዓቶች… ወዘተ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ማንጸርያዎች ናቸው። የኢሬቻን እና ሌሎች የዋቄፈናን እምነታዊ ትውፊት ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች እንደ ጣኦት አምልኮ ይመለከቱታል። ይህን እምነት ቀመስ ማኅበራዊ ቅራኔ ለመፍታት ኦሮሞነትን የሁሉም ማንነት አድርጎ ለማስቀጠል በሚደረገው የብሔርተኝነት ወግ መጣረሶችን ስንመለከት የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥትም ሆነ ብሔረ ሀገር ግንባታ ገና ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶችን የሚያስጉዝ እንደሆነ እንገነዘባለን። በአንድ ብሔር መካከል እንኳን ገና ጋርዮሻዊ ሕልም የለም። ብሔሮችን አንድ አድርጎ ኢትዮጵያን ወደ ብሔረ ሀገርነት ለማሳደግ ገና ብዙ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ፈተናዎችን መራመድ ይጠይቃል። በኢትዮጵያ ያሉ ተጣራሽ ፍላጎቶች ከወረዳ እስከ

ማዕከላዊ መንግሥቱ እስካሉ አደረጃጀቶች ድረስ ይዘልቃሉ። ከተጣራሽ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ሃይማኖት ነው።

የኢትዮጵያዊነት የሀገረ መንግሥት ግንባታ ተረክ አስማሚ ባለመሆኑ፣ ብዙ በደቡብ[113] ኢትዮጵያ የሚገኙ የሙስሊም ልሂቃን ኢትዮጵያዊነት በራሱ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ያነሡ ዘንድ ተገደዋል። ይህ ጥያቄ ምላሽ አለማግኘቱ ኢትዮጵያዊነትን በክርስቲያኑ እና በሙስሊሙ ዓይን የተቀራረበ ትርጓሜ ለመስጠት አስቸጋሪ ሆኗል። ለአንዳንድ ሙስሊም ልሂቃን ኢትዮጵያ የመጣችበት የዐፄያዊ ሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት በሙስሊሙ ጭቆና ላይ የተገነባ እንደሆነ ያትታሉ። የእነዚህን ሙስሊሞች ተረክ ደግሞ ሕወሓትም ሆነ ኦነግ በብሔርተኝነት ጽንስሳቸው ቀድመው ተጋርተዋቸዋል። ብሔርተኝነት በልዩ ሁኔታ ታሪካዊ ማስኮረፊያ ይፈልግ ስለነበር፣ ሙስሊሙ በሀገረ መንግሥት ግንባታው እንዳይስማማ ለማድረግ ጥረዋል። የዘመን ቆጠራውን ሳይቀር የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች በተቀራራቢነት ሊቀበሉት አልቻሉም። ሙስሊሞችን የሀገረ መንግሥቱ ግንባታ ባይተዋር በማድረግ በኩል ተዛናፊው የፖለቲካ ተረክ አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የኢሕአዴግ አስተዳደርም ከትናንታዊ የኢትዮጵያ የወል ትዝታ ተፋትቶ አዲስ ማንነት ለመፍጠር ስለሚተጋ ለእስልምና እና ለወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ተሻይ እድልን ይሰጣል። በምትኩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥሪት መግፋቱን ይቀጥላል። ነገሩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሚያደርገው ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

---

[113] ደቡብ ማለት የደቡብ ክልል ማለት ሳይሆን በዳግማዊ ምኒልክ አማካኝነት ወደ ማዕከላዊ መንግሥቱ የተካተቱ የሶማሌ፣ የጋምቤላ፣ የኦሮሞ፣ የሲዳሞ… አካባቢን ማለት ነው። ሰሜን ማለት ደግሞ አማራ፣ ትግራይ.. እንደማለት ነው። አቅጣጫው ከሀገረ መንግሥት ግንባታው ሂደት ጋር የተያያዘ ነው። ሰሜኑ በብዛት የአብሲንያ ሥርዎ መንግሥት እየተባለ ይጠራል።

ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት አባቶች እና የእምነቱ ተከታይ ልሂቃን ለፖለቲካው ትኙ መሆናቸው ነው። ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የኮሚኒዝምን እምነት ጠል አስተምህሮ ለመሞገት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተቋቋመው ማኅበረ ቅዱሳን እምነታዊ አስተምህሮ ላይ ብቻ የተጣበቀ ስለሆነ ዓለማዊ አተያዩ ደካማ ነው። ስለ ሀገረ መንግሥቱ ፖለቲካዊ አዝማሚያ ብዙ አይገመግምም።

በሌላ በኩል ማኅበረ ቅዱሳን እና ቤተ ክህነት ተደጋጋፊ አለመሆናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ3 ሺህ ዘመን ታሪካዊ ውለታዋ እንዲደበዝዝ ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያኗ ለውጥን መሠረታዊ የእምነት አስተምህሮዋን ባልተቃረነ እና ትውፊቷን ባስቀጠለ መንገድ ካልተቀበለች የመቀጨጭ አደጋ ተጋርጦባታል።

ኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥትነቷን በብሔር እና ብሔረሰብ ስትገልጽ፣ ኢኮኖሚ እና ማኅበረ-ፖለቲካዋም በብሔር ቋጠሮ ውስጥ የገባ ሆኗል። ቀጣይ የፋይናንስ እና የሀገራዊ ቀለም ሁናቴም በእምነት ላይ የወደቀ መሆኑ አይቀርም። እምነታዊ ባንኮች፣ ሚዲያዎች፣ ፍርድ ቤቶች ወዘተ ስለሚመሠረቱ ልክ እንደ ብሔረሰቦች የጎሪጥ መተያየቱ አይቀሬ ይሆናል። ሃይማኖቶች ወደ ኢኮኖሚው ከዘለቁ ጠላታቸው ሰይጣን ሳይሆን ሌላኛው ሃይማኖት ይሆናል። በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት፣ የዓረቡ እና የምዕራቡ ዓለም ተቃርኖ በውስጡ እምነታዊ የኢኮኖሚ ሽሚያ አለበት። በኢትዮጵያም ንግድ በሙስሊሙ፣ የመንግሥት ቢሮክራሲ በብዛት በክርስቲያኑ የተሞላ ነው። መሬት የክርስቲያኑ ሲሆን፤ እደጥበብ እና ንግድ የሙስሊሙ መስሏል።

የመሬት ሕጉ መሬትን የብሔረሰቦች እና የመንግሥት መስጠቱ ነው እንጂ ሙስሊም ነጋዴዎች በግለሰብ ደረጃ መሬት በመግዛት የኢኮኖሚ እምነታዊ መደቡን ማፍረስ ይችሉ ነበር። ይህ

ታሪካዊ እና እምነታዊ የምጣኔ ሀብት መደብ በሃይማኖቶች እና በመንግሥት በየፈርጁ ካልተመለሰ ግጭት ቅርብ ይሆናል:: የቀጣዩ ዘመን የግጭት ሥጋት ማንነታዊ ፖለቲካ ሲሆን፤ ብዙውን እጅ ደግሞ የሃይማኖት ጉዳይ መያዙ ቅርብ ይመስላል::

4.5 የሃይማኖት ዲፕሎማሲ

የሀገር ውስጡን ፖለቲካ ሚዛን ለማስጠበቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀዳሚ ስፍራ ትይዛለች:: ባላት የተከታይ ብዛት፣ በሃገረ መንግሥት ግንባታው ባደረገችው ሚና፣ ሀገራዊ ባህል እና ታሪክ ላይ የራሷን ቀለም ስለጻፈች በሀገሪቱ ፖለቲካ የኃይል ሚዛንን የመወሰን አቅም አላት:: የኢትዮጵያ ታሪክን ከቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ነጥሎ ለማየት በራሱ ፈታኝ ነው:: የመንግሥትነት እና የሃይማኖት ድርብ ሚና ስለነበራት በዘመን ቆጠራ፣ በሕግ፣ በፍልስፍና፣ በፊደል ቀረጻው፣ በሙዚቃ እና በሌሎች የሥነ-ሕዝብ መለያዎች ሁሉ አሻራዋ ጉልህ ነው::

በሌላ የሐሳብ ጥግ እስልምናና ፕሮቴስታንት ለውጭ ዲፕሎማሲ የኃይል አሰላለፍ በላጭ ሚና አላቸው:: እስልምና በሙስሊሙ ዓለም ዓለም አቀፍ ጥበቃ ይደረግለታል:: እስልምና ከሃይማኖትነቱ ባለፈ የሥነ-መንግሥት ምንጭ ነው:: ብዙዎቹ እስልምና በሚበዛባቸው ሀገራት እስልምና መንግሥታዊ ሃይማኖት ነው:: በሰሜን አፍሪካ እና በዓረብ ሀገራት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሆኖ ያገለግላል:: በመሆኑም ከውጭው ዓለም ለመገናኘት የኢትዮጵያ እስልምና ጠቃሚ የዲፕሎማሲ ሜዳ ሊሆን ይችላል:: ከ1966 ዓ.ም. በኋላ የመጡ ብሔርተኛ ኃይላት ወገንተኝነታቸውን ከሙስሊሙ ዓለም ጋር አድርገው ጉርሻ ተቀብለዋል::

ፕሮቴስታንትም ለዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚበጅ አንዱ የክርስትና ዘውግ ነው:: እነኦነግ የብሔርተኝነት እህል ውኃቸውን ከጀርመን ጋር ያደረጉት ሃይማኖት ቀመስ በሆነ ፖለቲካ ምክንያት ነው::

‹‹ኦሮሞ ጥቁር ጀርመን›› ነው የሚሉትም የጀርመን ሉተራውያን ናቸው:: በኢሕአዴግ ዘመን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት የነበሩት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ኦሮሞ ጥቁር ጀርመን ነው ያሉት ቄስ ሀሰል ብላት የተባሉ ጀርመናዊ ናቸው ይላሉ:: ቄሱ፣ መነሻ የሚያደርጉት ጀርመናዊው ሰባኪ እና የማኅበረሰብ አጥኚ ክራፕፍን ነው::

አጥኚው በ1836 ዓ.ም. የሉተራዊ ሃይማኖቱን ሊያስፋፉ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አማርኛ፣ ግእዝ እና ኦሮምኛን በእግረ መንገድ ተማረ:: ክራፕፍ በአማራ እና በትግራይ አካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትና የማኅበረሰቡ ኑሮም ሆነ ፖለቲካ ስለሆነ ሌላ ሃይማኖት ለመቀበል ዝግጁ አልሆንለት አለ:: ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሲያመራ እምነት ተከታዮችን[114] አገኘ:: ለእነዚህም ሃይማኖት ሰበከ፤ አስተማረ:: ክራፕፍ በዚህ አጋጣሚ ኦሮሞ ጋር ልዩ ግንኙነት ፈጠረ:: ክራፕፍ ወደ ኬንያ አቅንቶ ፕሮቴስታንትነትንም ሰብኳል:: በኬንያ የሚገኙ ኦሮሞዎችንም አገኘ:: ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ[115] እንደሚተርኩት ‹‹*ቄስ ሃሰል ብላት የክራፕፍን መንገድ ተከትሎ፤ የኦሮሞዎች የአካል ቅርጽ እና ጥንካሬ ከጀርመን ጋር ይመሳሰላል:: ጥንታዊ ጀርመኖች ገንፎ ተመጋቢ እና ከብት እያረቡ በየቦታው የሚስፋፉ ነበሩ፤ ኦሮሞውም እንደዛው ነው:: ጀርመን በጀርመን፣ በአውስትራሊያ እና በስዊዘርላንድ ተስፋፍቶ እና ተበትኖ ይገኛል:: ኦሮሞም በኬንያ እና በኢትዮጵያ ተበትኗል:: ጀርመን ተደራጅቶ አውሮፓን ሁሉ በቁጥጥሩ ለማስገባት ሞክሯል:: ኦሮሞም ተደራጅቶ ሁሉን አሰባስቦ ክርስቲያናዊ መንግሥት ማቋቋም አለበት::*›› ሲሉ እኛ ኦነጎችን ይመክሩን ነበር ብለዋል::

---

[114]Journals of Isenberg and Krapf,Text of Book at Archive.org

[115]*እፎይታ መጽሔት*፣ 6ኛ *ዓመት ቁጥር* 1 *መስከረም-ጥቅምት* 1993 *ዓ.ም*.

ቄስ ሃሰል ብላት በጀርመን የኦነግ ጭንቅላት ነበሩ የሚሉት ዶክተር ነጋሶ፤ ኦነግ በእንደዚህ ዓይነት የሂትለር ጓድ ዘረኛ እና ተስፋፊ ቄስ መመራቱ የልዩነት ምንጭ ሆኖ ከኦነግ አፈንግጠው ወደ ኦሕዴድ(ኦዴፓ) እንዲገቡ እንዳደረጋቸውም ለእፎይታ መጽሔት ተናግረዋል፡፡ የኦሮሞ ሰብዓዊ ልማት ማኅበር የመሳሰሉ የሲቪክ ማኅበራትም በበርሊን ሚሲዮናውያን እርዳታ አማካኝነት ለመቋቋም ችለዋል፡፡ የጀርመን ሰባኪያን በኦሮሞ ብሔርተኝነት ውስጥ የላቀ አበርክቶ አድርገዋል፡፡

በእርግጥ ሃይማኖት ብቸኛ የዲፕሎማሲ መገንቢያ አይደለም፡፡ ቢሆንም ግን እንደ አውዱ በታሪክ እና ዛሬ በሚሆነው ፖለቲካ ጭምር ሃይማኖትን እንደ አንድ የዲፕሎማሲ አማራጭ መጠቀም ተለማጅ ባሕርይ ሆኗል፡፡

ምዕራፍ አምስት

አብዮቶች እና እርምጃቸው

5.1 አብዮት

ፍትሕ የአሸናፊዎች ሎሌ ናት፡፡ ዓለምም የባለድሎች ገጸ በረከት ናት፡፡ ተሸናፊዎች የአሸናፊዎች የጉዳይ ሁሉ መልመጃ ናቸው፡፡ እውነትም ብትሆን የበላዮች ገረድ ናት፡፡ የሕዝብ መሪነት የተረጋገጠበትን-**ዴሞክራሲን** የወለደችው የግሪኳ አቴንስ ከተማ ዴሞክራሲ ለሴቶች እና ለባርያዎች አያስፈልግሞ ብላ ደንግጋ ነበር፡፡ ዴሞክራሲን አሳደግሁት የምትለው አሜሪካም ብትሆን በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ 10 ባሪያዎችን እንደ ስድስት ዜጋ እቆጥራለሁ ብላ አውጃ ፍጹም ቸር መሆኗን ለማሳየት ሞክራ ነበር (ዳሩ በነማርቲን ሉተር ኪንግ አብዮት ኢ-ሕጋዊው ሕግ ተሸሯል፤ ሕግ ብዙ ጊዜ ፍትሃዊ አትሆንም፡፡ ሳትሆን በአብዮት ትታረማለች፡፡ ሕግ የአሸናፊው መግዣ መሣሪያ በሚሆንበት ጊዜ ሕግን አለማክበር ለፍትሕ እንደ መቆም ይቆጠራል)፡፡

የግብጽ ፈርኦናውያን ሀበሻ ጳጳስ ሆኖ መምራት አይችልም ብለው በፍትሃ ነገስት[116] ደንግገዋል፡፡ ኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖትን በይፋ ከተቀበለችበት ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ጳጳስ በብድር ከግብጽ

[116] ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ ዐጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት

እያመጣች 1ሺህ 600 የሚደርሱ መስከረሞችን አሳልፋለች፡፡ አሸናፊ የሆነው የሃይማኖት ቀኖና ሳይቀር ሠርቶ ይመለካል፡፡ ከ190 ከሚልቁ የተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገራት መካከል አሜሪካ ብቻዋን 180 ምናምኑን ሀገር ውሳኔ የመሻር አቅሞ አላት፡፡ አብላጫ ድምጽ፣ ዴሞክራሲ፣ ፍትሕ… ለተሸናፊው አይሠራም፡፡ ፍትሕ በተሸናፊ ታዛ የለም፡፡ ኢየሩሳሌም በአሜሪካ ፊታውራሪነት በ2010 ዓ.ም. የእስራኤል ዋና ከተማ ሲሆን፤ ፍልስጥኤም የኔ ነው ብትል ሰሚ አላገኘችም፡፡ ምክንያቱም፣ እውነት እና ፍትሕ የአሸናፊው ተላላኪዎች ናቸውና፡፡

አምባገነኖች ሕግ ይሠራሉ፡፡ ደካሞች በሕጉ ይመራሉ (ይተገብራሉ)፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰው እና ምድሩ የእኔ ነው፡፡ ሥልጣኔም ከፈጣሪ የተሰጠኝ ነው አሉ፡፡ ሕዝቡም አዎ ብሎ ጃንሆይ ወይም ጥላየ፣ ከለላየ ብሎ ለመጥራት ተገደደ፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱ አንድ አብዮተኛ በሺ ጸረ ሕዝቦች ይመነዝራል ብለው ማሉ፡፡ ሕዝቡ በመሐላቸው ተገዛ፡፡ ዓለም ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ አሸናፊዎች ናት፡፡

የአምባገነኖችን መሐላ ለማፍረስ እምቢ ባይነት ያስፈልጋል፡፡ ይህ እምቢ ባይነት አብዮትን ይፈጥራል፡፡ በተሳካ አብዮት ሕግ እና ፍትሕን ለማኅበረሰብ በእኩልነት ማደል ይቻላል፡፡ አሲምግሉ እና ሮብሰን የተባሉ የሥነ-እድገት አሳቢያን ሀገራት ለምን ይወድቃሉ ብለው በ2012 ባወጡት ዝነኛ መጽሐፋቸው ለሀገራት ውድቀት መነሻ ሕዝብ ያሸነፈበት አብዮት[117] አለመደረጉ ነው የሚል ጭምቅ ሐሳብ ያነሣሉ፡፡ ጸሐፍቱ በአብነት የግብጽን ጉዳይ ያነሣሉ፡፡

ግብጽ ከአፍሪካ ምድር የቀደመ እና የወፈረ ሥልጣኔ ባለቤት ብትሆንም፤ ሥልጣኔዋ ከዘመን ጉዞዋ ጋር አብሯት አልተከተለም፡፡

[117]Daron Acemoglu and James A.Robinson, **why nations fail.**

ግብጽ በመጀመሪያ በኦቶማን ቱርክ፣ ከዚያም በ1789 ደግሞ በፈረንሳዩ ጦረኛ ናፖሊዮን ቦናፓርቲ፤ ቀጥሎም በእንግሊዝ እጅ ሥር ወድቃ እስከ 1952 በምርኮ ኖራለች። በ1952 ግብጽ ባደረገችው አብዮት ከእንግሊዝ ተላቃ በነሙባረክን መሰል ቤተሰባዊ ሥርዎ መንግሥታት ሥር ወደቀች። ፕሬዝዳንት ሙባረክ በ2011 የጸደይ አብዮት ሲፈነገሉ፤ የሀብት መጠናቸው 70 ቢሊየን ዶላር እንደደረሰ እነ ሮብሰን መዝግበዋል። አሲሞግሉ እና ሮብሰን ከግብጽ የአብዮት ታሪክ የተወሰኑ የፖለቲካ ሊሂቃን (ቡድኖች) አሸነፉ እንጂ ሕዝብ አላሸነፈም የሚል ድምዳሜ ይሰጣሉ።

ሕዝብ አሸናፊ ያልሆነበት አብዮት ፈረቃዊ አምባገነናዊነትን ከማስፈን ያለፈ ለእድገት እና ሥልጣኔ መነሾ አይሆንም። እንግሊዝ በ1688፣ ፈረንሳይ በ1798... ያደረጉት አብዮት የሕዝብ አሸናፊነት የተረጋገጠበት ስለነበር ሕዝባዊ ፖለቲካ እንዲመሠረት አድርጓል። ሕዝባዊ ፖለቲካው ደግሞ እነ እንግሊዝን ወደ ኢንዱስትሪ እና ቴክኖሎጂ አብዮት ገፍቷቸዋል። እነ አንግሊዝ በአብዮታቸው የኢኮኖሚ ጡንቻቸውን ሲያፈረጥሙ፤ የሌሎች ሀገራት አብዮት ግን ለተወሰኑ ቡድኖች ብቻ ሆኖ በመቅረቱ ሊመክን ችሏል። እንግሊዝ እና ፈረንሳይ ባደረጉት አብዮት የዓለም አሸናፊ ሀገር ሆነው ስለወጡ ዓለምን በራሳቸው ባህል እና እሳቤ ልክ በቅኝ ግዛት ሰበብ ፈጥረዋል። ብዙ ሀገራት እንግሊእኛን እና ፈረንሳይኛን ለመናገር የተገደዱት ሁለቱ ሀገራት ባደረጉት የፖለቲካ መሻሻል ምክንያት ነው።

በአፍሪካ የተደረጉ የ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ ከቅኝ ግዛት ቀንበር ነጻ እንውጣ (Pan Africanism) የሚሉ አብዮቶች ብዙዎቹ የመከኑ ነበሩ። የተወሰኑ ሀገር በቀል ቡድኖች የራሳቸውን ሀገር ቅኝ ለመግዛት ምቹ እድል ያገኙበት አብዮት ሆኖ አልፏል። ሀገር በቀል ቅኝ ገዥዎች ተፈጥረዋል። ለአብነት ግብጽ በእንግሊዝ

ከምትገዛ እና 70 ቢሊየን ዶላር ከደሀ ጉረሮ ነጥቆ በያዘው በፍጹም አምባገነናዊው ፕሬዝዳንት ሙባረክ ከምትመራ የቱ ይሻላት ነበር?! መቼም በ2011 የዓረብ አብዩት ትሻልን ሰድጀ ትብስን አገባሁ የሚያስብል ብሂል የግብጽ ወጣቶች በጣሂር አደባባይ ሳይተርቱ የቀሩ አይመስሉም።

5.2 የአብዮት መነሾዎች

ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች፣ የሥርዓቶች መበስበስ፣ የልሂቃን መቀናጀ እና የሕዝቡ የንቃተ ፖለቲካ መዳበር.... ለአብዮት ገፊ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህም አምባገነን መንግሥታት ሕዝብ እንዳይነቃ ማሥራብን እና ማደደብን በስልትነት ይጠቀማሉ። ዶክተር ፀሐይ ጀምበሩ እንደሚሉት ሕዝብን አደደቦ ለመግዛት *ሚዲያን በብቸኝነት መያዝ፣ ታሪክን ማወናገር እና ትምህርትን ለፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀሚያ ማደረግ*[118] የማደደቢያ ማስፈጸሚ ስልቶች ናቸው ይላሉ።

5.3 አደድቦ መግዛት

የደደበ ማኅበረሰብ ጭቆናን ባህል ያደርጋል። መገዛትን ልማድ አድርጎ ለመብት መታገልን እንደ ነውር ሊቆጥር ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚተረከው ሙሴ በፈርዖን አገዛዝ ሥር የነበሩ እሥራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት ሲታገል እስራኤላውያን ግን የግብጽ ዱባ ናፈቀን ብለው አጉረምርመዋል። እስራኤላውያን በወቅቱ ከነጻነት ይልቅ መገዛትን ለምደዋል። ድህነትን እና ጭቆናን ለምዶ እንደመኖር ዓይነት የማኅበረሰብ በሽታ የለም። በ1953 ዓ.ም. በኢትዮጵያ በተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት ሕዝቡ ጃንሆይን ለመገልበጥ ማሰብ እንደ ምጻት ቀን ቆጥሮታል። የስምንተኛው ሺ የመድረሱ ደወል አድርጎ ወስዷል። ቀዳማዊ

[118] ዶክተር ፀሐይ ጀምበሩ፣ የአንጎሌ ሁካታ

ኃይለ ሥላሴ ‹‹ፍጹም›› ተደርገው በሚዲያው፣ በትምህርቱ እና በምድጃ ዳር ተረት መነገራቸው ሕዝቡ ቢጨቆንም፣ ለጽድቅ እንደሚከፈል መሥዋዕትነት ተመልክቶታል፡፡ ጣሊያን በኤርትራ እና በሊቢያ በ1928 ዓ.ም. አካባቢ ደግሞ በኢትዮጵያ ቅኝ ለመግዛት ስትመጣ መጀመሪያ ያደረገችው ትምህርት ላይ እና የተማረው ላይ መዝመት ነበር፡፡ ትምህርት ቤቶችን የጦር ምሽግ ስታደርግ፤ መምህራንን ደግሞ በአርበኝነት እየጠረጠረች ወደ እሥር አስገባች፡፡ የቅኝ ተገዥ ሀገራት ተማሪዎች በጥቅሉ ከአምስተኛ ክፍል በላይ እንዳይማሩ እግድ[119] ጣለች፡፡

በሌላኛው አጥናፈ ዓለም ደግሞ፤ ዛሬም ድረስ ኮሚኒስቷ ሰሜን ኮርያ የኪም ጁን ኡንን ቤተሰብ እንደ መላእክት ቤተሰብ በመቁጠር ለመቃወምም ሆነ ለመተቸት ማሰብ በሕዝቡ ሥነ-ልቦና ዘንድ በነውርነት መዝገብ ሰፍሯል፡፡ ብሔራዊ መዝሙሩ፣ የታሪክ ትምህርቱ፣ የእውነት እና እምነት ምንጭ የኪም ቤተሰብ ተደርጎ በሥርዓተ ትምህርቱ ተሰድሯል፡፡ ኪም ጁን ኡን በሰሜን ኮርያውያን ዘንድ ከሰው ዘለል ገጽታ መላበሱ እንደ ሰው ቢመገብም መጸዳጃ ቤት ግን እንደማይሄድ ተደርጎ ተስሏል፡፡ የፖለቲካ ንግርቱ በፈጠረው እሳቤ ምክንያት እንደ ኪም ጁን ኡን ጸጉር መስተካከል፣ በስሙ መጠራት፣ የለበሰውን መልበስ ሁሉ ክልክል ሆኗል፡፡

በሳውዲ ዓረቢያ ያለው ሁኔታም ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ የሳውዲ ዜጎች በዘውዳዊ መንግሥት ዛሬም ድረስ እየተመሩ፤ ነጋሾቻቸውን ብቸኛ የእምነት፣ የእውነት፣ የገንዘብ ምንጭ አድርገው ይወስዷቸዋል፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ሀገራት ለሕዝቡ ጭቆና ባህል ሲሆን፤ መጨቆን ደግሞ ለመሪው የመሪነት ደንብ ነው፡፡ ይህ በሆነበት ጊዜ ነጻ አውጭው ከጨቋኙም፣ ከተጨቋኙም ሁለት ጎን ስለት ይወጋዋል፡፡ ነጻ አውጭው ካሸነፈ፣ ጨቋኙንም

[119] ሀብታሙ አለባቸው፣ ታላቁ ተቃርኖ (2009 ዓ.ም.)

ተጨቋኙንም ነጻ ያወጣዋል። እንደ መሃተመ ጋንዲ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ዓይነት የሰላማዊ ትግል አራማጆች የጨቋኞችን መጥፎ ሞራላዊ ባሕርይ በማሳየት ጨቋኖች ጭቆናቸውን እንዲጠሉት በማድረግ ረጋጮችንም ነጻ አውጥተዋል።

5.4 አደህይቶ መግዛት

ሌላኛው የአምባገነን መሪዎች ባሕርይ ማሥራብ ወይም ማደህየት ነው። የተራብ ሰው የሆዱ ጥገኛ ስለሚሆን ከፍ ብሎ ወንበር ላይ ስለበቀሉ እሾሆች ነቀላ ሊያስብ አይችልም። ትግሉ ቁርሱን በልቶ እራቱን እንዴት እንደሚበላ፣ ካናቴራ እንዴት እንደሚለብስ፣ ስለወር የቤት ኪራይ የክፍያ ምንጭ ወዘተ አብዝቶ ይጨነቃል። የቤተ መንግሥት ወሬ ቅንጦት ወይም የማይደረስበት መስሎ ይታየዋል። የሩሲያው ጆሴፍ ስታሊን ለኅብረተሰባዊ አብዮቱ አይመቹም ያላቸውን የዩክሬን ብሔሮች መሬታቸውን እንዳያበቅል በማድረግ፣ ገበያ በመዝጋት፣ መሬት በቀጥታ በመንጠቅ… ሰው ሠራሽ ርሀብ ፈጥሮ ሚሊየኖችን ለሞት እና ለስደት ዳርጓል። በ1932 እና 1933 ዓ.ም. አርሶ አደሮች በርሀብ ቀያቸውን እየለቀቁ ሲሰደዱ የስታሊን አገዛዝ እየተከተለ በተለቀቀው መሬት የመንግሥት እርሻ ድርጅት እንዲከፈት ማድረግ ችሏል።

የስታሊን ደጋፊዎች ይሄን ፕሮግራም የኅብረተሰባዊ መንደር ምሥረታ(villagization) አንድ አካል አድርገው ሲወስዱት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ግን ርሀባዊ ሽብር ብሎ ፈርጆታል። በዚህ ስታሊን ፈጠር በሆነ ርሀብ ከ7 እስከ 10 ሚሊየን ሰዎች ሕይወታቸው እንዳለፈ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ2003 ዓ.ም. ያወጣው ሪፖርት ያሳይል። ስታሊን በዚህ የማሥራብ ሂደት ለጊዜው የዩክሬንን ብሔርተኝነት እና ከሶቭየት ኅብረት የመገንጠል ስሜት እንዲቀንስለት አድርጓል። ሴራው ግን ለዘላቂ መፍትሄ

ሳይሆን ቀርቶ፤ ዩክሬን በ1991 ነጻ ሀገርነቷን አውጃለች:: የሌኒንም ሆነ የስታሊን የእዝ ሰንሰት በ1991 በተነሣ የልገንጠል አብዮት ሙሉ በሙሉ ተቆራርጦ ሲወድቅ፣ ታላቋ ሶቬት ኅብረት (ሩሲያ) ወደ 15 ሀገር እንደ ጫጩት ልትፈለፈል ችላለች::

የስታሊን አድናቂ የሆነው የኢራቁ ሳዳም ሁሴንም በኤፍራጥስ እና ጤግሮስ ወንዞች የሚገኙ የማርሽ ዓረብ ብሔረሰቦችን የወደፊት ፖለቲካ ሥጋት ይሆናሉ ብሎ በማሰብ ወንዛቸውን አድርቆ ለርሀብ እና ስደት ጋብዟቸዋል:: የሱሜራውያን ሥልጣኔ ባለቤት እንደሆኑ የሚነገርላቸው ማርሽ አረቦች በደቡባዊ ኢራቅ ይገኛሉ:: ማርሾች ልክ እንደ ኢራን የሺኣ ሙስሊም ተከታዮች በመሆናቸው በ1980ዎቹ በተደረገ የኢራቅ እና የኢራን ጦርነት የኢራን ወታደሮች ደጋፊ መስለው ታይተዋል:: የሺኣ ሙስሊምን ያቀነቅናሉ:: በዚህ ቂም የቋጠረው ሳዳም ሁሴን በመጽሐፍ ቅዱስ ከግዮን ወንዝ ጋር በአቻነት የሚጠሩትን ኤፍራጥስ እና ጤግሮስ ወንዞችን ጠልፎ ወደ ማርሽ ብሔረሰብ እንዳይፈሱ አደረገ::

ወንዝ እና ሐይቃቸውንም በኬሚካል አደረቀው:: የ5 ሺህ ዘመን የሥልጣኔ ባለቤት የሆኑት ሱሜራውያን(ማርሽ ዓረብ) ከ90 በመቶ በላዩ በስደት እና በሞት አካባቢያቸውን ለቀቁ:: ከ1980ዎቹ በፊት በማርሽ ግዛት ከ500 ሺህ በላይ ማርሾች ይኖሩ ነበር:: በ2003 እ.ኤ.አ ግን በኤፍራጥስ እና ጤግሮስ ወንዝ ዳርቻዎች የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር ወደ 40 ሺህ ዝቅ አለ:: ሳዳም እንደተመኘው አካባቢው እንኳን የተቃዋሚ ፓርቲ መፈልፈያ ሊሆን ለመኖርም የማይሆን እንደ ሳሃራ በረሃ ደረቅ እና የሞት መንደር ሆነ:: ማርሾችም እንኳን ሳዳምን ሊቃወሙ የስደት ድንኳን ለማግኘትም ፈተና ሆነባቸው::

ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምም በሰፈራ ሰበብ በግዳጅ በወሰዱት እርምጃ ብዙዎች በበሽታ ሲሞቱ፤ ሌሎቹ ደግሞ በርሀብ ሊሞቱ ችለዋል። ስታሊን በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላለ ፖለቲከኛ ለብዙዎች አርአያ ሰብ ሆኖ ስለወጣ፤ ብዙዎቹ ስታሊን ያደረገውን ለማድረግ ተጣድፈዋል። የስታሊን ደቀመዝሙሮች ደግሞ አገዛዛቸውን በማደደብ እና በማደህየት ላይ መሥርተዋል።

በርሀብ እና በስደት ያለ ሕዝብ የዕለት አጀንዳው ዛሬ መሽቶ ነገ እንዴት ይንጋ የሚለው ጉዳይ ብቻ ይሆናል። የተራብ ሁሉ ለጭቆናዊ አገዛዝ ማደሩ አይቀርም። በኢትዮጵያም ከጭቆና ጋር ተላምዶ መኖር እሴት የሆነ ይመስላል። የነበረው ሂዶ፣ የመጣው ሁሉ ሲገዛ የሄደውን እየተቹ ያለውን እያወደሱ መኖር ተለማጅ የፖለቲካ ባህል ሆኗል። በኢትዮጵያ የተፈጠሩ አብዮቶች ሁነታዊ እንጂ ሁነት ዘለል ሆነው የተቃና ተቋም እና ሥርዓት ለማቆም አልዋሉም። አብዮቶች ከዘመቻ፣ ከጭብጨባ እና ከመፈክር ድንፋታ ተሻግረው ተቋማዊ ቅርጽ የያዙ አልነበሩም።

አቶ ኃይለ ማርያም ወርደው ዶክተር አብይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆኑ የሕዝቡን አቀበባል በተመለከተ ሚያዚያ 27 ቀን 2010 ዓ.ም. በማኅበራዊ ሚዲያ ጭብጨባን በተመለከተ እንዲህ ታዝቤ ነበር፡

5.5 የጭብጨባ ገጾች

መድረኩን ስትመራ፣ ነገሩን ስትካካ

ታዳሚህ በሙሉ ቢያጨበጭብልህ በፍጹም አትርካ

ጭብጨባ ከሆነ ሁለት ፊቶች አሉት

በፍስሃ እርካታ እጅን ሚያሻሹበት

ወይ በንዴት በታከት እጅን ሚደቁበት

ሕዝቡ ጠየቀ፡፡
‹‹ከተሞቻችን ልማት አላዩም፤ ኢንዱስትሪም
አልተስፋፋም?!”

‹‹ደብረ ብርሃን፣ ደሴ፣ ጎንደርና ማርቆስ በዐዬዎቻችሁ ቀድመው የለሙ ከተሞች ናቸው፡፡ ገዥ መደቦች ያለሟቸው ስለሆኑ አሁን እኛ በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ከተሞችን ለማካካስ እናለማለን፡፡›› ጭብጨባው የአቶ መለስ ዜናዊን ንግግር አቋረጠው፡፡ አቶ መለስ በጭብጨባው እንደምንም ብለው አየር ከሳቡ በኋላ፡ ‹‹ይገርማል! ባሕር ዳርን የመሰለች የዓባይ እና ጣና በረከት ያደረባት ለምለም ከተማ በኢንዱስትሪ ጭስ ትታፈን ብሎ መጠየቅ ነውር ይመስለኛል፡፡›› ጭብጨባው አቋረጣቸው፡፡

የተሰብሳቢው ጭብጨባ ባሕር ዳር እንደ ዱባይ ወይም ኒወርክ ልትለማ ነው የተባለ ይመስል ነበር፡፡ ጭብጨባው ከጣናው ሞገድ ድምጽ ልቆ ተሰማ፡፡

አቶ መለስ በአጨብጫቢዎች እየተዝናኑ፡‹‹ አስቡት ባሕር ዳር፣ የጎጃም አካባቢ በተፈጥሮ የለማ ነው፡፡ የለምለም ምድር ባለቤቶች ናችሁ፡፡ ኢንዱስትሪ ይሄን ልምላሜ ያከስለዋል፡፡ ያጠፋዋል፡፡ መስኖ እና ጤፍን በመስመር በመዝራት መጠቀም ነው፡፡ ጎጃም እኮ በምሥራቅ አፍሪካ ለምለሙ ምድር ነው፡፡ የገጠር ልማታችን መሠረቱ ጎጃም ነው፡፡›› አቶ መለስን አሁንም ጭብጨባው አቋረጣቸው፡፡

… .

ሌላኛው ትዕይንት በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት ፊት ቀጥሏል፡፡ “ጤፍ ተወደደ የምትሉት ልክ ነው፡፡ ዛሬም መሬታችን ጤፍ እያለማ ነው፡፡ ነገር ግን በልማታዊ መንግሥታችን ጤፍ ተመጋቢው ስለጨመረ ፈላጊው እና አቅርቦቱ አልተመጣጠነም፡፡ ከኢሕአዴግ በፊት ጤፍ የማይበላው አሁን ጤፍ እንጀራ መብላት

ጀምሯል:: ሰዉ የኑሮ ሁኔታው ተቀይሯል:: በዚህ ምክንያት ጤፍ ተወደደ:: የዋጋ ንረቱ 11 በመቶ በማደጋችን ምክንያት የመጣ ለውጥ ነው:: እንቁላልም የናረው ትናንት እንቁላል የማይበላው ዛሬ መብላት በመጀመሩ ነው:: በሌላ በኩል፣ በደቡብ በቤንች ማጂ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ አማራ ተፈናቀለ የሚባለው የትምክህተኞች ደርጋዊ ወሬ ነው:: በእርግጥ ደን መንጣሪ እና መጤ የሆኑ የምሥራቅ ጎጃም ዞን ተስፋፊዎች ተፈናቅለዋል:: አማራ ተፈናቀለ የሚባለው ግን በሬ ወለድ የትምክህት ኃይሉ ውሸት ነው::›› ለአቶ መለስ ንግግር የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችል የጭብጨባ ኃይል ከፓርላማው መነጨላቸው:: (የአቶ መለስን ንግግር ይዘቱን እንጂ ቃል በቃል አልወሰድኩትም::)

ባዶ ጭብጨባ የባዶነት ምልክት ነው:: የተሰጠውን ሁሉ ሳይጠይቁ እየዋጡ በሚያጨበጭቡ፣ አዕምሮአቸው ሳይሆን እጃቸው ብቻ ለማጨብጨብ በጋለ ሰዎቻችን ተጎድተናል:: … .

በኢሕአዴግ የዘመን ስሌት ታሪክ ከዳግማዊ ምኒልክ ይጀምራል:: ዳግማዊ ምኒልክ፣ ንግሥት ዘውዲቱ (ልጅ ኢያሱ ሁነኛ የሥልጣን ዘመን አልነበረውም:: ይታለፋል::)፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ አቶ መለስ ዜናዊ፣ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ሃገሪቱን ስድስት መሪዎች መርተዋታል:: ሰባተኛው እንደ ንጉሥ ሳሊበላ በእናታቸው ትንቢት ተነግሮላቸው፣ ትንቢቱ እንደሚደርስ አምነውም ፎቶ ከማንም ጋር ሳይነሣ፣ አንዲት ፈረንሳያዊት ብታፈቅራቸው እንኳን ንጉሡን መደፋፈር ነው ብለው ራሳቸውን ለንጉሥነት ጠብቀው የመጡት ዶክተር አብይ አህመድ ናቸው:: (የትንቢቱ ታሪክ ከራሳቸው አንደበት የተወሰደ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ሚኒስትሮቻቸውን ሲያስለጥኑ ሰባተኛው ንጉሥ እንደምሆን ትንቢት ተነግሮልኛል ብለው በይፋ

ተናግረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ እያንዳንዱ ሰው የመዝፈን፣ የመጻፍ፣ የመምራት ተሰጥኦ አለው። እኔ ደግሞ ተሰጥኦየ ልመና ነው ብለዋል። በልመና ክህሎታቸው ከተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት ወደ 3 ቢሊየን ዶላር እንዳገኙ በኩራት ተናግረዋል)። ሰባተኛው ንጉሥ እየተናገሩ ነው፡ "እኛ ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያዊ፣ ስንሞት ኢትዮጵያ ነን""

ጭብጨባ!!

‹‹ማንም ኢትዮጵያዊ በየትም ቦታ እኩል ነው። ዕድላችን መደመር ነው። አንድ ነን። ምሥራቅ አፍሪካም በቅኝ ገዥዎች የተሰመረ መስመር እንጂ አንድ ሕዝብ ነው።"

ጭብጨባ!!

"የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የገባር ሥርዓትን እና ጨቋኝ ገዥ መደብን በመታገል ጀግና ናቸው።"

ጭብጨባ!!

የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሞተር ነው። የወልቃይት ጥያቄ የመሠረተ ልማት እና መልካም አስተዳደር ነው።››

ጭብጨባ!!

‹‹የአማራ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት ሙቷል። ደምቷል። የወልቃይት ጥያቄ የመልካም አስተዳደር ሳይሆን የማንነት ነው። የወልቃይት ዐማራ አስመላሽ ኮሚቴዎችን አነጋግራለሁ።››

ጭብጨባ!!

…

ጭብጨባ እንዴት እና ለምን ብሎ ለመጠየቅ ዕድል ይነፍጋል። ከላይ የተዘረዘሩት ንግግሮች ይዘተ ነገር ቢተነተኑ አንዳንዶች የሚፋለሱ፣ ላያቸው ብቻ የሚያምር የሚመስል ነው። ግን በጭብጨባ ስለሚታሸጉ በማሸጊያው ውበት ብቻ ምኞታችን እያመን እንኖራለን። ጭብጨባ ሀገሪቱ በጠያቂ ትውልድ እርጣት ውስጥ እንደገባች ያሳያል። በእርግጥ ሥርዓቱ ጠያቂን እየገፋ፤ ወፍራም እጅ ያለው አጨብጫቢን... ብቻ ማቀፉ ጭብጨባው እንዲደምቅ አስችሎታል። አሳቢ ጭንቅላቶች ወንበሩን ለአጨብጫቢ እጆች ለቀው ውሎ እና አዳራቸው ዘብጥያ ሆኗል። ከትምህርት ተቋማት ይልቅ የኢትዮጵያ እሥር ቤቶች የምርጥ ጭንቅላት ባለቤቶች ናቸው።

...

አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እየተናገሩ ነው።‹‹ከሰማይ በታች የማንፈታው ችግር አይኖርም። ኢሕአዴግ ታድሷል። ስመራችን ጠርቷል። ኢሕአዴግ ለጋ ድርጅት ስለሆነ ገና ዴሞክራሲን አልገነባም።›› ክብር እና ሞገስ ለአቶ ኃይለ ማርያም የሚል ጭብጨባ ለሁለት ሳምንት ሙቆ ቆየ።

... .

በጭብጨባው መሃል ሕዝባዊ ተቃውሞዎች በአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ላይ ቀጠሉ። ‹‹ተቃውሞው፣ የጠባቡ እና የትምክህተኛው፣ የኤርትራ እና የግብፅ ተላላኪዎች ነው። ሕዝቡ ጥያቄው የመልካም አስተዳደር ነው።›› አቶ ኃይለ ማርያም ይሄን ሲናገሩ ዳጎስ ያለ ጭብጨባ ተበረከተላቸው።

... .

በሌላኛው ሳምንት ተቃውሞው ሲበረታ‹‹እኔ የለውጡ አካል ልሆን ሥልጣን ለቅቂያለሁ።›› ሲሉ ሕንጻ የሚበሳ የሙገሳ ጭብጨባ ቀረበላቸው።በሥልጣን ላይ ቆይቸ ችግር እፈታለሁ ሲሉ

ያጨበጨቡት፣ እለቃለሁ ሲሉም ያጨበጭባሉ። እጅ አያስብም። በማያስቡ እጆች ጠያቂ ጭንቅላቶች በጭብጨባ ደንቁረዋል።

...

‹‹የአማራ ሕዝብ ከግንቦት 20 ቀን 1983 ወዲህ በስሙ መነገድ ቁሟል። በፊት ሌሎች ብሔሮች በገዥ መደብነቱ በጥርጣሬ ስለሚመለከቱት ይፈናቀል ነበር። አሁን አማራው እንደ ሌሎች ብሔሮች አንገቱን ቀና አድርጎ እየተጓዘ ነው›› የብአዴን ካድሬው በተሰብሳቢው ጭብጨባ ንግግሩን አቋረጠ። የጭብጨባው ወላፈን ሲያልፍ፡ ‹‹የአማራ ሕዝብ የብሔሮች መብት ከተከበረ ወዲህ በቋንቋው የመጠቀም መብቱ ተረጋግጧል። ዛሬ አማርኛ መናገር አያሳፍርም። በንጉሡ እና በደርግ ጊዜ በአማርኛ መናገር ያሳፍር ነበር።››

ጭብጨባው ደራ።

‹‹ትምክህተኞች እና የግንቦት ሰባት ተላላኪዎች አማራ በዚህ ሥርዓት እንዳልተጠቀመ፣ እንደተፈናቀለ፣ እንደሞተ... ያወራሉ። የፀረ ሰላም ኃይሎች እና የድሮ ሥርዓት ናፋቂዎች አማራን የፌደራል ሥርዓቱ እንደተጫነው ይናገራሉ። እናንተ ደግ የአማራ ሕዝቦች ለእነዚህ ትምክህተኞች ጆሮ ንፈጓቸው። አጋልጧቸው። እናት ደርጅታችን ኢሕአዴግ ትምክህተኛን አከርካሪውን ሰብረነዋል ብሎ ገምግሟል። ድርጅታችን ብአዴንም የትምክህተኞችን ዋሻ ያፈርሳል። የዐፄውን እና የደርግን አሐዳዊ ሥርዓት ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ላይ ለመጣል የውሕደት የአማራ ገዥ መደቦች ላይነሡ እንጥላቸዋለን።›› አሁንም፣ አዳራሹ በጭብጨባው ተናወጠ። እጃቸው ብቻ በሚንቀሳቀስ ሙታን አጨብጫቢዎች ስለታማ ጭንቅላቶች በድምፅ መበከል ዝገዋል። ጭብጨባ መስማማት ቢሆን ኖሮ በስማቸው የሚማልባቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሙተውም ይመሩ ነበር። ግን ጭብጨባ ብዙ ጊዜ የአዳራሽ ውስጥ ስካር ነው። ጭንቅላቶች ካልተናገሩ፣ እጆች ብቻ ከመሰከሩ መማር አለመማር

ነው:: የሞራል ተጠየቅም ያስነሣል:: ለምን? እንዴት? የሚሉ መዛኝ ጭንቅላቶች ወደ አደባባይ ይመጡ ዘንድ መንገዱ ካልተከፈተ በጭብጨባ የሚወዛ ደረቅ መሬት የለም:: በሙቀት የሚወዛው የአጨብጫቢው እጅ ብቻ ነው:: ምክር ቤቶች እና የሕዝብ እንደራሴዎች በሕወሓት ኢሕአዴግ ዘመን ከ1 ነጥብ 2 ትሪሊየን ብር በላይ ከሀገር ሲሸሽ፣ ሕዝብ አዋጥቶ ሊገነባው የነበረው የዓባይ ግድብ በሙስና ሲገታ፣ በማዕከላዊ ንጹሐን ሲንኮላሹ... ከማጨብጨብ ያለፈ መጠየቅ አልቻሉም:: የብዙው ሕዝብ ወኪሎች ጭንቅላት ጸጉር እንጂ ሐሳብ አልተሸከመም:: ወኪልነታቸው ለሕዝብ ሳይሆን ለከርሳቸው ነው:: አጨብጫቢነት መሪዎቻችንን አዚማም አድርጓል:: የሕዝብን መሠረታዊ ጥያቄ አፍኖ በጊዜ ሂደት የአመፅ መነሻ ሆኗል:: ጃንሆይ በአጨብጫቢዎች ባይደነቁሩ ኖሮ በላይ ዘለቀም ባልተሰቀለ፣ መፈንቀለ መንግሥቱ ብሎም አብዮቱ ባልተቀሰቀሰ ነበር:: ግን ጃንሆይ በጭብጨባው ሙቋቸው ተዘናጉ:: የአብዮቱ ጎርፍም ቤተ መንግሥት ድረስ ገብቶ ወሰዳቸው:: ለኮሎኔል መንግሥቱም ሆነ ለአቶ መለስ እንዲሁም ለአቶ ኃይለ ማርያም ጭብጨባ ትክክለኛ የሕዝብን ስሜት እንዳያደምጡ መሰናክል ሆኖባቸው ቆይቷል:: በታሪክም ተወቃሽ ሆነዋል:: ጭብጨባን ፍሩ::

አቶ መለስ በ2004 ዓ.ም. ሲያርፉ ኢሕአዴግ በሙት መንፈስ ሀገር ለመምራት ከጀለው እና የሚከተሉትን ዜናዎች በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በኩል አስነበበ::

‹‹በአዲስ አበባ የሚገኙ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በአቶ መለስ ሞት ሕይወታችን ጨልሞብናል አሉ:: የጎዳና ተዳዳሪዎች ታጋይ እንጂ ትግል ስለማይሞት የአቶ መለስን ራዕይ ለማስቀጠል በተሰማራንበት ዘርፍ በርትተን እንሠራለን ብለዋል››[120] (ኢቴቪ፣ ኢትዮጵያ 2004 ዓ.ም.)

[120]በአቶ መለስ ሞት ወቅት ከዓይኑ እንባ በደንብ የቀዳ እና ጥቁር በጥቁር ለብሶ ያለቀሰ ለሹመት ወይም ለሽልማት ስለሚታጭ የማልቀስ እና የማዘን ውድድሩ በርትቶ ነበር::

ኢቲቪ በ2010 ዓ.ም. ደግሞ የባለፉት ዓመታት ቆሻሻ ሥራ የተሠራበት እና መንግሥት የሸብር ተግባር የፈጸመበት ዓመት ነበር ብሎ የእነ አቶ መለስን አገዛዝ ወረፈ:: ሕዝቡም የሚዲውን አጨብጫቢነት ታዝቦ ‹‹ አምላኬ ሆይ እባክህ ታሪኬን እንደ ኢቴቪ ቀይርልኝ›› ብሎ አጨበጨበ::

ሚዲያዎችም የጭብጨባ መሪዎች ናቸው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ሚዲያዎች የፓርቲ ልሳናት ሲሆኑ፤ ጋዜጠኞችም ባለሙያ ሳይሆኑ የጭብጨባ አጋፋሪዎች ናቸው:: የሚዲያዎች ክስረት አጨብጫቢ ሕዝብ እና አስጨብጫቢ ሀሳዊ መንግሥት እንዲፈጠር አድርጓል:: በተለያየ ጊዜ ለተደረጉ ጠጋኝ እና ሥርነቀል አብዮቶች ሚዲያዎች ሕዝቡን በማስጨብጨብ ለገዥዎች አሳልፈው ሰጥተውታል::

...

ዶክተር አብይ አህመድም ሕወሓት ያቆሰለውን የሕዝብ ስሜት በማከክ በጅማሯቸው ሕዝቡን እንደ ጎርፍ ነድተውታል:: ሕዝቡ የሚወደውን እየተናገሩ፣ ሕዝቡ የሚወደውን ለመሥራት ግን ተቋም እና ሥርዓት ሳይዘረጉ አረፈዱ:: ጭብጨባው ዓመት ሳይደፍን በእርግማን ተደመደመ::

በአንዳንድ ሚዲያዎች *‹ሴተኛ አዳሪዎች በአቶ መለስ ዘመን ደንበኛ እና ገቢያቸው እንደጨመረላቸው ተናገሩ›* የሚል አሽቃባጭ ዜናም ወጥቶ ነበር:: የከብቱ መዋያ ሁሉ መለስ ፓርክ ተብሎ ሲከለከል ከብቶች ግጦሽ አጥተው ቤት ለመዋል ተገደዋል:: አስለቃሾች ሽልማት በሽልማት ሆነዋል:: ፖለቲከኞች እስከ 2008 ዓ.ም. ደረስ ከወንበራቸው ራስጌ የአቶ መለስን ፎቶ ለጥፈው የአቶ መለስን ራዕይ ለማስቀጠል ‹ በዘንደሮው የመኸር እርሻ ስንዴን በመስመር እንዘራለን › እያሉ የአቶ መለስን የአረንጓዴ ልማት አበርክቶ ሲዘክሩ ከርመዋል:: የአቶ ኃይለ ማርያም የጠቅላይነት ጊዜም በመንፈሰ መለስ እየተመራ በ2010 ዓ.ም. አጋማሽ ቀለም አልባ ሆኖ ተገባዷል:: ለመለስ ያላዘነ የመንግሥት ሠራተኛ በ1ለ5 አደረጃጀት እየተገመገመ ውጤት ተኮር ይቀነስበት ነበር:: ኢሕአዴግ ሰውን በ1ለ5 ከተቆጣጠረ በኂላ፤ የፍጆታ ምርቶችንም (ዱቄት፣ ስኳር፣ ዘይት…) በእጁ አስገብቶ ለአቶ መለስ ጥቁር ያልለበሰ እና ያላነባ ቀበሌዎች ስኳር እና ዘይት ነፍገው ነበር:: በ2005 እና 2006 ዓ.ም. ለአቶ መለስ ማልቀስ አዋጭ የድለላ ሥራ ሆኖ ባጅቷል:: አቶ መለስ እስከ 2010 ዓ.ም. በራዕይ በአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አካል አማካኝነት መግዛታቸው የሕወሓትን የበላይነት ለማስቀጠል የእድሜ መጨመሪያ ክኒን ሆኖ አገልግሏል:: ሕወሓት ከነሐሴ 2004 አስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. መግዛት የቻለችው ለመለስ ራዕይ የተንበረከከ ኢሕአዴግን በመፍጠር ነው::

‹‹ሁሉን ትመኛለህ ግን ሁሉን ታጣለህ›› እንዳለው ደራሲ በዓሉ ግርማ ካለመርህ ሁሉን ለማስደሰት በመንታ ተቃርኖዎች የሔዱበት መንገድ ከጫጉላ ሽርሽር ያለፈ አልሆነም፡፡

5.6 የአብዮት ጉዞ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ ከጥገናዊ የፖለቲካዊ እርምጃ ወጥተው ወደ ሥር ነቀል ለውጥ ያመዘኑ ሁለት ደመማቅ አብዮቶች ተደርገዋል፡፡ የመጀመሪያው ለ3ሺህ ዘመን ኢትዮጵያን ተከትሎ የመጣው ሃይማኖት ቀመስ የሆነው የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ያከተመመበት የ1966ቱ አብዮት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ አሐዳዊ ሥርዓት የተገባደደበት የ1983ቱ ብሔረሰባዊ አብዮት ነው፡፡ የ1966ቱ አብዮት ዘውዳዊ ሥርዎ መንግሥት የወደቀበት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ታሪክ እና ባህል ሁሉ የተሻረበት ሥር ነቀላዊ እምቢተኝነት ነበር፡፡ የ1983ቱ አብዮት የ1966ቱ አብዮት ተቀጥያ ሲሆን፤ በጫካ ትግል የነበሩ ርዕዮተ ዓለማዊ ቅኝቶች ወደ መንግሥት መዋቅር የመጡበት ጊዜ ነበር፡፡ የ1966ቱ ሥር ነቀላዊ አብዮት በወጣቶች እና በተማሪዎች ጎልቶ የወጣ ቢሆንም፤ የዘውዳዊ ሥርዓቱ ወታደር የሆነው የደርግ አባላት ሥልጣነ መንግሥቱን ሊቆጣጠሩት ችለዋል፡፡ ተማሪው፣ በርዕዮተ ዓለም ፍቅር እንደነደደ፣ የሶሳሊዝሙን ፍልስፍና ከኢትዮጵያ ወግ ጋር ሳያገናኘነው በመፈክር ብቻ ሊመክን ችሏል፡፡ የተማሪዎች ንቅናቄ የፈጠረውን አብዮት ተከትሎ ደርግ ማርክሳዊ ሆኖ ለ17 ዓመት ወታደራዊ መንግሥት ሆኖ ገዝቷል፡፡ ደርግ በአብዮት እንደተፈጠረ ሁሉ ነፍጥ አንጋች ዘውግ አቀፍ ብሔርተኞች በፈጠሩት አብዮት ወድቋል፡፡

5.7 ደርግ እንዴት ወደቀ?

ዶክተር ፈንታሁን አየለ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከድል ወደ ውድቀት ብለው ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም. የነበረውን የወታደር ታሪክ በጥናት በተነተኑበት መጽሐፋቸው ለደርግ ውድቀት ምክንያቱን የሕዝብ ድጋፍ ማጣትን፣ ስሑት ስትራቴጂን እና የምልመላ እና የአደረጃጀት ችግርን ያነሣሉ፡፡

ሀ) ከሕዝብ መራቅ

ደርግም ሆነ ኢሕአዴግ አብዮታቸውን ሲጀምሩት፣ ሕዝብን በተስፋ አስክረው ነበር፡፡ ያለፈውን አምባገነንነት እየነቀፉ፤ የእነርሱን ተሻይነት ለማሳየት ታትረዋል፡፡ ደርግ እንደነ ሌኒን በቀያይ መስመር ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም የሚል መፎክር ደጋግሞ አሰማ፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ ያለምንም የመደብ ልዩነት አንድ ናቸው አለ፡፡ ሕዝቡ ዘውዳዊ ሥርዓቱን እንዳይናፍቅ ጃንሆይ የፈጸሙት ሰውን የማሥራብ እና የእሳቸውን ቅንጦት እያወዳደረ በየሚዲያው አሳየ፡፡ ደርግ ለሕዝቡ ብቸኛ አማራጭ መስሎ በጫጉላ ሽርሽሩ ወቅት ታየ፡፡ አንድ ዓመት ደፍኖ ሳይጓዝ 60ዎቹን የጃንሆይ ሹመኞች፣ ራሳቸው ጃንሆይን… አብዮታዊ አርምጃ ብሎ ረሸናቸው፡፡ ትንሽ ዘግየት ብሎም እስከ 1970 ዓ.ም. ብቻ 10ሺህ[121] የሚደርሱ ወጣቶችን በየአደባባዩ እየገደለ መንገድ ላይ አሰጣቸው፡፡ በ1975 ዓ.ም. ደርግ ብሔራዊ የውትድርና አዋጅ አውጆ ወጣቱን የጦር ማገዶ አደረገው፡፡ በገጠሩ ያለፈቃድ የሰፈራ መርሐ ግብር ተዘርግቶ አርሶ አደሩን ከቀየው መንቀሉ፤ የሚያመርተውን ምርትም በነጻነት እንዳይሸጥ መከልከሉ ደርግን ሕዝቡ አንቅሮ እንዲተፋው አደረገ፡፡ ዶክተር ፈንታሁን በጥናታዊ መጽሐፋቸው ከሕዝብ ፍቅር የተነጠለ ሠራዊት የመዋጋት ወኔውን ያጣል የሚል ሐሳብ ያቀርባሉ፡፡

[121] *ዶክተር ፈንታሁን አየለ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከድል ወደ ውድቀት* (1967-1983) ፣ 2010 ዓ.ም.

ለ) ስሑት ስትራቴጂ

ደርግ በመጋቢት 1970 ዓ.ም. የዚያድ ባሬን ጦር ካብረከረከ በኋላ፤ የምሥራቁ ድል በሰሜንም ይደገማል ብሎ እየፎከረ በአስመራ የናቅፋ ተራሮች ሥር የኤርትራ አማጺያንን ደበደበ። ደርግ የተለያዩ የችግር ሽለቆዎችን በተመሳሳይ አረማመድ ለመሻገር አሰበ። በሶማሊያ ወረራ ሀገሬ ብሎ የዘመተው ኢትዮጵያዊ ለደርግ ብሎ ለመዋጋት ግን አልተነሣም። ለአማጺያን ብሎ የሚያወርደው ብትር በእግረ መንገድ ፍንጥርጣሪው ንጹሓን ላይም አረፈ። ሕዝቡ ለአማጺያኑ ጫካ ሆኖ ደበቃቸው። ደርግ የአማጺያኑን እና የሕዝቡን አንድነት ከመለያየት ይልቅ የአማጽያን ደጋፊ ናቸው ያላቸውን ሁሉ በኃይል መደብደብ መረጠ። ይህም ለአማጽያን ደጋፊ አጎረፈላቸው። ሕዝቡ ለደርግ መረጃ እየደበቀ ለአማጺያን ከመስጠቱ ባለፈ፤ ከሕዝብ ጎን የሆኑ የሕይዎታቸው ሹመኞች የጦር መረጃ ከደርግ ቀድመው ለአማጺያን በመለገሳቸው ደርግ ድንብርብሩ ወጣ። ግማሽ ሚሊየን ሠራዊት የነበረው ደርግ ከየብሔሩ በወጡ ንዑሳን አማጺያን ሊፈረካከስ ችሏል። ሕዝብን በፍቅር ያላሸነፈ ፖለቲካ በጦር ብዛት አይጸናም። ለአዲስ ችግርም አሮጌው መፍትሄ እልባት(remedy) አይሆንም።

ሐ) የሀገር በቀል እውቀት ችግር

ስታሊን ሳያስበው ሂትለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በጀርመን ጦር ድንገት ወረረው። ስታሊን በድንጋጤ አርሶ አደሩን እና ምንም የጦር ልምድ የሌለውን ሩሲያዊ ሁሉ ወደ ጦር ማገደው። በተዋጊ ብዛት ጀርመንን ሩሲያ በርሊን ድረስ አሸነፈች። ከዚህ ድል በኋላ፣ የስታሊኗ ሩሲያ በብዙ ጦር ጠላትን ማንበርከክ ይቻላል በሚል ከጥራት ይልቅ ብዛት ላይ አተኮረች። ወደ ኢትዮጵያም ተሞክሮዋን አጋራች። የኢትዮጵያ ሠራዊትን ሩሲያዎች ሲያሠለጥኑ በሦስት ወር ሥልጠና ብቻ አርሶ አደሩን በብዛት መማገድ ላይ አተኮሩ።

የሩሲያን ምክር ሰምቶ ብዙ ወታደር ለማግኘት በግዳጅ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ወታደር አሰለጠነ። ትምህርቱም ማርክሳዊ እና ሌኒናዊ እንጂ ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖች ታሪክ አልነበረም። ወታደሮች ስለ ካርል ማርክስ እና ኤንግልስ እንጂ ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ሀገር ስላዋቀሩበት መንገድ አልተሰበከላቸውም። የደርግ ፖለቲካ የቆመበትን ተረከዝ ብቻ እንዲያላምጥ የተገደደው ወታደር ዘግይቶም ቢሆን፤ የውጊያ ሥነ-ልቦናው መቀዝቀዙ አልቀረም።

በግዳጅ የመጣ ወታደር መዋጋት ሰለቸው። ከ1970-1978 ዓ.ም. በአስመራ አካባቢ ከነበሩ ወታደሮች መካከል 57 ከመቶው ደርግን ከዱ። ዶክተር ፈንታሁን አየለ እንዳጠኑት፤ ከሀገር ባህል እና ወግ ይልቅ በማርክሲዝም እና ሌኒኒዝም የሰለጠነ ውስን ወታደር የገዳሞ መነኮሳትን ሳይቀር አስገድዶ ደፈረ። ይህ የጥቂት ወታደሮች ድክመት የመላው ሠራዊት ባሕርይ ተደርጎ በአማጽያኑ ተነገረ። ሕዝቡም ወታደሩን አምርሮ ጠላ። የተጠላው ሠራዊት ተስፋ በመቁረጥ የታጠቀውን ሩሲያ ሠራሽ መሣሪያ ሳይተኩስበት በሽሽት መልክ ለአማጺያኑ አስረከበ። አማጽያኑ በደርግ መሣሪያ እና ወታደር እየታገዙ ጉልበታቸውን አፈረጠሙ። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በ1980 ዓ.ም. ወደ ሞስኮ አቅንተው የድሮ ወዳጃቸውን ሩሲያን የመሣሪያ ድጋፍ ጠየቁ። የወቅቱ የሩሲያ ፕሬዝዳንት ሚካኤል ጎርባቾቭ የቀዝቃዛው ጦርነት እንዲያከትም ይፈልጉ ነበር። ከአሜሪካ ጋርም እርቅ ፈጽመዋል። የበርሊን ግንብ እንዲፈርስ ከጅለዋል። ጎርባቾቭ የሰላም እና የነጻነት ጥሪያቸውን በመላው ዓለም እያሰሙ ባሉበት ወቅት ኢትዮጵያም የሰላም መሣሪያ እንጂ ነፍጥ አያስፈልጋትም ብለው ኮሎኔል መንግሥቱን ፊት ነሷቸው።

በሩሲያ ሐሳብ እና ትጥቅ የወፈረው የደርግ ወታደራዊ መንግሥት፤ በጎርባቾቭ መምጣት ከሳ። በጎርባቾቭ አማካኝነት ሁለቱ የምዕራብ

እና የምሥራቁ የካፒታሊዝም እና የኮሚኒዝም የፖለቲካ ፍልስፍና እርቅ ፈጸመ። የነማርክስ እና የነሌኒን ፍልስፍና ለምዕራቡ ካፒታሊዝም እጁን ሰጠ። ደርግም ከሩሲያ ኮሚኒዝም መውደቅ ጋር አብሮ ወደቀ። አሜሪካም የደርግን ከሩሲያ ጋር ማበር ለመበቀል በአምባሳደር ኸርማን ኮኸን አማካኝነት ሻዕቢያ፣ ሕወሓት እና ኦነግን ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት አስጠጋች።

ኮሎኔል መንግሥቱም ወደ ቀደመ ጓዳቸው ወደ ሮበርት ሙጋቤ መንደር ወደ ዚምባብዌ ሀራሬ አቀኑ። በ1953 ዓ.ም. በነመንግሥቱ ንዋይ ተጀምሮ በ1966ቱ አብዮት የወደቀው ዘውዳዊ መንግሥት በትረ መንግሥቱን ለደርግ አስረከበ። ደርግ ራሱን በራሱ ጥሎ ገንጣይ እና ወንበዴ ለሚላቸው ብሔርተኛ ኃይሎች ወንበሩን አሳልፎ ሰጠ። ደርግ የተፈለፈለው ከዘውዳዊ መንግሥቱ የጃጀ ሥርዓት አፈንግጦ ሲሆን፤ ኢሕአዴግም የተወለደው ከደርግ የስንፈት ሰንኮፍ ነው። አምባገነን መንግሥታት ሃቀኛ ተፎካካሪን ቀድመው ስለሚያጠፉት በብዛት የሚወድቁት ከራሳቸው በሚወጣ አፈንጋጭ ቡድን ወይም ጦር ነው። በደርግም ሆነ በዘውዳዊው መንግሥት የተፈጠረውም ይሄው እውነት ነው።

5.8 ኢሕአዴጋዊው አብዮት

ኢሕአዴግ የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በጀመረበት ወቅት የመጣ ብሔረሰባዊ ድርጅት ነው። የ1966ቱ አብዮት ውልድ የሆነው ኢሕአዴግ ከደርግ የሚለየው ጭቆናውን ከመደባዊ ይልቅ ብሔራዊ ነው ብሎ ለብሔረሰባዊ ማንነት መታገሉ ነው። ደርግ እና ኢሕአዴግ በማርክሳዊ አብዮታቸው እና በመሬት ፖሊሲያቸው ልዩነት የላቸውም። ኢሕአዴግ የኮሚኒዝሙ ግንብ በምሥራቁ ክፍለ ዓለም ሲፈረካከስ ስለደረሰ የጫካ ሕልሙን ጭንብል አልብሶ ቅይጥ ርእዮተ ዓለም ይዞ ለመምጣት ሞከረ።

በ1987 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግሥት የሰብዓዊ እና የዴሞክራሲያዊ ድንጋጌዎች ከምዕራባውያኑ የነጻነት ዴሞክራሲ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፤ የመሬት እና የኢኮኖሚ ፖለሲው ግን ከኮሚኒስት ሀገራት ጋር ያቀራርበዋል። ኢሕአዴግ በ1983 ዓም ፊቱን ለዓለም ያስመታው በሁለት ጎን የተሳለ ሰይፍ ሆኖ ነበር። ይሄን ማድረጉም በአንድ ገጹ ከምዕራባውያኑ ድጋፍ ሲያስገኝለት በሌላ ስሉ ገጹ ደግሞ የተመሠረተበትን ኮሚኒስታዊ መንፈስ እና መዋቅር ሳይለቅ እንዲሻገር አድርጎታል። ለዚህም ኢሕአዴግ ቅብ አምባገነን እንዲሆን አድርጎታል። ዓይን ያወጣ አምባገነን ቢሆን ኑሮ የሕዝብ መሠረቱም ሆነ የውጭ ግንኙነቱ ተበላሽቶ ብዙ ሳይራመድ ሊቆም ይችል ነበር።

5.9 የኢሕአዴግ ሕልም

የኢሕአዴግ ሕልሙ እንደ ቻይናው ኮሚኒስት ፓርቲ ለክፍለ ዘመናት አውራ ሆኖ በሀገሪቱ ላይ መንገስ ነው። ልማታዊ መንግሥት፤ አንድ ፓርቲ አውራ ሆኖ፤ ሥልጣን በተወሰኑ ልሂቃን ተከማችቶ እንዲቆይ አድርጎ በተራዘመ ሂደት የልማት ፕሮጀክቶች እንዲፈጸሙ ያደርጋል። ለዚህም ለኢሕአዴግነት የተመቸች አዲስ ኢትዮጵያን ለመፍጠር ታግሏል። ማኅበረ መሠረቱም የገጠሩ ሕዝብ እንደሆነ በተደጋጋሚ በይኗል። አቶ መለስ ዜናዊ ‹‹ማኅበረ መሠረታችን የገጠሩ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ነው። የከተማው እና ምሁሩ ብዙ ቢንጫጫ በምርጫ ኮረጆው ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ኢሕአዴግ በገጠሩ ሕዝብ እየተመረጠ እንደ ጃፓን እና ሜክሲኮ ፓርቲዎች ከ50 እስከ 100 ዓመት ይገዛል››[122] ሲሉ በአንደበታቸው በተደጋጋሚ ተደምጠዋል።

[122] ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ የነጻነት ጎህ ሲቀድ

ኢሕአዴግ ለሐሳብ ጥራት የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው። በእርግጥ ለአምባገነን መንግሥታት ሐሳብ አንድ ብቻ ተደርጎ ስለሚታሰብ፤ ከፓርቲው ውጭ ያሰበ እንደ አሸባሪ ሊታይ ይችላል። አርሶ አደሩ ፓርቲያዊ ሐሳብ ስለሌለው ለኢሕአዴግ ምቹነት አለው። በ1986 እና በ1992 ዓ.ም. አጃቢ ኢሕአዴግ ቀመስ ተፎካካሪዎችን ይዞ ኢሕአዴግ ወደ ምርጫ ገብቷል። በ1992 ዓ.ም. የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማግስት ስለነበር ለቅድመ ዝግጅት አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን ከምዕራባውያኑ እርጥባን ለማግኘት ምርጫውን አድርጓል። ምርጫውንም ብቻውን ተጫውቶ አሸነፈው።

በ1997ም ከ1992ቱ ምርጫ ተምሮ በአሸንፋለሁ እብሪት ወደ ምርጫው ዘለቀ። ለቅብ ሲባል ነጻ ሚዲያዎች ስለነበሩ፤ የቅንጅትን እና የኢሕአዴግን ሐሳብ ፀሐይ አስመቱት። ኢሕአዴግ የቅንጅትን ያህል ሐሳብ ማፍለቅ ተሳነው። የከተማው ሕዝብ ከኢሕአዴግ እሳቤ እየኮበለለ ወደ ቅንጅት ተጠጋ። የኔ ማኅበረሰባዊ መሠረቴ ነው የሚለው አርሶ አደሩም በሁለት ወር በተሠራ ፕሮፖጋንዳ ቅንጅትን ተቀበለ። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ኢሕአዴግ ለ100 ዓመት ቀርቶ ለ50 ዓመት መግዛት እንደማይችል ገባው።

ከሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ቅብ አምባገነንነቱን ፍቆ ነፍጥ አንሥቶ ወደ ፍጹም አምባገነናዊነቱ ተለወጠ። በጅምላ ማሰር እና መግደልን ባሕርይው አደረገ። የሚጠየቀውን መመለስ ሳይሆን የሚጠይቀውን በሙሉ አሰረ። ኢሕአዴግ ፍጹም አምባገነን ሆኖ የስለላ መዋቅሩን እስከ ቤተሰብ ድረስ ዘረጋ። ገበሬውን ከጥር እስከ የካቲት በተፈጥሮ ሀብት ሥራ ሰበብ ተራራ እያስወጣ አቧድኖ አይነኬ ርዕዮተ ዓለሙን አጠመቀ። የመንግሥት ሠራተኛውን በ1ለ5 ጠመደው። ወታደሩንም በየጋንታው በግምገማ እና ሂስ ተቆጣጠረው። በሕዝቡ ላይ የጥርጣሬ ድባብ ሰፈነ። በአንድ መሥሪያ ቤት የሚሠሩ ባለሙያዎች በ1ለ5 እርስ በርሳቸው ሲቋሰሉ እየዋሉ የመንግሥትን ሥራ ለመገምገም ጊዜ አጡ።

ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ብሎ ሕዝቡን በተስፋ ጋተው። ሕዝቡ በተስፋ እየጠገበ በ1997 ዓ.ም. አታስፈልገኝም እንዳላለ፤ በ1999 ዓ.ም. ፀሐዩ መንግሥታችን ብሎ አሞካሸው። ፀሐዩ ኢሕአዴግ በ2002 ዓ.ም. 99.6[123] ከመቶውን ሲያሸንፍ፤ በ2007 ዓ.ም. ጭራሽ መቶ ለመቶ ዘጋሁት ብሎ ፍጹም አሸናፊነቱን አወጀ። በ2007 ዓ.ም. ምርጫ ኢሕአዴግ ቅብ አምባገነናዊነቱን ረስቶ፤ ዓይኑን በጨው ታጥቦ ፍጹም አምባገነናዊነቱን ያወጀበት ጊዜ ነበር። መቶ በመቶ አሸንፌያለሁ ያለው ኢሕአዴግ ዓመት ሳይደፍን የተቃውሞ ማዕበል በየሀገሪቱ ጫፎች ይንጠው ጀመር። የታፈነ ድምጽ ጉልበት አለው። ጉልበቱ ከምርጫው ማግስት በአማራ እና በኦሮሞ ወጣቶች በቅዋሜ ታይቷል። ኢሕአዴግ ልክ እንደ ደርግ በወታደር ብቻ ለመምራት አስቦ ከመስከረም 2009 እስከ 2010 ዓ.ም. መጨረሻ አጋማሽ ድረስ በአስቸኳይ አዋጅ አገዛዙን ለማሻገር ቢሞክርም ሳይሳከለት ቀርቷል።

ከየካቲት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የኢሕአዴግ የኃይል ሚዛን ክሹፍ በሆነ ለውጥ ሰበብ ከሰሜናዊ የኢትዮጵያ ንፍቀ ክበብ ወደ ደቡባዊው አቅጣጫ ተጠግቷል። የሀገረ መንግሥት ግንባታውም ከዳግማዊ ምኒልክ ወፍራም አሻራ ለመሸሽ አፍርሶ በመሥራት ላይ ተቸከለ። ኢሕአዴግ ለውጥ ብሎ ያለምንም ፍኖተ ካርታ በእውር ድንብር እየተመራ ከድጡ ወደ ማጡ ቁልቁል ነጎደ። የኢሕአዴግ ግንባሮች ከእናት ፓርቲው በላይ ሆነው ገነው ሲወጡ የኢትዮጵያ ህልውናም አብሮ ጠየመ። ሞት እና መፈናቀል የፖለቲካው አሻራ ሆነ። ብሔራዊ ክልሎች ከሀገሪቱ በላይ ፖለቲካዊ ጡንቻቸውን አፈርጥመው እርስ በርሳቸው ትክሻ ለትክሻ ለመለካካት ተፎካከሩ። በኦዴፓ በኩል እንደ ሕወሓት የኢሕአዴግ አስኳል ለመሆን በሚያደርገው ስልት አልባ ሩጫ መንገራገጬ አንድነትን የበለጠ

[123]በ2002 ምርጫ ወደ ፌዴራሉ ፓርላማ የገቡት ከአንድነት ፓርቲ ግርማ ሰይፉ ማሩ የተባሉ ከአዲስ አበባ የተወከሉ አንድ ተፎካካሪ ብቻ ነበሩ። ሌላው የኢሕአዴግ ሆኗል።

ሰብሯል። ነፍጠኞችን ሰብረን አዲስ አበባን ከ150 ዓመት በኋላ ተቆጣጠርናት እያለ የቅኝ ተገዥነት የፖለቲካ ሥራቱን ተቋማዊ ለማድረግ ጣረ። ባህል እና ትውፊቱን፣ ሥርዓት እና ታሪኩን ከአማራ ጋር ኢ-ተገጣጣሚ አድርጎ ሠርቶታል።

አብዮቱ ከጠጋኝነቱ ወጥቶ ወደ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ አለማምራቱ፣ ወጣቱ እየሞተ የጠየቀው ጥያቄ ዳግም ሳይመለስ ተቀብሯል። እንደተለመደው ያልተመለሰ ጥያቄ እንደ ረመጥ እየሰፋ ሂዶ ቋያ ሆኖ ባለወንበሩን ማንደዱ አይቀርም። ባለወንበሩም ረመጡን በአመድ እያዳፈነ የአገዛዙን እርባናቢስ ዕድሜ ለመጨመር መጣሩ የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መለዮው ነው። ዳሩ፤ ረመጡም ነበልባል ሆኖ ሲወጣ፣ ወንበሩም ይከስላል። ሕዝብ እንጂ ወንበር ዘላለማዊ አይሆንም። ነገር ግን አምባገነኖች ለሚጠፋው ወንበር፤ የማይጠፋውን ሕዝብ ለማጥፋት ይሠራሉ።

5.10 ኢሕአዴግ እና የዓረቡ ጸደያዊ አብዮት

ምርጫ 97 ብዙውን ቁስለኛ አድርጎ፤ ቀሪውንም እስረኛ አድርጓል። ነጻ ፕሬሱም ታግቷል። ፍረጃውም በዝቶ የእግዜር ሰላምታ ያህል ዘወትራዊ ልማድ ሆነ። በተለይ የፍረጃ ሰንሰለቱ ጠብቆ የታሰረው በወታደሩ አካባቢ ነበር። መስከረም 1999 ዓ.ም. የወቅቱ የመከላከያ ዮኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው[124] ጽጌ ለአቶ መለስ ዜናዊ በደብዳቤ ‹‹በወታደሩ ያለው ችግር እየተባባሰ ነው። በሕክምና ኮሌጅ ፈተና ሳይቀር የወቅቱ የጦር አዛዥ ሳሞራ የኑስ ጣልቃ እየገቡ እንደሆነ›› ለአቶ መለስ ይጠይቃሉ። አቶ መለስም ብርጋዴር ጀኔራል አሳምነውን እና ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሌ ጥላሁንን ማዕረጋቸውን ገፈው አባረሯቸው። ከ22ሺህ በላይ አማራ ወታደሮች ከነጀኔራል አሳምነው ጋር አብረው ተባረሩ። በሌላ በኩል

[124]ፍትሕ መጽሔት፣ አንደኛ ዓመት ቁጥር 33 ሰኔ 2011 ዓ.ም.

ደግሞ በ1998 ዓ.ም. በብርጋዴር ጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራ የኦሮሞ ተወላጅ የሆነ ወታደር የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊትን ከድቶ ከኦነግ ጋር አስመራ ሂዶ ተቀላቀለ። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከ16 ሺህ በላይ ኦሮሞኛ ተናጋሪዎች ኦነግ ናችሁ በሚል ተባረሩ።

ከምርጫ 97 በኂላ አማራው እስከ 2001 ዓ.ም. በቅንጅት ስም ሲመታ፤ ኦሮሞው ደግሞ ከ1983 እስከ 2010 አጋማሽ በኦነግነት እየተፈረጀ ተኮርኩሟል። ከ2001 ዓ.ም. በኂላ አማራው ከቅንጅት ሽርፍራፊዎች በተፈጠረው በግንቦት ሰባት ሰበብ መታሰሪያ መንገዱ ሆኗል። በሚያዝያ 2001 ዓ.ም. ከመከላከያ የተባረሩ አማራዎች በብርጋዴር ጀኔራል አሳምነው ጽጌ ተመርተው ለመፈንቅለ መንግሥት ተዘጋጁ። ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ይሄን ሁነት ‹‹በዚህች ሀገር ሰማይ ሥር ዳግም ተራሮችን የሚያንቀጠቅጥ ትውልድ አይፈጠርም›› የሚለውን የነ መለስ ታብዮ የናጠ ክስተት አድርጎ ይወስደዋል።

በ2001 ዓ.ም. ከቅንጅት አንዱ ክንፍ ግንቦት ሰባት ብሎ ከኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ጋር ተቀናጅቶ በነፍጥ የታገዘ ትግል እንደሚያደርግ አሳወቀ። በዚህ ሁሉ ውጥረት ውስጥ የዓረቡ አብዮት በሰሜን አፍሪካዋ ቱኒዝያ እየተቀጣጠለ የመን እና ግብጽን አዳረሰ። እንደ እስክንድር ነጋ ዓይነት ጋዜጠኞች የዓረቡ መሰል አብዮት በኢትዮጵያም ተፋፍሞ ለውጥ እንዲመጣ ቀሰቀሱ። ኢሕአዴግ መንግሥትን የሚተቹትን ሁሉ ሚዲያዎች እየዘጋ፤ ጋዜጠኞችንም አሰረ። ግንቦት ሰባትንም በ2003 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኛነት ፈረጀው። ግንቦት ሰባት፣ ኦነግ እና ኦብነግ በኤርትራ ሆነው ለሻዕቢያ አሽከር ከመሆን የዘለለ ተጨባጭ ሚና አልነበራቸውም። ነገር ግን በስማቸው የሽብርተኝነት ሕግ ወጥቶ ኢሕአዴግ ዓይኑ ያላማረውን ሁሉ መቅጫ አደረገው። ይህም በሕዝቡ የከፋ ምሬትን ፈጠረ። በኢትዮጵያ በ2003 እና 2004 ዓ.ም.

የነበረው ጭቆና እና የኢኮኖሚ ንረት ሕዝቡን ለብሶት ዳርጎት ነበር፡፡

የቱኒዝያው ተወላጅ ምስኪኑ ሙሀመድ ቡኣዚዝ በ2002 ዓ.ም. አትክልት እና ፍራፍሬ በመሸጥ ይተዳደራል፡፡ አትሸጥም ተብሎ ሲከለከል ራሱን በአደባባይ አቃጠለ፡፡ የቦኣዚዝ መቃጠል በቱኒዝያ የተቃውሞ ማዕበል አስነሣ፡፡ የቱኒዝያን ፈላጭ ቆራጭ መንግሥትም ከመንበሩ አነሣ፡፡ ቱኒዝያ አብዮቷን ወደ ሊቢያ ስታጋባ ጋዳፊ ከመንበራቸው ተፈነቀሉ፡፡ የጋዳፊ መፈንቀል ሊቢያን ለማያቋርጥ አመጽ ጋበዛት፡፡ ከሶሪያ እስከ የመን ድረስ አብዮቱ ተቀጣጠለ፡፡ በግብጽም ሆስኒ ሙባረክን በሙሀመድ ሙርሲ፣ ሙርሲንም በአብዱል ፈታህ አልሲሲ የተካ አብዮት አካሄደ፡፡

በኢትዮጵያ በደቡብ ክልል ዳውሮ ዞን በኑሮ ውድነት እና በመልካም አስተዳደር እጦት የተሰቃየ የኔሰው ገብሬ የተባለ መምህር ኅዳር 2004 ዓ.ም. ራሱን እንደ ቦኣዚዝ አቃጠለ፡፡ የየኔሰው ራስን ማቃጠል ግን እንደ ቦኣዚዝ ብዙዎችን ለአመጽ እንዳይጠራ ኢሕአዴግ ተከላከለ፡፡ የየኔሰውን አስከሬን ለቤተሰብ ሳይቀር አላሳይም አለ፡፡ ግጥምጥሞሹ እና መንግሥታዊ በደሉ የዓረቡ እና የኢትዮጵያው ተቀራራቢ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ ግን የአብዮቱ ማዕበል ፈጥኖ አልደረሰም፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአንድ ቁመው የሚታገሉበት ሀገራዊ ርዕይ ልሂቃን አልሠሩም፡፡ በሌላ ገጽ ደግሞ ኢሕአዴግ እንደ ዘውዳዊው መንግሥት መሬት እና ሰውን፣ ሕግ እና ተቋሙን የብቻው ይዞ የተቃውሞ ድምጾችን አስቀድሞ አፈናቸው፡፡

5.11 የውጭ ጠላት ፈጠራ እና የዓረብ አብዮት መቆረጥ በኢትዮጵያ

የግብጽ ፖለቲካ በአብዮቱ አልረጋ ብሏል። የኢትዮጵያ ፖለቲካም ከድህረ ምርጫ 97 ጀምሮ በመታፈን ውስጥ ነው። ሁለቱም የዓባይ ዳር ልጆች ፖለቲካቸው ታሟል። ኢትዮጵያ የታመመውን ፖለቲካዋን ዓባይን በመገደብ ሀገራዊ ሕልሟን አድሳ ለመቆም መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. ዓባይን ለመገደብ አወጀች። ከሆስኒ ሙባረክ ፍንገላ በኋላ የመጡት ሙሀመድ ሙርሲ‹‹ ግብጽ የናይል ስጦታ ብቻ ሳይሆን ናይልም የግብጽ ስጦታ ነው። አንድ ጠብታን የናይል ውኃ በጠብታ ደማችን እንመነዝራለን›› ሲሉ የጦር ቅስቀሳ በኢትዮጵያ ላይ አደረጉ።

ሙርሲ የዚህ ቅስቀሳ ዋና ዓላማ ያደረጉት ግብጻውያን በውስጥ ፖለቲካ ሽኩቻ ውስጥ ከሚገቡ ኢትዮጵያን እንደጠላት በማሳየት የግብጽን ብሔራዊ አንድነት ለማስጠበቅ ነበር። በሀገር ውስጥ ያለውን አመጽ ለማስታገስ ሙርሲ የውጭ ጠላት ፈጠራ ላይ አተኮሩ። ግብጽ ኢትዮጵያ ከማንኛውም ዓለም አቀፍ ተቋም ብድር እንዳታገኝም የዲፕሎማሲ ግንኙነት አድርጋ ተሳካላት። ሙርሲ ግን በ2004 ዓ.ም. ጊዜያዊ ሕገ መንግሥት ሲያረቁ የፕሬዝዳንቱን ሥልጣን ላለመገደብ ያደረጉት ጥረት እና ከሙስሊም ብራዘርስ ሁድ ጋር ያላቸው የበዛ ግንኙነት በግብጻውያን ዘንድ አልተወደደላቸውም። የግብጽ ፖለቲካ ዋና አጋፋሪ የሆነችው አሜሪካም ለሙስሊም ብራዘርስ ሁድ በጎ ዕይታ የላትም። ሙርሲ በሥልጣን ከአንድ ዓመት ሳይዘሉ በወታደሩ ተፈንግለው ወደቁ። ከወታደሩ ክንፍ ማርሻል አብዱል ፈታህ አልሲሲ ወደ ፕሬዝዳንትነት መጡ። የሙርሲ የውጭ ጠላት ፈልጎ፤ ሀገራዊ ፖለቲካውን የማርጋት ስልተ መንገድ አዋጭ አልሆነም።

በሌላ መንገድ ደግሞ አቶ መለስ *‹‹ግድቡን ለመገንባት ወታደሮችም፣ ኢንጅነሮችም፣ የገንዘብ ምንጮችም.. እኛው ነን:: ታላቅ ነበርን ታላቅም እንሆናለን:: ግድቡን ለመገንባት ግብጽ ብድር ማስከልከል፣ እርስ በእርሳችን ማተራመስ፣ የጦር ኃይሏን በማብዛት የዓባይ ወንዝ የሚነካቸው ሀገራትን ከጎኗ እንዲሆኑ ማስፈራራትን በስትራቴጅነት ትጠቀማለች:: ግብጽ አጠቃላይ የወታደር እና የፖሊስ ኃይሏ 6 ሚሊየን ይደርሳል:: ይህም ሆኖ አንፈራም:: ግብጽ በኢትዮጵያ ወረራ መፈጸም አትችልም:: እኛን የሚያስፈራን ነጭ ለባሹ ነው:: ነጭ ለባሹ ከሻእቢያ፣ ከአልይቃዳ እና ከአልሸባብ ጋር እየተደራደረ የኢትዮጵያን ገናናነት ወደ ታች እየመለሰ ነው:: ኢሳይያስ የግብጽ ቅጥረኛ ነው:: እነ ግንቦት ሰባት፣ ኦነግ... የትምክህት እና የጥበት ኃይላት የመሳሰሉት ደግሞ የኢሳይያስ ነጭ ለባሽ ሎሌዎች ናቸው:: የሀገር ውስጥ ነጭ ለባሾችን ለማምከን የጸረ ሽብር አዋጅ አዘጋጅተናል:: የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎች ነጭ ለባሽ ላለመሆናቸው ራሳቸውን ይፈትሹ!!››*[125] ብለው የኢትዮጵያውያንን ስሜት ቀሰቀሱ:: ሕዝቡ ብቸኛ ጠላቱ የዓባይን ግድብ የሚነካበት የውጭው ጠላት አድርጎ አሰበ::

በዚህ ትይዩ ኢሕአዴግን እንደ ልማት አምባሳደር፤ አቶ መለስም እንደ ዓባይን ለመገደብ የደፈረ ጀግና መሪ ታዩ:: ዓባይ ከ2003 እስከ 2010 ዓ.ም. ብሔራዊ አጀንዳ እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ የዓላማ መዳረሻ ሆኖ ቆየ:: ስለዚህ ልማቱ እንዳይደናቀፍ፣ እርስ በርስ ከተከፋፈልንም ለግብጽ እና ሻዕቢያ ወረራ እንጋለጣለን በሚል *ሥጋት* ኢሕአዴግ እንደ ሀገር ጥላ እና ከለላ በሕዝቡ ታየ:: ኢሕአዴግ ከሌለ ሕዝብ አዋጥቶ የሚገነባው የህዳሴው ግድብ የለም ተብሎ ታሰበ:: ኢሕአዴግ ይሄን ሕዝባዊ ሕልም ተጠቅሞ ፖለቲካውን የሚተቹ ልሂቃንን የሻእቢያ እና የግብጽ ተላላኪ እያለ በሕዝብ እያስጠላ ያስር እና ይገርፍ ያዘ:: አኬልዳማ ብሎም

[125]የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ሚያዝያ 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዘጋቢ ፊልም አሠርቶ ተቃዋሚዎች የቱን ያህል የጥፋት ኃይል እንደሆኑ በመንግሥት ሚዲያዎች አሳየ:: የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር(ኦብነግን) የአልሸባብ ክንፍ አድርጎ ሲፈርጅ፤ የአኬልዳማው የበኩር ልጅ ነው ያለውን ኦነግን ከግብጽ ተላላኪነት ጋር አያይዞ በዘጋቢ ፊልሙ አሳየ::

ግንቦት ሰባትን በትምክህት ኃይል ዝርዝር ውስጥ በሻዕቢያ ተላላኪነቱ በፊልሙ አሳየ:: ከዚያም ሀገር ውስጥ የፖለቲካ ንቃት ያላቸውን ደግሞ በግንቦት ሰባት፣ በኦነግ እና በኦብነግ አንጃነት ፈርጆ በሽብር ከሰሰ:: ሕዝቡም አውነት መስሎት ጉዳዩን በዝምታ ተቀበለው:: እንዲህም እንዲያም ሆኖ የአመጽ ደመና ያንጃበበባት ኢትዮጵያ የዓረቡን አብዮት ወደ ቅጥረ ግቢዋ ሳታስገባው ቀረች::

5.12 የዓባይ ግድብ እንደ እድገት በኅብረት ዘመቻ

በሥላሴ እና በለሆሳስ ነገሮችን ከአሉበት እየሸረሸረ የመጣው ወታደራዊው ደርግ ለማኅበረሰብ ልማት በሚል የተማረውን ሁሉ ወደ ገጠር እንደ ቻይናው ማኦ ዘዱንግ አሰማራው:: በታኅሳስ 12 ቀን 1967 ዓ.ም. በጃንሜዳ የእድገት በኅብረት ዘማቾች የድጋፍ[126] ሰልፍ ተደረገ:: ትምህርት ቤቶች ሁሉ ተዘግተው የተማረው ወደ ገጠር ዘመቻ ተሰማራ:: ‹‹ያልተማረ ይማር፤ የተማረ ያስተምር›› ብሎ ደርግ የመማር አብዮት ቀሰቀሰ:: ሙዚቀኞች እድገት በኅብረትን አስመልክተው ዘመሩ:: በ1966 ሲሻኮት የነበረው ተማሪ ሁሉ ሐሳቡን ልማት ዘመቻው ላይ አሳረፈ:: ዘመቻው በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ለትምህርት መስፋፋት እና ለሌሎች ልማቶች በጎ አስተዋጽኦ አድርጓል::

[126] ባሕሩ ዘውዴ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ* ከ1847 እስከ 1983

የኢሕአፓ ሰዎች እንደሚሉት ግን የዘመቻው ዋና ዓላማ፣ የተማሪውን ወደ ገጠር በትኖ በደርግ ላይ እንዳይነሡ ለማዘናጋት የታሰበ ነበር። ደርግ የተማሪውን ሁሉ ወደ ገጠር ልኮ፤ ይቃወሙኛል ያላቸውን ሁሉ አብዮታዊ እርምጃ እየወሰደ፤ አብዮታዊ መስመሩን እያቀለመ ቆየ። መኢሶንን አጋሩ አድርጎ ኢሕአፓን ከመታ በኋላ፤ መኢሶንንም አናጥሎ መታው።

ኅብረተሰባዊ አብዮቱን ያልተቀበለ የተማረ እንዳይኖር አደረገ። የደርጉ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሀገሪቱ ወታደራዊ ንጉሥ ሆነው ወጡ። ለመውጣታቸው ደግሞ የፖለቲካ እግራቸውን እስኪተክሉ የተማሪውን ለልማት ዘመቻ ከከተማ ማባረራቸው በአንጻሩ የተረጋጋ ጊዜን ፈጥሮላቸዋል ማለት ይቻላል። በዘመቻው ከ60 ሺህ[127] በላይ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለእውቀት እና እድገት ዘምተዋል። በኋላም ኢሕአፓ ወደ ከተማ ገብቶ የከተማ ትግል ቢጀምርም አልተሳካለትም።

የህዳሴው ግድብም እንደ እድገት በኅብረት ዘመቻ ከትንሽ እስከ ትልቅ አጀንዳው እንዲሆን አድርጎ ለኢሕአዴግ ምቹ ሜዳን ፈጥሮለታል። ነሐሴ 14 ቀን 2004 ዓ.ም. አቶ መለስ ሲያርፉ፤ ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር በቁጭት አንብቷል። ኢሕአዴግም የሕዝቡን ስሜት ተረድቶ የአቶ ኃይ ለማርም ደሳለኝን የ6 ዓመት የአገዛዝ ዘመን የመለስ ራዕይ ማስፈጸሚያ አደረገው። ኢትዮጵያም ከነሐሴ 14 ቀን 2004 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ድረስ በአቶ መለስ ራዕይ አማካኝነት ተመራች።

አቶ መለስ በራዕይም የመምራት የገዘፈ የሕዝብ ቅቡልነት ካገኙባቸው ሀገራዊ ሥራዎች አንዱ ትልቁ የዓባይ ግድብ ፕሮጀክት ነበር። በመለስ ራዕይ መመራት የዓባይን ግድብ እንደማገባደድ እና

[127] ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ ትግላችን 2004 ዓ.ም.

ኢትዮጵያን ከከተማ እስከ ገጠሩ በብርሃን ወጋገን እንደመሙላት ታሳቢ ተደርጓል። የዓባይ ግድብ[128] ጅማሮ በሚጋጭ ሕልም ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቡድኖችን ወደ ተቀራራቢ ስምምነት ያመጣ አንድ ታላቅ ሀገራዊ ሕልም ነበር።

ሀገር፤ ያደረ ታሪክን እና የነገ የጋራ ሕልምን ይፈልጋል። በኢትዮጵያ ያለው ጠርዝ ረገጥ ሽኩቻ ሊቃናም የሚችለው ሁሉም በፍትሃዊነት የሚጋራው ሀገራዊ ፕሮጀክት ሲኖር እና የፖለቲካ ትንታኔውም ከዓለም ሀገራት ጋር በንጽጽር ሲሠራ ነው። የኃይል አሰላለፍን በሀገር ውስጥ ካለ የፖለቲካ ክንፍ ጋር ብቻ እያሰሉ፤ በመተንተን… የሚሠራ ፖለቲካ ሀገራዊ ሕልምን ለማሳከት አይውልም። ኦሮሞው እድገቱን እና ፖለቲካውን ከአማራ አንጻር ብቻ ከተነተነ፣ ትግሬውም ከሶማሊያው አንጻር ብቻ እድገት እና ልማቱን ካሰላ የእርስ በርስ ውድድርን ብቻ አንግሶ በሌለ ልማት ግጭትን ደግሞ ይመርቃል። የኢትዮጵያን ልማት ከብሔረሰቦች አንጻር ከመመልከት ከጎረቤት እና ከዓለም ሀገራት አኳያ መመልከት ሩቅ ለመሻገር ይበጃል።

128 አብይ አህመድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ከመጡ በኋላ፤ የዓባይ ግድብ በመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) አማካኝነት ገንዘቡ እንደተመዘበረ ይፋ ወጣ። 60 በመቶ አካባቢ ተጠናቋል ተብሎ ሲዘገብ የነበረ ቢሆንም፣ ከ24 በመቶ ያለፈ እንዳልሆነ ተነገረ። አቶ መለስ ግድቡ በ5 ዓመት ይጠናቀቃል ብለው ነበር። እንደ አቶ መለስ ግድቡ በ2008 ዓ.ም. መጠናቀቅ ነበረበት። ነገር ግን ከሁለት ዓመት በኋላ እንኳን በ2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ግድቡ በ10 ዓመትም አይጠናቀቅም ብለው ሕወሓት የሠራውን በማንኳሰስ የራሳቸውን ኢሕአዴግ ከፍ ለማድረግ ሞከሩ። ወዲያውም የግድቡ ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ስመኘው በቀለ መስቀል አደባባይ ላይ ሐምሌ 19 ቀን 2010 ዓ.ም. ተገድለው ተገኙ። የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንገ ኮርፖሬሽን(ሜቴክ) ዋና ሓላፊ የነበሩት ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘው ወዲያው ታሰሩ። አውሮፕላን እና መርከብ ሁሉ የሕወሓት ጀኔራሎች እንደዘረፉም ተነገረ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሕወሓትን በመክሰስ በሕዝብ እንዲወደዱ እና መንግሥታቸው እንዲጸና አድርገዋል። በሕወሓት መጠላት ላይ የዶክተር አብይ አስተዳደር መንግሥታቸውን ለማጽናት የሄዱበት መንገድ ከዓመት በላይ በቅቡልነቱ ሊዘልቅ አልቻለም።

5.13 ኢሕአዴግ እና ተቋማዊ ተረክዙ

ኢትዮጵያ በጦርነት ድል እንጅ ፖለቲካዋ ብዙ ጊዜ አሸናፊ አልሆነላትም:: የቅርቡን ከአድዋ እስከ ኢትዮ-ኤርትራ አውደ ውጊያዎች ብንመለከት የጦር ድልን እንጂ የፖለቲካ አሸናፊነትን ብዙ አናይም:: በ1928 ዓ.ም. በዳግም ጣሊያን ወረራ ወቅት በኢትዮጵያ አርበኞች እና በፀሄ ኃይለ ሥላሴ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ከአምስት ዓመት በኋላ ጣሊያን ተሸንፋ ተባራለች:: የጣሊያን መባረር የኢትዮጵያን የጦር ድልን ያመለክታል:: ከድሉ በኋላ ግን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጣሊያን ጋር ያደሩ ልሂቃንን ሾሙ:: አርበኞች[129] በፖለቲካው ተገለው ከጂዎች ለሽልማት ተበረታቱ:: የኢትዮጵያ ፖለቲካም የፈሪዎች እና የባንዳዎች ተደርጎ በአርበኞች ተፈረጀ:: እነ በላይ ዘለቀ እና ደጃዝማች አበረ ይማምን… የመሳሰሉ አርበኞች በባንዳ ፖለቲካ አንገዛም ብለው ተነሡ:: ከዚያም በረዥም ሂደት የ1953ቱ አብዮት ተከሰተ::

በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ በ1970ዎቹ መግቢያ የተደረገው ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ:: የጦርነት ድሉ ግን በደርግ ፖለቲካ ላይ፣ የሕዝብ አሸናፊነት የተረጋገጠበት አልነበረም:: ከ1989 ዓ.ም. መጨረሻ አስከ 1992 ዓ.ም. አካባቢ የተደረገው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሲደረግ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ቢጠናቀቅም፣ የፖለቲካ አሸናፊነት ግን ፈጽሞ አልተስተዋለበትም:: የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤት አላደረጋትም ወይም ጦርነቱ ሌላ ያተረፈላት ነገር የለም::

[129] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አርበኞችን ሳይሾሙ፣ ባንዳዎችን ያቀረቡበት ምክንያት ባንዳዎች የተሻለ የቢሮክራሲ እና የእውቀት ችሎታ ስለነበራቸው እንደነበር ልጅ ዳንኤል ጆንቴ መስፍን (የኢትዮጵያ አርበኞች ማኅበር ፕሬዝዳንት) ናሁ በተባለ ቴሌቪዥን ሐምሌ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. በተላለፈ መርሐ ግብር ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: አርበኞች በሀገር ፍቅር ወኔ ነዲድ ስሜት ያላቸው እና ለሀገር ሲሉ ራሳቸውን ለሞት ያመቻቹ ቆራጦች ናቸው:: ነገር ግን ብዙዎች የተማሩ አልነበሩም:: የቢሮክራሲ እጥረት ነበረባቸው የሚል ድክመት ይነሣባቸዋል:: በዚህ ምክንት ጃንሆይ ሥልጣን ለተማረው እየሰጡ ያልተማሩ አርበኞችን ፊት ነሡ የሚል ተረክ ከመሳፍንቱ ወገን ይነሣል::

ኢትዮጵያውያን በጦርነት እንጂ በፖለቲካ ያለማሸነፋችን መንስኤ ሥርዓት እና ሀገራዊ ርዕይን የሚሸከም ነጻ ተቋም አለመፈጠሩ ነው። የአክሱሙ ወደ ላሊበላ፣ የሐረሩ ወደ ጎንደር... የሚሻገረው ሥልጣኔ እንኳ የተቆራረጠ እና የመላውን ሕዝብ ባህል የቀየረ አይደለም። ፋሲለደስ ቤተ መንግሥት ጎንደር ላይ ቢሠራም፤ ያን የመሰለ የሕንጻ ውቅር ግን ወደ ሕዝቡ አልተሸጋገረም። እውቀቱ በጥቂት ልሂቃን ብቻ የታጠረ ነበር። በነጋሲው እና በአንጋሹ መካከል ያለው የማኅበራዊ ደረጃ ልዩነት የተራራቀ በመሆኑ ሕዝቡ የልሂቃኑን በጎ ነገር የሚቀስምበት ሜዳ እንኳን የለም። ሀገር በተመጋጋቢነት የምትጓዘው ባህላዊውንም ይሁን ዘመናዊውን ቢሮክራሲ የተከተለ ተቋማዊ መዋቅር ሲኖር ነው።

የኢትዮጵያ ታሪክ ከመንግሥትነት ባሕርይው ይልቅ የፓርቲነት ተክለ መዋቅር ባለው ሥርዓት የተሞላ ነው። የኢትዮጵያ መልክ የገዥዎች አምሳል እንጂ ገዥዎች የኢትዮጵያዊነት ቀለሞች መሆን አልቻሉም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ የደርግ እንዲሁም የኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ቀለም ይለያያል። ኢትዮጵያዊያን በመንግሥትነት ዘመናቸው ያስቀጠሉት የቆዳ ቀለማቸውን ብቻ ነው። ሌላው ነገራቸው እንደመንግሥታቸው ባሕርይ ሲቀያየር ኖሯል። ለዚህ ሁሉ የሥር ምክንያት የማይቆራረጥ ሥርዓት እና ትናንትን ከዛሬ አገናኝቶ ወደ ነገ የሚገፋ አሻጋሪ ተቋም አለመኖሩ ነው። በኢሕአዴግ ጊዜም የተፈጠሩ ተቋማት የፓርቲያዊነት ግልጋሎት ከመስጠት ያለፈ ትናንትን በዛሬ ትክሻ ላይ ለነገ የሚያስረክቡ አልነበሩም።

5.14 ተቋማዊ ስንጥቆች

የመንግሥት የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት[130] የተማረውን ይቀጥራሉ:: መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ቀጣሪ ነው:: ስለዚህ ተቋማት የሥራ እድል መፍጠሪያ አማራጮች ሆነዋል:: መንግሥትም ኢንቨስተር ነው:: ተቋማት እና ፓርቲው አንድ እና ያው በመሆናቸው የተማረው ለመቀጠር ፓርቲውን መደገፍ አሊያም አለመተቸት ሳይጻፍ የጸደቀ ግዴታው ይሆናል:: የተማረው በልቶ ለማደር ሲል አስመሳይ እና የሐሳቡን የማይኖር ብኩን ሆኗል:: በኢትዮጵያ ለመኖር የገዥውን ፓርቲ ሐሳብ መሸከም ተቋማት ያስገድዳሉ:: መንግሥት ብቻ ሥራ ፈጣሪ በሆነበት ሀገር ውስጥ፣ ተቀጣሪዎች

---

[130]ተቋም ሲባል ባህላዊ ወይም ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶችንም ይጨምራል:: ለምሳሌ ቤተሰብ፣ እድር፣ እቁብ፣ የጋብቻ ሂደት፣ ልዩ ልዩ ልማዶች፣ ትውፊታዊ መሰባሰቦች እና ባህላዊ ክዋኔዎች ሁሉ ኢ-መደበኛ ተቋማት ናቸው:: ተቋም ማኅበረሰብ ፍላጎቱን የሚያሸክምበት ሥራዓተ መዋቅር ነው:: ኢ-መደበኛው ተቋማት ንቁ ሆነው ማኅበረሰቡን ባያስተሳስሩ ኖሮ ኢትዮጵያ የየመን እና የሶሪያ እድል ይገጥማት ነበር:: በመደበኛ ተቋማት ስለመገንጠል ቢታወጅም፤ በኢመደበኛ ተቋማት ጋብቻን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ሕዝቡ እንዳይለያይ ሆኖ ተጋምዷል:: ተሰባጥሯል:: በአምልኮ እና በባህላዊ ኑባሬው ምክንያት በብሔርተኞች ተረክ ሊለያዩ የተፈለጉ ሕዝቦች አንድ ሆነው ተሠርተዋል:: መደበኛ ተቋማት የባህላዊው ተቋምን ያህል ከዛሬ ያለፈ ሕልም ቢኖራቸው ኖሮ ሀገሪቱ እድገት እና ሰላሟ ለዜጎቿ ምቹ ይሆን ነበር:: ኢትዮጵያ ከ1928 እስከ1933 ዓ.ም. ድረስ ለ5 ዓመታት ያህል መንግሥት አልባ ሆና እያለ ያለምንም መንግሥታዊ ተቋማዊ አመራር፤ ሕዝቦቿ ተደራጅተው ሀገራቸውን ነጻ አውጥተዋል:: ዘውዳዊው መንግሥት ወደ ወታደራዊው፣ ወታደራዊው ወደ ዘውጌው ኢሕአዴግ ሲሸጋገር የተወሰነ ጊዜም ቢሆን የመንግሥት ተቋማት ሥራ አቁመው ነበር:: ነገር ግን ሕዝቡ በፈጠረው ማኅበራዊ ተቋም(ሕሊናዊ ተቋም) ምክንያት የከፋ አደጋ አልተከሰተም:: **ኢትዮጵያ የተማሪ ያጠፋት ሀገር ናት::** በተማረው የሚመሩ ተቋማት(አካላዊ ተቋማት) ለሕዝቡ እና ለሀገር ሳይሆን ለፖለቲከኞች ሥልጣን ማወፈሪያ ማዕከሎች ናቸው:: በአድዋ ጦርነት ሕዝቡ በማኅበራዊ አኗኗሩ ባዳበረው ሀገራዊ ሕልም ተነሥቶ ሁሉም ከየአካባቢው ለሀገሩ ተዋግቷል:: በ1970 ዓ.ም. በሶማሊያ፣ በ1990 ዓ.ም. በኤርትራ… ኢትዮጵያ ያደረገቻቸው የሀገር ሉዓላዊነትን የማስከበር ጦርነቶች ከአድዋው ጋር ሲነጻጸር ያነሰ የሕዝብ ስሜትን ያስተናገደ ነበር:: በሶማሊያ የኢሕአፓ፣ በኤርትራ ደግሞ የኦነግ አባላት ኢትዮጵያውያን አንዳንዶች በኢትዮጵያ በኩል ተሰልፎ ለመዋጋት ዝግጁዎች አልነበሩም:: ኢሕአዴግ የፈጠራቸው ተቋማት ሀገራዊ ሕልም ሳይሆን ፓርቲያዊ ርዕይ ስላላቸው ትናንትንም ሆነ ነገን አያልሙም:: ሥልጣን የሥራ ቅጥር መስሎ ስለተተረጎመ ባለሙያ ማለት የፓርቲ ሰው ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ነው:: ባለሙያ እና ካድሬነት ፣ መንግሥታዊ ተቋም እና ገዥው ፓርቲ… ጋብቻ ፈጥረዋል::

የመንግሥት ጥገኛ ሆነው ይታሰራሉ። የተማረው በሀገሪቱ ፖለቲካዊ መሻሻል እና እድገት ላይ አስተዋጽኦው የሳሳው ከእሥር ቤት በማይሻሉ መንግሥት ፈጠር ተቋማት በመሥራቱ ነው። ተቋማቱ ለገዥው መታመንን እንጂ ሙያን አያከብሩም።

አንድ የወታደርነት ሙያ ያለው ሰው ፓርቲውን ለመጠበቅ ከተማ ለከተማ እንደመደበኛ ፖሊስ ሲዞር ይውላል። የሀገር ስዕል የሆነው የመከላከያ ሠራዊት ከሀገር ዳር ድንበር በላይ ዜጎች በመንግሥት ላይ ለተቃውሞ ሲወጡ ነፍጥ ስቦ ይገድላል። መከላከላያ ሠራዊት የፓርቲ ዘበኛ እንኳን መሆን መስሎ ከታየ አደገኛ ነው። በ1983 ዓ.ም. ግማሽ ሚሊየን ይደርሳል የተባለው በደርግ ጊዜ የነበረ የኢትዮጵያ ሠራዊት የተበተነው የኢሠፓ አስፈጻሚ ነው ተብሎ ስለታሰበ ነበር።

ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም. የነበረውን ወታደር ኢሕአዴግ የደርግ ነው ብሎ ካባረረ፤ ከ1983 እስከ ኢሕአዴግ መጨረሻ የነበረ ወታደርም በኢሕአዴግነት ተፈርጆ የመባረር እጻ አለበት ማለት ነው። ሂደቱ እንዲህ ከሆነ ወታደሩ ለአገዛዙ ባሪያ ሆኖ የሥርዓቱ ዘበኛ የመሆን እድሉን ሰፊ ያደርገዋል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ ተቋማት የአገዛዙ እድሜ ማራዘሚያ ክኒን ናቸው ወደ ሚል ድምዳሜ ይገፋል። ተቋማት የሀገሪቱን ትናንት እና ነገ በዛሬ መንገድ ላይ የሚያሻግራቸውን ትክሻ እንደ ጤዛ ወዲያው ተኖ ለሚረግፈው ፓርቲ ተሸካሚ ሆነዋል። ተቋማት እና ገዥ ፓርቲው ከተጋቡ አምባገነንነት ሕጋዊ መስሎ ይወለዳል። ይፋፋል። ሀገር ርዕይ አልባ ትሆናለች። መድሎ ተቋማዊ እና ሥርዓታዊ ይሆናል።

በኢትዮጵያ የዘላቂ የተቋም ግንባታ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በአርያነት መጥቀስ እንችላለን። ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስካሁኑ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያዊነት

የታሪክ፣ የትውፊት፣ የባህል፣ የጥናት እና ምርምር ሙዳይ ሆና ታገለግላለች። ከአክሱም እስከ ዛጉዌ፣ ከሸዋ እስከ ጎንደር ያለውን የነጋሲነት እና የሥልጣኔ ሂደት ቤተ ክርስቲያን መሃል ሆና በማስታረቅ ሀገር እንዲጸና አድርጋለች። ምዕራባውያን ክርስትናን ለአፍሪካ በሰባኪዎቻቸው አማካኝነት እንዳመጡት ቢናገሩም፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ከራሳቸው ከአውሮፓውያን ቀድማ ሃይማኖታዊ ተቋም ሆናለች።

የክርስትና የመስፋፋት ምንጩ አውሮፓ ነው የሚለውን ትርክት ቤተ ክርስቲያኗ ውድቅ አድርጋዋለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ቆጠራዋ እና ታሪኳ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ተቋማዊ ጸጋም ናት። ቤተ ክርስቲያኗ በኢየሩሳሌም ሳይቀር የራሷን ገዳም የገነባች እና የኢትዮጵያን ቀለም በእስያ ያነበረች ተቋም ናት። ንጉሥ ገዳም(ዴር ሱልጣን ገዳም) በኢየሩሳሌም ዛሬም ድረስ ግብጽ የእኔ ነው የሚል ጥያቄ ብታነሣም በኢትዮጵያ ይመራል።

ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ሀገራት ሳይቀር ቀዳማዊ ተቋም የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከ1966 ዓ.ም. በኋላ ይሄን ተቋማዊ ባህሏን ላለመቀበል በርካታ አሻጥሮች እየተሠሩባት ነው። ደርግ ቤተ ክርስቲያንን የሶሻሊዝም መንበር ለማድረግ ሲሞክር፤ ኢሕአዴግም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማስረጫ ማዕከል ብሔር ብሔረሰብ ለማስባል ሙሉ ሙከራ አድርጓል። ያም ሆኖ ግን ቤተ ክርስቲያን ብዙ መሪዎቿ ከአገዛዙ ጋር አቅላቸውን ስተው ቢያጎበድዱም፣ በቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓታዊ መዋቅር ላይ ያመጡት ለውጥ የሳሳ ነው።

በተለይም ኢ-መደበኛ የሆነው(ሕሊናዊ ትውፊቱ) የቤተ ክርስቲያናዊ የጋብቻ እና የማኅበራዊ ተራክቦ ተቋማዊ ሁነት ከአምና እስከ

ዘንድሮ እንደ ገዥዎች ሁኔታ አልተቀያየረም፡፡ የእምነት ተቋማት መግባቢያቸው ሰውነት ስለሆነ አማራው ከኦሮሞው፣ ትግራዩ ከሲዳማው… እንዲጋባ በማድረግ ድርብ ማንነት ያላቸው ልጆች እንዲወለዱ ሆኗል፡፡ የነገረ ሃይማኖት እና የመንፈሳዊ ጉዳዮች ተመራማሪ እና ፈላስፋ፣ ገጣሚ እና ጋዜጠኛ የሆነው ሰለሞን ደሬሳ ለሪፖርተር መጽሔት በወርሃ መስከረም 1991 ዓ.ም. በሰጠው ቃለ መጠይቅ ስለኢትዮጵያውያን ድርብ ማንነት ገላጭ ንግግር አድርጓል፡፡ *‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጦ እኔ አማራ፣ት ግሬይ፣… ነኝ ማለት አይቻልም፡፡ በሴት አያቶቻችን በር አፍ ማን እንዳለፈ ስንቶቻችን ነን የምናውቀው? የኔን ጥሩ ኦሮሞነት እግዚአብሔር እና ሴት አያቴ ወይም እናቴ ናቸው የሚያውቁት፡፡››* ሲል በኢትዮጵያ በጦርነት እና በንግድ ከሚፈጠር ማኅበራዊ ተራክቦ በተጨማሪ ጋብቻ የሚፈጥረውን ድርብ ማንነት ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ድርብ ማንነት(ቅይጥ) ያላቸው ልጆች ከነገዳዊ ማንነት ይልቅ ለኢትዮጵያዊ ማንነት እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡ የእምነት ተቋማት መሠረታዊ አስተምህሮም በትንሹ ኢትዮጵያዊነት አሊያም ዓለም አቀፋዊነትን ያማከለ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ከቀደመው ፓርቲ የወረሳቸውን አካላዊ ተቋማት ኢሕአዴግኛ[131] ለማድረግ ሲል በርካታ ጥፋቶችን ፈጽሟል፡፡

[131]የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽንን በብቸኝነት አገዛዙ ከያዘ በኃላ ቴሌ የደንበኞችን ስልክ በመጥለፍ ለደኅንነቱ ያቀብላል፡፡ የውሸት ሪፖርትም ለአገዛዙ በሚያመች መንገድ እየፈበረከ በቴሌ መረጃ አቅራቢነት ለእስር ተዳርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድም አገዛዙን የሚተቹትን አሳሳፍሮም ማለቱ የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከአዲስ አበባ ወደ ባሕር ዳር በአዲስ አበባ ጉዳይ ከባሕር ዳር ሕዝብ ጋር ለመምከር ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. ባሕር ዳር ተገኝቶ ነበር፡፡ ነገር ግን አየር መንገዱ ከባሕር ዳር ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ቲኬት ቆርጦ መሳፈር አትችልም ተብሏል፡፡ ኢሕአዴግ ነባር ተቋማትን ለስለላ እና ተፎካካሪን ለማጥቃት ይጠቀምባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ሰውን በውሸት አሸባሪ ነው ብሎ ለማስወንጀል የሐሰት የባንክ ሪፓርት እየሠራ ብዙዎችን ለእስር ዳርጓል፡፡ ሐምሌ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ጽጌን መፈንቀለ መንግሥቱን መርቷል የሚል ዘገባ እማኝ ሆኖ የቀረበው የንግድ ባንክ ደብተር ነበር፡፡ ነገር ግን ደብተሩ የአሞላል ቅጹን እንኳን በትክክል ያልተከተለ ስለነበር ንግድ

ታላቁ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መተግበሪያ ለማደረግ የካድሬ መንደር አድርጓል። ሥርዓተ ትምህርቱን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር መቀበሉን ትቶ ስለ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ያተኮረ አድርጎ ሀገራዊ ማንነትን በሥርዓተ ትምህርቱ ተፍቋል። የታሪክ ትምህርት ትኩረት ተነፍጎ፤ ኢትዮጵያን በኢሕአዴግ ባሕርይ የሚገልጸውን የሥ-ነዜጋ እና ሥነ-ምግባር ትምህርት ለትውልዱ ተሰጥቷል። ሥርዓተ ትምህርቱ የኢሕአዴግ የሥልጣን ማራዘሚያ ሆኖ ተቀርጿል።

5.15 ሚዲያ

ሚዲያ የሀገር መልክ ነው። የዓላማ መሪ ነው። ፖለቲካ የራስን እውነት የመፍጠር ሂደት ነው። የእውነቱ መፍጠሪያ የማስፈጸሚያ መንገዱ ደግሞ ሚዲያ ነው። ሰው ከእንስሳት የሚለየው ባህል በመኖሩ ነው። ባህል ከእሳቤ ይመነጫል። እሳቤ በሚዲያ ተሸምኖ በየሰው ልጆች ጭንቅላት ልባስ ይሆናል። ሃይማኖተኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ወይም ነቢዩ ሙሀመድን ከእዝነልቦናቸው አቅርበው የሚመለከቷቸው በዓይን አይተዋቸው ሳይሆን በሚዲያ ንግርት ነው። ሃይማኖት ሳይቀር የሚዲያ ተግባቦት ስብከት ውጤት ነው። ሚዲያ የጭንቅላት አለቃ ነው። የዓለም የድርጊቶች ስዕል ንድፉ የሚወጣው በሚዲያ ነው። ትውልድን እና ሀገርን በስሜት ከሚያናብቡ ተቋማት መካከል ሚዲያ ዋና ሚናውን ይወስዳል። ለዚህም ነው ሚዲያ ከፓርቲ ምርኮኝነት ወጥቶ የሕዝብ ንብረት እንዲሆን የጋዜጠኝነት ሳይንሱ የሚያስገድደው።

ባንክም፤ መንግሥትም ትዝብት ውስጥ ወድቀዋል። በደብተሩ ዜግነት በሚለው ጉለሌ፣ ሥራ በሚለው ስልክ ቁጥር.. ተሞልቶበት ታይቷል። በጥቅሉ ተቋማት የሕዝብ ሳይሆን የአገዛዙ መሣሪያ ሆነዋል። ሕዝብ ማገልገላቸውን የእግረ መንገድ ሥራ አድርገው ዋነኛ የመጋረጃ ጀርባ ሥራቸው ከአገዛዙ ጋር እየወገኑ የራሳቸውን ደንበኛ መሰለል እና ማግለል ሆኗል። የተቋማት አለመታመን በድምሩ የሀገር ፍቅር ስሜትን ትንሣኤ ለሌለው ሞት ይዳርገዋል። ሀገርንም ትናንት እንዳይኖራት አድርጎ ልቦና ያርቃል። መማርንም ሙያ በተቀበረበት ሀገር ውስጥ ፋይዳቢስ ያደርጋል።

5.16 ሚዲያ በኢትዮጵያ

በአውሮፓ የሚዲያ ፍልስፍና መሠረት፤ ሚዲያ ከሕግ አውጭው፣ አስፈጻሚው እና ተርጓሚው ቀጥሎ በአራተኛ የመንግሥነት መዋቅርነት ይቀመጣል:: የተቋማት እና የአገዛዞች እንቅስቃሴ ድምር በሚዲያ ይገለጻል:: ከመብት አንጻርም ሐሳብን በነጻነት መግለጽ የመብቶች ሁሉ ርዕስ ነው:: ስለዚህ የአንድን ሥርዓት ሂደት ለማጥናት ሥርዓቱ በሚዲያው ስለሚገለጽ የሚዲያውን ባሕርይ ብቻ ማጥናት ዝርዝር ጉዳዮችን ለማጤን መንገድ ይከፍታል::

በኢትዮጵያ ሚዲያ በኅትመት ዘርፍ በአማርኛ ቋንቋ መታተም የጀመረው በ1895 ዓ.ም. በአዕምሮ ጋዜጣ ነው:: አዕምሮ ጋዜጣ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እየታተመች ከ24 አስከ 200 ቅጂዎች ትሠራጭ ነበር:: በራዲዮ ዘርፍ ደግሞ ከታኅሳስ 24 ቀን 1927 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ራዲዮ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን፤ ሙሉ ሥርጭቱን መስከረም 2 ቀን 1928 ዓ.ም. በጃንሆይ ንግግር አብስሯል:: በጣሊያን ወረራ ወቅት የኢትዮጵያ አርበኞች የኢትዮጵያ ራዲዮን ለጠላት ፕሮፖጋንዳ እንዳይውል ብለው ሙሉ በሙሉ አውድመውታል[132]:: የቴሌቪዥን ሥርጭት ደግሞ ጅማሮውን ያደረገው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 33ኛ ዓመት[133] የዘውድ በዓላቸው ሲከበር፤ በጥቅምት 23 ቀን 1957 ዓ.ም. ነበር::

ዘመናዊው የኢትዮጵያ ሚዲያ ወደ ግልጋሎት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ባሕርይው ለገዥው የተንበረከከ ሆኖ ቀጥሏል:: በዘውዳዊው መንግሥት ዘመን ዘውድ ጭኖ ነጋሽ ሆኖ ሲታይ፣ በደርግ ደግሞ የኅብረተሰባዊት አብዮትን ቀይ አክሊል ደፍቷል:: በ1953 ዓ.ም.

---

[132] መዝሙር ሃዋዝ፣ የብዙኀን መገናኛ እድገት በኢትዮጵያ 2011 ዓ.ም.::

[133] ዝኒ ከማሁ

ከታኅሳሱ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የኢትዮጵያ ራዲዮ መንግሥቱ ንዋይ ከ40 ዓመት በላይ ያለው ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲገደል የሚል ጽሑፍ ከኪሱ ተገኘ ብሎ ዘገበ። በዚህም ሕዝቡን በዕድሜ ከ40 ዓመት በታች እና በላይ ብሎ አቧደነ። ሽማግሌ ወጣትን ጠላ። ወጣቱም ሽማግሌውን እንደወግ አጥባቂ ተመለከተው። የታኅሳሱ መፈንቀለ መንግሥት በየካቲት አብዮት ከ13 ዓመት በኋላ ስኬታማ ሲሆን፣ ደርግ የኢትዮጵያ ራዲዮን የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ድምጽ ብሎ የኅብረተሰባዊነት መዝሙር ማዘመሪያ አደረገው።

ከጳጉሜን 1966 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ መስከረም 2 ቀን የኢትዮጵያ ቴሌቪዝን በጃንሆይ ጊዜ የደረሱ የርሀብ ሰቆቃዎችን ለእይታ አበቃ። ደርግ ጃንሆይንም ወዲያው ፈነገለ። ከእንቁጣጣሽ ማግስት መስከረም 2 ቀን ጃንሆይን ደግፎ፣ ደርግን ነቅፎ የተወሰነው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰልፍ አደረገ። ደርግ ሰልፉን አስቀርጾ የአዲስ አበባ ሕዝብ ደርግን ደግፎ ሰልፍ ወጣ ብሎ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አስነገረ። ይህን ዜና ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ የመጀመሪያው የደርግ የሚዲያ ነጭ ውሸት አድርገው ይወስዱታል።

የአብዮታዊቷ ኢትዮጵያ ድምጽ የሆነው የኢትዮጵያ ራዲዮ እና ቴሌቪዥን ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች ለደርግ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ አደረ። በእንግሊዝኛ ቋንቋ በየዕለቱ ለአንድ ሰዓት ለዚምባብዌ ነጻ አውጭዎች ከመመደቡ ባለፈ፣ ለደቡብ አፍሪካ እና ለሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ቀንበር ነጻ እንዲወጡ የትግል ሚዲያ ሆኖ አገልግሏል። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለሙጋቤ ወደ ሥልጣን መምጣት እና ለዚምባብዌ ነጻነት በኢትዮጵያ ራዲዮ እና ቴሌቪዝን በኩል ዳጎስ ያለ ውለታ ውለዋል። በሀገር ውስጥ የሾሳሊዝም ሥርጸት ዘመቻ እና አማጺያንን የመምታት ፕሮፖጋንዳ፣ በእንግሊዝኛ ደግሞ የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል

ማቀጣጠያ ሆኖ አገልግሏል። በደርግ ወቅት የኢትዮጵያ ሚዲያ የዘመቻ እና የነጻ አውጭነት ሚና ይዞ ቆይቷል። በዚህ ውስጥ የጋዜጠኝነት ሙያዊ ሥነ-ምግባር እና የሚዲያ መርሆ የሚባል ነገር አይታሰብም። ኢሠፓ ይዘቱን ይጽፋል፤ ጋዜጠኛው ያነባል።

አንዳርጋቸው ጽጌ በምሁራኑ የደብተራ ባህል መስረጹ የሀገሪቱን እድገት ገድቧል ይላሉ። ምሁራን ልክ እንደ ደብተራዎች ማነብነብ [134]እንጂ ከገሃዱ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ አገናዝበው መፍትሄ ሰጭ ምርምር ለማቅረብ አልቻሉም። የአንዳርጋቸው የደብተራ ባህል ብያኔ ከምሁራን የበለጠ ጋዜጠኞችንም ይገልጻል። ጋዜጠኛው ይግባውም፤ አይግባውም በአገዛዞች የተደረሰውን ሁሉ ያነበንባል። ልክ ደብተራው[135] በአምላክ መንፈስ ተጽፏል ብሎ የሚያስበውን መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ሌሎች መንፈሳዊ መጽሐፍትን ሳይጠይቅ አምኖ እንደሚያነበው ሁሉ፤ ጋዜጠኛውም ገዥው ያለውን በልክነት የመስፈር ሥርዓታዊ አገዛዙ ያዝዘዋል።

5.17 ሚዲያ እና ኢሕአዴግ

ኢሕአዴግ ከደርግ የሚለየው በቅብ አምባገነንነቱ ሲሆን፤ ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል በሚያደርገው ጥረት የሚዲያ ነጻነትን ጅማሮ አሳይቷል። የግል እና የመንግሥት ሚዲያዎች እንዲመጡም አድርጓል። ከ1984 እስከ 1990ዎቹ መግቢያ ከ200 በላይ[136] የግል እና የመንግሥት ጋዜጦች እንዲሁም 87 መጽሔቶች

---

134 አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ 1997 ዓ/ም።

135በእርግጥ ደብተራነት መጠየቅን እና መፈላሰፍን፣ ነገሮች መመርመር፣ ከተባለው እና ከታየው ባሻገር መመልከት እና ማመስጠርን የሚጠይቅ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ርዕሠ ማእርግ ነው። አንዳርጋቸው ደብተራን በሸምዳጅነት መውሰዳቸው ከእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል። ደብተራነትን በማራከስ የታሪክ ጥራዞች ማደብዘዝ፣ የሀገር ፍቅር እና አንድነት የሚያያዙ ጉዳዮችን ሥሪት ለመናድ ደብተራን እንደ ተረት ነጋሪ በማየት ሀገር ለማሳሳት በዘውገኞች ዘንድ በአሉታ ጥቅም ላይ ውሏል።

136Nicole Streamlau, The press and the poltical restructuring of Ethiopia (2012). Journal of eastern Africa studies, Oxford University.

ያለምንም ገደብ የኀትመት ሚዲያውን ተቀላቅለዋል፡፡ የኀትመት ውጤቶች ከፖለቲካ ትችቱ ባለፈ፤ የወሲብ ጉዳዮችን በአደባባይ በማውጣታቸው ከኢሕአዴግ በላይ ማኅበረሰቡ ማጣራት(ሳንሱር) እንዲደረግ ለመጠየቅ ተገዷል፡፡ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ሚዲያዎች ልቅ ሆነው ወጣቱን ለወሲብ አነሣስተው ኤች.አይ.ቪ እንዲስፋፋ እያደረጉ ነው የሚል ወቀሳ ሁሉ ደርሶባቸው ነበር፡፡

ነገር ግን የመንግሥት ሚዲያው መሠረታዊ ፍልስፍና ከኢሕአዴግ ፓርቲያዊ መርህ የሚቀዳ ነበር፡፡ ደርግ የጃንሆይን ሰሃ/አበሳ እየመዘዘ ሲያሳይ እንደነበረው ሁሉ፣ ኢሕአዴግም የደርግን እንከን እየፈለፈለ የራሱን መስመር ጥራት ለማሳየት ሞክሮበታል፡፡ በተለይ ከ1983 እስከ 1997 ደርግ አማራ ነው የሚል የአቻነት ትርጓሜ ሰጥቶ አማራውን ለማጥፋት ተጠቅሞበታል፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያን በኤርትራዊው ተስፋየ ገብረአብ እንዲመራ አድርጎ እንደ ቡርቃ ዝምታ ዓይነት መጽሐፍ በመንግሥት ድጋፍ እንዲጻፍ አድርጓል፡፡ እፎይታ የሚል መጽሔት በነተስፋየ ገብረአብ እየተዘጋጀ የትምክህት ኃይሉ አከርካሪው ይሰበራል፤ ተራራውን ያንቀጠቀጠው ትውልድ ዳግም በኢትዮጵያ አይፈጠርም የሚል ደማቅ ደማቅ ፕሮፖጋንዳዎች ተዘሩ፡፡

በምርጫ 97 የግል ሚዲያዎች የፖለቲካ ንግርቱን ተቆጣጠሩት፡፡ ኢሕአዴግንም እርቃኑን አስቀሩት፡፡ አምባገነን አገዛዞች ሐሳብ ስለሚያጥራቸው ሐሳብን በጉልበት ይገላሉ፡፡ ድህረ ምርጫ 97ን ተከትሎ የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ይበልጥ ስለታማ እየሆነ ከኢሕአዴግ ሐሳብ ውጭ ያሉ እሳቤዎችን ቆረጠ፡፡ ጋዜጠኞች ወደ እሥር አየተላኩ፤ ጋዜጦችም ታሸጉ፡፡ በዚህ ምክንያት የመንግሥት ሚዲያዎች ብቸኛ የመረጃ ምንጭ ሆነው ታዩ፡፡ የሚዲያዎች የመረጃ ምንጭም ኢሕአዴግ ብቻ ሆነ፡፡ ፓርቲው ሲበርደው ጃኬት መደረብ፣ ሲሞቀው ጃኬት ማውለቅ ዘወትራዊ

የመንግሥት ሚዲያዎች ባሕርይ ሆኑ፡፡ ኢሕአዴግን የሚተቹ ልሂቃን እንደ ጸረ ልማት እና ጸረ ሰላም ተደርገው ተፈረጁ፡፡

ፍረጃውን ለማጽናትም አኬልዳማ፣ ጅሃዳዊ ሀረካት፣ አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ… የሚሉ የውንጀላ ዘጋቢ ፊልሞችን አስተጋቡ፡፡ በሌላ በኩል የኢሕአዴግን ተክለ ቁመና ለማግዘፍ የሕወሓት እና የብአዴን የትጥቅ ትግል ድሎችን፣ የግንቦት ሃያ እና የብሔር ብሔርብሔረሰቦች በዓላት፣ የልማታዊ መንግሥት ቱርፋት እና የኢሕአዴግ ግሥጋሴ… የሚሉ የፕሮፖጋንዳ ይዘት ያላቸው ጭብጦች የሚዲያዎች ማንጸሪያ ሆኑ፡፡ ስለማኅበረሰብ ችግር እንኳን መዘገብ ሚዲዎች ዘንግተውት ነበር፡፡

በ2008 ዓ.ም. በሀገሪቱ ድርቅ ተከስቶ ነበር፡፡ በዚህ ድርቅ ልጆ ሞተብኝ ብላ ብርቱካን አሊ የተባለች የሰሜን ወሎ ሀብሩ ወረዳ ነዋሪ ለቢቢሲ ተናገረች፡፡ ራበኝ ብላ በመናገሯ ከመንግሥት የኮሚኒኬሽን ዘርፍ ማስፈራሪያ መልዕክት ከመድረሱም በላይ የመንግሥት ሚዲያው ደግሞ ዜናውን አስተካክሎ ‹‹ወይዘሮ ብርቱካን ልጃቸው የሞተው በድንገተኛ በሽታ እንጂ፤ ተርቦ አይደለም›› ተብሎ ተዘገበ፡፡ ወይዘሮ ብርቱካን በሚዲያዎች ጫና መራቧን እንኳን አስተባበለች፡፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ታኅሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙስና ተወንጅለው ከ12 ዓመት እስር በኋላ ሲወጡ ‹‹እስሩ ጥሩ ነበር፡፡ ሰብአዊ መብቴ ተጠብቆልኛል፡፡ ኢሕአዴጎች እንደ ታሳሪ ሳይሆን እንደ ጓድ ያዩኝ ነበር›› ብለው በኢቴቪ በግዳጅ ተናገሩ፡፡ ሌላ ጊዜ በናሁ ቲቪ እንደተገረፉ፤ ተገደው ፓርላማ ድረስ እንደተናገሩ ይፋ አወጡ፡፡ ግለሰቦች እንኳ ተገደው መንግሥት የሚፈልገውን ብቻ በሚዲያው እንዲናገሩ ሆነዋል፡፡ በማዕከላዊ የነበሩ ታሳሪዎች በውሸት ያልሆኑትን ሆነው ለሚዲያ ከተናገሩ ከእስር ለመለቀቅ እንደ አንድ መደራደሪያ ነጥብ ሆኖም ነበር፡፡

ሚዲያው የውሸት ፋብሪካ መሆኑ በትውልዶች እንዲሁም በመንግሥታት መካከል ያለመተማመን ግርዶሽ ጥሎ አልፏል። በዚህም የመንግሥት ሚዲያዎች የዕለቱን ሰዓት እና ቀን ሲያስተዋውቁ ሳይቀር እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ተደራሲው ጥርጣሬ ውስጥ ገባ። በኃይለ ሥላሴ አምላክ እየተባለ በመንግሥት ይማልና ይታመን እንዳልነበር፤ ዛሬ መንግሥት ወተት ነጭ ቀለም አለው ቢል እንኳን የመታመን እድሉ ዝግ ሆኖበታል። ቀደም ባለው ጊዜ ባለሥልጣን ስለሚታመን አጀብ አልነበረውም። ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ እስከ ደርግ ባለሥልጣናት የኢሕአዴግ ጊዜውን ያህል በፍርሃት ታጅበው ዓይንቀሳቀሱም ነበር። የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ከኢትዮጵያ ነባራዊ እሴት ስለወጡ አይታመኑም። ስለማይታመኑም በጠባቂ ብዛት የራሳቸውን ደሴት ፈጥረው ከሚመሩት ማኅበረሰብ ጋር በአካልም ሆነ በመንፈስ ሊቀርቡ አልቻሉም።

በኢትዮጵያ ሕግ ላይ አንድ ተደጋግሞ የሚነገር የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ሥርዓተ ሕግ አለ። በወቅቱ ሰው የገደለ ቅጣቱ መግደል የሚል ሕግ ይስተጋባ ነበር። የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ልጅ ሰው ገደለ። ንጉሡ ከልጅነቱ ይልቅ ለሕጉ እና ሥርዓቱ ወግነው ልጃቸው እንዲገደል አስወሰኑ። ሕግ እና ሥርዓት፤ እሴት እና ወግ ራስን ገሎም ቢሆን የሚከበርባት ሀገር ነበረች።

ሁለት ደመኞች እጅ እና እጃቸው ተቆራኝቶ ያለጠባቂ ፍርድ ቤት ድረስ ቀኑን ሙሉ ተጉዘው አቤቱታቸውን ያቀርባሉ። ለሕግ ታምነው መንገድ ላይ አይጣሉም ወይም ከሕግ ለመሰወር አይሸሹም። በሕግ አምላክ እና በሰንደቅ ዓላማው ሲባል የቀደመው ሰው በቅዱስ ገብርኤል ወይም በአላህ የተባለ ይመስል በቀላሉ ይማረካል። ለሕግ እና ለሰንደቅ ክብር ሲል ይንበረከካል። ይህን ሁሉ ሥርዓት ግን ሚዲው ዋሾ ሆኖ፤ ሥርዓተ መንግሥቱም ጸረ-እሴት ሆኖ በመተከሉ ቀልጧል።

ሚዲያው የማኅበረሰቡ ባህላዊ ወግ እና ሞራል፣ እሴት እና ሕግ ሁሉ እንዲወድም አድርጓል። ይህም የኢትዮጵያዊነትን ሕሊናዊ እሳቤ ገድሎ አካላዊ መሰነጣጠቅ ሁሉ እያደረሰ ነው።

በመንግሥት ሚዲያዎች ስለታሪክ ማውራት ተወግዞ፣ የእነ ቴዎድሮስ ካሳሁን ዓይነት ሙዚቃዎች እንዳይተላለፉ ተከልክለው ቆይተዋል። የአማራ ግዛተ አሐድ (ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ እና ጎንደር) ፉከራ እና ሽለላን ያካተቱ ሙዚቃዎች እንዳይተላለፉ በትምክህት አራማጅነት ተፈረጁ። እንደ ሕወሓት ኢሕአዴግ ባሕርይ ብሔረሰባዊ ሚዲያዎች የተፈለፈሉ ሲሆን፤ ሁሉም ግን ድምጻቸው እንጂ የሚለየው ይዘታቸው ተመሳሳይ ነው።

የመንግሥት ሚዲዎች የኢሕአዴግ ማዘዣ ጣቢያ በመሆናቸው፤ እነዚህን የሚቃረን የትግል ሚዲያዎች ብቅ አሉ። ጋዜጠኝነትም ሙያ ሳይሆን የነጻ አውጭ የጫካ ታጋይ መሰለ። ከምርጫ 2007 በኋላ ኢሕአዴግ የፓርላማ ወንበሩንም መቶ ለመቶ ዘግቶ ሚዲያውን፣ ፍትሕ እና ጸጥታውን ሙሉ በሙሉ አፈነው። በአፈናው መሃል ማኅበራዊ ሚዲያው አዛዥ የለሽ ማኅበረሰባዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ መጣ። የሕወሓትን ገመና ያለ ይሉኝታ እያወጣ ደፋው። የመንግሥት ሚዲያ ከአጀንዳ ሰጭነት ወደ ተቀባይነት እና ተከላካይነት ወረደ።

የፖለቲካ ትርክቱን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ማኅበራዊ ሚዲያ ሲቆጣጠረው የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በ2008 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባኤ ላይ ማኅበራዊ ሚዲያ የሀገሬ ፈተና ሆኗል፣ ዓለም ያድነኝ ሲሉ ተማጸኑ። ተማጽኖአቸው ግን ሰሚ አላገኘም። ጦማርያንን በማሰር እና የጡመራ ገጾችን በመዝጋት ከችግሩ ለመውጣት ቢሞከርም አልተቻለም። ማኅበራዊ ሚዲያው እንደ ዓረቡ የ2003 ዓ.ም. አብዮት

ሁሉ ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም. ባደረገው ትግል የኢሕአዴግን ቅርጽ ቀይሯል፡፡ ከ2010 ዓ.ም. በኋላም የአብይ አህመድን አስተዳደር በትክክል በማሳየት ለሌላ ትግል ጋብዟል፡፡ የመንግሥት ሚዲያም ከገዥው ሥር ከመንበርከክ ሳይወጣ የአሸናፊው ሁሉ አጃቢ ሆኖ ዘልቋል፡፡

አብይ አህመድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲመጡ ልክ ደርግም ሆነ ሕወሓት እንዳደረጉት፤ የመንግሥት ሚዲያ ሕወሓትን ኮንኖ በማዕከላዊ እሥር ቤት የደረሰውን የሰብዓዊ መብት ቀውስ እና በዓባይ ግድብ ላይ የተመዘበረው ሀብት በዘጋቢ ፊልም እንዲታይ ተደርጓል፡፡ በማኅበራዊ ሚዲያው ከሕወሓት አገዛዝ ነጻ የወጣው የመንግሥት ሚዲያው አሮጌውን አገዛዝ አርፍዶ እየተቸ፣ ለአዲሱ አገዛዝ የሎሌነትን ባሕርይውን ቀጥሎበታል፡፡ በመንግሥት ሚዲያ[137] ስንፍና እና አዳሪነት ምክንያት ማኅበራዊ ሚዲያውም

[137]ማኅበራዊ ሚዲያ እንደ አምስተኛ መንግሥት ይታያል፡፡ በእርካሽ ክፍያ፣ የትም ሆኖ ያለ ማዕከላዊ ማዘዣ ጣቢያ እንደየግለሰቡ ባሕርይ ሚዲያውን መጠቀም ያስችላል፡፡ በባለሀብቶች እና በገዥ መንግሥታት ብቻ ተይዞ የቆየውን ከላይ ወደ ታች የሚፈስ የመረጃ ፍሰት አቅጣጫ አስቀይሮታል፡፡ በአሳታፊነቱ እና በአካታች የሚዲያ ባሕርይው ምክንያት በ2019 ስልሳ በመቶው የዓለም ሕዝብ የመረጃ ምንጩ ማኅበራዊ ሚዲያ ሆኗል፡፡

ማኅበራዊ ሚዲያ ሁሉንም አባላተ ስሜቶች ደምሮ ስለሚያሠራ እንደ ስድስተኛ የስሜት ህዋስ ይቆጠራል፡፡ ማንበብ እና መጻፍን፣ መስማት እና ማየትን፣ በልቦና መረጃ መዳሰስን ሁሉ አዝሎ ይዟል፡፡ የቀደመው የመንግሥት ሚዲያ ትውልድን የቀረጸው ለአገዛዙ በሚመች ሁኔታ ነበር፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያው ደግሞ በተቃራኒው ነጻ የመውጫ ሜዳ ሆኖ መጥቷል፡፡ ይህ በመሆኑም ሁሉ ጋዜጠኛ፣ ሁሉ ታጋይ፣ ሁሉ ሀያሲ፣ ሁሉ የፖለቲካ ተንታኝ መስሎ እንዲታይ አድርጓል፡፡ በዚህ መሃል መጠላለፍ እና ማኅበረሰባዊ እሴት አልባነት ይንጸባረቃል፡፡ ይህ የሚመነጨው ግን ከማኅበራዊ ሚዲያው ባሕርይ ሳይሆን ፖለቲካው ማኅበረሰቡን ከቀረጸበት መንገድ እና ማኅበረሰቡ ለፖለቲካው ባለው አተያይ የሚወሰን ነው፡፡ የሀገሪቱ ፖለቲካ ፈር ከያዘ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀሙም አብሮ ያድጋል፡፡ በማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ ያለው ጠርዝ ረገጥ አካሄድ ምንጩ ማኅበረሰቡን ከሚመራው አካል ነው፡፡ ማኅበረሰብ በጠቢባን ከተመራ ማኅበራዊ ሚዲያውም የጠቢባን መንደር ይሆናል፡፡ **እፍ ያነዳል፤ እፍ ያለማል፤** ምንም ነገር እንደአጠቃቀሙ ይወሰናል፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያ እንደ አፍሪካ ላሉ አውነት እና አውቀት ከገዥው መንግሥት በሚመነጭባቸው ሀገራት የጭቁን ወገነ ድምጽ ነው፡፡ እያንዳንዱ ዘመን የራሱ ቀለም ስለሚኖረው፣ ይሄኛው ዘመን የበይነ መረብ ሆኗል፡፡ በበይነ መረብ ዘመን ላይ ሆኖ ከማኅበራዊ ሚዲያ ማምለጥ አይቻልም፡፡ እንደ ቻይና ያሉ ሀገራት ከምዕራባውያን ጋር ባላቸው የቴክኖሎጂ ፍጥጫ ምክንያት ማኅበራዊ ሚዲያን ለማገድ ቢሞክሩም፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡

የሐሳብ መሪ ሆኖ ገኖ ወጥቷል፡፡ ሚዲያው ነጻ ባልወጣበት ሀገር ውስጥ ሌላው ተቋም ነጻ ሊሆን አይችልም፡፡ ሚዲያ የተቋማት ሁሉ ስዕል ነውና፡፡

ነጻ ተቋም ሳይኖር ግለሰቦች (መሪዎች) ጊዜያዊ ተቋም ይሆናሉ፡፡ እነዚህ መሪዎች ሲጠፉ ሕግ እና ሥርዓት አብሮ ይወድማል፡፡ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለ17 ዓመት ተቋም ነበሩ፡፡ ወደ ዚምባብዌ ሲኮበልሉ የደርግ ሥሪት ሁሉ ፈረሰ፡፡ የደርግ ኢትዮጵያዊነት ወንጀል መስሎ በ1987 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት ተረቀቀበት፡፡ በ2004 ዓ.ም. አቶ መለስ ሲሞቱ የሰሜን ጫፍ የፖለቲካ የበላይነት ላላ፡፡ ኢሕአዴግ አንድ ድርጅት ሆኖ እንኳን በተቋማዊ ባህሉ ስሥነት ምክንያት ከአቶ መለስ እስከ ዶክተር አብይ የተለያየ ቅርጽ አለው፡፡ ዶክተር አብይም ራሳቸውን እንደለውጥ መሪ እና ለውጥ ተቋም አቆሙ እንጂ ነጻ እና ገለልተኛ ተቋም አልፈጠሩም፡፡ ዶክተር አብይ ሲወርዱ፣ አሻራቸውን ሁሉ ተኪያቸው ያጠፋል፡፡ ግለሰቦች ተቋም በሆኑበት ሀገር ውስጥ በትናንት ላይ ዛሬ ተደምሮ ነገ አይሠራም፡፡ ሀገር በመፍረስ እና በመታደስ አዙሪት ውስጥ ሆና እንቧለሌ እየተሽከረከረች መኖሯ ልማዷ ይሆናል፡፡ እነሊቢያ ከጋዳፊ ጋር የወደቁት፤ እነ ሱዳን ከአልበሽር መወገድ ጋር አብረው የዘመሙት፣ እነሶማሊያ ከዚያድ ባሬ መጥፋት ጋር አብረው መንግሥታቸውን ያጠፉት፣ እነዮጎዝላቪያ ከማርሻል ቲቶ ጋር አብረው ከምድረ ገጽ የጠፉት… መሪዎቻቸው ፍጹም አምባገነን ሆነው ተቋም ስለነበሩ ነው፡፡

አምባገነን መሪዎች ሥልጣን ሲለቁ ሀገር ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ የከፋ አወዳደቅ ትወድቃለች፡፡ የሀገር ህልውና በግለሰቦች መቆም የለበትም፡፡ የአፍሪካ ሀገራት በግለሰቦች (በመሪዎች) የቆመ ህልውና ስላላቸው ሥልጣኔያቸውን እና በጎ ነገራቸውን ማንበር አልቻሉም፡፡ አማራጭ ሐሳብ ያላቸው ልሂቃንም ነጻ ተቋማት

ስለሌሉ አሻራቸውን ማኖሪያ መንበር አላገኙም፡፡ ልሂቃኑም በተስፋ መቁረጥ አድርባይ እና ከራሳቸው መሠረታዊ ፍላጎት ውጭ የረባ ነገር የማያስቡ ሆኑ፡፡

የብዙ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ትግል ኮንዶሚኒየም(መጠለያ) እና የሚያስተምሩትን ትምህርት በመጨመር ትርፍ ክፍያ ማሳደድ እንጂ የተስተካከለ መንግሥታዊ እና ማኅበረሰባዊ ውቅር እንዲመጣ አይደለም፡፡ የተማረው ነጻ የሚወጣው ብዙ ባልተማረው እና በወጣቱ ሕይወት በተከፈለበት ትግል ሆኗል፡፡ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ከገዛዱ ከባቢያዊ ሁኔታ ጋር የሚስማማ ርዕይ ስሌላቸው ማኅበረሰብን የሚቀይር ቁምነገር ሲሠሩ አይታይም፡፡

5.18 ምሁሩ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ

የየካቲ የ1966ቱ አብዮት መነሻው የተማረው ወገን ነው፡፡ የተማረው ርዕዮተ ዓለምን እንደ ሃይማኖት አምልኮ ሥር-ነቀላዊ ለውጥን ሽቶ ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በባሕርይው ከሳይንስ ጋር ተፋትቶ ከሴራ ጋር የተጋባ ነው፡፡ ምክንያታዊነት፣ ወጥ ዓላማ እና ጥናታዊ ምርምር… የሚሉ ጭብጦች ከፖለቲካው ንቅናቄ መንፈስ ውስጥ የሉም፡፡ ምሁርነት ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ጋር አብሮ መሻገር አይችልም፡፡ በ1966 የሆነውም ይሄው ነው፡፡ የለውጥ ሐሳቡ በተማሪዎች ተወለደ፡፡ የለውጥ ፍሬው ግን ብዙም ባልተማሩ በደርግ ወታደሮች ተለቀመ፡፡ የተማረው አገልግሎቱ ከንድፈ ሐሳባዊ ሂደት ሳያመልጥ ቀርቶ ደርግ በጠመንጃ መንግሥትነት መሠረተ፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ‹‹ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው›› እያሉ በእሳቸው ላይ የሚያሴሩትን ቀድመው ረሸኗቸው፡፡ በኮሎኔል መንግሥቱ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የምክንያት ጉልበት እና ሳይንሳዊ ጥበብ የለም፡፡

ያለው ሴራ ነው። ሴራ ደግሞ በየትኛውም ዋጋ ውጤት ግኹ ላይ ብቻ ያተኩራል። ምሁራን በሂደቱ ሲሻኮቱ፤ ደርግ ከውጤቱ ዛፍ ላይ ወጥቶ ከዛፉ የሚያወርዱትን ባለወንጭፎች ከላይ ሆኖ ያወርዳል።

የደርግ ተፎካካሪዎች ኢሕአፓ እና መኢሶን የምሁራን ስብስቦች ነበሩ። ምሁርነታቸው ግን ደርግን ለመጣል የሚያስችል ጥበብ አላበረከተላቸውም። ምሁራን መሬት ላይ ያለውን ሀቅ ቶሎ የመረዳት፣ እንደ ሁኔታው ተቀያያሪ የመሆን እና የግብ መንገድን የመለየት ችግር ተስተውሎባቸዋል። እንዲያውም አንዳርጋቸው ጽጌ ወያኔን ለስኬት ያበቃው ከምሁራን ስብስብ የራቀ[138] ሆኖ በመመሥረቱ ነው ይላሉ። ይህ መሆኑ የአንድ ጉዳይ አመንዣኪዎች ሳይሆኑ ከዓለም ነበራዊ ሁኔታ ጋር እንዲቀያየሩ አስችሏቸዋል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብልግናን በክህሎትነት ይጠይቃል። ብልግና ደግሞ በትምህርት እና በምክንያት ለተሞረደ ምሁራዊ ጭንቅላት አይታዘዝም።

በኢሕአዴግ ዘመን ዝቅተኝነት በወለደው ስሜት በሚመስል ሁኔታ ምሁራን ትምክህተኛ ናቸው ተብለው በወያኔ ተፈረጁ። ምሁራዊ ትምክህትን ለማስተንፈስ ሲባል በ1985 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 42 ምሁራን ከማስተማር ታቅበው ተባረሩ። አምባገነን መንግሥታት ሐሳብ ስለማይወዱ የሐሳብ ባለቤቶችን ብዙ አይፈልጉም። እናም ኢሕአዴግ በተለይ ከ1983 እስከ 1997 ዓ.ም. የጤና ዘርፉን በምህንድስና፣ ግንባታውን በቲያትር፣ ፖለቲካውን አንደኛ ደረጃ ትምህርት አጠናቀው ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በዲግሪ ባስመረቃቸው ካድሬዎች ለመምራት ተገዷል። ምርጫ 97ን ተከትሎ ኢሕአዴግ የመሀይማን ስብስብ ነው የሚል የምርጫ ማጉያ ሆኖ በቅንጅት ወጣ። ሕዝቡም ማዕረግ ማምለክን

[138]አንዳርጋቸው ጽጌ፣(1997)፤ ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ

ተያያዘው። ከምርጫ 97 በኋላ ካድሬው ሁሉ እየተማረ ወይም ዲግሪ በደላላ እየሸመተ ሕዝቡ ያልተማረ አይገዛንም የሚለውን አቋም አሻረ።

በዚህ መሃል ግን አንድ ነገር እውነት ነው። ምሁሩ በኢሕአዴግ የፖለቲካ ገበያ ውስጥ ሻጭም፣ ገዥም መሆን አልቻለም። ደሴት ሠርቶ ምርምሩ ወደ ላይ ሂዶ ለፖሊሲም ሆነ፣ ወደታች ለማኅበረሰብ ለውጥ አላገዘም። ከፖለቲካው ምሁር ጠልነት ባሻገር፣ ምሁራን ራሳቸው ጠያቂ አለመሆናቸው የሀገሪቱ እውቀት ከካድሬው ወደ ምሁሩ እንዲፈስ ሆኗል። ካድሬው በብቸኝነት የሐሳብም፣ የጥናትም፣ የገንዘብም ሆነ የፖለቲካ የሥልጣን ምንጭ ራሱን አድርጎ ሹሟል። እውነት እና ውሸት የሚጣራው በተማረው ጥናት ሳይሆን፣ በካድሬው የሴራ ፖለቲካ ትንተና ነው።

ለአብነት ኢትዮጵያ 2011 ዓ.ም. ሀገራዊ የትምህርት ፍኖተ ካርታ በምሁራን ተጠንቶ ለገቢራዊነቱ ሲጠበቅ በፖለቲካ ልሂቃን ተሸሯል። ዋና ዓላማው ሀገራዊ ርዕይን ለመሰነቅ የትምህርት ሥርዓቱ ከ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ጀምሮ ፈተናው ሀገር አቀፍ እንዲሆን፣ ስለኢትዮጵያ እና ጎረቤት ሀገራት ማኅበረ ፖለቲካ ጉዳይ ማጥናትን ያስቀደመ ነበር። ነገር ግን ፍኖተ ካርታው ክልልነትን አሳስቶ ብሔራዊ ሀገራዊነትን ያጎላል፣ አሐዳዊነትንም ጠሪ ነው በሚል ቅቡልነት ተነስቶታል። አማርኛ ቋንቋ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሰጠት የለበትም፣ የአሐዳውያን ቋንቋ ነው የሚል ወቀሳም ተነስቶበታል። ትምህርት የፖለቲካ ልሂቃን የዓለማ ማስፈጸሚያ እንጂ ሳይንስነቱ በመዘንጋቱ የምሁራን ሚናም ላልቷል።

በ1985 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር[139] የገጠመው ፈተናም ትምህርትን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ተደርጎ በፖለቲካ ልሂቃኑ መቀንቀኑ ነበር። ልክ እንደ ሕገ መንግሥቱ ትምህርት ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እንዲል ተደረገ። በክልሎች የበቀል ትምህርት ተሰጠ። በኦሮሚያ ባሉ ትምህርት ቤቶች የበቀል መዝሙሮች የሕፃናት መቅረጫ ሆኑ።

ዋን ነፍጠኛኝ ጎዬ ያደዶን ጉበዳ
ወረ ኩፌ ሃፌ ሰንቶኮ ያደዳ
ኦቶ ሴና ቀብኑ ሴና ኬኛ ደብኔ
ኦካ ኢልሞ ሆላ ከራቲ ቀለምኔ

[139]የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዝዳንት የነበሩት ፕሮፌሰር ታየ ወልደ ሰማያት በ1980ዎቹ የትምህርት ቀረጻው የብሔር ፖለቲካው መሣሪያ ሆኗል ብለው ተቃውመው ነበር። ትምህርት በብሔር ከሆነ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል ሂዶ ለመሥራት አስቸጋሪ ይሆናል። በአንድ ሀገር ውስጥ ሆነው ፍጹም የማይግባቡ እና የማይደራረሱ ክልሎች ይፈጠራሉ ሲሉ ቀድመው ተናግረው ነበር። በ1982 ዓ.ም. ፕሮፌሰር ታየ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ሥልጣን ሊለቁ ይገባል ብለው ፊት ለፊት የተጋፈጡ ጀግና ምሁርም ናቸው።

ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች በፖለቲካል ሳይንስ የዳበረ እውቀት ያካበቱት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ታየ ትናንት ሆነው ዛሬን ቢመለከቱም ሰሚ አላገኙም። ይባስ ብሎም ከ1988 እስከ 1994 ዓ.ም. ድረስ ወደ እስር ተወርውረው አሳቢ ጭንቅላታቸው ከጥናት ተለይቶ ቆየ። በርካቶች ሥርዓተ ትምህርቱን የተቃወሙት ወደ ዘብጥያ ወርደዋል። የኢትዮጵያ ጡረተኛ መምህራን ማኅበር ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ ከበደ ደስታ በእስር ቤት ተሰቃይተው አርፈዋል። ፕሮፌሰር ታየ በዓለም የወዝ-አደሮች ድርጅት(ILO) እና በሰባዊ መብት ተሟጋቾች አማካኝነት ከእስር በ1994 ዓ.ም. ተለቀዋል። የእነ ፕሮፌሰር ታየን ሙግት ተከትሎ ምሁራን በሙሉ በትምክህት ተፈርጀው ትምክህታዊ ምሁራን የሚል የግምገማ መስፈርት ወጥቷል። እነ ፕሮፌሰር አሥራት ደርግን የኮሚኒዝም ትምህርት እንዳይሰጥ ሲሞግቱ፣ ኢሕአዴግም ትምህርትን እንደ ሕገ መንግሥቱ በብሔር ጥላቻ ተከፋፍሎ እንዳይሰጥ መክረው ነበር። የመከሩት ሁሉ ግን ከየሥራ ዘርፋቸው ተባረዋል።

ልክ ጣሊያን የኢትዮጵያ ምሁራንን ቀድማ እንደገደለችው ሁሉ፤ ኢሕአዴግም ለእውነት የኮበለሉ ምሁራንን ከማጥፋት አልቦዘነም። በዚህም ብዙዎቹ የዛሬ ምሁራን አድርባይ፣ ፈሪ እና አስመሳይ ሆነዋል። ከፖሊሲ እና ከሀገር ስትራቴጂ ማሰላሰል ወጥተው በወሲብ እና በንዋይ ጥም ወድቀዋል። ለፖለቲካም ጀርባቸውን ሰጥተዋል። ፖለቲካውም በምክንያት ሳይሆን በስሜት በሚዋኘው ሩቅ ዓላማ በሌለው ልሂቅ ቁጥጥር ሥር ወድቋል። የሀገሪቱ ተረክ እና ወግም ደረቅ እና አብሮነትን የሚገድል ሆኗል።

ማል ጀዴ ቃብሳየ ሂሪያን ኬኛሌ

ዮ ያደቻን ኦሌ ሚሺጊ ጎተዴ

ከናን ቢራ ኢያዱ ኤዮ ቲያ ያዳ

ከን ቢራ ኢያዱ ሰበ ቲያ ያዳ

ትርጉም፡

ነፍጠኛ የሠራውን ማሰብ ያንገበግባል

ታሪክ ሲኖረን እንደሌለን

እናት ሲኖረን እንደሌለን

እንደ በግ ግልገል በየመንገዱ ታርደን

ያንን ያሰብንለት ምሽግ ያዝን

ሌላ ማሰብ አንፈልግም ከእናታችን በቀር(ከኦሮሚያ)...እያለ ይቀጥላል።

ይህ የኦሮምኛ ተናጋሪ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸው የሚዘምሩት ሙዚቃ/መዝሙር ነው። መዝሙሩ ከኦሮሚያ እናቴ ውጭ ሌላ ማሰብ አልፈልግም፤ ኢትዮጵያ የነፍጠኞች ናት የሚል አውድ አለው። ይህ የትምህርት መዝሙር በቀጥታ የኦነግ የፖለቲካዊ እሳቤ ነው። በትግራይ ያለው የትምህርት አሠጣጥም ከኦሮሚያው ጋር የተቀራረበ ነው።

ከ1985 ዓ.ም. በኋላ የተማሩ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር እንኳ ለማወቅ እድል ተነፍጓቸዋል። የኦሮሚያ ክልል መዝሙር ውስጥ "ጡሪ ወጋ ዲባ ዲጋን ሲራ ኒቅኔ (የመቶ ዓመት እድፍሽን በደማችን አጠብንሽ)" የሚል ስንኝ ይገኛል።[140]

[140] Oromiyaa/2/ haadha seenaa guddaa
Hadhuura oromootaa galma sirna gadaa
Dachee heeraa fi seeraa haadha caffee odaa
Badhaatuu gabbattuu magarsituu hundaa

የመዝሙሩ ጭብጥ ከምኒሊክ ቅኝ ግዛት ተላቀቅን፣ እምየ ኦሮሚያ ሀገሬ የሚል ጨመቅ ቋጥሯል:: የዚህ መዝሙር ይዘት ወደ ባህል እንዲያድግ በትምህርት መንገድ ተሰናድቷል::

ትምህርት የፖለቲከኞች መርሆ ሆኗል:: ፖለቲካችን ደግሞ ከምግባር የተፋታ የኒኮሎ ማካቬሊ ሴራ እና በቀል በመሆኑ፤ ትምህርት በቀል ሆኖ እየተሠጠ ነው:: በዚህ ሂደት ሳይንሳዊ ምሁራን ፋይዳ ቢስ ይሆናሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ ምሁሩ ለሀገር በቀል እውቀት የሰጠው ትኩረት ስስ በመሆኑ እና ካድሬው ደግሞ እውነትን ራሱ በሚመቸው መንገድ ፈጥሮ ማኅበረሰቡን ለመሥራት መሞከሩ በሀገሪቱ ላይ የእሴት ግጭት ፈጥሯል:: የማኅበረሰቡ እሳቤ እና የሚመራበት

Xurii bara 100 dhiigaan sirraa dhiqinee
Wareegama qaaliin alabaa kee ol qabne
Gammanne gammadii bokkuu deebifannee
Nagaafi dimookiraasii tabaroo namummaa
Misooma amansiisaa guddina atattamaa
Uummattoota waliin jaalalaa fi tokkummaa
Wabii jireenyaatiif goone kaayyoo cimaa
Hirree gamteeffannee kaanenu abdadhuu
Oromiyaa lalisii dagaagii jiraadhuu !!!

የኦሮሚያ ሕዝብ መዝሙር ትርጉም

ኦሮሚያ/2/ የትልቅ ታሪክ እናት
የኦሮሞዎች እምብርት የገዳ ሥርዓት አዳራሽ
የሕግና ሥርዓት መሬት የጨፌ ኦዳ እናት
የብልጽግና የልምላሜ ሁሉን አብቃይ እናት
የመቶ ዓመት እድፍ በደማችን አጠብንልሽ
በብዙ እልፍ አልቂት ባንዲራሽን ከፍ አደረግን
ደስ ብሎናል ደስ ይበልሽ ስልጣንን መልሰን አገኘን
ሰላምና ዴሞክራሲ የሰብአዊነት መብት
አስተማማኝ ልማት ዘላቂ ልማት
ከሕዝቦች ጋር ሰላምና ፍቅር
ለመኖር ዋስትና ትልቅ ዓላማ አድርገን
ኃይላችንን አሰባስበን ተነስተናል ተማመኚብን
ኦሮምያ አብቢ ለምልሚና ኑሪ !!!

ፖለቲካ ተቃርኖ ያጠቃው ነው፡፡ በፖለቲከኛው እና በማኅበረሰቡ እሴት መካከል ያለው ተቃርኖ ሀገሪቱን በቅኝ ግዛት የምትመራ አስመስሏታል፡፡ የሀገሪቱ የተለያዩ የእሳቤ አድማሶች ተደጋጋፊዎች ሳይሆኑ በተቃርኖ የሚጠፋፉ ናቸው፡፡ የሀገሪቱ ሁኔታም የዜሮ ድምር እንቆቅልሽ የተጣባው ሆኗል፡፡ ትምህርቱ እና የማኅበረሰቡ ኑሮ፣ ፖለቲካው እና የሀገሪቱ እሴት ተዛምዶ የላቸውም፡፡

የመማርን ማኅበራዊ እና ሙያዊ የሥራ እርከን የሚከተለው ሐሳብ በደንብ የሚገልጸው ይመስለኛል፡፡ አንደኛ ደረጃ የሚወጡት በጣም ጎበዝ እና ባለተሰጥኦ ተማሪዎች ሀኪም እና መሃንዲስ ይሆናሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ብርቱ ተማሪዎች ደግሞ ሕግ እና ቢዝነስ አጥንተው አንደኛ ለሚወጡ ተማሪዎች አለቃ ይሆናሉ፡፡ ሦስተኛ እርከን ላይ የሚወጡት ሰነፍ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ ወደ ፖለቲካ ይገቡና አንደኛ እና ሁለተኛ የወጡትን ይመሯቸዋል፡፡ ጭራሽ ከትምህርት የወደቁት ወታደር ይሆኑና ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡትን ሁሉ በመዳፋቸው ሥር አስገብተው ይገዛሉ፡፡ ምንም ያልተማሩት ደግሞ ነብይ ወይም ጠንቋይ ይሆኑ እና የሁሉም ወገኞች አዳኝ ሆነው ይመጣሉ፡፡ የተማሩት ሁሉ ያልተማሩትን በሃይማኖት ነብይ ነን ወይም በልማድ ጠንቋይ ነን ብለው ስለነገ የሚተነብዩትን ይከተላሉ፡፡ ብዙ መማር የበለጠ የእዝ ሰንሰለቱን ያበዛል[141]፡፡ የፖለቲካ ማኅበራዊ ሥሪቱ ባልተስተካከለበት ሀገር ውስጥ ሙያ ክብር ያጣል፡፡ ብዙ የተማሩት ታክቲክ እና ስትራቴጂ ነድፈው አሸናፊ ሐሳብ ይዘው ቢመጡም እንኳን፣ ሐሳባቸውን ገቢራዊ ለማደርግ መንግሥት መሆን አይችሉም፡፡

[141] በ2010 ዓ.ም. የአፍሪካን የትምህርት እና የማኅበራዊ እርከን በተመለከተ የዚምባብዌው ፕሬዜዳንት ሮበርት ሙጋቤ ተናገሩት ተብሎ በማኅበራዊ ሚዲያው ሁሉ ተለቆ የበይነ መረቦች ሁነኛ መነጋገሪያ የነበረ ሐሳብ ነው፡፡ ሐሳቡን በትክክል ሙጋቤ ላይናገሩት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሙጋቤ ለአፍሪካውያን እንደ ኢትዮጵያዊው አባ ገብረሐና የተረት መፍጠሪያ በመሆናቸው በእሳቸው ስም ብዙ አባባሎች እና ኃይለቃሎች ይነገራሉ፡፡ ማንም ይናገረው ማን ሐሳቡ ግን ገኸ ነው፡፡

በአፍሪካ የመጨረሻ የሥልጣን ወሳኙ አካል ሐሳብ ያለው ምሁሩ ሳይሆን ነፍጥ ያለው ወታደሩ ነው::

ይህ መሆኑ ወታደሩን ገዥው መንግሥት አገልጋይ አድርጎ፣ ሐሳብ ያላቸውን ልሂቃን ሁሉ ከመንግሥት በተቃራኒ ካሰቡ እንዲኮረኮሙ አድርጓል:: *የኢትዮጵያ ብሎም የአፍሪካ ዋነኛ ችግርም እውቀት ከገዥው እንጂ ከምሁሩ አለመፍለቁ ነው::* በምርጫ 97 ቅንጅት አዲስ አበባን እና ብዙ ከተሞችን ማሸነፍ ቢችልም፣ ወደ መንግሥትነት እንዳይመጣ በየክልሉ የምርጫ ኮረጆው በጸጥታ ኃይሉ ተገለበጠበት:: ቅንጅት እንኳን ሀገር ሊመራ የቅንጅት አባል ነኝ ማለትም ከሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ወንጀል ተደርጎ በጸጥታ ኃይሉ ዱላ ጸና:: በሐሳብ ርቀት፣ አማራጭ መንገድ ይዞ በመምጣት፣ በፖለሲ እና በስትራቴጂ… ቅንጅት ከኢሕአዴግ የተሻለ ነበር:: ነገር ግን መንግሥትነት የሚገኘው በምርጫ ኮረጆ በልጦ በመገኘት እና የጠራ ሐሳብ በመያዝ ሳይሆን በጉልበት እና በብልግና ሆኖ በመመንዘሩ ቅንጅት ታስሮ ኢሕአዴግ መንግሥት ሆነ::

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተምኔት (ሐሳብ) እና ሕልም አልባ[142]ሆኖ መተከሉ የፖለቲካ ትንታኔውን በነውር፣ በጭካኔ፣ በመከዳዳት፣ በመወነጃጀል፣ በጥርጣሬ፣ በሴራ… የታጀበ አድርጎታል::

---

[142]አንዳርጋቸው ጽጌ ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ ብለው ጥር 1997 ዓ.ም. ባሳተሙት መጽሐፍ እንዳብራሩት፣ የኤርትራ ሀገር መሆንን ያህል ግዙፍ ውሳኔ በሕወሓት ዘንድ የተወሰነው መጠጥ ቤት ላይ ነበር። ኤርትራ ሀገር ስትሆን የምሁራን ጥናት እና ምርምር ታሳቢ አልተደረገም። ሕወሓት እና ሻዕቢያ መቀሌ ከሚገኝ ቡና ቤት ላይ ሆነው ተስማምተው የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት መሆኑን በጋራ አወጁ። የሕወሓት ዓላማ ሻዕቢያን ተወዳጅቶ ከኢሕአፓ ማራቅ ነበር። ሕወሓት የሻዕቢያ ፍጡር ሆኖ፣ ከኢትዮጵያ ጥቅም ተቃርኖ አደገ። ኢሕአፓን ሕወሓት ከሻዕቢያ አናጥሎ መታ። የባሕር በርም ሕወሓት አያስፈልገኝም ብሎ ለሻዕቢያ ሸለመ። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ነገን እና ሀገርን የሚያሻግር ጥናታዊ ርዕይ የለም። የመንግሥት ፖሊሲዎች እና ግዙፍ ግዙፍ ውሳኔዎች የሚወጡት ከምርምር ማዕከላት ሳይሆን፣ ከመሸታ ቤቶች እና ከሌሎች ኢ-መደበኛ አውዶች ነው።

ሕዝቡንም ለፖለቲካ ትኙ አድርጎ ‹‹ፖለቲካ እና ኤሌክትሪክን በሩቁ ነው›› የሚል የስንፍና ተረት እንዲያላምጥ አስገድዶታል። መማርም የባርነት መንገድ መስሏል። የተማረው በሀገሪቱ ላይ ያለው ሚናም ዝቅተኛ ነው። ነጻ እና አካታች ሥርዓታዊ መዋቅር ሀገሪቱ እስካላበጀች ድረስ በተማረው እና ባልተማረው መካከል ያለው መደባዊ የሚና ልዩነት በተግባር አይታይም። የምሁሩ ሚና አገዛዙ በትግል ካከተመ በኋላ በምልሰት አገዛዙ እንዴት እንደወደቀ ትንተና ከመሥራት ያለፈ ዛሬን አስተካክሎ ነገን መሥራት የሚያስችል ሐሳብ ማፍለቅ ላይ አልተሰማራም። ማፍለቅ ቢችልም አካታች እና ፈቃጅ ተቋማት የሉም።

ከ1966ቱ ሥር-ነቀላዊ አብዮት በኋላ የመጡ ጽንሰ ሐሳቦች በሙሉ ሳይንሳዊ ትንታኔ የራቃቸው የሴረኛ ፖለቲከኞች ፍጆታ ብቻ ሆነዋል። በደርግ ጊዜ የነበረው ኅብረተሰባዊነት ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ይል ነበር። ያለ ደም እንዴት ኢትዮጵያ ልትቀድም ትችላለች የሚል ፍኖተ ካርታ ግን የለም። እሳቤውን ያለምንም ምሁር ፈጠር ፍኖተ ካርታ ለማንበር ነፍጥን መረጠ። ነፍጡ ውድቀቱን አፋጠነው። በኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ ልማታዊ መንግሥት ለፖለቲካ ልሂቃኑም ሆነ ለምሁራኑ ግልጽ አይደለም።

ምሁራን ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እሳቤ ከኢሕአዴግ ልሂቃን ከመማር ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም(በእርግጥ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተግባሩ ተነሥቶ መበየን ካልተቻለ፣ ለራሳቸው ለኢሕአዴግ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናትም ግልጽ አይደለም)። ይህ ደብዛዛ ርዕዮተ ዓለም ምሁራን በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ ልል ሚና እንዳላቸው ያሣያል። ብዙ የትምህርት ተቋማት ቢኖሩም፣ የሀገሪቱን ማኅበረ ፖለቲካ ተረድተው መፍትሄ ሲሠሩ አይታዩም። የሚሠሩ ጥናቶች በብዛት የዕለት

ጥቅም መፈለጊያ እንጂ ወደ መሬት የሚመነዘር ጠብ የሚል ረብ የላቸውም። ምሁራን የሽምደዳ ንባባቸውን ከነባራዊ ሁኔታው ጋር አለማጣጣማቸው እና የፖለቲካ ልሂቃንም ለሴራ እንጂ ለሳይንስ ሩቅ መሆናቸው ትምህርትን ፋይዳ ቢስ አድርጎታል።

በእርግጥ በታመመ ፖለቲካ ውስጥ ጤነኛ ሙያን መፍጠር አይቻልም። በሽተኛ በሆነ ፖለቲካ ውስጥ ጤነኛ ሐሳብ ሁሉ ማደሪያው እስርቤት ነው። በብዛት ንጹሕ ጭንቅላቶች ከትምህርት እና ምርምር ተቋማት ይልቅ መገኛቸውን ማረሚያ ቤት አድርገዋል። ሐሳብ በሚታሰርበት ሀገር ውስጥ ዕድገት እና ጋርዮሻዊ ርዕይ ይጨነግፋሉ።

ዘመናዊ ቢሮክራሲ ባልተጠናከረበት እና ብዙ ምሁር ባልተፈራበት ወቅት በዳግም የኢትዮ-ጣሊያን ጦርነት (1928-1933 ዓ.ም.) ሕዝቡ በአርበኞች እየተመራ ያለማዕከላዊ መንግሥት ተደራጅቶ ነጻ ሀገር ፈጥሯል። ይህን መሰል ሕሊናዊ ተቋም ሀገሪቱ በምትመራበት አውዳሚ እና ስታሊናዊ የኩረጃ ፖለቲካ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሟሸሸ ሄዷል።

5.19 የምኒልክ የተቋም ተረከዝ እንደ አብነት…

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ካድሬዎች በችሎታ ሳይሆን በታማኝነት የሚሰባሰቡበት የአድርባዮች ማኅበር ነው። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሥልጣን ሲመጡ የልጅ ኢያሱ ተቀናቃኞችን እና የእሳቸው ደጋፊዎችን ብቻ በዙሪያቸው ሰበሰቡ። ይህም በማይጨው ጦርነት የአድዋ ድል እንዳይደገም አደረገ። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለአብዮቱ ታማኞችን ብቻ ሰብስቦ ጸረ አብዮት ናቸው የሚላቸውን ሁሉ በጅምላ አሰረ፤ ገደለ። ግማሽ ሚሊየን ሠራዊት የነበረው ደርግ በተከለተለው ችሎታን ያላማከለ ስልተ መንግሥት በመንደር ተገንጣዮች በዝረራ ተሸነፈ።

ኢሕአዴግ የደርግም ሆነ የጃንሆይ ደጋፊዎችን በድሮ ሥርዓት አራማጅነት ፈርጆ፤ ምሁራንን ደግሞ በትምክህተኛነት ከሰሰ። የኢሕአዴግ ማኅበረ ፖለቲካም በችሎታ ሳይሆን በታማኝነት ተመሠረተ። አድርባይነት እና አስመሳይነት ምንጩም ይህ አጉል የታማኝነት መስፈርት ነው። ኢሕአዴግን መምከርም ሆነ የተቃውሞ ሐሳብ ማቅረብ በራሱ ኢሕአዴግ ውስጥ ውግዝ ሆነ። ስለዚህ የኢሕአዴግ ሰዎች ማጨብጨብ እና መሪን ማምለክ ብቻ ሚናቸው ሆነ። ታማኝነት እንጂ ችሎታ መስፈርቱ ባልሆነ የመንግሥት ግንባታ ውስጥ የምሁራንን ሚና ማሳደግ አይቻልም። በመንግሥት መዋቅር የሚታቀፉ ምሁራንም በብዛት በታማኝነት እንጂ በችሎታ የሚመለመሉ ስላልሆኑ አድርባይ እና የአምባገነን መንግሥት እድሜ አራዛሚዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ዐፄ ምኒልክ በተቋም ፈጠራ እና መሪን በችሎታ በመመደብ እጅግ የረቀቁ ነበሩ። ችሎታ እንጂ የንጉሡ ታማኝ መሆን መስፈርት አልነበረም። ንጉሡ እኔን ሁን ሳይሆን ኢትዮጵያን ምሰል ማለት ይቀናቸዋል። የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የዳግማዊ ምኒልክ ተቀናቃኝ ነበሩ። በእምባቦ ጦርነትም በይፋ ተዋግተዋል። ሃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ በምዕራባዊ የሸዋ ክፍል ግብር አላስከፍልም ብለው ከምኒልክ በተቃራኒ ቁመው የተዋጉ ነፍጠኛ ነበሩ። ምኒልክ አሸነፉ እና የጦር ሚኒስትር እንዲሁም በ1900 ዓ.ም. የደቡብ ኢትዮጵያ ዋና አስተዳዳሪ አደረጓቸው። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከምኒልክ ጋር በመስማማታቸው የጎጃምን ጦር መርተው ለአድዋ ተሰልፈዋል። እነ አባጅፋር፣ እነ ካዎጦና(ወላይታ)…ሁሉ የምኒልክ ተቀናቃኞች ነበሩ። ቢሆኑም ዐፄ ምኒልክ ችሎታቸውን ለመጠቀም በአስተዳድሩ ሹመት ሰጥተው ኢትዮጵያን ለማቅናት ተጠቅመውባቸዋል። ለዚህም ይመስላል በአድዋ ጦርነት ማንም አኩርፎ ከጣሊያን ጎን በካጅነት ሳይሰለፍ ሁሉም ለሀገሩ ተዋግቶ የጋራ ድል የመጣው።

ለኤርትራ እና ለኢጣሊያ የቀረበ ግንኙነት የነበረው ባሻ አውዓሎም ሳይቀር ከኢትዮጵያ ጎን ሆኖ የተዋጋው የዐፄ ምኒልክ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ችሎታን አድናቂ እና አካታች ሆኖ በመውጣቱ ነበር። ባሻ አውዓሎም በምኒልክ ታምኖ ወታደራዊ መረጃውን ባያቀናጅ ኖሮ የአድዋ ድል በአንድ ቀን ብቻ በድል የመጠናቀቁ ሂደት ሊራዘም ይችል ነበር።

ዐፄ ምኒልክ ለፖለቲካቸው ችሎታን እንጂ ሃይማኖትን፣ ነገድን፣ የጀርባ ምክንያትን መስፈርት አላደረጉም። አለማድረጋቸው የተደራጀ የጦር ኃይል፣ ከተማ፣ ሕግ፣ ሥርዓተ መንግሥት እና ሉዓላዊ ሀገር እንዲያቆሙ አስችሏቸዋል። ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ የብዙ ተቋማትን ዳህራዊ ጅማሮ ብናጠና የዳግማዊ ምኒልክ አሻራ ታትሞ ይወጣል። ለዳግማዊ ምኒልክ የተቋም ግንባታ ስኬት ደግሞ ለአዳዲስ ፈጠራዎች ያላቸው ቀናኢ እሳቤ እና የመንግሥታቸውን መዋቅርም መምራት በሚችሉ ጀግና መኳንንት እና ንጉሦች ማዋቀራቸው ነው። አንድ ፖለቲከኛ የጥሩ ፖለቲከኛነቱ ሚዛን የሚለካው ባዋቀረው ተቋም እና ባደራጀው የሰው ኃይል ነው።

ዐፄ ምኒልክ ሙተው መምራት የቻሉት እና ትውልዱን እየተከተሉ የነገሡት ለእሳቸው ጥገኛ የሆነ ተቋም አለመፍጠራቸው ነው። ምኒልክ የፈጠሯቸው ሕሊናዊ እና አካላዊ ተቋማት ለሀገሪቱ ጥገኛ ናቸው። በመሆኑም የምኒልክ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ሐሳብ በድጋፍም ሆነ በተቃውሞ ኢትዮጵያ እስካለች ድረስ ከኢትዮጵያ እጣ ጋር አብሮ ይዞራል። ከምኒልክ ንግሥና ጋር አብሮ የሚያከትም ሥርዓተ መንግሥት አልፈጠሩም። ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥቶች በተቋማቸው በፈጠሩት ምስል እስከ መመለክ ደርሰዋል። የጃማይካ የራስ ተፈሪያን የራስታዎች ንቅናቄ እና በጥቁሮች ደምቆ የተቀነቀነው የኢትዮጵያዊነት የአፍሪካ ብሔርተኝነት መነሾው ዐፄ ምኒልክ እና ወራሾቻቸው የፈጠሩት የተቋማዊ ቅቡልነት ማሳያ ነው።

የአፍሪካ አንድነት መሥራቾች በ1950ዎቹ የአማርኛ ቋንቋ እና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ትውፊቶች በአፍሪካ መገለጫነት እንዲወሰዱ ባይሳካም ፍላጎታቸውን አሳይተው ነበር። ነገር ግን ጸረ ታሪክ እና ጸረ እሴት የሆነው የኮሚኒስት አማኝ የሆነው ትውልድ የኢትዮጵያን ነባራዊ ታሪክ እና ሥሪት ለመናድ ሥራው አደረገ። የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሐውልት እንኳን በአፍሪካ ኅብረት ግቢ እንዳይተከል ራሱ ኢሕአዴግ ታገለ።

የጋናው መሪ የኩዋሜ ንኩርማህ ሐውልት ከተፈሪ መኮንን ቀድሞ እንዲቆም ያደረጉት የኢሕአዴግ ሥሪት ውጤት የሆኑት ልሂቃን እንጂ ሌሎች አፍሪካውያን አይደሉም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካ ኅብረት ተቋም ፈጠራ እና ማደራጀት በራሳችን ሰዎች ከዘገየ በኋላ ሐውልታቸው በ2011 ዓ.ም. በአፍሪካ ኅብረት ግቢ ሊቆም ችሏል። ተቋማትን ማንበር ሳይሆን ማፍረስ፤ ፈርሰው አዲስ የተፈጠሩ ተቋማትን በአድርባይ ልሂቃን ሞልቶ የፓርቲ ርዕዮተ ዓለም ጥገኛ ማድረግ… ለተሻጋሪ ተቋማት ግንባታ አምካኝ መንገዶች ናቸው። የተቋማት ምክነት በቀጥታ ሀገርን በፍርሰት መንገድ ላይ ያሳፍራል። በምኒልክ የተቋም ግንባታ መንገድ በተመሳሳይ ፍጥነት ሀገሪቱ ብትቀጥል ኖሮ፤ የኢትዮጵያ እድገት እንደ አሜሪካ ባይሆን እንኳን እንደ ደቡብ ኮርያ እና ህንድ መሆኑ ግን አይቀርም ነበር።

5.20 የተቋም መጨንገፍ የፈጠረው ኤካኛው ተቋም

ተቋማት በአጎንባሽ ልሂቃን ስለተሞሉ፣ የሕዝብን ርዕይ ለመሸከም ጀርባቸው ጎባጣ ነው። በዚህም መንግሥታዊ ተቋማት እና ጠያቂ ልሂቃን ጥል ላይ ናቸው። ብዙዎችም ከመደበኛ ተቋማት እየኮበለሉ ወደ ኢ-መደበኛ ተቋማት ተጠልለዋል። በዚህ የሐሳብ መስመር በተለይ ወጣቶች ይገኙበታል። ተቋማት ወጣቱን በበጎ

አይመለከቱትም፡፡ ስለማይመለከቱት ወጣቱ ራሱን በራሱ አደራጀ፡፡ በአማራ ፋኖ፣ በሶማሊያ ሄጎ፣ በሲዳማ ኤጄቶ፣ በኦሮሚያ ቄሮ፣ በጉራጌ ዘርማ፣ በትግራይ ዲጂታል ወያኔ፣ በወላይታ የላጋ ወዘተ የሚሉ የወጣት አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡

እነዚህ የወጣት አደረጃጀቶች በኢሕአዴግ ክንፍ በሊግ፣ በፌዴሬሽን፣ በማኅበር... የተደራጀውን መዋቅር አፈረሱት፡፡ ቅቡልነት አሳጡት፡፡ በአማራ ወጣት ማለት ፋኖ ሆነ፤ በኦሮሚያም ወጣት ሁሉ ቄሮ ሆነ፡፡ ኢሕአዴግ አካታች የሆነ ተቋም ባለመገንባቱ አብዛኛውን እና የፖለቲካ ጉልበት ያለውን ወጣቱን አጣ፡፡ በ2010 ዓ.ም. አጋማሽ የታየው ቅርጻዊ ለውጥ መሠረቱ ፋኖ፣ ቄሮ... የሚባሉ የወጣቶች ክንፍ ናቸው፡፡ መደበኛው መንግሥታዊ ተቋም ባለበት እየረገጠ ለውጥን ሲያወግዝ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች ለለውጥ ፋና ወጊ ሆነዋል፡፡

በአምባገነን ሥርዓት ውስጥ ሥርዓቱን የሚጥሉት በመጨረሻ ጊዜ ወይ ወታደሮች አሊያም በኢ-መደበኛ አደረጃጀት የተቀናጁ ወጣቶች ናቸው፡፡ ችግሩ ኢ-መደበኛ አደረጃጅቶች ለሁነት መቀናጀ እንጂ ለውጤት አይሆኑም፡፡ ከአመጽ የዘለለ ሥርዓታዊ እና መዋቅራዊ ሥሪት ስለሌላቸው ነባሩን ከማፍረስ አልፎ አዲሱን ሥርዓት ለመትከል መሰናዶ ያጥራቸዋል፡፡ ልሂቃን መንገድ ጠራጊ ሆነው የወጣቱን ንቅናቄ ቅርጽ ቢያስይዙት ለአብዮታዊ ለውጥ ይጋብዝ ነበር፡፡

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥሪተ ተቋም ላይ ያፈነገጡ ወጣቶች መዳረሻቸው ከኢትዮጵያዊነት እሴት እና ባህል ያፈነገጠ ጠርዝ ረገጥ ሌኒን ቀመስ ብሔርተኝነት ነው፡፡ ወጣቶቹ ለዓላማ ሟችነታቸው እና ጭቆናን ላለመሸከም ያደረጉት እምቢ ባይነት በታሪክ ፊት ሞገስ ያስገኛቸዋል፡፡ ነገር ግን ወጣቶቹ የሀገሪቱን መዳረሻ ያሰላ ፖለቲካዊ ቀመር ስላልነበራቸው ከትናንት እስከ ዛሬ ላለው ፖለቲካዊ ህመም

መነሻ ሆነዋል። በወቅቱ ወጣቶች ከማርክስ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ጋር ብቻ የሙጥኝ ማለታቸው ነገን ጋረደባቸው። እኛም የዛሬ እዳ ከፋይ ለመሆን ተገደናል። ሀገረ መንግሥት ግንባታውም ፀሐይ እንዳገገረው የዋልካ መሬት ነቃቅቷል።

በመንግሥታዊ ተቋማት ዝለት ምክንያት የተፈጠሩት የዛሬዎቹ የወጣት አደረጃጀቶችም የሀገሪቱ ፖለቲካ ነጋዊ መስመር እንዲኖረው በታቀደ እና ስልተ-መዳረሻው የተነደፈለት ንቅናቄ ያስፈልጋቸዋል። ሶማሊያ ወጣቶች (ሄጎ) በዕለተ ቅዳሜ እና እሁድ ሐምሌ 28 እና 29 በ2010 ዓ.ም. ከሶማሊያ ውጭ በሆኑ በክልሉ ነዋሪዎች ላይ በወሰዱት እርምጃ ዘግናኝ ክስተት ተፈጽሟል። አብያተ ክርስቲያናት እና ካህናቱ በአንድ ላይ ተቃጥለው ወደ አመድነት ተቀይረዋል። ሴቶች ተገደው ተደፍረዋል። ተቋማት ወድመዋል። በወቅቱ በሶማሊያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በአቶ አብዲ ሙሀመድ እና በክልሉ ልዩ ኃይል በሄጎ አጋዥነት የተሠራ ጥፋት ነበር። ይህ ክስተት አቶ አብዲ ሙሀመድን ወደ ዘብጥያ እንዲወርዱ አድርጓል። የሶማሌ ክልል ህልውናም ሙሉ በሙሉ በማዕከላዊ መንግሥቱ እዝ ገብቶ ቆይቷል። የኦነግን ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ መግባት ተከትሎ በመስከረም መጀመሪያ 2010 ዓ.ም. አቀባበል ከተደረገ ማግስት በቡራዩ በቄሮ ጅምላ ጭፍጨፋ ደርሷል። ሴቶች ተደፍረው፣ አዛውንቶች ተገድለዋል። በሻሸመኔ ጃዋር ሙሀመድን ለመቀበል የወጣ ቄሮ አንድን ወጣት ሰላይ ነው ብሎ ሰቅሏል። በኦሮሚያ አባ ቶርቤ(ባለሳምንት) የሚል የገዳይ ወጣት ቡድን ተደራጅቶም ባለሥልጣን ጠለፋ ላይ ተሰማርቶ ሁሉን አቀፍ ቀውስ ፈጥሯል።

ሲዳማ ክልል ይሆናል በሚል ከተነሣው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም. ኤጀቶ በርካቶችን ገድሎ፤ ሌሎችን አፈናቅሏል። አብያተ ክርስቲያናትም ወድመዋል። በአማራም

በ2011 ዓ.ም. ሁለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች ሰላዮች ናቸው በማለት በወጣቶች ተገድለዋል።

እነዚህ ዝርዝር አብነቶች የወጣቱ አደረጃጀት ከስሜት እና ከሞቅታ፣ ከአመጽ እና ከቀቢጸ ተስፋ የሚመነጩ ናቸው። የወጣቶች አደረጃጀት ከመንግሥት መዋቅር ማምለጡ የመንግሥት ዝለት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። የወጣቶች የጥርጣሬ ምንጭም ራሱ መንግሥት ያለመታመኑ ውጤት ነው። የሀገረ መንግሥቱን መጨናገፍም ያሳያል።

የሶማሊያ ሀገረ መንግሥት በኀሳ ሲፈረካከስ እና በውጭ ኃይላት ሲጠለፍ ወጣቱ ኩርፊያ ውስጥ ገባ። ገብቶም አልሸባብ ብሎ በዓረብኛ ተደራጀ። አልሸባብ በአማርኛ የወጣት ኃይል ማለት ነው። ይህ ኃይል የሳላፊ የእስልምና የእምነት አስተምህሮውን የትግሉ ዋቢ አድርጎ ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ የምሥራቅ አፍሪካ የራስ ምታት ሆኗል። ከኢራቁ ኡስማን ቢላደን መር ከሆነው አልቃይዳ ከተባለው ቡድን የቀጥታ ተዛምዶ ያለው አልሸባብ፤ ከናይጀሪያው ቦኮሃራም ጋር ሆኖ ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም ሥጋት ሆኗል። የሶማሊያ ፖለቲካም ወጣት አልባ ሆኗል። የወጣቱ ልብ ለአልሸባብ ተማርኳል። የአፍሪካ አምባገነን መንግሥታት ለወጣቱ ዝግ መሆናቸው በአንድ በኩል ወጣቱ አማጺ ብቻ እንዲሆን በሌላ ገጽ ደግሞ ተሳዳጅ ሆኖ የውቅያኖስ እና የሃሩር ሲሳይ ሆኗል።

በ1986 ዓ.ም. በሩዋንዳ የሁቱ እና የቱትሲ ዘግናኝ ወገን ለወገን እልቂት የተመራው በሀገረ መንግሥት ውቅሩ ባኮረፉ ኢንተራሃምዊ (Interahamwe) ብለው ራሳቸውን ባደራጁ የወጣት ኃይሎች ነበር። የሁቱን ብሔር ገናናነት እንመልሳለን ብለው የተነሡትት ኢንተራሃምዌዎች በሩዋንዳ የሁቱ ባለሥልጣናት መሪነት በ100 ቀናት ብቻ አንድ ሚሊየን የሚደርሱ ሩዋንዳውያንን በጅምላ አረዱ። ከቱትሲ ጎሳዎች ከጥቅል የሕዝብ ብዛት መካከል 70 በመቶዎችን

ገደሉ። ከ500ሺህ የማያንሱ ሴቶችን ደፈሩ። ኤች አይ ቪ/ኤድስ በተደፋሪዎችም በደፋሪዎችም እኩል ተዛመተ። የሩዋንዳ መልክ ጠየመ። ሩዋንዳ እንደ ሀገር ለመቆም የሀገረ መንግሥት ጉልበቷ አልጸና ብሏት ተንፏቀቀች።

የዚህ ሁሉ ሥረ መንስኤ የተቋማት መዛል እና ወጥ ካለመሆን የሚመነጭ ነው። ለአብነት በሩዋንዳ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሁቱ ጎን ሆና ቱትሲን ስትነቅፍ፤ ሚዲያዎችም በጸረ ቱትሲ ንቅናቄ ተጠመዱ። ተቋማት በዓላማ እና በመርህ በተደራጀ ተቋማዊ መዋቅር ካልተመሩ ሕዝብን መሰብሰብ አይችሉም። የተበተነ ሕዝብ ደግሞ በጥቂቱ እንደ አልሸባብ እና ኢንተራሃምዌ ጅምላ ጭፍጨፋ ይከፍታል። ሲከፋ ደግሞ እንደ ኩርድ እና ጅብሲ(ሮማኒ) ብሔር መንግሥት አልባ እና ተንከራታች ሕዝብ እንዲፈጠር ይሆናል። የሶሪያ እና የሊቢያ ውድቀትም መሠረቱ ተሻጋሪ ተቋም አለመኖር ነው። በሊቢያ ሞሀመድ ጋዳፊ የሁሉ ነገር የእዝ ማዕከል ግዙፍ ግለሰባዊ ተቋም ነበሩ። ሲወድቁ ሀገሪቱ አብራ ወደቀች። ወጣቱም ተቧድኖ ሕልሙን አጨንግፎ ወደ አመጽ ተሰማራ።

አመጽ ሐሳብ ማያርቀውን የገነገነ አምባገነን መንግሥት ከወንበሩ ለመነቅነቅ ይበጃል። ከአመጹ ጀርባ ግን በአስተማማኝ ሁኔታ በልሂቃን ተቋም እና መዋቅራዊ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። አምባገነኖችን ከጀርባ ሥርዓት ባላቆመ አመጽ ከማውረድ ይልቅ አለማውረድ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ተሻይ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

የወጣቱን ስሜት በመጠቀም አምባገነኖችን ከመንበራቸው መነቅነቅ ይቻላል። ዋናው ግን አምባገነኖች ከወረዱ በኋላ ሀገሪቱ የምትመራበትን ሥርዓት መፍጠር ላይ መተኮር ይኖርበታል። አምባገነኖች የዕድሜያቸው ከመርዘም እና ከማጠሩ በስተቀር መውረዳቸው አይቀሬ ሀቅ ነው። ነገር ግን ሲወርዱ ቀጣዩ ሀገረ

መንግሥት ግንባታ ከብሶት ሕክምና እና ከስሜት ጭብጨባ ጸድቶ የታቀደ አሻጋሪ ጋርዮሻዊ ርዕይ ይፈልጋል። በሀገራችን የተደረጉ ጠጋኝ እና ነቃይ አብዮቶች የተሻለ ዕድል የነጠፈባቸው የአብዮቱ ፍሬ የሚለቀምበት ሕግ እና ተቋማዊ ሥርዓት ቀድሞ ስለማይበጅላቸው ይመስላል።

5.21 ከነጋዊ ሥጋት የሚለቀም ፍሬ

ፖለቲካ ነገ ነው። ነገ ታስቦ ዛሬ ይሠራል። ስለዚህ ጥሩ ፖለቲከኛ ለነገ ስጉ መሆን ይገባዋል። ሰማይ ቢወድቅ እንዴት ካስማ(ባላ) አቁሜ ሕዝቦቸን ማዳን አለብኝ ብሎ አስቀድሞ መፍትሄ መሥራት አለበት። መሬት አጋድላ ብትንሸራተት የሚመራው ሕዝብ የት ይሰፍራል ብሎ ለሥጋቱ አቻ እልባት አስፍሮ በችግር ጊዜ ከስሜት እና ከድንጋጤ ሊርቅ ግዴታው ነው።

ፖለቲከኛ የተፈጥሮ እና የፍጥረታት ሁሉ አለቃ ለሆነው የሰው ልጅ መሪ በመሆኑ ከአምላክ ቀጥሎ የአዳኝነት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ፖለቲካቸው የሰመረላቸው ሀገራት የ500 ዓመት እና ከዚያ በላይ ስትራቴጂ ነድፈው ዛሬን ለነገ ይሠራሉ። ጋሪባልዲ ጣሊያንን፣ ቢስማርክ ጀርመን፣ ሙስጠፋ አታቱርክ ቱርክን፣ ዐፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን፣ ማንዴላ ነጻ ደቡብ አፍሪካን… ወዘተ ሲፈጥሩ ወይም ሲያድሱ ነገን አስበው ነው። ዐፄ ምኒልክ ከ1881 እስከ 1887 ዓ.ም. ባለው ቀድመው የነገድ አጥሮችን በመስበር አንድ ሀገር ባይመሠርቱ ኖሮ በ1888 ዓ.ም. በአድዋ ጣሊያንን ማሸነፍ አይቻልም ነበር። ንጉሡ ሸዋን ብቻ ይዘው ቢሆን ኖሮ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጎጃም፣ ንጉሥ ሚካኤል ከወሎ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ከትግራይ ወዘተ የየአካባቢያቸውን ጦር መርተው ወደ አድዋ ላይዘምቱ ይችሉ ነበር። የኢትጵያ አካላዊ ቅርጽም የዛሬውን ንድፍ/ቁመና አይዝም ነበር።

ጣሊያንም ኢትዮጵያን ንቃ መመልከቷ ለውድቀት ዳርጓታል። አድዋ ጠላትን ከመናቅ መሥጋት እንደሚገባ ሁነኛ አስተማሪ ትዕይንተ ጦር ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ሀገር ለመገንባት ሴባስቶፖልን የመሰለ መድፍ የሠሩት ጠላትን በመሥጋት ነበር። ሥጋት የፈጠራ እና የመፍትሄ ምንጭ ነው። በአንጻሩ ከአድዋ ድል በኋላ በአሸናፊነት ሥነ-ልቦና የውጭ ሀገር ጠላትን ያለመሥጋት ሁኔታ ተስተጋብቶ ነበር። በአንጻሩ ጣሊያን ለ40 ዓመታት በሥጋት ስትናጥ ቆይታ እንደገና ኢትዮጵያን ወረረች። ወረራውም ለ5 ዓመታት ያህል ለኢትዮጵያ አስቸጋሪ ሆኖባት ቆየ። ኢትዮጵያ እንደ አድዋ በአንድ እሁድ ማሸነፍ አልቻለችም። ምክንያቱም በመሥጋት ቅድመ መከላከል አላደረገችም።

ብዙዎች የዓለም ሥልጣኔዎች የወደቁት ባለመሥጋት ወይም በምቾት ነው። የሮም ገናና ሥልጣኔ መሪዎቹ በወሲብ እና በብልሹ አሠራር ተዘፍቀው ወደቁ። በኢትዮጵያም ከአክሱም እስከ ጎንደር ያሉ ሥልጣኔዎች ያለመቀጠላቸው አንዱ መንስኤ ሥጋት አልባ ምቾት ነው። ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ በከተቡበት የታሪክ ጥራዛቸው የዐፄ ቴዎድሮስ የስኬት ምንጩ ምቾት አልባ መሆኑ እና ለታላቅ ዓላማ ለመሞት መዘጋጀቱ ነው ሲሉ ያመሰጥራሉ። ሞትን መናቅ የዐፄ ቴዎድሮስ የድሉ መሰላል ነበር። በአንጻሩ የጎንደር ነገሥታት በምቾት ፍለጋ እርስ በርሳቸው እየተገዳደሉ፣ ፊውዳላዊ ዘር እየቆጠሩ፣ የማስገበር ኃይላቸውን ሳያጤኑ በመቆየታቸው የአካባቢ ባላባቶች(የአውራጃ ንጉሦች) ከማዕከላዊ መንግሥቱ በላይ ሆነው ማስገበር ችለዋል። ዐፄ ልብነ ድንግል ጦር ርቋቸው በመቆየቱ ሰንፈው ሽንብራ ኩሬ(ሞጆ) አካባቢ በግራኝ አህመድ ተሸነፈው ወደ ሰሜን ሸሽተዋል። ግራኝ አህመድም ለ15 ዓመታት ያህል የኃይል የበላይነቱን ይዞ በኢትዮጵያ ሥሪት ላይ ለውጥ አመጣ። የተዳከመው የእነ ዐፄ ልብነ ድንግል ሥርዎ መንግሥት ኦሮሞዎች ከደቡብ ወደ ሰሜን

ለሚያደርጉት መስፋፋት ምቹት ሰጥቷል። የኢትዮጵያ ቅርጽም በመሠረታዊነት ሊቀየር ችሏል። ፖለቲከኛ ስጉ እና በድሎት ጊዜ ክፉን አስቦ ካልሠራ በድንገተኛ ሁኔታ አይወድቁ አወዳድቅ ሊገጥመው ይችላል።

የሮም መሪዎች በድሎት በወሲብ ሲማግጡ፤ በሚንቋቸው እና እንደ አውሬ በሚፈርጇቸው ጀርመኒኮች እና ካውካሶች ተወረው ገናና ሥልጣኔያቸውን በድንገት ጥለዋል። የኃያላኑ ውድቀት መንስኤው ነገን አቅርቦ ያለማየት ውጤት ነው። ፖለቲካ በዛሬ ብቻ ሳይሆን በነገው ይተመናል። ነገን ዛሬ ላይ ሆኖ ለማበጀት ሥጋት ያስፈልጋል። ለሥጋቱ ደግሞ ከችግሩ የበለጠ መፍትሄ ይቀመጥለታል። ይሄ ሲሆን ሀገር ተሻጋሪ ሥርዓት ፈጠር ተቋማዊ ሕልም ይኖራታል።

ለአብነት በመፍትሄ በታጀበ ሥጋት የተመራችው እስራኤል ወጣቶቿን ራስን የመከላከል ሥልጠና ከመስጠቷ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶቿ እንኳን ባላንጣዎቿ ተኩስ ቢከፍቱ ብላ በየተቋማቱ ምሽግ ሠርታለች። ሞሳድን የመሰለ ውስብስብ እና ምሥጢራዊ የስለላ ተቋም ፈጥራለች። ይህም እስራኤል ማለት አሸናፊ የሚል ሕሊናዊ ተቋም በየዓለም ማኅበረሰቡ ቀርጻለች። እስራኤል ከተሸነፍን አንኖርም፤ እጣችን የሚወሰነው በማሸነፍ ብቻ ነው በሚል ቀስቃሽ ንግርት ትውልድ ስለፈጠረች በመከላከያ፣ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ በግብርና ዝመና... የዓለም ቁንጮ ሆናለች።

ከአማራ ወይም ከኦሮሞ ሕዝብ የእስራኤል ሕዝብ ብዛት ከ4 እስከ 5 እጥፍ ያንሳል። የቆዳ ስፋቱም ከአንድ የኢትዮጵያ ክልል የሚበልጥ አይደለም። ከምዕራብ መጀመሪያ ወደ ምሥራቅ መጨረሻ እስራኤልን በተሽከርካሪ ለመጓዝ ከሁለት ሰዓት በላይ

አይፈጅም። የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር ከአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ብዙ የሚርቅ አሀዝም የለውም። ነገር ግን ያላትን የሰው ኃይል እና ውስን የተፈጥሮ ሀብት ሳይንሳዊ ፈጠራ አክላ በመጠቀም የፕላኔቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር ለመሆን ችላለች።

ኢትዮጵያን ስንመለከት ሕዝቡም ሆነ ፖለቲከኛው ስጉ አይደሉም። ኢትዮጵያ ፈጣሪ የመረጣት እና የማይጥላት ለምለም ሀገር ናት እያሉ ከሀገሪቱ ላይ መለኮታዊ ሥልጣን እያከሉ መፋዘዝ ይታያል። ኢትዮጵያን በመለኮታዊነት መበየን ለሕሊናዊ ሀገር ግንባታ የሚበጅ ቢሆንም፤ አምላክ ይጠብቃታል ብሎ ብቻ አለመሥጋት ግን ለማኅበረሰባዊ ውድቀት ይዳርጋል። እስራኤል አምላክ ልዩ አድርጎ እንደፈጠራት ታስብ ነበር። ግን ፈርሳ ቆይታለች። የመን እና ሶሪያ ሕዝቦቻቸው ሀገራቸውን በመለኮታዊነት ጸጋ የሚገልጹ ነበሩ። ነገር ግን ከመፈራረስ እና ከመበስበስ አልዳኑም። ሀገር ሥጋት ያዘለ መፍትሄ ያስፈልጋታል። ሀገር የምትታደሰው፤ ከአዚሚም የምትባንነው በነጋዊ ተስፋ እና ሥጋት ነው።

ኢትዮጵያውያን ሥጋት አልባ በመሆናችን በሰማዩ ዝናብ ብቻ ታምነን እናመርታለን። ሞፈር እና ማረሻ አዋደን በበሬ እየሳብን ዛሬም እንደ ትናንቱ እናርሳለን። ዝናቡ ለዓመታት ቢቆም ብለን ለሥጋቱ መፍትሄ አልሠራንም። የሕዝብ ቁጥሩ እየጨመረ መሬት እየጠበበች የአስተራርስ ሂደቱ ግን ትንሽ ሕዝብ በነበረበት ጊዜ እንዳለው ነው። ባል እና ሚስቱ ይዘውት የነበረ መሬት ወልደው 12 ቤተሰብ ሲያፈሩ አስተራርሱም ሆነ የመሬቱ መጠን ተመሳሳይ ነው። ያውም መሬቱ በለምነቱ ይቀንሳል። በዚህም የተንጠራራ ፍላጎት እና ድንክ አቅርቦታዊ ትስሥር ይፈጠራል። ነገን በሥጋት እና በመፍትሄ ስለማንቀበለው ችግሩ ደራሽ ጎርፉ ሆኖ ይወስደናል። ይህ ደግሞ እንስሳዊ ባሕርይ ነው። የሰው ልጅ ተፈጥሮን መግራት እና ነገን አስቦ አሸንፎ ማለፍ አለበት።

ፖለቲካችንም በተመሳሳይ ትናንትን በትዝታ የሚዋልል እንጂ ነጋዊ ሕልም የለውም፡፡ ፖለቲካችን ለትናንት እንጂ ለነገ አይሰጋም፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ መርሁ በሁለት ባላዎች ላይ የተንጠለጠለ ሆኗል፡፡ የመጀመሪያው ጨለምተኝነት ሲሆን መነሻውም የትናንት ስሁታዊ የታሪክ አረዳድ ነው፡፡ በትናንቱ ታሪክ ተበድያለሁ በሚል የሚሰለፉ የፖለቲካ ኃይሎች ኢትዮጵያ የተገነባችበትን ሕሊናዊ ቅርጽ ተመልሰው ማጥፋት ላይ ተሰማርተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በትናንት ታሪክ ጠግበው ለማደር የሚሞክሩ የዛሬ ስቃይን በትናንት የሚያክሙ የፖለቲካ ኃይሎች አሉ፡፡ በሁለቱም ጎራዎች መካከል ነገ የለም፡፡ ነገ ከሌለ ሕልም የለም፡፡

የትናንት ሙገሳ ወይም ወቀሳ እንጂ የነገ ትልም ከፖለቲከኞች ጠረንጴዛ ላይ አልተቀመጠም፡፡ ለትናንት ዛሬ ላይ ምላሽ መስጠት ስለማይቻል ትናንትን ወቃሽ ብሔርተኞች ኢ-አክታሚ ፍላጎት ይዘዋል፡፡ ለአብነት የኦሮሞ ብሔርተኞችን ምን ሰጥቶ ማርካት እንደሚቻል ግልጽ አይደለም፡፡ ብሔርተኝነቱ አይጠረቄ እና አይወሰኔ ፍላጎት ስላለው ከግጭት እና ከተቃውሞ ጋር ኅብረት ፈጥሯል፡፡ ብሔርተኝነት በራሱ ተለጣጭ እና ለራስ ሰፊ ግምትን ስለሚጠይቅ የግፊያው ማዕበል ጉልበት አለው፡፡ ይህ ጉልበት ደግሞ ካለነጋዊ ሕልም በትናንት ላይ ብቻ ሲመሠረት ያለውን እያጠፋ፤ የሌለውንም ስለማይተካ አውዳሚ ቅርጽ መያዙ አይቀሬ ሆኖ ይቀመጣል፡፡

አጠቃሎ

ኢትዮጵያ የረዘመ የሥነ መንግሥት ታሪኳን አንብራ የቆየች የአፍሪካውያን እና የጥቁሮች የስልጣኔ ማሳያ ሀገር ናት። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ሃይማኖት በተቋም ግንባታ ሂደት ውስጥ የላቀ አሻራ አለው። ሀገራችንም ክርስትናን እና እስልምናን በቀዳሚነት ተቀብላ ሃይማኖቷን ከባህል እና ትውፊቷ ጋር ሰም እና ወርቅ ያደረገች ሀገር መሆኗ ልዩ ቀለምን ችሯታል። ክርስትና የሥነ መንግሥት ምንጭ ሆኖ ሥነ እውቀትን፣ የቤተሰብ አስተዳድርን፣ ሥነ ሕንፃ፣ ሥርዓተ ጽሕፈት እና ሂሳብን ከእሴት ጋር አጋብቶ ሀገራዊ ቀለም እንዲሆን አድርጓል። እስልምናም በንግድ እና በማኅበራዊ ተራክቦ ለሀገረ መንግሥቱ ወዝ ሆኖ ቆይቷል። ሁለቱ ሃይማኖቶች ፖለቲካን ሠርተው ሀገር አቁመዋል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና የመንግሥትነት ምንጩ በብዙው ሃይማኖት ነው። ለዚህም ይመስላል፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ታሪክ ኢ- ተነጣጣይ ሆነው የሚታዩት።

የሕዝቦች ሞዛይክ የሆነችው ሀገራችን ከአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ወራሪ ያላንበረከካት፤ በራሷ እሴት እና ወግ የቆመች ሀገር መሆኗ ለሕዝቦቿ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያንም የኩራት ደጀንነት ሚናን ታቅፋለች። የነጻነት እና የድል፣ የስልጣኔ እና የአንድነት አብነት የሆነችው ኢትዮጵያ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የመጣችበትን መንገድ የሚሽር አብዮት ገጠማት። ለዘመናት ክብሯን አስጠብቃ፣ በነጻነት ማማ ላይ ተደላድላ የኖረችው ሀገር፤ በምሥራቅ አውሮፓ ርዕዮተ ዓለም ቅኝ ተገዛች።

ርዕዮተ ዓለሙም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ግጭት ፈጠረ። ይህ ግጭት ግለሰቦችን፣ ሕዝቦችን፣ ቡድኖችን… ወዘተ በጥርጣሬ ያፈራረጀ የሥነ ማኅበረሰብ ውቅርን ፈጥሯል። መለያየት የፖለቲካው አዝማች ሆኖ በዘውጌ ፖለቲከኞች ዘንድ ተደጋግሞ ይዜማል። ዜማው ኋላቀርነትን እየጠራ፣ አለመስማማትን እየጋበዘ በድህነት ታጅቦ ግጭት ሥራ ሆኗል። ለዚህ ሁሉ ስብራት መንስኤው ከሕዝቡ ሥነ ልቦና ጋር የቀረበ የሀገር በቀል እውቀትን ያማከለ ሥርዓታዊ መንግሥት አለመተከሉ ይመስለኛል። ፖለቲካችን እንደ ነጻ ሀገር በራሳችን የኑሮ ልምድ ተለክቶ መሰፈር ነበረበት። እንደ ደቡብ አፍሪካ በቅኝ ገዥ ርዕዮተ ዓለም ለማደግ ታሪካዊ ልምድ ያጥረናል። በራሳችን መንገድ ተጉዘን እንዳንሄድ የ1966ቱ ሌኒን ቀመስ ፖለቲካ ሀገር በቀሉን እውቀት ነቅሎታል። የሀገራችን ሁኔታ ከዚህም ከዛም ያልሆነ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ተጣብቶታል። የኢትዮጵያ የሥነ መንግሥት ሁኔታ ለዜጎች ምቹ ይሆን ዘንድ የተሻለ የፖለቲካ ሥሪት ያስፈልጋል።

የተማሪዎችን አብዮት በንግርት አጎልብቶ፣ ደርግ እና ኢሕአዴግ መንግሥታዊ ውቅርን ያበጁበት መንገድ ውስን የፖለቲካ ልሂቃንን ፍላጎት ያማከለ እንጂ በይዘቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመጥን አይደለም። የምክንያታዊነት እና የፈጠራ ጉልበት ላልቶ ሴራ እና ምቀኝነት ከማማው ላይ ወጥቷል። ስለዚህ የአንድ ሀገር ዜጎችን ደመኛ የሚያደርግ የፖለቲካ ሥሪት መናድ ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ለሀገራዊ ምልክቶች ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል። እንደ ብሔሮች የተዛነፈ ፖለቲካዊ ተረክ ሁሉ፣ የሃይማኖቶች የሀገረ መንግሥት ግንባታ ታሪክ እና ሂደት ሥርዓት እና ተቋም ካልተዘጋጀለት የሃይማኖት ጉዳይ ሌላ ፈተና ሆኖ መምጣቱ አይቀርም። ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የመገናኛ ብዙኃን የዘገባ ይዘት፣ የፖለቲከኞች ተረክ… ወዘተ ልዩነቶችን አስገንዝቦ

ወደ አንድ ሀገረ መንግሥት ማዕቀፍ ለማምጣት መሥራት ቀጠሮ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆን አልነበረበትም። ትልቁ የልዩነት እና የግጭት ማጥበቢያ መንገድ ልማት ነው። ሥራ ነው። ዜጎች በሥራ ከተጠመዱ የጋራ ገበያ ይፈጠራል። ገበያው በማንነት መቧደንን አስቀርቶ ዜጎች በንግድ እና ምጣኔ ሀብት እንዲደራጁ ያደርጋል። በዚህ ውስጥ ግለሰቦች በማንነታዊ ቡድንነት ሳይሆን በችሎታቸው ተወዳድረው ለመቅደም ይሯሯጣሉ። በዚህም ደቧዊነት(መንጋነት)፣ ጎሰኝነት፣ ወንዜነት ላልቶ ዜግነታዊ እሳቤ ይጎለብታል። በኋላቀር ግብርና በምትመራ ሀገር ውስጥ የወፈሩ ልዩነቶች ቶሎ አይሟሙም። ልዩነታቸው ሟሙቶ የውሕዳን ሀገረ መንግሥት የሚቆመው ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ነው። የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት የተለያዩ ማንነቶችን በመሰበዝ ተቀጣሪዎች ለችሎታ እና ሐሳብ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል። ልማቱ በነጻ እና ሕዝባዊ ተቋማት፣ በተፋጠነ ቢሮክራሲ፣ በሚችል የሰው ኃይል ከተመራ አድሎአዊነት ቦታ ያጣል። ዜጎችም መንግሥታቸውን እና ሀገራቸውን ይወዳሉ። የቻይና የእርስ በእርስ ግጭት የቆመው በልማት ነው። ቻይና በግማሽ ክፍለ ዘመን ውስጥ የዓለም ሁለተኛ ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ሀገር ሆናለች። ዛሬ የቻይና ውድድር አሜሪካን በልጦ ዓለምን ስለማስገበር እንጂ ስለ ሀገር ውስጥ ቡድን መበላለጥ አይደለም ። የእኛ ውድድር ግን ገና የትግራዩ ከአፋሩ፣ የኦሮሞው ከሲዳማው፣ የአማራው ከጉራጌው ጋር ነው። በዜግነታችን ከዓለም ሀገራት ጋር ለውድድር መቅረብ አልቻልንም። የሀገር ውስጥ በጥላቻ የወፈረ የፖለቲካ ተረክ ልማቱን ሳይሆን ጥሉን አሳድጓል። ሕሊናዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ አብዮት ሀገሪቱ ያስፈልጋታል። ኢሕአዴግ ተቋማትን ፈጥሮ ያለፈበት መንገድ የመንግሥትነት ባሕርይ የሌለው እና ለውስን ቡድኖች ብቻ የሚጠቅም ነው።

የ1966ቱ የፖለቲካ ንግርት መታረቅ እና መታረም ይኖርበታል።

ንግርቱ ካልታረቀ የማይታረቁ ብሔሮች የሀገርን አካል ሊሰብሩ ይችላሉ። የጥላቻ ፖለቲካ ትውልዱን ምክንያት አልባ እና ለሳይንሳዊ ፌጠራ ዝግ ያደርገዋል። በመሰለኝ እና በደሳለኝ በማስበየን፣ የማገናዘብ እና የማሰላሰል ኃይሉንም ያቀጭጫል። በስሕተት ምክንያት በውሸት እንዲኖር ያደርጋል። በሐሳብ የሚመራ ፖለቲካ ደርጅቶ፣ የፓርቲ ሳይሆን የሕዝብ ተቋማት ከደረጃ የቅራኔ ጫፎች ተላጭተው ለምለም ሳር ያበቅላሉ። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በፖለቲከኞች ሳይሆን በገለልተኛ ልሂቃን አስጠንቶ ማሻሻል፣ ማኅበረሰባዊ ንቃትን መጨመር፣ ታሪክን ከሴራ ፖለቲካ መተንተኛነት ማራቅ፣ ለሀገራዊ እሴቶች ዋጋ መስጠት የቀጣዩ ዘመን ሥራ ቢሆን፤ ከ1950ዎቹ ጀምሮ የተበላሸውን ፖለቲካ አክሞ የሀገረ መንግሥት ግንባታውን ማስቀጠል ይቻላል። ሰርሳሪ ተረከዞች የረገጡት መሬት ሁሉ እንዳይቦረቦር የተረከዙን ተዋጊነት ማጥፋት ተገቢ ነው። የሰርዛሪ ተረከዙ ምንጭ በውሸት እና ከሀገር በቀል እውቀት ርቆ የተገነባው የፖለቲካ ተረክ ነው። ይህ ሰርሳሪ ተረከዝ በተሻለ ቅርርብ የተሠራውን ሀገረ መንግሥት ሳይበትነው መከርከም ይኖርበታል። ተረከዙ አያራምድም። ይልቁንም ገዳይ እና ተገዳይ፣ አቁሳይ እና ቁስለኛ በመፍጠር የጥላቻ ቡድነትን ያወፍራል።